# እፎይ-ታ

የጥሞና ጽሑፎች

ያሬድ ጥላሁን (ወንጌላዊ)

Copyright@2016 Yared Tilahun
Efoyta, Devotional Writings
Printed in the United States of America

ይህን መጽሐፍ ወይም ማንኛውንም የመጽሐፉን ክፍል ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት፣ መገልበጥ፣ መቅረጽ ወይም በሌላ መጽሐፍ በስፋት መጥቀስ አይቻልም። ሆኖም ከዚህ መጽሐፍ ለጥናት፣ ለማስተማሪያነት ወይም ለማንኛውም ለትርፍ ሳልሆነ ዓላማ ከመጽሐፉ በከፊልም ሆነ በብዛት መጥቀስ ቢያስፈልግ ከአሳታሚው በወረቀት ፈቃድ ማግኘት ወይም የጸሐፊውንና የአሳታሚውን ስም በመጥቀስ መጠቀም ይቻላል።

በተለየ ሁኔታ ካልተጠቀሰ በቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ከታተመው የቀ. ኃ. ሥ. የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

የሽፋን ምስል፦ fiverr®

አሳታሚ
Golden Oil Ministries
9301 Georgia Avenu Suite #4
Silver Spring, MD 20903
U.S.A
Yared.tilahun@goldenoil.org
ISBN 978-0-9987038-0-0



ለምወዳት ባለቤቴ ለምኞቴ ክፍሌ ስዩም

# ምሥጋና

የጥሞና መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሳሳሁት በ2015 ዓ.ም ጥቅምት ወር ላይ የእስያ ፈርጥ በሆነችው ሲንጋፑር የተዘጋጀውን የአለም አቀፍ ክርስቲያን ጸሐፊዎች (Litworld) ሴሚናር ስካፈል ነው። ከስብሰባው ቀናት በአንዱ በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የቡድን ውይይት ሲደረግ እግር ጣለኝና በጥሞና ጽሁፎች ዙሪያ ገለጻ የሚሰጥበት ክፍል ገባሁ። ምዕራባዊያኑ ለአጠቃላዩ ክርስቲያን ተደራሲ ከሚሆኑት የጥሞና ጽሁፎቻቸው ባሻገር በዕድሜ፣ በጾታ፣ በሙያ ከፋፍለው ለወንድ፣ ለሴት፣ ለጎረምሳ፣ ለልጃገረድ፣ ለባል፣ ለሚስት፣ ለአርጉዝ፣ ለእናት፣ ለተማሪ፣ ለምሩቅ፣ ለአገልጋይ፣ለምዕመን፣ለበሽተኛ፣ ለስፖርተኛ እያሉ የሚያዘጋጁቸው የጥሞና ጽሁፎች እንዳሏቸው አስተዋልኩ። እንደ ልማዴ ወደ አገሬ በሃሳብ ዘወር ስል ከትርጉም በዘለለ በአገርኛ ቃና የተጻፉ የጥሞና ጽሁፎች እምብዛም እንዳልሆኑ አየሁና እንዳች ነገር ለማበርከት ውስጤ ተነሳሳ።

ከሁሉ አስቀድሜ ይህን በጎ መፈለግ በውስጤ ለፈጠረውና የማድረግ አቅም ለሰጠኝ ለቅዱስ እግዚአብሔር አምልኳዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ባለቤቴ ምኞቴ ክፍሌ፣ ልጆቻችን ቅዱስ ያሬድ እና ፍቅር ያሬድ በጻፍኩ ቁጥር ሳነብላቸው እነርሱም ያለመታከት ሲያደምጡኝ፣

አድናቆታቸውንና አርምታቸውን ሲለግሱኝ ይህን ጅምር እዚህ አድርሰውታልና ከልብ አመሰግናቸዋለሁ። ከመጀመሪያው ረቂቅ የተወሰኑትን ክፍሎች በማንበብና ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት ከጎኔ የቆሙት አቶ ሚኪያስ በላይ፣ ዘማሪ ገዛኸኝ ሙሴ፣ አቶ ሄኖክ ሚናስ፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌታቸው አብዲ፣ መጋቢ ወርቁ ለገሠ፣ አቶ ሙሴ ማሞና ባለቤቱ ለመለም ደበሌን እግዚአብሔር ይባርካችሁ ማለት እወዳለሁ። ወዳጄ ተወልደ መኮንን እንደ ልማዱ የመጽሐፍ ቅርጽ ስለ ሰጠው ምሥጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ወንድሜ ሁንዴ ተከሌ የሽፋን ዲዛይን በማዘጋጀት ሂደት ስላደረግከው አስተዋጽኦ በብዙ ተባረክ። ዘወትር በአገልግሎቴና በሕይወቴ ትልቅ ሥፍራ ያላቸው ወ/ሮ ዘለቃ በቀለ (ቃቁ) እና ኮ/ል ከፍሌ ሰዩም (አባቢ) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስላደረጋችሁት አስተዋጽኦ እግዚአብሔርን ስለ እናንተ ከልብ አመሰግነዋለሁ። ስማችሁን በዚህ ጽሑፍ ያልጠቀስኩ ነገር ግን በመንገዴ ሁሉ የጌታን ቸርነት ያሳያችሁኝ ብዙ ወገኖች አላችሁ፤ ልብን የሚያይ የጸጋ ሁሉ አምላክ ቸርነቱን ያብዝላችሁ።



# ማውጫ


ምሥጋና ........ i

መግቢያ ........ 1

1 ቀራጺው ........ 5

2 ጉልቻ ወይስ ፈርጥ? ........ 7

3 ቅዱስ ሽሽት ........ 10

4 "እኛ አትሂዱ እንልም!" ........ 13

5 የውሃ ዋና ........ 16

6 የስዊዝ ቸኮሌት ........ 18

7 የፍቅር ነፀብራቅ ........ 20

8 ልኬት ........ 22

9 አንዳችን አንተኛ! ........ 25

10 የምኞት አባዜ ........ 28

11 ልውጠት ........ 31

12 የሁመራ ቆይታዬ ........ 33

13 አልችልም? ........ 35

14 ራስን መተዋወቅ ........ 37

15 ግደልና ስቀለው! ........ 40

16 ሥራ የላትም? ........ 42

17 አገላብጠው! ........ 44

18 ቀልደኛ ........ 47

19 ጸረ-ቫይረስ ........ 49

20 አጃቢ ፖሊስ ........ 51

21 የተቀቀለ ቀንድ ........ 54

"የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።"

# መግቢያ

ከመቼው መሸቶ ከመቼው እንደ ነጋ ለመገመት አስቸጋሪ ነው። ቀኑ እንደ ወፍ በዓይናችን ፊት ብር ብሎ ያልፋል። ድሮ ድሮ ‘ጊዜው ይሮጣል’ ይባል ነበር። አሁን ግን ይሮጣል የሚለው አይገልጸውም፤ ‘ይበራል’ ቢባል ይቀላል። ምድር እሽክርክሪቷን የጨመረች እስኪመስል ድረስ ሁሉ ነገር በጥድፊያ ይከወናል። ሕይወት በውክቢያ ተሞልታለች። ሰው ችኩል ሆኖአል፤ ሁሉ ነገር በፍጥነት እንዲሄድለት ይፈልጋል። እፍታ እንደ ዘላለም ይረዝምበታል። የሥልጣኔው ምጥቀት፣ የቴክኖሎጂው ርቅቀት ነገርን ሁሉ አጡዞታል። በዓይን እርግብግቢት ቅጽበት መልዕክቶች ውቅያኖስ እቋርጠው ሌላው ጥግ ይደርሳሉ። ሰው ግን በዚህም አልረካም፤ አሁንም የበለጠ ፍጥነት ፍለጋ ይዘረጋል።

ሩጫው ወዴት ይሆን? ሰው በሥጋው እየሮጠ መንፈሱ ግን እንዳንቀላፋ አልያም እንደፈዘዘ ነው። ሆዱ እየጠገበ፣ነፍሱ እየተራበች ነው። ጡንቻው እየፈረጠመ፣ እምነቱ እየላላ ነው። ውጭው እያማረበት፣ ውስጡ እየተንሳቆለ ነው። ሰው እንደ እንስሳት ሥጋና ደም ብቻ አይደለም። በውስጡ መንፈስ ያለበት፣ በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረና ዘላለማዊነት የተጎናጸፈ ክቡር ፍጡር ነው። ሰው የሁለት ዓለማት ነዋሪ፣ የሁለት ማንነት ባለቤት ነው። ስለዚህ አንዱን ጥሎ፣ ሌላውን አንጠልጥሎ ሊጓዝ አይገባም። “ሰው ምን ይለኛል?” ብሎ እንደሚጨነቅ ሁሉ “እግዚአብሔር ያየኛል” ብሎ ሊያስብ ይገባዋል። በመብላትና በመጠጣት የሥጋውን ረሃብ እንደሚያስታግስ፣ የነፍሱንም ረሃብ በእግዚአብሔር ቃል ሊያጠግብ ይገባዋል።

በእርግጥ ይህን ለማድረግ ፋታ ያስፈልጋል። እንደ ለንሰለት ከተቀጣጠለው የቀኑ የሥራ፣ የመብል፣ የመዝናኛ፣ የመገናኛ የጊዜ ሰሌዳ መሐል የነፍስን ነገር ለእፍታ ጣልቃ ለማስገባት ቁርጠኝነት ይጠይቃል። የ "እፎይ-ታ" ስያሜ የመነጨው በውጥረት በተሞላ አለም ውስጥ ፋታ ሲገኝ ለአፍታ የምትነበብ፣ ጊዜ የማትፈጅ፣ ለሁሉም ዓይነት አንባቢ የምትመች በመሆኗ ነው። በአማርኛ የሥነ-ቋንቋ ሥርዓት ብዙውን ጊዜ ከአንድ ቃል መጨረሻ "ታ" መጨመሩ ከ "ታ" በፊት ያለውን ቃል ሰዎች ደጋግመው እንደሚሉት/እንደሚናገሩት የሚያመለክት ሲሆን ድግግሞሹን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለማስቀረት "ታ" እንደ ማስሪያ ታገለግላለች። ለምሳሌ፡- እለኝ-ታ፣ እቤቱ-ታ፣ እልል-ታ፣ ጫጫ-ታ፣ ጋጋ-ታ፣ እሩም-ታ፣ እምቢ-ታ፣ አንድም-ታ እና የመሳሰሉት ቃላት በ 'ታ' መታሰራቸው ተደጋግመው መባላቸውን ያመለክታል። "እፎይ-ታ" ም ደጋግሞ "እ-ፎ-ይ..." ማለትን ያሳያል።

የጥሞና የአጻጻፍ ዘውግ የአንባቢውን ጊዜ ሳይሻማ በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናትን ልማድ ለማዳበር ስለሚረዳና የሕይወት መስተዋት ሆኖ ራስን ስለሚያሳይ ጠቀሜታው ብዙ ነው። በምሳሌዎች ተከሽኖ ስለሚቀርብ የተረዱትን በተግባር ለመተርጎም ያግዛል። በጊዚያችን ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድንሆን፣ለመንገዳችን ምሪት እንድናገኝ፣ በተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ እንድንበረታና ጸንተን እንድንቆም፣ በእግዚአብሔር ደስ እንዲለን፣ ከሌሎች ውድቀትና መነሳት እንድንማር፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግና ክርስቶስን እንድንመስል ይረዳናል። የጥሞና



ጽሁፍ ቤተሰብን በመሰብሰብ በጋራ የቃሉን ማዕድ ለመቋደስ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት በየዕለቱ የጥሞና ጽሁፎችን የማንበብ ልማድ የኑሮ ጫናን በመቀነስና በሽታን በመከላከል ጤናማ ሕይወት ለመምራት ያግዛል።

"እፎይ-ታ" በዚህ ሩጫ በበዛበት ዓለም ውስጥ የተመጋቢውን ጊዜ ሳትሻማ የነፍስን ረሃብ የምታስታግስ ጣፋጭ ሕብስት ናት። አንባቢ ለጥናት ለፊ ጊዜ መመደብ ሳያስፈልገው በ 5 ደቂቃ ውስጥ ሊያጣጥማትና ተግባሩን እየከወነ በማሰላሰል ሊያመነዥጋት የሚችል ምጥን ጉርሻ ናት። በየዕለቱ የምትነበብ እንደመሆኗ መጠን ሳያሰልሱ የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብና የማሰላሰል ብሎም የመተግበር ልማድ በአንባቢዎቿ ውስጥ ታዳብራለች። በውስጧ 60 የተለያዩ ተረኮችን ያዘለች እንደ መሆኗ ሳይታወቅ እየጣፈጠ እንደሚወርድ ምግብ ወደ ውስጥ ገብታ መድኃኒት የምትሆን በልክ የተሰነገች የጥሞና መድብል ናት።

ቅዱስ ቃሉ "አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ . . ." እንዲል "እፎይ-ታ" ም ትምህርቷን በምሳሌ እያዋዛች የምክርና የተግሳጽ ገበታዋን ታሰናዳለች። በእያንዳንዱ ጽሁፎች ውስጥ የሰፈሩት ምሳሌዎች የጸሐፊው የጉዞ ገጠመኞች፣ የልጅነት ትዝታዎች፣ የቅርብና የሩቅ ንባባት ውጤት ናቸው። አንዳንዶቹ የባሕር ማዶ ተረኮች ሲሆኑ ከዘመን ርዝማኔና የመጀመሪያ ጸሐፊዎቹ ካለመታወቃቸው የተነሳ ምንጭ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ሆኗል። ቁምነገሩ የሕይወት ተሞክሮ መሰነቅ ነውና አንባቢያን ትምህርታዊነቱ ላይ እንዲያተኩሩ ይመክራል። ምሳሌዎቹ በእግዚአብሔር ቃል ተቀምመው፣

በጸሎት ተሰንገው እንባብያንን ለተግባራዊ ሕይወት እንዲያበቁ የተሰናዱ የእለት እንጀራ ናቸውና ሳይሰተንጎሉ በየዕለቱ ቢነበቡ ጠቀሜታቸው ይጎላል።

"እፎይ-ታ" እንጎቻ-ወግ ናት። በመጠን ትንሽ ብትሆንም በይዘት ሙሉ ናትና። እንጎቻ መጠኗ ይነስ እንጂ ቅርጽና ይዘቷ ከትልቁ እንጀራ አይለይም። በዚህ የመጽሐፍ ሌማት ውስጥ የተደረደሩ የሕይወት ቃል እንጎቻዎችም ትንንሽ ይምሰሉ እንጂ እንድ ትልቅ ጽሁፍ ሊይዘው የሚገባውን ማንነት ያነገቡ ናቸው። እንደ ዕለት እንጀራ አንድ እንዱን እያወጣን ብንመገብ ነፍሳችን ይታደሳል፣ ልባችን ይቀደሳል። የቆሰለው ሕይወታችን ሲፈወስ፣ ያረጀው ማንነታችን ሲታደስ፣ የራቀው ጤናችን ሲመስለ ይታወቀናል።

ታዲያ "እፎይ-ታ" ለምን በ 60 መጣጥፎች ተወሰነች? ለሚል ጠያቂ መልሱ፤ የታዳሚዎቿን የምግብ ፍላጎት ለመመርመር የተላከች ቅምሻ መሆኗ ነው። ታዳሚዎቿ "ጣመን ድገመን" ካሉ ከስድሳ ወደ መቶ ሃያ፣ ከመቶ ሃያም ወደ ሦስት መቶ ሰድሳ እምስት የማታድግበትና የመንፈቅ ብሎም የእመት ስንቅ ይዛ የማትመጣበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ወሳኙ የአንባቢያኗ ምላሽ ብቻ ነው። ለዛሬው የ 60 ቀናት ወይም የሁለት ወራት ስንቅ እነሆ እላለሁ።

ሠናይ ንባብ

ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁን

ጥር 2009 ዓ.ም / ጃኑዋሪ 2017



# 1
# ቀራጺው

*«እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናቸውና፤»*
*ሮሜ 8፥28-29*

የአውሮፓው ሕዳሴ ፈርጥ የሆነችውን የጣልያኗን ፍሎረንስ የጎበኘ የሥነ-ስዕል እፍቃሪ በመካከለኛው ዘመን ቅርጻ ቅርጾች ውበት ነፍሰ አይቀርለትም። በከፍያ ከሚጎበኙ ቤተ መዘከሮቿ ባሻገር ከተማይቱ በራሷ ክፍት ሙዚየም መሆኗን ለማስተዋል ጊዜ አይፈጅም። ጥንታዊ ሕንፃዎቿ፣ በየቦታው የተሰየሙ ሐውልቶቿ ዓይን ይሰርቃሉ፤ ነፍስ ይማርካሉ።

ከፍሎረንስ የሥነ-ቅርጽ ገጸ በረከቶች እንዱና ዋነኛው በ1501 ዓ.ም ተጀምሮ በ1504 ዓ.ም የተጠናቀቀው የማይክል እንጀሎ «ዳቪድ» የተሰኘ አስገራሚ ሐውልት ነው። 5.17 ሚትር ርዝማኔ ያለውና ከዕብነ በረድ ተቀርጾ ዕርቃኑን የቆመው የመጽሐፍ ቅዱሱ ዳዊት ምስል በአለም ላይ እስካሁን ድረስ በሰው እጅ ከተቀረጹ ሃውልቶች ሁሉ 'ወደር አይገኝለትም!' የተባለለት የቅርጻ ቅርጾች ሁሉ ቁንጮ ነው። በከተማየቱ እምብርት በሚገኘው ጋላሪያ አካዳሚያ የስዕል እልፍኝ የቆመው ይህ ቅርጽ ትኩር ብሎ ለተመለከተው፣ በሥራ ሥሮቹ ደም የሚዘዋወር፣ በአካል እንቅስቃሴና በሥራ የዳበረ ቁመና ያለው እስትንፋስ ቀረሽ ሰው የሚመስል ነው።

ይህ ሐውልት በ1504 ዓ.ም መኸር በሰንዱቅ ተሸፍኖ በብዙ ጥንቃቄ *በፒያሳ ዴላ ሲኞሪያ* ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ሲከፈት የዚያኔዎቹን የፍሎረንስ ነዋሪዎች በግርምት ውጧል። በሥፍራው ከነበሩት ታሪክ ጸሐፊዎች አንዱ *ቫሳሪ* «ጥንታዊያኑንም ሆነ ዘመናዊያኑን ሐውልቶች ድምጻቸውን የነጠቀ» በማለት አወድሶታል።

የዚህ ሐውልት ታሪክ በተነሳ ቁጥር አብሮ የሚነሳው እስገራሚ ነገር በተመረቀ ዕለት ሚካኤል አንጀሎ ከጋዜጠኞች ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ ነው። ከጋዜጠኞቹ አንዱ ወደ ሚካኤል ተጠጋና «ዳዊትን ለመቅረጽ ሃሳቡ እንዴት መጣልህ?» ሲል ጠየቀው፤ ማይክል አንጀሎም «እኔ ዳዊትን አልቀረጽኩም፣ ይህን የዕብነ-በረድ ቋጥኝ በእንድ ገበሬ እርሻ ላይ አገኘሁት፤

እንድወስደው ይፈቅድልኝ እንደሆነ ስጠይቀው ፈቀደልኝ፤ ወደ ስዕል አዳራሼ አምጥቼ አቀምኩት። አልፎ አልፎ ወንበር ስቤ ከድንጋዩ ፊት ለፊት ተቀምጬ ትኩር ብዬ የማየት ልማድ ነበረኝ። አንድ ቀን እንደ ልማዱ በትኩረት ስመለከተው ዳዊትን በድንጋዩ ውስጥ አየሁት፤ ያኔ መዶሻዬንና መሮዬን ይዤ ተነሳሁና ዳዊት ያልሆነውን ድንጋይ ሁሉ አራገፍኩት፤ እነሆ ዳዊት ተገለጠ። ስለዚህ እኔ ዳዊትን የሸፈኑትን ድንጋዮች አራግፌ ገለጥሁት እንጂ ዳዊትን አልሰራሁትም» በማለት መለሰለት።

ልክ እንዲሁ እኛም በወንጌል እውነት አምነንና ክርስቶስ ኢየሱስን የነፍሳችን መድኃኒት፣ የሕይወታችን ጌታ አድርገን ተቀብለን ከሆነ በውጭ ማንነታችን ስንታይ ቅርጽ አልባ ቋጥኝ ልንመስል እንችል ይሆናል። በውስጣችን ግን የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በመንፈሱ ይኖራል። የሕይወት ቀራጺው እግዚአብሔር ትኩር ብሎ ሲመለከተን ልጁን በእኛ ውስጥ ያያል። ከዚያማ መዶሻና መሮውን ያነሳና በኪነ ጥበቡ ክርስቶስን የማይመስለውን ሁሉ ከእኛ ላይ በማስወገድ በሥጋዊ ማንነታችን ውስጥ ተሰውሮ የኖረውን ልጁን በእኛ ሁኔታ ይገልጠዋል። እኛን ከማይከል አንጀሎ ዳዊት የሚለየን፣ የእያንዳንዱ ምት ህመም የሚሰማን፣ ማንነታችን ተገምሶ ሲወድቅ የሚያሳሳን ሕያዋን ድንጋዮች መሆናችን ነው። ነገር ግን ቀራጺያችን ሁሉን ቻይ ነውና በጸጋው ሁሉን ያስችለናል፤ ለጊዜው ቢያመንም የዘላለሙን ክብር እያሰብን ለመሠራት እንታገሣለን።

**ተጨማሪ ንባባት፦ 2ቆሮ. 3፥18, ዘፍ. 1፥26, 1ቆሮ. 15፥42-57**

### ጸሎት

*ክቡር ጌታ ሆይ የልጅህን ሕይወት ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። ክርስቶስ በውስጤ እንዳለ አምናለሁ፤ እንዲገለጥም እሻለሁ። እባክህ ሥራኝ! ልጅህን የማይመስለውን ባሕሪ ከላዬ እያፈረሰክ በውስጤ ያለውን ክቡር ሕይወት ግለጠው። በዚህ ሁሉ ውስጥ እንድታገስና ለክብር እንድበቃ ጸጋን አብዛልኝ። አሜን።*



# 2
# ጉልቻ ወይስ ፈርጥ?

*“በዚያም ቀን አምላካቸው እግዚአብሔር እንደ ሕዝቡ መንጋ ያድናቸዋል፤ እነርሱም ለአክሊል እንደሚሆኑ እንደ ከበሩ ድንጋዮች ይሆናሉ፥ በምድሩም ላይ ይብለጨለጫሉ።” ዘካ. 9፥16*

በንግሥት ቪክቶሪያ ዘመነ-መንግሥት በደቡብ አፍሪካ የተሰማራ አንድ ታሪክ ጸሐፊና ተመራማሪ የአገሬውን ሰዎች እያናገረ፣ ታሪካቸውንና አኗኗራቸውን እየመረመረ፣ ገጠመኞቹን በጽሁፍ እያሰፈረ ሲዘዋወር ቦትስዋና ይደርሳል። በዚያ ጥቂት ቀን ከከረመ በኋላ ወደ አገሩ ለመመለስ በጉዞ ላይ እያለ ይመሽበታል። የአካባቢው ሰዎች ብቻቸውን በሚኖሩ አንዲት አሮጊት ጎጆ ውስጥ እንዲያድር ያመቻቹለትና ወደ ደሳሳዋ ጎጆ ይዘልቃል።
ጎጆዋ ምግብ የሚበሰልባትም የሚበላባትም፣ እንግዳ የሚጫወትባትም የሚተኛባትም ባለ አንድ ክፍል አልፍኝ ናት። እንግሊዛዊው ተመራማሪ በጎጆዋ አንድ ጥግ መደብ ላይ ተነጥፎለት በጉዞ የዛለውን ሰውነቱን በአንቅልፍ ለማሳረፍ ሲመቻች በቤቱ መሐል እሳቱ ያልጠፋ ባለ ሶስት ጉልቻ ምድጃ ያያል። ጎጆው ከደረቅ ሣር የተሠራ መሆኑን ሲያይ አሳብ ገባውና በውሃ እንዲያጠፉ ለአሮጊቷ በምልክት ተናገረ። አሮጊቷም አይኑ እያየ እሳቱን አጠፉ።

እንግሊዛዊው እንግዳ ሌሊት በድንገት ከእንቅልፉ ነቃ፤ ወደ ጎጆው መሐል ሲመለከት ከመተኛታቸው በፊት እንዲያጠፉት የነገራቸውና ያጠፉት የምድጃ ፍም እየነደደ ያያል። በድንጋጤ እየተደናበረ ከኮሮጆው ውስጥ ለመንገድ የያዘውን ውሃ አውጥቶ ወደ ምድጃው በመሄድ ውሃ አርከፈከፈበትና ወደ መደቡ ተመለሰ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ከመደቡ ሆኖ ሲመለከት አሁንም ምድጃው መሐል ትርከከ ያለ ፍም ይታየዋል። ካሁን አሁን ጎጆው በእሳት ተያይዞ፣ ነበልባሉ ሲንቀሳቀል፣ ጢሱ ሲጉተለተል፣ አካባቢው ሲጋይ፣ ባለፉት ወራት በብዙ ድካም የመዘገበው ማስታወሻ ሲቃጠል በዓይነ-ሕሊናው እየታየው ተረበሸ። በዕንቅልፍ የሞጨሞጨውን ዓይኑን ደጋግሞ እያሸ ተመለከተው። እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ስላሰበ ድጋሚ ድምጹን አጥፍቶ ወደ ምድጃው አመራ።

ስካ የእሳት ፍም የመሰለው ነገር እሳት ሳይሆን ለጉልቻ በተቀመጠው ድንጋይ ላይ የተጣበቀ አንዳች የሚያኽል ንጹህ አልማዝ ነው። ወደ መደቡ ተመልሶ የከበረ ድንጋይ ያለበትን የጉልቻ ድንጋይ ታቅፎ የሁኔታውን አስገራሚነት ሲያሰላስል ሳለ ዕንቅልፍ ድብን አድርጎ ወሰደው። በማሰዳ በበሩ ስንጥቅ የሚገባው የፀሐይ ጨረር ዐይኖቹ ላይ ሲርገበገብ ከዕንቅልፉ ነቃ። ካደረበት ጎጆ ከመውጣቱ በፊት ወደ አሮጊቷ ተጠግቶ ስለ አዳሩ ምስጋና ካቀረበ በኋላ ከሦስቱ የጉልቻ ድንጋዮች አንዱን መውሰድ እንደሚፈልግ ይነግራቸውና ፈቃዳቸውን ይጠይቃል። አሮጊቷ አላመነቱም፤ ፈቀዱለት። ጥቂት ገንዘብ ከኪሱ አውጥቶ እጃቸው ላይ ካኖረ በኋላ ተሰናብቷቸው ሄደ።

ያ ከቦትስዋና የአሮጊት ጎጆ ከጉልቻ ድንጋይ ጋር የተወሰደ አልማዝ፣ ደቡብ አፍሪካን በእግርና በፈረስ ተጉዞ፣ አትላንቲክ ውቅያኖስን በመርከብ አቋርጦ እንግሊዝ ደረሰ። ሆላንድ ውስጥ በሚገኙ ታዋቂ የአልማዝ ቀራጺዎች ተበጅቶና ኄጠኛ ከፈፍ ተሰርቶለት በእንግሊዟ ንግሥት ዘውድ ላይ አረፈ።

አበው «ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል!» እንዲሉ ከአፍሪካ አፈር የተገኙ ወርቆችና አልማዞች ብቻ ሳይሆኑ ከወርቅና ከአልማዝ የሚከብሩ ልጆቿ በአልባሌ ዋጋ ወደ ምዕራቡ ዓለም ሲጋዙ ኖረዋል፤ አሁንም በመጉረፍ ላይ ናቸው። በጉያችን እያሉ በውስጣቸው የተቀመጠውን የከበረ ሥጦታ በአስተውሎት ማየት ባለመቻላችን ሌሎች አይተውልን ከዓይናችን ሥር ወስደዋቸዋል። ንቀን ምድጃ ሥር የጣልናቸው ምርጦቻችን ባዕድ ምድር ሄደው ዕምቅ ዐቅማቸው ታውቆ፣ በዘመናዊ ትምህርት ተሞርደውና በምዕራቡ ባሕል ለስልሰው ለዘውዳቸው ማስጌጫያ፣ ለኃያልነታቸው ማቆያ፣ ለተጽዕኗቸው ማከረሚያ ዋና መሣሪያ ሆነዋል።

መቼ ይሆን አፍሪካ ከስመመኗ ወጥታ፣ ከሸሰብታዋ ነቅታ አልማዞቿን የምትጠበቀው? የከበሩ ድንጋዮቿን ጉልቻ ብላ መጥራት የምታቆመው? መቼ ይሆን በራሷ አልማዞች ላሸበረቀው የባህር ማዶ ዘውድ መስገድ አቁማ የራሷን ዘውድ በራሷ ልጆች የምታስጌጠው? መቼ ነው ወንድ ልጆቿን ወርቅ፣ ሴት ልጆቿን አልማዝ፣ ሕፃናቶቿን የዕንቁ ቡቃያ፣ አዛውንቶቿን የክብር ጌጥ ብላ የምትጠራው? መቼ ይሆን?



ተጨማሪ ንባባት፦ ዘጸ. 28፥6-21, ኢሳ. 54፥11-14. የሐ. ራዕይ 21፥9-14

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ፦ ከላይ በቃልህ እንዳነበብኩት አንተ የከበረ ድንጋይ የምትለው በደምህ የዋጀሃቸውንና በእጅህ የቀረጽሃቸውን ሰዎች እንጂ የሚጠፉ ወርቅና ብርን አይደለም። እባክህ የአፍሪካ የፖለቲካ መሪዎች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ አባቶችና እናቶች፣ መምህራን እና የሚመለከታቸውን ሁሉ የልብ ዐይኖቻቸውን እንድትከፍት እጸልያለሁ። በአህጉሪቱ የሞላውን፣ በአምሳልህ የተፈጠረውን የሰው አልማዝ አርቫ የሚመለከቱበትና አከብረው የሚይዙበትን ጥበብ እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ። እኔም በዚህ ውስጥ ያለኝን ድርሻ እንድወጣ ጸጋን ታብዛልኝ ዘንድ፣ ትጋትን ታጎናጽፈኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። ለሜን።*

# 3
# ቅዱስ ሽሽት

*"ከዝሙት ሽሹ! . . ." 1ቆሮ. 6፥18*

ከእንቅልፍ ያነቃኝ ሕልም ነው። በሕልሜ አንድ ቤት ውስጥ ለተሰበሰቡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሳስተምር ቆይቼ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ነኝ። የቤቱ መውጫ በር ከሩቅ ይታየኛል ነገር ግን በአጠገቤ ባለው የጓሮ አጥር ጥግ የተገነጠለ ቆርቆሮ አያለሁ። በልቤ ለምን በዚህ በኩል አልወጣም ብዬ ዐለብና ቆርቆሮውን አጥፌ በማዕዘኑ ሥር ለመሹለክ ስጎነበለ ገና ግማሽ ጎኔ ሳይወጣ አንዳች የሚያካከሉ ውሾች አየሁ። መውጣቴን ለቀጥል ከመካከላቸው አንዱ እየተሰፈነጠረና እየጮኸ ወደ እኔ ሲጋልብ ደንግጬ ተመለሰኩና በአጥር መውጣቴን ትቼ በበሩ ለመውጣት ወሰንኩ፤ ወዲያው ከእንቅልፌ ነቃሁ።

መብራቱን ሳላበራ የት እንዳለሁ ማለብ ጀመርኩ። ለአገልግሎት ከቤት ከወጣሁ ወር ሆኖኛል። በጀርመን ከተሞች ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ ከሽቱትጋርት በባቡር ተሳፍሬ የሆላንድ ከተማ በሆነች ዘ ሄግ ሁለት ቀናት ቆይቼና አገልግሎቴን ጨርሼ ወደ ጀርመን ለመመለስ ትናንት ምሽት አምስተርዳም ገብቻለሁ። ያደርኩት ከ ዘሄግ ኮንፈራንስ ይዞኝ የመጣው አምስተርዳም ከተማ የሚኖር ወንድም ቤት ነው። አሁን የት እንዳለሁ አርጋግጫለሁ፤ እናም አልጋ ላይ ሆኜ ጥቂት ሕልሙን ካሰላሰልሁ በኋላ ወርጄ ተንበረከኩና ጠላት ከፊቴ ካስቀመጠው ከማናቸውም ወጥመድ እንዲጠብቀኝ ጌታን ተማጽኜ ተነሣሁ። ቁርስ እየበላሁ ዝንኛዋን አምስተርዳምን እንዲያስጎበኘኝ ከአንድ ወንድም ጋር ቀጠሮ መያዜ ትዝ አለኝ። አምስተርዳም ስመጣ ይህ የመጀመሪያዬ ስለ ነበር ያለኝን ጊዜ አብቃቅቼ መግቢያ መውጫዋን ለመጎብኘት ውስጤ ቋምጧል።

አስጎብኚዬ ከተማይቱን 'ከሱ ይልቅ ላሳር!' እስከሚባል ድረስ ጠንቅቆ ያውቃታል። ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት አደንዛዥ ዕጽ እያጨሰም፣ እያሰጨሰም ያልገባበት የጨለማ ጥግ እንደሌለ አጫውቶኛል። ወደ ጌታ ከመጣ በኋላ ተከታታይ ትምህርቶቼን በቴፕ አግኝቶ ሰለሰማና ስለ ተጠቀመ በዚህ አጋጣሚ ከተማይቱን በማስጎብኘት ፍቅሩን ለመግለጽ ጓግቷል። ተገናኝተን ከባቡር ጣቢያው በመነሳት ጉብኝቱን ተያያዝነው።



ከጥቂት ቆይታ በኋላ እምብዛም ወደ ግራና ቀኝ መታጠፊያ የሌለው አንድ ቀጭን መንገድ ይዘን ቁልቁለት መውረድ ጀመርን። አስጎብኚዬም "ይህ መንገድ ወደ 'ቀይ መብራት ጎዳና' የሚወስደው ነው፤ አምስተርዳም መጥቶ ይህን ሳይጎበኝ የሚሄድ የለም" አለኝ። ይሄኔ አንድ ትልቅ የማይታይ እጅ ደረቴ ላይ አርፎ ወደ ኋላ የሚገፋኝ ያህል ተሰማኝ። ቆም አልኩና "ይህ የቀይ መብራት ጎዳና ሴቶች በከፊል ዕርቃናቸውን ሆነው በመስታወት ውስጥ የሚታዩበት ነው? አልኩት ፈጣን መልስ በሚሻ ድምጽ። ፊቱን ቅጭም አድርጎ "አዎን!" አለኝ።

ከዚህ ቀደም እንደሰማሁት ከሆነ ይህ ጎዳና ሴቶች ራቁታቸውን ሆነው ለዝሙት የሚቀሰቅስ እንቅስቃሴ እያሳዩ በመስኮት የሚቆሙበትና ተመልካቾቻቸውን ለወሲብ የሚጋብዙበት በዓለም የታወቀ፣ በአገሩ ሕግ የተደገፈ ዘመናዊ የሴት አዳሪዎች ጎዳና ነው። ይህን ለማየት ከዓለም ዙሪያ የመጡ የትዬለሌ ጎብኚዎች ከፊታችን እየተጋፉ ያልፋሉ። ወዲያው የማለዳው ህልም ትዝ አለኝ። በልቤ "አገልግሎቴን ጨርሻለሁ፤ በሰላም በገባሁበት በር ብወጣ ይሻለኛል፤ አጥር መጣስ አይበጀኝም። ይሄ የውሾች እንጂ የሰው መንደር አይደለም፤ ጩኸታቸው ልበናዬን እንዲረብሽ ለምን እፈቅዳለሁ?" አልኩና ወደ አስጎብኚዬ ዞር ብዬ "ወዳጄ! ይሄ የእኔ ከልል አይደለም፣ ብመለስ ይሻለኛል፤" በማለት እግዚአብሔር ከፋትን ከማየት ስለ ታደገኝ እያመሰገንሁ ወደ ጀርመን ይዞኝ የሚምዘገዘውን ፈጣን ባቡር ለመጠበቅ ባቅራቢያ ባለ ካፌ ተቀመጥሁ።

በፍልሚያ ላይ መሸሽ የፈሪነት እንጂ የጀግንነት መገለጫ ተደርጎ አይወሰድም፤ ፍጥጫው ከዝሙት ጋር ሲሆን ግን ማሸነፊያው መንገድ፣ ድል መንሺያው ስልት መሸሽ ብቻ ይሆናል። ስለዚህ ጀግና ሳያመነታ ይሸሻል። የበጎ ወታደር መለያው ጠላትን መጋፈጥ ብቻ ሳይሆን ለጦር ያስከተተውን መታዘዝ ስለሆን «ሽሽ» ሲባል መሸሹ ጀግና እንጂ ፈሪ እያሰኘውም። ቤት በእሳት ሲያያዝ ከአደጋ ለማምለጥ ጀርባ ሰጥቶ መሮጥ እንጂ ማቄን ጨርቄን እያሉ ወደ ቤት መሰሰ ቀለሰ እንደማይባል ሁሉ ከዝሙት ወላፈን ለማምለጥ ከመሸሽ ሌላ ምንም አማራጭ የለም።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ኤፌ. 5፥3, ዕብ. 13፥4, ምሳሌ 5፥7-14**

**ጸሎት**

*አቤቱ፡- በዘመኔ ሁሉ ከዝሙትና ወደ ዝሙት ከሚያመሩ ነገሮች ጠብቀኝ፣ የምሸሽበትንም ጸጋ አብዛልኝ፤ አጉል ደፋር ሆኜ ወጥመድ ውስጥ ከመግባት፣ ካዘጋጀህልኝ ክብር ከመጉደል ጠብቀኝ። በተፈጥሮ የሰጠኸኝ ማንነት ቅዱስ እንደሆነ አውቄ አንተ ባሰመርኸውና ለክብርህ በሚሆነው መንገድ ብቻ በአግባቡ እንድጠቀምበት እርዳኝ። አሜን።"*



# 4
# "እኛ አትሂዱ አንልም!"

*"የመቶ አለቃውም መልሶ፡- ጌታ ሆይ፥ በቤቴ ጣራ ከታች ልትገባ አይገባኝም፤ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል። እኔ ደግሞ ለሌሎች ተገዥ ነኝና፥ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ፤ አንዱንም፡- ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም፡- ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም፡- ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል አለው።" ማቴ. 8፥8-9*

በአብዮቱ ፍንዳታ ማግሥት ብሔራዊ ቴያትር በሚል ስያሜ የተሰወጠው የቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቴያትር ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ቤተ ተውኔቶች ሁሉ ግዙፋና ሥመ ጥር ነው። የተንጣለለው እዳራሽ፣ የፎቁ ላውንጅ፣ ፏዬ በመባል የሚታወቀው ስፊ ካፌቴሪያ፣ በጀርባ ያሉ ቢሮዎች፣ የዘመናዊ፣ የባሕላዊና የረቂቅ ሙዚቃ ክፍሎች፣ የውዝዋዜና የተውኔት ክፍሎች፣ በፊት ለፊት ያሰው ከተማውን ሲያይና በከተማው ሲታይ የሚውለው ግራር በመባል የሚታወቀው ካፌ ሰቲያትር ቤቱን የማይረሳ ግርማ ካጎናጸፉት ገጽታዎቹ ዋነኞቹ ናቸው።

ዕድሜዬ ገና በእሥራዎቹ እጋማሽ እያስ በጥበብ ፍቅር ተነድፌ ውሎዬ ብሔራዊ ቲያትር ከሆነ ሰንብቷል። በተለያየ አጋጣሚ እንጋፋ ከሚባሉት የአገሪቱ ዕውቅ ከያኒያን ጋር የማሳሰፍ ዕድሉ ነበረኝ። የአንድ ቀኑን ግን ፈጽሞ እልረሳውም። በግራር ካፌ የኢትዮጵያ ምድር ያፈራቻቸው ፈርጥ ከያኒያን በጠረጴዛ ዙሪያ ከብ ስርተው ወግ እያደመጡ ቡና ይጠጣሉ። እኔም ማኪያቶዬን ይዤ በመካከላቸው ተሰይሜያለሁ። በአጠገቤ ብርቅዬው ወግአየሁ ንጋቱ ተቀምጧል፤ ከጎኑ የማትጠገበው እለምፀሐይ ወዳጆ አሰች፤ ከሷ ሰጥቆ ሲራክ ታደሰ፣ ተከሌ ደስታ ሌሎችም ተቀምጠዋል። የሁሉም ዐይንና ጆሮ ግን የተተከለው በጋሽ (ሎሬት) ጸጋዬ ገብረመድህን ላይ ነው። በዚያ በምጥ የሚወጣ በሚመስል ቃላቸውና ጎርናና ድምፃቸው እንድ የጥንት ገጠመኝ ይተርኩልናል። ሁላችንም የሎሬቱን ንግግር በቡናና በማኪያቶ እያወራረድን በተመስጦ እንሰማለን።

"በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ኦቴሎ ቴያትርን ይዘን ወደ ሌጎስ ናይጀሪያ ሰመሄድ ተወሰነና ከቤተ መንግሥት ፈቃድ ሰማግኘት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን እጅ እንድንነሣ እኔና ተሰፋዬ ገሠሠ ተመረጥን። ተሰፋዬ ትልቅ ከሚባሉ ቤተሰብ ሰሰወጣ እጅ አነሳስ ያውቅ ነበር፤ እኔ ግን

አምብዛም አልነበርኩም። የመጀመሪያ ቀን ንጉሡ ፊት የምንቀርብ መስሎን ነበር፤ ከብዙ ደጅ ጥናት በኋላ ግቡ ተባልን። በር ተከፈተ፣ መጋረጃው ተገለጠ፤ ወዲያው አንዱ የቤተ መንግሥት አጋፋሪ "እጅ ንሣ!" በማለት ጆሮ በሚሰነጥቅ ድምፅ ጮኸ፤ ለጥ አልን፤ ቀና ስንል የቀረብነው ጃንሆይ ፊት ሳይሆን አንድ የቤተ መንግሥቱ አልፍኝ አስከልካይ ፊት እንደ ነበር ተረዳን። ደጃዝማቹ ጉዳያችንን ጠይቀውን እኛም አስረድተን ቀጠሮ ተቀብለን ወጣን።

ይህ ነገር በሚቀጥለውም ቀጠሮ ተደገመና በሌላ አልፍኝ አስከልካይ ፊት እጅ ነስተን ንጉሡን ለማየት ቀጠሮ ይዘን ወጣን። በሦስተኛው ተሰላችተንና ተዳክመን ሄድን፣ ከብዙ ጥበቃ በኋላ በር ተከፈተ መጋረጃ ተገለጠ ገባን "እጅ ንሣ!" የሚለው ትዕዛዝ አምቧረቀ፤ ለጥ አልን ስንነሳ አውነትም ጃንሆይ ፊት ለፊት ተሰይመዋል። ደነገጥን፤ ይባስ ብሎ ድንክ ውሻቸው እግራችን ሥር እየተሽከረከረች ታሸተን ጀመር። "ሂጅ" አትባል ነገር የንጉሥ ውሻ ናት። እንደምንም ታግሠን ቆምን።

የቴያትር ቤቱ ባለ አደራ በንጉሡ ፊት ቲያትሩን ወደ ሌጎስ ይዞ ለመሄድ ፈቃድ ከመጠየቅ ባለፈ መወድስ የሞላበት ረዥም ንግግር አደርገው እንደጨረሱ ጃንሆይ በለሆሳስ "እኛ አትሂዱ አንልም" አሉ። 'ምን ማለታቸው ነው?' የሚለውን አሰበን ሳንጨርስ "እ-ጅ ን-ሣ!" የሚለው ድምጽ ዳግም አምቧረቀ። ወዲያው ውጡ ተባልን፤ ደጅ ሆነን ምን ማለታቸው ነው? ሂዱ ነው? አትሂዱ ነው? እያልን ስንነጋገር "እንኳን ደስ አላችሁ" የሚሉን በዙ። ለምን ነው? ብለን ስንጠይቅ "እኛ አትሂዱ አንልም" ማለት እኮ ሂዱ ማለት ነው ተባልን። በዚያ መሠረት ቴያትሩን ይዘን ወደ ሌጎስ አቀናን። ብለው ጋሽ (ሎሬት) ጸጋዬ ትረካቸውን ፈጸሙ።

አሁን አሁን ሳስበው የምድራዊ ንጉሥ ቃል እንዲህ ውድ ከሆነና በአንዲት ቃል ትልቅ ነገር ከተከናወነ የዘላለሙ ንጉሥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ምን ያህል ኃያል ይሆን? በፍጹም ልባችን አምነን ብንቀበለው ምንኛ የማድረግ ሥልጣን ያጎናጽፈን ይሆን? ንጉሥ ብዙ መናገር አያስፈልገውም፤ የአንዲት ቃሉ ሃሳብና መልዕከት ከገባን የማንሻገረው ድንበር፣ የማናልፈው ከልል አይኖርም። ይህን ታሪክ ባስታወስኩ ቁጥር "አወይ የንጉሥ ቃል!" ያሰኘኛል።



**ተጨማሪ ንባባት፡- መክ. 8፥4. መዝ. 28፥1-9. 2ጢሞ. 3፥16**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ፡- የምድር ነገሥታት ሁሉ በሞት ተሸንፈው ክብርና ሥልጣናቸውን አጥተዋል። አንተ ግን በሰማያዊ ዙፋንህ ለዘለዓለም ጸንተህ ትኖራለህ። አቤቱ በአንተ ፊት መቅረብ እንዴት መታደል ነው! ቃልህንስ ሰምቶ መታዘዝ እንዴት ያለ ብፅዕና ነው! አቤቱ ቃልህን እንዳምንና እንድታዘዝ ጸጋን አብዛልኝ። አሜን።*

# 5
# የውሃ ዋና

*"እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፏልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም።" ዘፀ. 20፥11*

በጅቡቲ የአየር ንብረት ግንቦት የንዳድ ወር ነው። ገንዘብ ያሰው በሰው ሠራሽ ማቀዝቀዣ ቢሮውን፣ መኪናውንና ቤቱን አቀዝቅዞ ጅቡቲ መኖሩንም የረሳው ይመስላል። እንደ እኔ ሳለ ሰደተኛ ግን ቅዝቃዜ ሩቅ ነው። የነበረኝ ብቸኛ አማራጭ እንደ ብጤዎቼ ቀይ ባህር ዳርቻ ሄዶ ውሃ ውስጥ መዘፍዘፍ ነው። ሰዋና አብረውኝ የሚሄዱ ጓደኞቼ አንዳንዶቹ የአሰብ ልጆች ስሰሆኑ ውሃ ሁሰተኛ ቤታቸው ይመስሳል። ሰእንደኔ ዐይነቱ የሸገር ልጅ ግን ውሃን ወደ ሆድ ማስገባት እንጂ ውሃ ውስጥ መግባት አይታሰብም። ከስድስት ወር በፊት ጅቡቲን በረገጥኩ በሳምንቱ ካልዋኘሁ ብዬ ተንደርድሬ ጥልቅ ውሃ ውስጥ ገባሁና የሚያወጣኝ ሽቼ "ወርያ (በሱማሊኛ 'አንተዬ' እንደማለት ነው) በአናታችሁ!!!" ብዬ ብጮህም የሚደርስልኝ አጥቼ በተኣምር ከሞት መትረፌን ፈጽሞ አልረሳውም። አሁንም ዳር ዳሩንም ቢሆን ውሃ ውስጥ መግባቴ እኔ ሆኜ ነው። በእርግጥ የውሃ ዋና ሰመልመድ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ። አጠገቤ ያሉትም የአሰብ ልጆች ያደፋፍሩኝ ነበር። ሆኖም መንሳፈፍ አልሆንልህ አለኝ።

አንድ ቀን ሁሉም ጥሰውኝ ሲዋኙ ብቻዬን ውሃው ዳር ሆኜ ሳሰላስል ከሩቅ አንድ ነገር ተመለከትሁ፤ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የብረት ኮንቴነሮች የተሸከመ አንድ ትልቅ ዕቃ ጫኝ መርከብ እኔ ያሰሁበትን የቀይ ባህር ውሃ ያቋርጣል። አንድ ሃሳብ በውስጤ ብልጭ አለ። "እኔ 70 ኪ.ግ የማልሞላ ሰው ልንሳፈፍበት ያቃተኝ ውሃ ብዙ ሺህ ቶን የሚመዝን መርከብ እንዴት ይንሳፈፍበታል? ውሃው *መርከቡን ከተሸከመ እኔን መሸከም እያቅተውም።* ስለዚህ ችግሩ ከእኔ እንጂ ከውሃው አይደለም። ባምነውና ራሴን ብጥል በእርግጥ ይሸሸከመኛል።" አልኩና ውሃ ውስጥ ገብቼ ለመንሳፈፍ ሞከርኩ፤ ሳይታወቀኝ ዋኘሁ። ይኸው እስከዛሬ ድረስ በተሰያየ የዋና ዓይነት እዋኛለሁ።



እግዚአብሔርም በስድስት ቀናት ውስጥ ሰማይንና ምድርን በቃሉ ሠራ፤ በሰባተኛው ቀን ግን አረፈ። ያረፈው ቃሉን ልኮ በሠራው *ሥራ* ነው። ሰውንም በዚህ *ሥራ* እንዲያርፍ አዘዘው። እግዚአብሔር በሰንበት ዐርፏልና ለሰው በሰንበት አለማረፍ ኃጢአት ሆነ። ለምን? አለማረፍ በእግዚአብሔር *ሥራ* አለማመን ነዋ! በእግዚአብሔር *ሥራ* ካለማመንና ካለማረፍ የባሰ ኃጢአት ከወዴት ሊመጣ ይችሳል?!

ልከ እንዲሁ እግዚአብሔር *ቃሉን* በ*ሥጋ* ልኮ በመስቀል ሞቱና በትንሣኤው *ሥራችንን* ሁሉ ሠራልን፤ በዚህም *ሥራ* እግዚአብሔር ዐረፈ፣ ጽድቁም ረካ። እነሆ ሰዎችን በክርስቶስ *ሥራ* አምነው እንዲያርፉ በወንጌል ይጣራል። ማመንና ማረፍ ተሰኗቸው በራሳቸው ጥረት የሚውተረተሩ ሁሉ ይሰጥማሉ። የሚተማመኑና ራሳቸውን በእርሱ ሳይ የሚጥሉ ግን ለዘሰዓለም ያርፋሉ። *የክርስቶስ ሥራ ትልቁን እግዚአብሔርን ማሳረፍ ከቻለ ትንሹን እኔንማ ማሳረፍ እንዴት ይሳነዋል? በፍጹም አይሳነውም።*

እስከ ዛሬ ስንት ጊዜ ወንበር ሳይ እንደተቀመጥን ቁጥሩን ማወቅ አይቻልም። ነገር ግን ከጉዞ ደከመን ወንበር ስናገኝ እንቀመጥና "እፎይ" እንላለን እንጂ ወንበሩ ይችለኝ ይሆን? በማለት ለማረጋገጥ አንጥርም። ሰው የሠራው ወንበር የሚያሳርፈን ከሆነ እግዚአብሔር በልጁ የሠራው *ሥራ* እንዴት ማሳረፍ ይሳነዋል? ውሃ ውስጥ መኖር ተፈጥሯችን ባይሆንም ውሃው ላይ በማረፍና በጥቂት ተገቢ እንቅስቃሴ ድርሻችንን በመወጣት እንደምንዋኝ ሁሉ በመስቀል ሳይ በተፈጸመው የክርስቶስ *ሥራ* በማረፍ በእፎይታ እግዚአብሔርን ማምለክና ማገልገል እንችሳለን። መልካም ዕረፍት!

**ተጨማሪ ንባባት፡- ማቴ.11፥20-30፤ ዘፍ.2፥2-3፤ ኢሳ.26፥3**

## ጸሎት

*አቤቱ በክርስቶስ ሥራ በእምነት ማረፍን ስጠኝ፤ በሥጋዬ ተፍጨርጭሬ በኃጢአት ከመዘፈቅ ጠብቀኝ፤ እኔ ሳርፍ መንፈስህ በእኔ ውስጥ ጽድቅን ይሥራ! አሜን።*

# 6
# የስዊዝ ቸኮሌት

*"ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሠል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፣ አንዳችም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፣ እርሱ ይበቃናል።" ፩ጢሞ. 6፥6-8*

ስዊትዘርላንድ በቸኮሌት ምርት በዓለም ቁጥር አንድ ከሚባሉት አገሮች ቀዳሚ ተርታ የምትሰለፍ ነች። ቸኮሌት ከሚያመርቱ ድርጅቶቿ መኻል ደግሞ "ኔስሌ" ስመ ጥሩው ነው። ይህ የቸኮሌት ፋብሪካ ያለ ዕረፍት የሚያመርት ቢሆንም እንኳ ሰንብኚዎች ዘወትር በሩ ክፍት ነው። እግር ጥሎት ስዊትዘርላድን የረገጠ ሰው የኔስልን ፋብሪካ የመጎብኘት ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ከጥሬው ካካዋ እንሥቶ እስከ ቸኮላት እሽጋ ድረስ የምርት ሂደቱ በግልፅ ይታያል። የተለያዩ ቀስማት ያላቸው ፈላሽ ቸኮሌቶች እሳልፎ በሚያሳይ ፕላስቲክ ቱቦ ውስጥ ወዲህ ወዲያ ይፈሳሉ።

ታዲያ ድርጅቱ ሰጎብኚዎች አስቀድሞ የሚሰጣቸው መመሪያዎች አሉ። አንደኛ፤ ማንም ሰው ምንም ዓይነት ምግብ፣ በተለይ ቸኮሌት ይዞ ወደ ፋብሪካው መግባት አይችልም (የምግብ መበከል ስለሚያሳስባቸው ከጦር መሣሪያ ባልተናነሰ ጎብኚዎች ምግብ መያዝ አለመያዛቸውን አበጥረው ይፈትሻሉ)። ሁለተኛው፤ በፋብሪካው ቆይታ ማንም ሰው የፈለገውን ያህል ቸኮላት መብላት ይችላል። ሦስተኛው ደግሞ፣ "ማንም ሰው ቁራጭ ቸኮሌት ከፋብሪካው ውስጥ ይዞ መውጣት አይችልም" የሚሉ ናቸው።

የዚህ ዓለም ኑሮአችን በጥቂቱ የኔስል ቸኮሌት ፋብሪካ መርሕን የሚከተል ይመስላል። ወደ ዓለም ስንመጣ መብል፣ ልብስ፣ ገንዘብ፣ ቤት፣ መኪና፣ ዲግሪ ወዘተርፈ ይዘን አልመጣንም። ሁሉን ያገኘነው እዚህ ዓለም ከገባን በኋላ ነው። በምድር ስንኖር ለመኖር የሚያስፈልገንን ሁሉ በአግባቡ የመጠቀም መብት አለን፤ እግዚአብሔርም የዕለት እንጀራችንን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል። ነገር ግን በሞት ከዚህ ዓለም ስንለይ አንድም ነገር ይዘን መሄድ አንችልም። በዓለም ያለው ሁሉ ለዕለት ፍጆታ ነው። የምንኖረው ለረዥም ዘመን ቢሆንም እንኳ የሰማዩን አባታችንን እንድንለምን የታዘዝነው የዕለቱን ብቻ ነው። ለሳም አጥተው፣ ከሰው ተጣልተው፣ ፈሪሐ እግዚአብሔርን ረግጠው ብዙ ሀብት የሰበሰቡ ሰዎች



የመሄጃቸው ቀን ደርሶ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ስትለይ ከሁለት ሜትር ጨርቅና ከአንድ ሳጥን በቀር የሚመደብላቸው በጀት የለም። እሱንም ይዘውት እንዲሄዱ ሳይሆን እስከሬናቸው እንዲሸፈንበትና ዐፅማቸው እንዲያርፍበት ነው።

ነገር ግን ሐዋርያው ዝቅ ብሎ እንደጻፈው (፩ጢሞ. 6፡ 18-19) እውነተኛና ዘላለማዊ ሃብት ዛሬ ምንም የሌላቸውን በመርዳት፣ ለተቸገሩ በጎ በማድረግ፣ ለጎደላቸው በማካፈል የምንሰበስበውና በሚመጣው ዓለም የምናገኘው በሰማይ ያከማቸነው ሃብት ብቻ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ፊሊ. 4፥11, ዕብ. 13፥5, እዮብ 1፥21**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ! በዚህ ዓለም ስኖር የሚያስፈልገኝ ጥቂት እንደሆነ አውቄ፣ የዕለት እንጀራዬን እንደምትሰጠኝ ባንተ ታምኜ፣ ከመጎምዠትና ከስስት ተጠብቄ፣ በትጋት ሠርቼ፣ ያገኘሁትን በረከት ለጎደላቸው በማካፈል አንተ ስትመጣ የምወርሰውን ዘላለማዊ ባለጠግነት እንዳሰብ እርዳኝ። አሜን።*

# 7
# የፍቅር ነፀብራቅ

*"አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ።" ዮሐ. 15፥9*

ብርሃን ማረፊያና መንፀባረቂያ ካላገኘ አይታይም። ለዚህ ነው በጨለማ የእጅ ባትሪያችንን ወደ ሰማይ ስናበራ የማይታየው፣ ወደ መሬት ስንዘቀዝቀው ግን ማረፊያ ስለሚያገኝ ብርሃኑ ተንፀባርቆ ይታየናል። የፀሐይ ብርሃን ከ93 ሚሊዮን ማይልስ ርቀት ወደ ምድር ሲመጣ የሚጓዘው በኅዋ ውስጥ ነው፤ ነገር ግን የብርሃኑ ጨረር ስንጥቆት የሚያልፈው ኅዋ ዘወትር ጨለማና ቀዝቃዛ ነው። ምክንያቱም የሙቀትና የብርሃን ኃይል ያዘለው ጨረር በኅዋ ውስጥ ማረፊያ የለውምና አይታይም፣ አይሞቅም። ያው ጨረር ግን ወደ ምድር ሲደርስ ይንፀባረቅና ያበራል፣ ይሞቃል።

ፍቅርም እንደዚሁ ነው፤ ተፈቃሪ በሌለበት አይታይም፣ አይታወቅም። እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ፍቅር የሆነው እኛን ሲወድ ብቻ አይደለም። እንዲያ ከሆነማ እኛ ባልነበርንበት ዘላለም ውስጥ እግዚአብሔር ፍቅር አልነበረም ልንል ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሳይፈጠርም በፊት ፍቅር ነው። ፍቅሩ በዘላለም ውስጥ ያረፈውና ያንፀባረቀው በልጁ ላይ ነው። እርሱ የክብሩ መንፀባርቅ እንደ ሆነ ሁሉ የፍቅሩም መንፀባርቅ ነው። አባት ልጁን ይወዳል። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ "አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል።" (ዮሐ. 3፥35) የሚለን። የሥላሴ አስተርዕዮ (መገለጥ) በታየበት በዮርዳኖስ ጥምቀት አብ ስለ ልጁ ሲመሠክር "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።" (ማቴ. 3፥17) ብሏል። ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ ድነታችን ሲጽፍ "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።" (ቆላ. 1፥14) በማለት መንግሥቱ የተሰየመው የፍቅሩ ማረፊያ በሆነው በልጁ እንደሆነ ጽፎልናል። ይሄ ሁሉ የሚያሳየን የአብ ዋነኛ የፍቅሩ መገለጫ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ነው።

"አብ ለወልድ ያለውን ፍቅር ማወቅ ለምን አስፈለገን?" እንል ይሆናል። ምክንያቱ ይህ ነው፤ እኛ የተወደድነው በራሳችን ሳይሆን በልጁ ነው። የተወደድንበትም ፍቅር ልጁ የተወደደበት ፍቅር ነው። ልጁ በዘላለም



ውስጥ የተወደደበትን ፍቅር ካላወቅን እኛ የተወደድንበትን ፍቅር ልክ ማወቅ አንችልም። ጌታ ኢየሱስ እኛን የወደደበት ፍቅር እርሱ ራሱ በአብ የተወደደበት ፍቅር ነው፤ *"አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፣ በፍቅሬ ኑሩ።"* (ዮሐ. 15፥9) ብሏልና። ወደ አብ ከመሄዱ በፊት በጸለየው የምልጃ ጸሎትም *"እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላከኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደወደድኋቸው ያውቃል . . . እኔንም የወደድህባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን . . ."* (ዮሐ. 17፥23-26) በማለት እሱ በዘላለም ውስጥ በተወደደበትና እኛ በተወደድንበት ፍቅር መኻል አንዳች ልዩነት እንደሌለ አስታውቆናል። ይህ ፍቅር *"ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅ የሚያልፍ ነው"* (ኤፌ. 3፥18)

በዚህ ዐይነት መለኮታዊ ፍቅር፣ በዘላለማዊ ልጁ ልክ መወደዳችን አያስደንቅም?! እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍቅር በልጁ ላይ እንዳንፀባረቀ፣ የልጁም በእኛ ላይ እንዳንፀባረቀ፣ በእኛ አማካይነት በዙሪያችን ባሉ ወንድሞችና እኅቶች ላይ ሊያንፀባርቅ ይገባል። ብርሃን የሚታየው ማረፊያ ሲያገኝ ነውና በእኛ ያደረው የእግዚአብሔር ፍቅር በሌሎች ላይ ማረፊያ ያግኝ።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ዮሐ. 5፥20፤ 17፡26፤ 3፥35**

## ጸሎት

| |
|---|
| *ቅዱስ አባት ሆይ፦ ምንም የሚያስወድድ ነገር ሳይኖረኝ ዘላለማዊ ልጅህን በወደድክበት መጠን ስለ ወደድኸኝ አመሰግንሃለሁ። አሁንም ይህ ፍቅርህ በእኔ ሳይገደብ በእኔ በኩል ወደ ሌሎች መፍሰስ እንዲችል የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል እንድጨክን ጸጋን አብዛልኝ። አሜን።* |

# 8
# ልኬት

*"የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፡ ብዙዎችም የሚረከሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፡ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ . . . ተጠንቀቁ።" ዕብ. 12፥15-17*

በልጅነቴ ቤታችን ከተገዙ ነገሮች ሁሉ የማይረሳኝ ነገር ቢኖር መኪና ነው። የአዲስ አበባ መንገድ እንደዛሬው ባልተጨናነቀበት ዘመን በቤታችን የራሳችን መኪና ቆሞ ማየት የሚፈጥረው የኩራት ስሜት ልዩ ነበር። በአዲሷ መኪናችን ብሔራዊ ቤተመንግሰት አካባቢ ያለውን ቁልቁለት ለንወርድ አባታችንን ፍጥነት እንዲጨምር በመማጸን የሚፈጠረው ልብ የሚነጥቅ ስሜት፣ ሠፈር ውስጥ ሰው በታመመ፣ እርጉዝ ምጧ በተፋፋመ ቁጥር በራችን ሲንኳኳ የሚፈጠረው የተፈላጊነት ስሜት እንደ ልጅ በአዕምሮዬ የማይረሳ ትዝታ ጥሎ አልፏል።

ታዲያ አባቴና እናቴ በመከራ ቆጥበው የገዟት ቮልስ ቫገን በሌሎች ባለቤቶች እጅ አስኪበቃት የለፋች ስለነበረች አንዳንዱ ከፍሏ አይሰራም። ለምሳሌ፡- በመሪው አጠገብ ከሚገኙት የነዳጅ፣ የሙቀት፣ የዘይት ጠቋሚ መሣሪያዎች ውስጥ ከሚሠራው የማይሠራው ይበልጥ ነበር። አባቴ ሩቅ መንገድ የሚሄድ ከሆነ የነዳጁ መጠን ስለሚያሳስበው ከአሮጌ የመጋረጃ ማንሸራተቻ ባዘጋጀው የብረት ዘንግ የመኪናዋን የፊት ኮፈን ይከፍትና የነዳጁን ቋት በግማሽ ዐይኑ ወደ ውስጥ እያሾለቀ መጥኖ ያዘጋጃትን የብረት ዘንግ ወደ ውስጥ ይሰዳል፤ ከዚያም አውጥቶ ልኩን ያያል። ይህንን ትዕይንት ለስንት ጊዜ ያህል እንደተመለከትኩ ማስታወስ ባልችልም ባጭሩ የዕድገቴ አንዱ ክፍል ነበር። የአባቴ መኪና ነዳጅ ማለቅና ባትሪ መድከም የሱ ብቻ ችግር አልነበረም፤ ወደድንም ጠላንም ቤተሰቡን ሁሉ ያካትታል። ችግሩ የተፈጠረው ቤት ውስጥ ከሆነ ከየጓዳው፣ ጉዞም ላይ ከሆነ ከመኪና ወርዶ መግፋትና በነዳጅ ማደያው መንከራተት የማይቀር ዕዳ ነበር።

መኪና የተሰራው ለመንቀሳቀስ ነው። ለመንቀሳቀስ ደግሞ ነዳጅ ያስፈልገዋል። ሹፌር መኪናይቱን ከመዘወሩ በፊት የነዳጁን ልክ ማወቅ ይጠበቅበታል። ክርስትናም ጉዞ ነው። ዘላለማዊ የሕይወት ጉዞ።



የሕይወት ጉዞ እንዲሠምር የእግዚአብሔር ጸጋ ያስፈልገዋል። ጸጋ ደግሞ እንደ ነዳጁ ሊሞላም፣ ሊጎድልም የሚችል ነው። ስለዚህ በየጊዜው ልኩን ማወቅ ግድ ይላል። አለዚያ ችግሩ የግለሰቡ ብቻ ሳይሆን የእምነት ቤተሰቡ ሁሉ ይሆናል።

የዕብራውያን መልዕከት ጸሐፊ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ለማመንና ለመመስከር፣ ስለ ስሙም መከራን ለመቀበል ቀዳሚ ለነበሩት አሁን ግን ከጊዜው ብዛት፣ ከመከራው ጽናት የተነሣ ልባቸው ዝሎ ወደ ቀደመው የሕግ ሥርዓት ለመመለስ በማፈግፈግ ላይ ላሉት መሢሃዊ አይሁዶች ስለ ጸጋ መጉደል እያስጠነቀቀ ይጽፍላቸዋል። የእግዚአብሔር ጸጋ "ለራሳችሁ" ብቻ ሳይሆን በዙሪያችሁ ካሉት "ለየትኛውም" እንዳይጎድለው በማለት። ምክንያቱም በአንዱ ሕይወት የሚከሰተው የጸጋ መጉደል ውጤቱ ብዙዎች የሚረከሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ ማስጨነቁ እንደሆነና ችግሩ የአንዱ ቢሆንም መዘዙ ግን ወደ ሁሉ እንደሚደርስ ያስረዳል። "እንግዲህ የራሴንም ሆነ አብረውኝ ያሉትን አማኞች ጸጋ መሙላትና መጉደል እንዴት አውቃለሁ?" እንል ይሆናል፤ በእግዚአብሔር ከመደገፍ ይልቅ በራሳችን የምንታመንና የምንመካ ከሆንን የጸጋ ጠቋሚው "ጎዶሎ" እያበራ ነው። ከምሥጋና ይልቅ በሆነ ባልሆነው የምናጉረመርም ከሆነ ጸጋ "ባዶ ነኝ" እያለ ነው። በክርስቶስ ያገኘነውን የመንፈስ ብኩርና አያቃለልን ለምድራዊ በረከት የምናለቅስ ከሆነ በርግጥ የጸጋ ልክ "አደጋ" ላይ ነው። ለራሳችን ሞተን ለእርሱ እንድንኖር የገባነውን ቃል ኪዳን ረስተን ለዚህ ዓለም በመመቾት ጌታን የምናስቀና ከሆነ ጸጋ "ተሟጧል" ማለት ነው። ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? መኪና ለሚነዳ ሰው ነዳጁ ጎዶሎ ሲያበራ የሚሰጠው ፈጣን መፍትሄ በአቅራቢያ ወደ ሚገኘው ነዳጅ ማደያ ሄዶ መሙላት እንደሆነ ሁሉ በሕይወትም ጸጋ ሲጎድል መፍትሄው በሚያስፈልገን ጊዜ የሚረዳን ጸጋ ወደ ሚፈልቅበት የጸጋው ዙፋን በእምነት መቅረብ ነው። ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የሚያቀርበን ሊቀ ካህን ድካማችንን ተረድቶ ሊረዳን ዝግጁ ነውና ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት ቀርበን ምሕረትን እንቀበል፣ ለራሳችንም ሆነ ለእምነት ቤተሰቦቻችን ይልቁንም ጸጋ እንደጎደላቸው ለታየን ጸጋን እንለምን፤ የጸጋ ሁሉ አምላክ ይሞላብናል።

ተጫማሪ ንባባት፡- 2ቆሮ. 6፥1፤ ዘዳ. 29፥18፤ ዕብ. 4፥1

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ አንተ የጸጋ ሁሉ አምላክ ነህ። ያለ አንተ ጸጋ አንዳች መሆንም፣ ማድረግም አልችልም። አባክህ ጸጋ ሲጎድለኝ አንዳውቅ፣ በአምነትም ወደ ጸጋህ ዙፋን ቀርቤ መምላት እንድንችል አርዳኝ። ሌሎች ወገኖቼንም ጸጋ ሲጎድላቸው አይቼ ከማማትና ከመፍረድ ይልቅ ጸጋ ይሰጣቸው ዘንድ እንድማልድ አርዳኝ። አሜን።*



# 9
# አንዳችን አንተኛ!

*«እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም።» መዝ. 121፡4*

ጊዜው እ.አ.አ መስከረም 7፣ 1940 ዓ.ም ነው። ዓለምን ለመቆጣጠር የተነሳው አዶልፍ ሂትለርና እሱ የሚመራው የጀርመን ናዚ ጦር የትኩረት አቅጣጫቸውን በመቀየር ሎንዶንን በአየር መደብደብ የጀመሩበት ዕለት ነበር። ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ገደማ 617 ተዋጊዎችን የጫኑ 348 የጦር አይሮፕላኖች ሎንዶንን ቀለበት ውስጥ አስገብተው ከሰማይ በሚዘንብ እሳት አጋይዋት። ሕንጻዎች እንደ ወረቀት ተቀዳደዱ፣ ግንቦች እንደ ልጆች መጫወቻ ፈራረሱ። ወደ መቶ የሚጠጉ ቦታዎች በእሳት ተያይዘው ይምቦገቦጉ ጀመር፣ ጢሱ የእንጉዳይ ቅርጽ ይዞ ሰማዩ ላይ እንደ ፈኛ እየተከመረ ምድሪቱን ከደናት። በከተማዋ ላይ የሚያስተጋባው ኃይለኛ የማስጠንቀቂያ የጩኸት ድምፅ፣ ወዲህና ወዲያ ሚሯሯጡ ወታደሮች ኮቴ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች ጩኸት፣ ከሚዘንበው ቁጣ ለመሸሽግ የሚራወጠው ሕዝብ ግርግር ትዕይንቱን የዓለም መጨረሻ አስመስሎታል።

ለ 57 ቀናት ያለማቋረጥ በቀጠለው በዚህ ድብደባ የለንደን ነዋሪዎች ሌሊቶችን የሚያሳልፉት ባገኙት መጠለያ ውስጥ ሲሆን የመሬት ውስጥ የባቡር ጣቢያዎች ዋነኛ መሸሸጊያ ሥፍራዎች ነበሩ። በአንድ ወቅት 177,000 በላይ የሚሆኑ ሰዎች በእነዚህ የምድር ውስጥ መሸሸጊያዎች ውስጥ ያድሩ ነበር።

40ኛ ዓመቷን በቅርቡ ያከበረችው ኤሚሊ ከቤተሰቧና ከጓደኞቿ ጋር በአቅራቢያቸው በሚገኘው የመሬት ውስጥ የባቡር ጣቢያ ላለፉት 32 ሌሊቶች አሳልፋለች። ኤሚሊ በዚያ በማይመች ሥፍራ ለማደር ይዛ የመጣችው ብርድ ልብሷንና መጽሐፍ ቅዱሷን ብቻ ነበር። ምንም እንኳ ከጫጫታውና አንዳንዴም የጀርመን አውሮፕላኖች ሲመጡ ከሚፈጠረው ፍርሃትና ግርግር የተነሳ ለማንበብ ፈጽሞ የማይመች ቢሆንም ሌሊት ላይ ሁሉ ሲተኛ መጽሐፍ ቅዱሷን ታነባለች።

የጀርመን አይሮፕላኖች እንደሚመጡ የሚያሳውቀው የሳይረን ድምጽ በሚያስተጋባበት አንድ ምሽት ኤምሊ አንድ ቤተሰቦቿን፣ ወዳጆቿንና በመጠለያው የነበሩትን ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነገር አደረገች፤ ብርድ ልብሷን

ጠቅልላ ለመሄድ ተነሳች፤ ወዴት እንደምትሄድ ሲጠይቋት ቆፍጠን ብላ ወደ ቤቷ እንደምትሄድና ከዛሬ ጀምሮ እዚያ እንደምታድር ነገረቻቸው። መጀመሪያ ከጭንቀቱ የተነሳ አዕምሮዋን የሳተች መሰላቸው ሆኖም ከብዙ ንግግር በኋላ ቁርጠኝነቷን አስረዳቻቸው፤ ካቅማቸው በላይ ስለነበር ተሰናበቷት። ኤሚሊ ወፍ ዝር የማይልበትን ጭር ያለ  መንገድ ይዛ ወደ ቤቷ አቀናች። ገብታ ምግቧን አብስላ ከበላች፣ ገላዋን ከታጠበች በኋላ የሌሊት ልብሷን ቀይራ ተኛች።

ያ ሌሊት ከወትሮው በባሰ መልኩ ሎንዶን ከተማ በናዚ የጦር አይሮፕላኖች የጋየችበት ነበር። ባካባቢያቸው የተካሄደውን የቦምብ ውርጅብኝ ያስተዋሉ የኤሚሊ ቤተሰቦች እዚያው ባሉበት በመሪር ዕንባ እርማቸውን አወጡ። ሲነጋና ድብደባው ጋብ ሲል ምንአልባት በድኗ ከተገኘ ለግብዐተ መሬት ለማብቃት ወደ ኤሚሊ ቤት አቀኑ። ዙሪያ ገባው ዶግ አመድ ሆኗል፣ አሁን ግምታቸው ወደ እርግጠኝነት ተቀየረ። ሆኖም ወደ ቤቷ ሲደርሱ ባስገራሚ ሁኔታ የሷ ቤት አልተነካም፤ ፈጥነው በሩን ሲያንኳኩ ግርምታቸውን ያባሰ ነገር ተፈጸመ፤ ኤሚሊ የሌሊት ልብሷን እንደ ለበሰች ከጥልቅ እንቅልፍ እንደነቃች በሚያስታውቅ ሁኔታ በሩን ከፈተችላቸው። ቤተሰቦቿ በደስታ ተጠመጠሙባት የደስታቸውን ምክንያት ለማወቅ «ምን አዲስ ነገር ተገኘ?» በማለት ጠየቀቻቸው። እነርሱም ዙሪያዋ ከፉኛ በጀት ሲደበደብ እንዳደረና መትረፏ እንዳስደነቃቸው ነገሯት። እርሷ ግን እንቅልፍ ድብን ስለ ወሰዳት ምንም እንዳልሰማች ነገረቻቸው። የኤሚሊ ቤተሰቦችና ወዳጆች ነገሩ ከአዕምሮ በላይ ስለ ሆነባቸው ኤሚሊ እንዴት ቤት ሄዳ ለማደር እንደ ወሰነች፣ ያ ሁሉ ድብደባ ሲካሄድ እንዴት እንቅልፍ እንደወሰዳት በጥሞና ጠየቋት፤ እሷም እንዲህ በማለት መለሰች «ከረዥም ጊዜ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ የማንበብ ልማድ ነበረኝ። እግዚአብሔርም ዘወትር በቃሉ ይናገረኛል። ይህ ችግር መምጣቱ ከቃሉና ከቃሉ ባለቤት ጋር ያለኝን ግንኙነት አላበላሸውም። አንድ ምሽት ባቡር ጣቢያ ውስጥ ተጠልለን ሳለ እንደ ልማዴ መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ «እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም። እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም።» የሚል ቃል አነበብኩ፤ እንኪያስ እግዚአብሔር እኔን ለመጠበቅ የማይተኛ ከሆነ እንዳችን መተኛት አለብን ብዬ ተኛሁ» በማለት ነገረቻቸው።



ዛሬስ እኛ እግዚአብሐር ሳይተኛ እየጠበቀን እኛም በፍርሃት መተኛት አቅቶን ይሆን? እርሱ ስለ እኛ እያሰበ እኛም ስለ ራሳችን በማሰብ ተወጥረን እየተጨነቅን ይሆን? እንግዲያስ ጭንቀትና ፍርሃታችንን አውጥተን እንጣልና በእግዚአብሄር መለኮታዊ ጥበቃ፣ መለኮታዊ እቅርቦትና መለኮታዊ ምሪት እንታመን። ያኔ ሥራችን የተሳካ፣ እንቅልፋችንም የጣፈጠ ይሆናል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ መዝ. 41፥2. ዘዳ. 33፥29, መዝ. 127፥2**

## ጸሎት

*አቤቱ፦ አንተ እንደ ቃልህ በዙሪያዬ የእሳት ቅጥርና ክብር ሆነህ ከክፉ ሁሉ ትጠብቀኛለህ። ሆኖም ይህ ጥበቃህ ፍሬ የሚኖረው እኔ ታምኜ ሳርፍበት ነውና በዚህ አጭር ታሪክ ውስጥ እንዳየኋት የእምነት ሴት ቃልህን ታምኜ በእረፍት እንድንኖር እርዳኝ።*

# 10
# የምኞት አባዜ

*"ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፤ ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፣ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፣ " ያዕ. 1፥14-15*

ለባላገሩ ውሻ የቅርብ ወዳጅ ነው። አባወራው ለአደን ሲወጣ፣ እረኛው ከብት ሲያሰማራ፣ እማወራዋ በጓሮ ስትሠራ ውሻ ከየትኛውም ትዕይንት የማይጠፋ የቤተሰብ አባል ነው። ሆኖም ዕድሜው እየገፋ ሲሄድ እንደ ድሮው ጮኾ ማባረር፣ ሰፈር ማስከበር ይሳነዋል። ታዲያ ሁስንተናው ሲዳከም የማይደከመው አንድ ነገሩ ብቻ ነው፤ ሆዱ! ባለቤቶቹ የዚህ የማይሠራ በላተኛ ነገር ይከነክናቸዋል። እንዳይገድሉት ከእጃቸው በልቶ ያደገ ነው፤ እንዳይተውት ቀለቡ መከራ ነው፤ እርቀው እንዳይጥሉት እሽትቶና አነፍንፎ ይመለሳል። ስለዚህ አንድ መላ መተዋል፤ ያረጀውን ውሻ አንገቱን ይይዙና አፍንጫው ጫፍ ላይ የበሰለ ቅቤ ይቀቡታል። እንደ ልማዱ ተኝቶ ሲያለከልክ ቅቤ ይሸተዋል፤ የት እንደሚሸተው ስለማያውቅ አፍንጫውን ወደ መሬት ተክሎ ያነፈንፋል። በተራመደ ቁጥር ወደሚሸተው ቅቤ የተጠጋ ስለሚመስለው እያነፈነፈ ይራመዳል፤ በተስፋ መራመዱንም ይቀጥላል፤ በቅርብ ያሸተተውን ቅቤ ለመብላት ባለው ጉጉት ተውጦ ወዳሸተተው ሳይደርስ ከቤቱ እንደወጣ ይቀራል። እሽትቶ ወደ ቀድሞው ቤቱ እንዳይመለስ የአፍንጫው ቅቤ ሌላ ነገር የማሽተት አቅሙን ስለሚያዳክም የመጣበት አቅጣጫ ግራ ስለሚገባው ወጥቶ ይቀራል፣ በዚያው ይሞታል።

የዚህ ዓለም ገዢ በሥጋ ምኞት ተነድፈን፣ ከሕይወት ርቀን እንድንቅበዘበዝ ለማድረግ የሚጠቀምበት ሥልት ካነበብነው የውሻው ታሪክ ጋር ይመሳሰላል። ምኞት እንደ አፍንጫ ቅቤ እየሳበ ያታልላል እንጂ ሆድ አይሞላም። እዳኝ ለታዳኙ የሚወደውን የሚያቀርብለት ሊቀልበው ሽቶ ሳይሆን በምኞቱ ገብቶ ሲያጠምደው ስለሚፈልግ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን ነቅተን ልንጠብቀው፣ ተግተን ልንቃወመው የሚገባ ቀንደኛ ጠላት ቢኖር ምኞት ነው። ዛሬ ትል ነው ብለን የናቅነውና የቀለብነው ምኞት፣ ነገ አድጎና ገዝፎ ሲነድፈንና ሊውጠን ይከጅላል። በሥጋ ከዓለም ጋር በምናደርገው የትኛውም



ተራክቦ ምኞት መጸነሱ አይቀርም። ይህ ጽንስ በጊዜ ካላጨነገፍነው በስተቀር አድጎ ኃጢአትን ብሎም ሞትን መውለዱ አይቀሬ ነው። ስዚህ ደግሞ ምኞትንና ራዕይን መለየት ግድ ይላል። የምንለየውም በዚህ ነው፣ ምኞት ከኋላ ሆኖ እያስቸኮለ ይነዳል፣ ራዕይ ግን ከፊት ቀድሞ በወዝብና በአውሎ ንፋስ ውስጥ በእርጋታ ይመራል።

በዘመናችን በባለጠግነት ምኞት ተነድፈው ስንቶች በጥፋትና በመፍረስ፣ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ፣ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተናም ወጥመድ ወደቁ!? ስለዚህ በምኞት ተይዘን ርቀን ሳንሄድ ቶሎ ወደ አባታችን ቤት በንስሓ እንመለስ። "ያደቆነ ሳያቀስስ አይለቅም" የሚለው አገራዊ ብኂል ሳይፈጸምብን ፈጥነን በጠላት ሓሳብ ላይ እንንቃ፤ ስለ ሥጋ ማሰብን ትተን በላይ ያለውን የሚያስበውን የክርስቶስን አእምሮ እንያዝ።

ምኞት በተፈጥሮው የምንጠላው ነገር ሲሆን አይችልም። ማንም ሰው የሚጠላውን ነገር አይመኝም። ምኞት ግን ስናየው የሚያምረን፣ ስናስበው የሚያስጎመዠን፣ ስናገኘው የሚያስመካን ነገር ነው። ስለዚህ በወጥመዱ ስንያዝ አይታወቀንም እንቁራሪት ከፈላ ውሃ ውስጥ ተስፈንጥራ እንደምትወጣ ነገር ግን ቀዝቃዛው ውሃ ቀስ በቀስ ሲሞቅ ሳይታወቃት በሙቀቱ እየተዝናናች ተቀቅላ እንደምትሞት እኛም ምኞት ወደ ኃጢአትና ሞት መስወጡ ሳይታወቀን ጉድ እንዳይሠራን ልንጠነቀቅ ይገባናል። በምኞት ፈረስ መጋለብ ስጊዜው ደስ ይላል፤ ችግሩ ገደሉ ጋ ሲደረስ ልጓም አለመኖሩ ነው። ምኞት ፈረስ እንጂ ልጓም የለውም። ምኞት ከኋላ ሆኖ ይነዳል እንጂ ከፊት ሆኖ አይመራም። "ውሃ ሲወስድ እሳስቆ" እንዲሉ እያስደሰተና እያዝናና በኃጢአት ሰፈር አቋርጦ ወደ ሞት አገር ይነዳል። ለምኞት መፍትሄው አንድ ነው "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ" ገላ. 5፥24 እንደሚል ሥጋና ምኞቱ ወዳከተሙበት ወደ ከርስቶስ መስቀል በእምነት መመልከት ብቻ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፦ መዝ. 7፥14፤ እዮብ 15፥35፤ ምሳሌ 7፥6-23**

**ጸሎት**

*ጌታ ሆይ፦ በዚህ ጥቂት ዘመኔ ብዙዎች በሥጋ ምኞት ተነድፈው ከሕያዋን መንደር፣ ከጥበቃህ ሰፈር ሲወጡ አይቻለሁ። መግቢያውን እንጂ መድረሻውን ሳላይ በምኞት ተጠፍሬ በምሕረትህ ያገኘሁትን ክቡር ሕይወት እንዳላጣ ጠብቀኝ። አንተ ዘወትር የነፍሴ ምኞት ሁንልኝ። አሜን*



# 11
# ልውጠት

*"የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።" ሮሜ 12፥2 [አ.መ.ት]*

አጠገብዎ ያለ ሰው በትከሻዎ ላይ አባ ጨጓሬ እየሄደ መሆኑን ቢነግርዎ ወዲያውኑ ምን ይሰማዎታል? ደስ እንደማይሎት መገመት አያስቸግርም። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎች ይህ ሲነገራቸው ሊጮሁ ወይም ያልተጠበቀ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ። አባ ጨጓሬ ምኑ ደስ ይላል? ነገር ግን በምትኩ በትከሻዎት ላይ ያረፈችው ቢራቢሮ መሆኗ ቢነገርዎ ደስ ሊሎት እንደሚችል አያጠያይቅም። ቢራቢሮ ለማየት ከሚማርኩና ደስ ከሚያሰኙ ፍጥረታት መካከል አንዷ ናት። በሕብረ ቀለም አጊጣ በክንፏ ወደ ላይ ከፍ ከፍ ስትል፣ በአበቦች ላይ አርፋ ስትቀስም፣ የሚያምሩ ክንፎቿን ስታርገበግብ ታይታ አትጠገብም። ነገር ግን ዛሬ በውበቷ የማረከችዎ ቢራቢሮና የተጸየፉት አባ ጨጓሬ አንድነታቸውንና ተዛምዷቸውን ምን ያህል ያውቃሉ? ደግሞ አባ ጨጓሬና ቢራቢሮ ምን አገናኛቸው? ይሉ ይሆናል። ይህ የለውጥ ኃይል ነው። ቢራቢሮ በቅጠሎች ላይ እንቁላል ትጥላለች፣ እንቁላሉ አድጎ ሲፈለፈል አባ ጨጓሬ ይወጣል፤ አባ ጨጓሬው ቅጠል እየበላ ያድጋል። አንድ የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርስ *'ክሪሰለስ'* የሚባል ቅርፊት መሰል ነገር ከውስጡ ያመነጭና ራሱን በቅርፊቱ ውስጥ ቀብሮ በግንድ ላይ ይንጠለጠላል። በዚህ መልኩ ሕይወት አልባ በድን መስሎ ሳይንቀሳቀስ ለረዥም ጊዜ ይቆይና በቅጽበት አንድ ቀን በቅጽበት ቅርፊቱ ቢራቢሮ ከውስጡ ተፍትልካ ትበራለች።

ይህ ሂደት በግሪክ ቋንቋ *'ሜታሞርፎሲስ'* በመባል ይታወቃል። *'ሜታሞርፎ* ለውጥ ማለት ሲሆን *'ሜታሞርፎሲስ'* የለውጥ ሂደት ማለት ነው። ይህን ትንግርት መሳይ ለውጥ "ለውጥ" [Change] የሚለው ቃል ብቻውን ሊገልጠው ስለማይችል ነው "ልውጠት" [Transformation] የሚለውን ቃል ለመጠቀም የተገደድነው። ልውጠት 'አሁን ያለው፣ በፊት የነበረው ነውን?' ለሚለው ጥያቄ "አይ፥አዎ" የሚል መልስ ይሰጣል። "አይ፥አዎ" ማለት በአንድ በኩል "አዎን!" በሌላ በኩል ደግሞም "አይደለም!" እንደ ማለት ነው። ምክንያቱም የአሁኑ የቀድሞው ሆኖ ሳለ

ነገር ግን ከቅርጽ ባሻገር የይዘት ለውጥ ስላመጣ፣ የአሁኑ የቀድሞው ነው ማለት ያስቸግራል። በሌላ በኩል ደግሞ የተቀየረው ራሱ ስለሆነ 'እሱ አይደለም' ለማለት ያስቸግራል። ለዚህ ነው 'ቢራቢሮ የሆነው አባ ጨጓሬው ነው?' ወይም 'ቢራቢሮው አባጨጓሬ ነበር?' ለማለት የሚያስቸግረን። ሆኖም እውነቱ 'አስገራሚና ተአምራታዊ ለውጥ ተለወጠ እንጂ ቢራቢሮ የሆነው አባ ጨጓሬው ራሱ ነው።

አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኙና ጌታው አድርጎ ሲቀበል በሕይወቱ የሚከናወነው ለውጥ [change] ሳይሆን ልውጠት [transformation] ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ጌታን ከማግኘታችን በፊት በነበረው ማንነታችንን እና ከዳንን በኋላ ባለው ማንነታችን መካከል ያለውን ልውጠት ለመግለጥ የተጠቀመበት የግሪክ ቃል *'ሜታሞርፎ'* የሚለው ነው። ይህ ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው ዳግም ስንወለድ ብቻ አይደለም። ድነንም በጌታ ሕጻናት ሳለን በሥጋ ሕይወት ቁጥጥር ሥር ያለው አዕምሯችን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሲሆን የሚከሰተውን ልውጠት ለመግለጽ ይህንኑ *'ሜታሞርፎ'* የተሰኘውን ቃል ይጠቀማል (ሮሜ 12፥2)። በመቀጠልም በጌታ መገለጥ ወቅት የተዋረደው ሥጋችን ተለውጦ የከበረውን ሥጋ ስንለብስ የሚከናወነውን የለውጥ አይነት ሲገልጽ ይህንኑ ቃል ዳግም ጥቅም ላይ ያውላል (2ቆሮ. 3፥18)።

የመንፈሳችን ልውጠት ባመንን ጊዜ ተከናውኗል፤ የሥጋችንም ልውጠት ጌታ ሲመጣ በጊዜው ይከናወናል። ነገር ግን አሁን በመከናወን ላይ ያለው የነፍሳችን ልውጠት እርሱም የአዕምሯችንን መታደስ ነው። ታዲያ ይህን ወሳኝ የለወጥ ሂደት ከንውን ምን ያህል እያስተዋልነውና እየተባበርን ይሆን? ለልውጠቱም ፍጥነት ቃሉን በመብላትና በማሰላሰል፣ በጸሎት በመትጋትና ፈቃዱን አውቀን በማድረግ ምን ያህል እስተዋጽዖ እያደረግን ይሆን?

**ተጨማሪ ንባባት፡- 1ጴጥ. 1፥14፣ ኤፌ. 4፥23፣ ቲቶ 3፥5**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ አንተ አትለወጥም! ነገር ግን ሁሉን ትለውጣለህ። "እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ" ብለህ ተስፋን ሰጥተሃል። አባክህ በአዕምሮዬ መታደስ እየተለወጥኩ የልጅህን መልክ እመስል ዘንድ ዕለት ዕለት ሥራኝ፣ ለውጠኝ። አሜን።*



# 12
# የሁመራ ቆይታዬ

*"ወደ አንተ እንዳይቀርቡ በልባብና በልጓም ጉንጫቸውን እንደሚለጕሙአቸው፥ ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።" መዝ. 32፥9*

ጊዜው በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር 1986 ዓ.ም ሲሆን የምገኘው ሰቲቱ ሁመራ ከተማ ነው። ከአዲስ አበባ መቀሌ ተጉዤ፣ ከመቀሌ ሽሬ እንዳ ሥላሴ ከርሜ ወደ መቀሌ መመለሻያዬ ሲቃረብ ሰቲቱ ሁመራ ሰላሉ ወገኖች ዝና ሰማሁና ሳላያቸው ላለመመለስ ወሰንሁ። የሽሬ ወገኖች "መንገድ የለም አባክህ አትሂድ!" ብለው ቢለምኑኝም አሻፈረኝ ብዬ ከሰቲት ሰሊጥ ሊያመጣ በሚሄድ የጭነት መኪና፣ መንገድ ባልወጣለት መንገድ ተከዜን ተሻግሬ፣ ወልቃይትንና በጠገዴን አቋርጬ ከአሥራ አምስት ሰዓታት ጉዞ በኋላ ከዚህ ቀደም በስም እንጂ በዐይን አይቼ የማላውቃት ሰቲቱ ሁመራ ደረስሁ።

በደሳላ ቤት ውስጥ በተዘጋጀልኝ መደብ ላይ ሌሊቱን ካሳለፍኩ በኋላ ሲነጋ ወጥቼ አካባቢዬን መቃኘት ጀመርኩ። ግራ ቀኝ ስመለከት አንድ ትኩረቴን የሚስብ ነገር አየሁ። ገበሬው በቤቱ አውድማ ላይ ከትልቅ የዋርካ ጉቶ ተፈልፍሎ በተሠራ ስታቴ መሳይ ነገር ውስጥ ወፍራም እንጨት ኢጋድሞ፣ እንጨቱን ከግመል ጋር አስሮ ግመሉን ያዞረዋል። አዟዟሩ ገርሞኝ በተመሰጦ ስመለከት የግመሉ ዐይን በጥቁር ጨርቅ እንደተሸበበ አስተዋልሁ። ጥቂት ተራምጄ ወደ ገበሬው አጥር ከተጠጋሁ በኋላ ምን እየሠራ እንደሆነ ጠየቅሁት። የሰሊጥ ዘይት እየጨመቀ እንደሆነ ነገረኝ። ጥያቄዬን በመቀጠል የግመሉን ዐይን ለምን በጥቁር ሻሽ እንዳሰረ ጠየኩት። "ዐይኑ ካልታሰረ በጄ ብሎ አይዞርም፣ ካልዞረ ደግሞ ዘይቱ አይጨመቅም፤ አሁን እሱ መኖውን ስለበላና በቂ ውሃ ስለ ጠጣ የሚያስበው ጉዞ ላይ መሆኑን እንጂ እዚህ እየዞረ እንዳለ አያውቅም" አለኝ። በቆምኩበት ስለ ግመሉ ሥነ-ልቦና ማሰብ ጀመርኩ። ለራሴ "ይሄኔ እኮ ግመሉ በሱ ቤት በረሃ እያቋረጠ ነው" አልኩ። ወዲያው መለስ ብዬ ጠላት የሰውን የልብ ዐይን ባለማወቅ ጨለማ ሸብቦ፣ በመምሠል አባዜ ደልሎ ፈቃዱን ለመፈፀም እንዴት እንደሚጠቀምበት ማሰብ ጀመርኩ።

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ክቡር ፍጡር እንጂ እንደሚጠፉት እንስሳት አይደለም። ሰውን ከእንስሳት ልዩ የሚያደርገው ልቦናው ነው። መልካምና ክፉን ፈትኖ ለማወቅ፣ የሚጠቅመውን ከሚጎዳው ለመለየት ልቦና ተሰጥቶታል። ልቦናው ከታወረ ግን ሰውም እንደ እንስሳ ይሆናል። የሚያደርገውን አያውቅም፤ ብቻ ስሜቱ ወደ ነዳውና ወደ መሰለው አቅጣጫ ይነጉዳል። ሰው ገንዘብ ሲያሳውረው፣ ሥልጣን ሲያስከረው፣ ፍትወት ሲያሾረው፣ ቅናት ሲሰብቀው፣ ጥላቻ ሲያጦዘው፣ ዝና ሲያናውዘው የሚያደርገውን አያውቅም፣ የፊትና የኋላውን አያስብም፣ ነገን አይመለከትም፣ ለሌሎች ስሜት አይጠነቀቅም፤ የሚጋልበው ሌላ ነውና ልቡን ለማድመጥ፣ ኅሊናውን ለመስማት ቀልብ የለውም። ይልቅ በሳዩ ላይ የተፈናጠጠውን ፈቃድ ለማድረስ በስሜቱ ይጋልባል፣ በሃሳቡ ይፈረጥጣል።

ይህ ዕጣ ከክርስቶስ ሕይወት ርቀው ለሚኖሩ ዓለማውያን ብቻ አይደለም። በአዕምሯችን መንፈስ ካልታደስን በቀር አማኞችንም አይምርም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *"እንግዲህ አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ . . . ።" (ኤፌ. 4፥17)* በማለት አማኞች እንደ እንስሳት በአዕምሮ ከንቱነት ከመመላለስ እንዲታቀቡ፣ በአምሯቸው መንፈስ እንዲታደሱና አሮጌውን አስወግደው አዲሱን ሰው እንዲለብሱ የሚመከረው። እንግዲህ እኛም እንደ ሰቲት ሁመራ ግመል በጽድቅ እየተጓዝን እየመሰለን የኃጢአት ስሊጥ እንዳንፈጭ ልቦናችንን ያበራልን ዘንድ፣ የዐይናችንንም መሸፈኛ ያነሳልን ዘንድ እግዚአብሔርን ልንማጸን ይገባል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ምሳሌ 26፥3፣ ያዕ. 3፥3፣ እዮብ 35፥11**

**ጸሎት**

| |
|---|
| *ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ድካሜን ታውቃለህ፣ በአዕምሮዬ ባለመታደሴ ምክንያት በከንቱ ኑሮ ተጠምጄና ተታልዬ የጠላትን ሃሳብ እንዳላስተናግድ ብርሃንህን ላክልኝ። የክርስቶስን አዕምሮ ስጠኝ፣ ፈቃድህንም አስታውቀኝ፣ የምንታዘዝበትንም ጸጋ አብዛልኝ። በኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ስም አሜን።* |



# 13
# አልችልም?

*"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።" ፊሊ. 4፥13*

በዚህ ከተማ ይህ ዓይነቱ የሰርከስ ትርዒት ሲታይ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። የከተማው ሰዎች ፈረስ የሚያስጋልበውንና ለቀናት ሲተከል የቆየውን ሰፊ ድንኳን አጨናንቀው ትርዒቱ የሚጀመርበትን ደቂቃ በጉጉት ይጠባበቃሉ። ወዲያው አንዳች የሚያህል ዝሆን በአንድ ፍሬ ልጅ እየተጎተተ ወደ መድረኩ ሲወጣ ተመለከቱ። ዝሆኑ ልጁ በሚሰጠው ትዕዛዝ እየተመራ የሚያስደንቁ ትዕይንቶችን ማሳየቱን ቀጠለ። ተመልካቹም በጭብጨባ፣ በጩኸትና በፉጨት አጀበው።

ሆኖም ከተመልካቾቹ መሃል አንዱን የመሰጠው ከዝሆኑ ትርዒት ጀርባ ያለው ሌላ እውነት ነው። *"ይህን የሚያህል ትልቅ አውሬ በዚህ አንድ ፍሬ ልጅ ትዕዛዝ እንዴት ሊገዛ ቻለ?"* ዝግጅቱ ተጠናቆ ሰው ሁሉ ወደ የፈናው ሲያመራ ይህ ሰው ወደ መድረኩ ጀርባ በመሄድ ለዝግጅቱ መሪ የከነከነውን ጥያቄ አቀረበለት። መሪውም *"የሰርከስ ዝሆኖች ታድነው የሚያዙት በልጅነታቸው ነው። "ኬዳ" ብለን እንጠራቸዋልን "ያልተገራ" እንደማለት ነው። "ኩሚስ" ወይም ለማዳ እስኪሆኑ ድረስ ሳቃይ በሞላበት ሥልጠና ውስጥ እናሳልፋቸዋለን። ከሥልጠናዎቹ አንዱ በሁለት ዛፎች መሃል ፈጽሞ ሊበጠስ በማይችል ጠንካራ ገመድ እናስረውና ምግብ ብቻ እየሰጠን ለረዥም ጊዜ እንተወዋለን። ያልተገራው ወጣት ዝሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የታሰረበትን ገመድ ለመበጠስ ባለ በሌለ ኃይሉ ሲታገል ይከርማል። እየገረፍን ያዘዝነውን እንዲያደርግ እናስገድደዋለን፤ ካላደረገ ሕመሙ እንዲጸናበት እናደርጋለን። ከረዥም ጊዜ በኋላ እንፈታውና ከዚህ ቀደም ከተገሩ 'ኩሚስ' ዝሆኖች ጋር እንዲያሳልፍ እንተወዋለን። ውሎ አድሮ አዕምሮው የታሰረበትን ገመድ መበጠስ እንደማይችል ስለሚያምን በትንሽ ገመድ ብታስረውም በጥሶ ለመሄድ አይሞክርም።"* በማለት ተረከለት።

እኛም ዛሬ የተገለጠልንን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ስንነሳ "አትችልም! አትችይም!" የሚል ድምጽ ፈጥኖ ይከበናል። በልጅነታችን ከወላጆቻችን፣ ከጎረቤቶቻችንና ከመምህራኖቻችን የሰማናቸው አሉታዊ

ንግግሮች ሕሊናችንን ያጨናንቃሉ። የእኛም አእምሮ ይህንን ተቀብሎ ያስተጋባል። *"እኔ ጥቁር ስለሆንሁ፣ ቋንቋ ስለማልችል፣ ዲግሪ ስሰሌለኝ፣ የመጣሁት ከማይታወቅ ብሔረሰብ ስለሆነ እንዲህና እንዲህ መሆን አልችልም"* እንላለን። እነዚህ ድምፆች ድምፅ ብቻ ቢሆኑ ባልከፋ ነበር፤ ነገር ግን ከታሪካችን፣ ከገጠመኞቻችን፣ በዙሪያችን ካሉ ጠንቅቀን ከምናውቃቸው እውነታ መሰል ከስተቶች ጋር ተዛምዶ ሰላላቸው ያለማመንታት እንድንቀበላቸው ጫና ያደርጉብናል። በእርግጥም የቀድሞ ያልተሳኩ ሙከራዎቻችንን፣ የኑሮ መደባችንን፣ የገንዘብ አቅማችንን፣ የትምህርት ደረጃችንን፣ የቆዳ ቀለማችንን . . . የምንመለከት ከሆነ እንደ *"ኩሚስ"* ዝሆን በውስጣችን ታላቅ ኃይል ይዘን በታናሽ እጅ የምንመራ፣ ሳንወድ የሌላውን ፈቃድ የምናደርግ የጠላት መጫወቻ ልንሆን እንችላለን። ነገር ግን በቀድሞ የሽንፈት ታሪካችንና በአሁኑ ውጪያዊ ገጽታችን ላንፈታ በውሰጣችን ያለውን ከሁሉ የሚበልጥ ኃይል እርሱም ክርስቶስን ከተመለከትን "አትችልም! አትችይም!" የሚለንን የሐሰት ድምፅ *"ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላሰሁ!"* በሚል የድል ድምፅ ሽረን የተገለጠልንን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሳችን ዘመን ፈጽመን ማለፍ እንችላለን።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ዮሐ. 15፥5፤ 2ቆሮ. 12፥9፤ ኤፌ. 3፥16**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ላንተ የሚሳንህ የለም! አንተ ችለህ ታስችላለህ። ተቃውሞ በሞላበትና በማይመስል ሁኔታ ውስጥ ያለፍርሃት ፈቃድህን ማድረግ አችል ዘንድ በፍርሃትና ባለማመን ከተያዝሁበት ማንኛውም ሥጋዊ አሰተሳሰብ ፍታኝ። አንተ ለሥራ ስትነሳ እኔም "በክርስቶሰ እችላለሁ!" ብዬ አብሬህ እንድንነሳ ጸጋን አብዛልኝ። አሜን።"*



# 14
# ራስን መተዋወቅ

*"ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ። አርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና፡- መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም ክርስቶስ ማለት ነው። ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልክቶ፡- አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው።" ዮሐ. 1፥41-43*

ዕድገቱና ኑሮው በገሊላ ባሕር ላይ የተመሠረተው ሰምዖን ወንድሙን እንድሪያስን ቀኑን ሙሉ አላየውም።[1] የዓሣ ማጥመዱን ሥራ ጥሎ የተሰወረበትን ምክንያት ለማወቅ አልቻለም። ማለዳ ከጓደኞቹ ጋር ዮሐንስ ወደ ሚያስተምርበትና ወደ ሚያጠምቅበት ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ እንደሄደ ቢያውቅም እንዲህ የሚያስመሸው ጉዳይ ይኖራል ብሎ አልገመተም። ይህን እሳብ እያወጣና እያወረደ ሳለ ድንገት አንድ ሰው ወደ እርሱ እየተንደረደረ ሲመጣ ከሩቅ ተመለከተ። ወንድሙ እንድርያስ ነበር። ከወትሮው ለየት ባለ የጋለ ሰላምታ ያጣድፈው ጀመር። ሰምዖን በወንድሙ ሁኔታ በመገረም "ምን ቢያገኝ ነው እንዲ የሚፈነጥዘው?" በሚል የፍንደቃውን ምሥጢር ለማወቅ ቸኩሏል። ደሰታና መገረም ተቀላቅለው በእንድሪያስ ፊት ላይ ይነበባሉ።

እንድርያስ ሕይወቱን ቀኝ ኋላ ያዞረውን ከሰተት ሊሸሽገው አልቻለም፤ ትንፋሹ ቁርጥ፣ ቁርጥ እያለ "መሢሕን አገኘነው፣ አሥር ሰዐት ያህል አብረነው አሳለፍን፣ በእርግጥ እሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።" አለው። "መ-ሢ-ሕ?" ሰምዖን ጆሮውን ማመን አልቻለም። "ነቢያት የተናገሩለትን፣ ቅዱሳት መጽሐፍት የመሠከሩለትን፣ እስራ ሁለቱ ነገዶች በናፍቆት ጠብቀው ያላዩትን፣ የእስራኤልን ተስፋ፣ የዓለምን ንጉሥ አገኘሁት! ነው የምትለኝ?" የማይመሥል ነገር ሆነበት። ሆኖም ወንድሙን ሊጠራጠር አልቻለም። አንድን ነገር በሚገባ ካላጣራ በስተቀር በቀላሉ የማይቀበል፣ የሰከነ ሰሜት ያለው መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። ሰምዖን ጊዜ አልወሰደም "እና... እኔንም ልታሰተዋውቀኝ ትችላለህ?" አለው የሰማውን ለማየት በተጣደፈ ድምጽ። "አዎን ማንም ሊቀርበው የሚችል፣ ከውጪ ስታየው

[1] በዮሐ. ፩፥41-43 ላይ የተመሠረተ የጸሐፊው ምናባዊ ዕይታ ነው።

ፈጽሞ የማይመስል፣ ስትቀርበው ግን ከውስጡ የሚወጣው ቃል ሕይወትህን የሚለውጥ አስገራሚ ሰው ነው።" አለው ትኩስ ትዝታውን እንደ ገና በሕሊናው እየሳለ። ስምዖን ከተቀመጠበት ተነሳ፤ ሥራ ላይ የዋለበትን ልብሱን አራግፎ፣ መጎናጸፊያውን ደርቦ እንድርያስ በመጣበት አቅጣጫ አብረው ነጎዱ።

ስምዖን ነገሩ ሕልም ይሁን እውን መለየት ተስኖታል። እግሮቹ በደመ-ነፍስ ይራመዱ እንጂ ልቡ ቀድሞ ሄዷል። ድንገት ከስመጠበት የሃሳብ ስመመን ባነነና "አሁን በእግዚአብሔር የተቀባውን ፊት ለፊት ላየው ነው? ላነጋግረው ነው?" በማለት ራሱን ጠየቀ። አጠገቡ ሲደርስ እንዴት ራሱን ለመሢሑ እንደሚያስተዋውቅ ያወጣና ያወርዳል። ሳይታወቃቸው በፍጥነት ይራመዱ ነበርና ቀን እንድርያስና ጓደኛው ኢየሱስን ተከትለው ወደ ሄዱበት ቦታ ደረሱ። ኢየሱስ በአንድ የበሰስ ዛፍ ሥር ድንጋይ ላይ ተቀምጧል። እንድርያስ ጠጋ ብሎ ሰላምታ ሰጠውና ወደ ጎን ፈቀቅ ብሎ ቆመ። ስምዖንም እንዴት ራሱን እንደሚያስተዋውቅ እያሰበ "ስ-ም-ዖ-ን እባላለሁ፤ የ-ዮ-ና ልጅ ነኝ ..." ለማለት ሲዳዳው ኢየሱስ ቀደም ብሎ በተረጋጋ ድምጽ "አንተ ስምዖን ነህ..." አለው። ስምዖን ራሱን ሳያስተዋውቅ ስሙ በመጠራቱ ተገርሞ "ይሄ እንድርያስ የቤታችን ሚስጥር አንድም አልቀረውም፤ ሁሉን ነግሮታል" በማሰት አሰበ። "ስምዖን መሆንህን በማወቄ ምን ይገርምሃል! ይህንንማ አንተን የሚያውቁ ሰዎች ሁሉ ያውቁታል፤ ይልቅ ልንገርህ አንተ ኬፋ ነህ! ጴጥሮስ! ዓለት ነህ! ለመቅደስ መሠረት የሚሆን ጽኑ ዓለት"።

ስምዖንና እንድርያስ ጊዜው ለሰ መሸ ቆይታቸውን ፈጽመው ወደ ቤታቸው ለመመለስ መንገድ ጀምረዋል። ስምዖን ግን በተለየ ስሜት ውስጥ ሰምጧል "እኔ ጴጥሮስ ነኝ? ጽኑ ዐለት? የመሠረት ድንጋይ?" በማለት ራሱን ይጠይቃል። ራሱን ሊያስተዋውቅ ሄዶ፣ ራሱን ተዋውቆ መመለሱ አስገርሞታል። በእርግጥ ስምዖንን በዐለትነት ማንም አያውቀውም፤ ወላጆቹም እንዲህ አያውቁትም፤ ሌላው ቀርቶ እርሱ ራሱ እንኳ ራሱን እንዲህ አያውቀውም። ዛሬ ግን ገና በሆድ ሳይሠራ ከሚያውቀው ጋር ተገናኘና ራሱን ተዋወቀ።

ዛሬ ስንቶቻችን ነን ራሳችንን ወላጆቻችን፣ ጓደኞቻችን፣ ዘመዶቻችን፣ መምህራኖቻችን... ወ.ዘ.ተ እንዲህ ነህ! እንዲህ ነሽ! ባሉን ተስማምተን



"እኔ እኮ እንዲህ ነኝ!" እያልን ያልሆነውን እየዘመርን የምንኖር? ኢየሱስ ክርስቶስን ስናገኝ ግን ዓለም ሳይፈጠር በሚያውቀን፣ በእናታችን ሆድ ሳንሠራ በመረጠን፣ እውነተኛ ማንነታችንን ሊነግረን በሚችል ጌታ ፊት እንቆማለንና ያኔ ከእውነተኛ ማንነታችን ጋር እንተዋወቃለን። እሱን ማወቅ ራስን መተዋወቅ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ዘፍ. 17፥5.15፤ 32፥28፤ 35፥10-11**

## ጸሎት

*ውዱ ጌታ፦ ዕቃን እንኳ ጠንቅቆ የሚያውቀው የሠራው ነው። እኔንም ከአንተ በላይ የሚያውቀኝ ማንም የለም። ለራሴ ራሴን ያወቅሁ ቢመስለኝም ዕውቀቴ ውሱን ነው። የእኔ ማንነት የተሰወረው በአንተ ውስጥ ነው። አንተን ሳውቅ ያን ጊዜ እውነተኛ ራሴን በአንተ ውስጥ አውቃለሁ። አባክህን ራስህን ግለጥልኝ። እንዳውቅህ እርዳኝ። ቃልህ የሚለኝን "ነኝ!" ለማለት፤ የማይለኝን "አይደለሁም!" ለማለት የጽድቅ ድፍረትን ሙላኝ። አሜን።*

# 15
# ግደልና ስቀለው!

*“የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከከፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።” ገላ. 5፡ 24*

የ11 እና የ12 ዓመቴን የልደት ሻማ ያጠፋሁት ጅማ ከተማ ውስጥ ነው። አባቴ የባንክ ሠራተኛ ስለነበር ለሥራ ሲቀየር የተወሰነ የቤተሰቡን ክፍል ይዞ ስለ ሄደ ራሴን ጅማ አገኘሁት። ጅማ እባብ በሽበሽ ነው። በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ እባብ ያየሁት እዚያ ነው። ቤት ውስጥ፣ ጓሯችን፣ ከቤታችን ውጭ ያሉ የአትክልት ሥፍራዎች ውስጥ እባብ አይቼ አውቃለሁ። የጅማ ልጆች *“እባብ ተገኘ”* ሲባል ከአዲስ አበባ እንደመጣሁት እንደ እኔ አይደነግጡም፤ ተረባርበው በእጃቸው በያዙት ነገር ይገድሉና ጫወታቸውን ወይም ሥራቸውን ይቀጥላሉ።

አንድ ቀን ጥሻ ውስጥ እባብ ተገኘና ከአካባቢው ሰዎች ጋር ተባብረን ቀጥቅጠን ገደልነው። ሞቷል ብለን ልንሄድ ስንል አንድ ጠና ያሉ ሰው ቁጣ በተቀላቀለበት ድምጽ *“እባብ ተገድሎ መሬት ላይ አይተውም፤ የሞተ ቢመስልም ከሄዳችሁ በኋላ አፈር ልሶ ይነሳል። ከገደላችሁ በኋላ ዛፍ ላይ ወይም አጥር ላይ መሰቀል አለባችሁ”* አሉን። የዚህን አባባል እውነትነት በሳይንሳዊ መንገድ ባላረጋግጥም በአገራችን በብዙዎች ዘንድ ስለሚታመንበት አንዳች ተጨባጭ ምክንያት እንደሚኖረው እገምታለሁ።

የእግዚአብሔር ቃል ከክርስቶስ ጋር ለኃጢአት እንደሞትን፣ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ ይነግረናል። ሆኖም ሞቷል የተባልነውና መሞቱን በእምነት የተቀበልነው አሮጌ ሰዋችን እንዳንዴ ሕያው ሆኖ ሲሠራ እናየውና ግራ እንጋባለን፤ *“ከሞተ እንዴት በእኔ ውስጥ ሊሠራ ቻለ?”* በማለት። አሮጌው ሰዋችን በእርግጥ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል፤ ሞቷል። ሆኖም ይህን ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት በክርስቶስ የተሠራ እውነት ዛሬ በእኛ ውስጥ እውን ለማድረግ መውሰድ የሚገባን እርምጃ አለ፤ ይኸውም ወደ ኃጢአት ብሎም ወደ ሞት ከሚወስደን የምኞት መንገድ መመለስ፣ የሰውነታችን ክፍሎች በሥጋችን ውስጥ ለሚሠራው የኃጢአት ምኞት እንዳይታዘዙ መከልከልና ጽድቅ፣ ምሕረት፣ ፍቅር፣



ንጽሕና የሞላበትን ማንኛውንም በጎ ምግባር ለማድረግ ራሳችንን ማስለመድ ነው።

ለኃጢአት የሚገዛው አሮጌው ማንነታችን ቢሞትም በሥጋችን ውስጥ የሚኖር የኃጢአት ኃይል መኖሩን መዘንጋት የለብንም። ይህ የኃጢአት ኃይል እንደ በፊቱ ባይገዛንም እንኳ በሥጋ እስክንሞት ወይም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መጥቶ የትንሳኤ አካል እስክንለብስ ይኖራል። ስለዚህ ለኃጢአት ከክርስቶስ ጋር ሞቻለሁ ብለን ልንዘናጋ አይገባም። በማናቸውም ጊዜ ለሥጋ ምኞት እርነት ከሰጠንና እንደ ሥጋ ፈቃድ ከተመላለስን እኛ እዛውንት *“የተቀጠቀጠው እባብ አፈር ልሶ ይነሳል”* እንዳሉት ኃጢአት ሥጋዊነትን ልሶ ነፍስ ይዘራል።

ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *“ወንድሞች ሆይ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፣ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይሰጥ . . . “* (ገላ. 5፥13) የሚለው። በሌላም ሥፍራ *“እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፣ ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ።”* (ሮሜ 6፥12-13) ይላል። በተጨማሪም *“እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፣ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ።”* [ሮሜ 8፡13] በማለት አሮጌው ሰዋችን ከክርስቶስ ጋር ቢሞትም እኛ ከኃጢአትና ከሥጋ ምኞት ለይተን ካልሰቀልነው ሥጋዊነትን ይልስና ይነሳል። ስለዚህ ብቸኛ መፍትሄው ሥጋን ከከፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር መስቀል ብቻ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ሮሜ 6፥6፤ 1ጴጥ. 2፥11፤ ገላ. 5፥16**

## ጸሎት

*“ጌታ ሆይ ለኃጢአቴ ሞተህ በእኔ በሕያውነት በሚኖረው የትንሳዔ ኃይል በኃጢአት ላይ ድልን ለለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሆኖም ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ ዳግም እንዳይሠለጥንብኝ በእኔ ውስጥ እውን የሆነውን ሞትህን በእምነት ማወጅና ሥጋን ከከፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር መስቀል እንድችል እርዳኝ። አሜን።”*

# 16
# ሥራ የላትም?

*"እንዲሁም እናንተ ባሎች ሆይ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንዲሚካፈሉ አድርጋችሁ አክብሯቸው።" 1ጴጥ. 3፥7*

መች እንደሰማሁት ወይም የት እንዳነበብኩት በውል ትዝ አይለኝም እንጂ አንድ ትምህርት አዘል ተረት አስታውሳለሁ። ሰውየው ባለ ትዳር ነው፤ ሚስትም ልጆችም አሉት። ከቤት ውስጥ ወጥቶ የሚሠራና ደሞዝ የሚያገኝ እሱ ብቻ ነው። ሚስቱ በቤት ትሠራለች፣ ሆኖም እሱ ይህ "ትሠራለች" የሚለው ቃል አይዋጥለትም። ሰዎች ስለ ሚስቱ ሲጠይቁት "ሥራ የላትም!" ማለት ይቀናዋል። የርሷ በውጭ ተቀጥሮ አለመሥራትና ደሞዝ አለማምጣት ይከነከነዋል እንጂ የቤቱ፣ የልጆቹና የራሱ በእንክብካቤ መያዝ አይታየውም።

አንድ ቀን ምሽት ከመተኛቱ በፊት በአልጋው አጠገብ ተንበርክኮ *"ጌታ ሆይ! ምን አለ እኔም ሴት ሆኜ እንደሷ ቤት አርፍ ብዬ ብውል?"* በማለት ምርር ብሎ ጸለየ ይባላል። እግዚአብሔርም *"ጸሎትህን ሰምቻለሁ ወደ ሴትነት አቀይርሃለሁ"* በማለት ተናገረው። ማለዳ ሲነሳ አንድ የሚያስገርም ነገር ሆን፤ እንደ ምኞቱ ከባለቤቱ ጋር ጾታ ተቀያይረዋል። እሷ ባል ሆና ወደ ሥራ፣ ልጆቹም ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ እየተንጎዳጎዱ ነው። ቁርስ እንዲሠራና እንዲያቀርብ እንደሚጠብቁት ሲረዳ ከአልጋ ተስፈንጥሮ ወርዶ ምግብ ማብሰሉንና ልጆቹን ማልበሱን ተያያዘ። እብልቶ ሲጨርስ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት አደረሰ። ወደ ቤት ሲመለስ የሚታጠበው ዕቃ ተከምሯል፣ ልብሱ ተቆልሏል። አጣጥቦ እንደጨረሰ የሚገዛው የቤት ዕቃ ፊቱ ድቅን አለ። በዋጋው መናር እየተገረመ ገዛዝቶ ተመለሰና ለምሳና ለራት ምግብ ማብሰሉን ተያያዘው። ሆኖም የቤቱ ክፍሎች እያንዳንዱ መጽዳት ያስፈልጋቸው ስለነበር ከጽዳት ወደ ምግብ ዝግጅት፣ ከምግብ ዝግጅት ወደ ጽዳት ሲመላለስ ቆየ። መብራትና ውሃ የሚከፈልበት ቀን ነበርና አንድ እፍታ ወጣ ብሎ ከፍሎ መጣ። እንዴም እፎይ ሳይል ልጆች ከትምህርት ቤት የሚመጡበት ሰዓት



ደረሰ። ልጆቹን ካመጣ ልብሳቸውን እንዲቀይሩ፣ ምግብ እንዲበሉ፣ የቤት ሥራቸውን እንዲሠሩ ካደረገ በኋላ ባል ለሥራ የሚለብሳቸውን ልብሶች መተኮስ ጀመረ። እየተኮሰ ላለ ሰዓት ደርሶ ኖሮ እጅሬ ባል ከተፍ አለ።

ለቤተሰቡ ሁሉ ራት አቅርቦ ከተበላ በኋላ ባል ቴሌቪዥን ሲመለከት፣ ልጆች ጌም ሲጫወቱ እሱ የተበላበትን ዕቃ ሲያጥብና ለነገ የልጆች ምሳ ሲያዘጋጅ ሰዐቱ ከምሽቱ እራት ሰዐት ሆነ። እንዴም ሳይቀመጥና እፎይ ሳይል የመኝታ ሰዐት በመድረሱ እየተገረመ በድካም ሰብርብር ያለውን ሰውነቱን ለማሳረፍ ወደ መኝታ ቤት ሲሄድ እጅሬ ባል መኝታው ውስጥ ገብቶ ለፍቅር ጫወታ ይጠባበቀዋል። ምንም ቢደክመው አማራጭ አልነበረውምና አብሮ አሳለፈ፤ ከዚያ በኋላ ግን ከድካሙ የተነሣ ምድር ይሁን ሰማይ ሳያውቀው ጧ ብሎ ተኛ። ማለዳ ሲነቃ ወዲያው ከአልጋው ወርዶ እንዲህ ሲል እግዚአብሔርን ተማፀነ *"እግዚአብሔር ሆይ አጥፍቻለሁ፣ አንተንም ባለቤቴንም በድያለሁ፣ ድካሟን ፈጽም አልተረዳሁም፣ ዛሬ ግን ትልቅ ትምህርት አግኝቻለሁ፤ ከዚህ በኋላ በአክብሮት እይዛታለሁ፤ ስለ ሥራዋም አመሰግናታለሁ፤ ለአሁኑ ግን ምህረት አድርግልኝና አባክህን ወደ ወንድነቴ፣ ወደ ባልነቴ መልሰኝ"* በማለት ጸለየ። እግዚአብሔርም *"ጸሎትህን ሰምቻለሁ፣ ምህረትም አድርጌልሃለሁ፤ ነገር ግን ማታ በነበረህ ግንኙነት ስለጸነስህ ሚስትነትህ ለሚቀጥሉት ዘጠኝ ወራት ተራዝሟል"* አለው ይባላል።

ነገሩ ቀልድ ነው፤ መልዕክቱ ግን ትልቅ ነው። ዛሬ ሚስቶቻችን በቤት የሚሠሩ ባሎች ለድካማቸው ምን ያህል ዋጋ እንሠጣለን? የሚቆጠር ገንዘብ ባያመጡም እንኳ እኛ የውጭውን ግንባር ስንፋለም እነርሱ የቤቱን ግንባር በመፋለም ለኑሯችን ስኬት ትልቅ አስተዋጽዖ እያደረጉ እንደሆን ምን ያህል እንረዳለን? እኩል ድርሻ ያላቸው የቡድን አባላት እንደሆኑ ተገንዝበን ምን ያህል የሚገባቸውን ክብር እንሰጣቸውለን? /

**ተጨማሪ ንባባት፥ ኤፌ. 5፥25፤ 1ቆሮ. 12፥23፤ ቆላ. 3፥19**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ስለ ሰጠኸኝ የትዳር ጓደኛ አመሰግንሃለሁ፤ የሚስትነት፣ የእናትነትና የቤት አመቤትነት ድርሻዋን እንዳከብርና እንዳበረታታት ዘወትር ጸጋን አብዛልኝ። አሜን።*

# 17
# አገላብጠው!

*"እርሱም፦ ሄደሽ ከጐረቤቶችሽ ሁሉ ከሜዳ ባዶ ማድጋዎችን ተዋሺ ኢታሳንሻቸውም አላት። ገብተሽም ከአንቺና ከልጆችሽ በኋላ በሩን ዝጊ፥ ወደ እነዚህም ማድጋዎች ሁሉ ዘይቱን ገልብጪ የሞላውንም ፈቀቅ አድርጊ አለ።" 2ኛ ነገሥት 4፥3,4*

ከባለቤቴ ጋር ስንጋባ የነበረን ብቸኛ ንብረት አንድ ከእንጨት የተሠራ የመጽሐፍ መደርደሪያ ነበር። እሱንም ከዚህ ቀደም አብሬያቸው የኖርኩ ወገኖች ወደ አሜሪካ ሲሄዱ የተውልኝ ነበር። በሠርጋችን ማግሥት እኔ ወላጆች ቤት ኑሮ ጀመርን። በዓመቱ ጎጆ መውጣት አሰብንና በሌ ሚካኤል አካባቢ በአራት መቶ ብር ቤት ተከራየን። ችግሩ የቤት ዕቃ አልነበረንም። የእኔ የወር ገቢ ከ 320 ብር ወደ 620 ብር ያደገው በቅርብ ነው። ከተለያዩ ወጪዎች ተርፎ የቤት ዕቃ ለመግዛት የሚያስችል አቅም አልነበረውም። ሆኖም ወደ ተከራየነው ቤት ለመግባት ስለወሰንን የቤት ዕቃ ማምረቻ ከነበራቸው ከማውቃቸው ወገኖች ቁም ሳጥንና አንዳንድ ዕቃዎች በብድር ወሰድኩና ገባን።

ብድር መከፈያው ጊዜ ደረሰ እኔ እጅ ላይ ገንዘብ አልነበረም። ከታክሲ ወርጄ ወደ ቤት የሚወስደውን ኮረኮንች መንገድ እየተጓዝኩ በውስጤ ማጉረምረም ጀመርኩ። "ጌታ ሆይ አንተን እያገለገልኩ፣ በጽድቅ እየኖርኩ እንዴት ገንዘብ እቸገራለሁ?" ድንገት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ወደ ልቤ መጣ። ቃሉን ማሰላሰል የዘወትር ልማዴ ስለ ነበር አልገረመኝም። ሙሉ ታሪኩ በ2ኛ ነገሥት 4፥1-5 የሚገኝ ሲሆን ነቢዩ ኤልሳዕ ወደ እርሱ መጥታ የተማጸነችውን በዕዳ የተያዘችውን የነቢይ ሚስት የሰጣትን መፍትሄ ያመለክታል። እሷ መልስ የፈለገችው ለጊዜያዊ ችግሯ ቢሆንም እሱ ግን ዘላቂ መፍትሄ ሰጣት። በእግዚአብሔር መንፈስ የመከራት ከሰፈሯ ባዶ ማድጋዎችን ሰብስባ በሯን ዘግታ በማሰሮዋ ያላትን ጥቂት ዘይት ወደ ሌሎች ባዶ ማሰሮዎች እንድታገላብጥ ነበር። ባዶ ማሰሮዎቹም በተዓምራዊ መንገድ ሞሉ።

የእግር መንገዴን እየጠበጠብኩ ይህን ከፍል በጥሞና ሳሰላስል "አንተስ በእጅህ ምን አለ?" የሚል የውስጥ ድምጽ አነቃኝ። ከኋላዬ የተናገረኝ ሰው ያለ ይመስል ተገላምጬ ተመለከትኩ፤ ሁሉ የራሱን መንገድ



የሚሄድ እንጂ ከእኔ ጋር የሚያወራ አንድም ሰው አልነበረም። ፊቴን ከመንገደኛው መልሼ የተናገረኝን ድምጽ በውስጤ መፈለግ ጀመርኩ። "ጌታ ሆይ፦ እኔማ አንተ ከሰጠኸኝ ጸጋ ውጪ ሌላ ምን አለኝ?! ያለኝ አንተው የሰጠኸኝ የቃልህ መገለጥ ነው። እንደ ሌሎች ገፍቼ አልተማርኩ፣ ወይ አልነገድኩ" በማለት ማጉረምረሜን ቀጠልሁ። "አገላብጠው" የሚል ድምጽ ተሰማኝ። "ምኑን?" አልሁ። "በውስጥህ ያለውን ቃል" የሚል ነገር ተሰማኝ "በ-ኢ-የ-ሱ-ስ ስ-ም!" በማለት መገሰጽ ቃጣኝ። ደግሞ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዴት ነው ትርፍ ለማግኘት የማገላብጠው? ይሄ ከእኔ ይራቅ!" አልሁ። ጥቂት በዝምታ ከተራመድሁ በኋላ "እሺ ባገላብጠውስ እንዴት ነው የማገላብጠው? ብዬ ጠየቅሁ። "በወረቀት ላይ" የሚል ነገር ተሰማኝ። ጉዳዩ መጽሐፍ ከመጻፍ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ገባኝ።

ትምሕርቶቼን የሰሙ በርካታ ሰዎች በጽሑፍ እንዳሰፍረው ጠይቀውኝ ያውቃሉ፤ ሆኖም ከስንፍናና ተቀምጦ የመሥራት ትዕግሥት ከማጣት ውጪ ሌላ ምክንያት አልነበረኝም። ያን ዕለት ግን ቤት ከመግባቴ በፊት በር ላይ ቆሜ እያንኳኳሁ በውስጤ ያለውን ቃል በወረቀት ላይ ለመገልበጥ ወሰንኩ። ስወስን አንድ ሰው ኮምፒውተር ብርቅ በነበረበት በዚያ ዘመን የግል ኮምፒውተር ቤቴ ድረስ ይዞልኝ መጣ፤ እንዲት ታይፒንግ ተምራ የተመረቀች ከዚህ ቀደም አይቻት የማላውቅ ወጣት "እጄን ማፍታታት እፈልጋለሁ" ብላ ልትጽፍልኝ ቤት ድረስ መጣች። አንድ በቅርቡ ንግድ የጀመረና ሥራው የተባረከለት የማላውቀው ሰው መጽሐፍ እየጻፍኩ መሆኑን ሰምቶ "እኔ ማሳተሚያውን እችላለሁ" በማለት ማሳተሚያ ገንዘብ ላከልኝ።

በዚህ መልኩ በኩር መጻፌ "እምልኮ" በ1989 ዓ.ም ተወለደች። "እምልኮ"ን ሰዎች ተሻሟት፤ በአገር ውስጥም ሆነ በባሕር ማዶ በብዙዎች ተነበበች። እውነት ለመናገር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እኔም ሆንኩ ቤተሰቤ የሚያስፈልገንን ገንዘብ አጥተን አናውቅም። የዚህች መጽሐፍ ፍሬ የእኔን ዕዳ ከመከፈልና በቀጣይነት ገንዘብ ከማስገኘት የዘለለ ነበር። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች እጅ ገብታ ለብዙ ቤተሰብ በረከት ሆናለች።

ዛሬስ አንተ፣ አንቺ በእጃችሁ ያለ፣ በጓዳችሁ የተሰወረ አብሯችሁ የሚኖር ነገር ግን ጠቀሜታውን ያልተገነዘባችሁት ስንት ሃብት ይኖር ይሆን?

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ትልቅ ድል ለማምጣት ትልቅ ነገር ተጠቅሞ እያውቅም። በቤታችሁ፣ በሕይወታችሁ ያለ ትንሽ የምትሉት ነገር ለእናንተና ለማታውቋቸው እዕላፋት ትልቅ በረከት ሊያመጣ ይችላል። እንደ ሙሴ በትር፣ እንደ ጌዲዮን ችቦና ማሰሮ፣ እንደ ኢያኤል ካስማ፣ እንደ ሰሜጋር የበሬ መውጊያ ወይም እንደዚያ የገሊላ ወጣት አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ በእጃችሁ ያለው ነገር ለብዙዎች በረከት ሊሆን ይችላልና "እገላብጡት"

**ተጨማሪ ንባባት፡- ዘጸ. 4፥2፣ መሳ. 3፥31፣ 4፥21፣ 7፥20፣ ዮሐ. 6፥9**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ሰጥተኸኛል፤ እኔ ግን ያለኝን እንኳ አላውቅም። የተሳካላቸውን ሰዎች ሳይ አደንቃለሁ። "ታድለው!" እላለሁ። እነሱ የተለዩ ፍጡር ይመስሉኛል። እኔ እዚያ መድረስ እንደምችል፣ ከራሴ አልፌ ለሌሎች በጎ አስተዋጽኦ ላበረከት እንደምችል፣ ከራሴ ዘመን ባሻገር ለትውልድ የሚተላለፍና ለዘላለም የሚታሰብ ነገር ማድረግ እንደምችል አላውቅም። እባክህ በእጄ ያኖርከውን፣ ለእኔ ተራ መስሎ የሚሰማኝን፣ አንተ ግን ለብዙዎች በረከት ልትጠቀምበት የምትችለውን ነገር እንዳይ አይኔን ክፈት። እንድፈጽመውም ትጋትን ስጠኝ። አሜን።*



# 18
# ቀልደኛ

*"ትንታግንና ፍላፃን ሞትንም እንደሚወረውር እንደ ዕብድ ሰው፣ ባልንጀራውን የሚያታልል፡- በጨዋታ አደረግሁት የሚል ሰውም እንዲሁ ነው።" ምሳሌ 26 ፥ 18 - 19*

ባል በቅርብ ጊዜ ያገባትን ሚስቱን "ይሄ ቴሌቪዥኑ ላይ ያለው የሴት ልጅ ፎቶ የማን ነው?" ይላታል። "ተማሪ ሆኜ የወለድኳት ልጄ ናት" ትለዋለች። በመገረም "ታዲያ ከመጋባታችን በፊት ልጅ እንዳለሽ ለምን አልነገርሽኝም?" ይላታል። እሷም መልሳ "እይ ልጅ ካለሽ አላገባሽም ትለኛለህ ብዬ ፈርቼ ነው" ትለዋለች። ሃዘን፣ ንዴት፣ ጥርጣሬ፣ ግራ መጋባት በሞላበት ስሜት "ታዲያ አሁን ልጅቱ የት ናት?" በማለት ይጠይቃታል። "እኔ በጊዜው የማሳደግ አቅም ስላልነበረኝና እባቷም ስለ ካደ ታላቅ እህቴ ቤት አደገችና አሁን የሷ ልጅ ተብላ ትጠራለች" አለችው። ይቺ ሴት ከማግባቷ በፊት ልጅ የላትም። እንደው የሚሆነውን ለማየት ብላ በባሏ እየቀለደች ነበር። ቆይቶ ፎቶው የታላቅ እህቷ ልጅ መሆኑን ተረዳ።

ከአመታት በኋላ ሆዱን ያመውና ይተኛል። ሚስት በጣም ትጨነቃለች። ሆስፒታል መሄድና መታየት አለብህ ባላ ትወተውተዋለች። ያቅማማል፤ እሷ ግን የግድ ትለውና ሐኪም ቤት ይሄዳሉ። የተለያዩ ምርመራዎች ይደረግለትና ለውጤት ይቀጠራል። በውጤቱም ቀን ባልና ሚስት አብረው ይሄዳሉ። ጉዳዩን ጨርሶ ከሐኪሙ ቢሮ ሲወጣ ውጤቱን ለመስማት በመጓጓት ሐኪሙ "ምን አለህ?" በማለት በጉጉት ትጠይቀዋለች። "የሚያሳዝን ነው! ካንሰር አለብህ ነው የሚለኝ" ይላታል ቆፍጠን ባለ ድምጽ። ድንጋጤ ዋጣት፣ ላብ አስመጣት። ደጋግማ "ሃኒ እውነትህን ነው?" ትለዋለች። እሱም እውነት መሆኑን ያረጋግጥላታል። ሆኖም ሰውየው ካንሰር የሚባል እልነበረበትም፤ ሐኪሙም ፈጽሞ ስለ ካንሰር አላነሳበትም። የታመመው የምግብ አለመስማማት ነበር። ትንሽ ቆይቶ "ስቀልድ ነው" በማለት የፎቶውን ብድር እየመለሰ መሆኑን በፈገግታ ነገራት።

ይህን ታሪክ ስሰማ እኔም በ1982 ዓ.ም ከአንድ ጓደኛዬ ጋር የቀለድሁት አጉል ቀልድና ከሳይ ባስፈርኩት የእግዚአብሔር ቃል ከፍል የተገሠጽኩት ተግሳጽ ትዝ አለኝ። በዘመናችን በአማኙም መካከል ቀልድ ይዘወተራል። ልብ ቀጥ ሊያደርጉ የሚችሉ አስደንጋጭ ነገሮች ላይ መቀለድ እንደ ኃጢአት አይቆጠርም። ሰውን የሚጎዱ፣ እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ ቀልዶች እንደ ዘመናዊነት እንጂ እንደ ዓለማዊነት አይታዩም። እንደ "ፕራንክ" ያሉ አንዳንድ ልምምዶች የሥልጣኔ መገለጫዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። የሚመዘኑት ሰውን በማሳቃቸው እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ባላቸው ዋጋ አይደለም።

በከፍሉ ላይ የተጠቀሱት ሦስት ነገሮች ማለትም ትንታግ (እሳት) ፤ ፍላጻ (ቀስት) እና ሞት (የሚገድል ነገር) በሰው ሕይወት ላይ አደጋ የሚያደርሱትን ያህል ለጊዚያዊ ደስታና ለፈገግታ የሚሰነዘሩ አስደንጋጭ ቃላት ሰውን ይጎዳሉ። ምን አልባት ጉዳቱ ወዲያው አይታይ ይሆናል። ነገር ግን በዘላቂ አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጤንነት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው። ደግሞም አንድ ጊዜ ቃታ ከተሳበ፣ ሰይፉ ከሰገባው ከወጣና ነራዴው ከአፎቱ ከተመዘዘ በኋላ መልሶ መዋጥ ወይም ጉዳቱን መቀልበስ የማይታሰብ ነው። እንዲህ አይነት ንግግሮች ሰሚውን የሚጎዱ ብቻ ሳይሆን ተናጋሪውንም የሚያቀሉ ናቸው። በቀጣይም ተዓማኒነትን ያሳጣሉ።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ኤፌ. 5፥4፣ ኢሳ. 50፥11፣ ምሳሌ 24፥28**

### ጸሎት

*ጌታ ሆይ፡- ሰው የከንፈሩን ፍሬ እንደሚበላ፣ ከንግግራችንም እንደምንጸድቅና እንደሚፈረድብን ቃልህ ይነግረናል። ባለማስተዋል በቀልድ ሰም ሰዎችን ባስደነገጥሁት አባክህ ይቅር በለኝ። ከእንግዲህ ወዲያ እንዲህ ያለውን አንተ የምትጠላውን የሚሰሙትንም የማያንጸውን ከንቱ ነገር ከመናገር ጠብቀኝ። እንደበቴ የሚገድል መርዝ ሳይሆን ሕይወትን የሚሰጥ ቃል የሚወጣበት የሕይወት ምንጭ ይሁንልኝ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።*



# 19
# ጸረ-ቫይረስ

*"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምሥጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።" ፊሊ. 4፥6*

ሐጎስ የአንድ ዕርዳታ ድርጅት የሂሳብ ከፍል ኃላፊ ነው። አሜሪካ ለሚገኘው ዋና ጽህፈት ቤት ሪፖርት የሚያቀርብበት ጊዜ ደርሶበት ተወጣጥሯል። ምንም እንኳ እንደልማዱ ሁሉን በጊዜ ሰርቶ ቢያጠናቅቅም ሪፖርቱን ያስቀመጠበት ላፕቶፕ (የጭን ኮምፒውተር) በፍጥነት አልሠራ ማለቱ ውጥረቱን አባብሶታል። ሰወትሮው በአስገራሚ ፍጥነት የሚሠራው ዘመናዊ ኮምፒውተር ዛሬ አንድ መዝገብ ለመከፈት ረዥም ጊዜ እየፈጀበት አስቸግሯል።

ዐይኑን በላፕቶፑ ገፅ ላይ ተከሎ ይጠባበቃል፤ እያንዳንዱ ደቂቃ የዘላለም ያህል ረዘመበት። ስልኩን አንስቶ የመሥሪያ ቤታቸው አይ ቲ ከፍል ባለሙያ ጋ ደወለና የላፕቶፑን ህመም ዘረዘረለት። ባለሙያውም በጥሞና ካደመጠው በኋላ እርግጠኝነት በተሞላበት ድምፅ "ላፕቶፕህ በቫይረስ ተጠቅቷል" አለው። ሐጎስ ግራ ተጋብቶ ቫይረስ እንዴት እንዲህ ሊያደርግ እንደሚችል ጠየቀው። ባለሙያውም *"ኮምፒውተርህ የተሰራው እንዲያስብ ነው፤ በጣም ትልቅና ውስብስብ የሆኑ ነገሮችን በሰከንዶች ውስጥ አሰቦ መልስ የመስጠት አቅም አለው። ቫይረስ ትንሽ ፋይል ነው፤ ነገር ግን ራሱን እያበዛና አላስፈላጊ ሥራ እየፈጠረ እንዲጨናነቅ ያደርገዋል። ያንተም ላፕቶፕ የገጠመው ችግር ይሄ ነው። መፍትሄውም ቫይረሱን አጥምዶ የሚይዝና የሚያጠፋ ፀረ-ቫይረስ መጫን ነው። ያንንም እኔ ፈጥኜ አመጣልሃለሁ"* አለውና ስልኩን ዘጋ። ሐጎስም መፍትሄ በማግኘቱ ተደስቶ ሥራውን ቀጠለ።

ኮምፒውተር በሰው አእምሮ ምሳሌ የተፈበረከ የሰው እጅ ሥራ ነው። አእምሮ ደግሞ ከማንኛውም ኮምፒውተር በላይ ረቂቅ የሆነና ትልቅ ከህሎት ያለው የእግዚአብሔር እጅ ሥራ ነው። አእምሮ ልክ እንደ ኮምፒውተር የተሠራው ለማሰብ እንጂ ለመጨነቅ አይደለም። በለሳሙ ጊዜ ብዙ ሃሳቦችን ያለ ችግር ማስተናገድና መፍታት የሚችለው አእምሯችን በቫይረስ ከተጠቃ ትንሹ ትልቅ፣ ሜዳው ዳገት ይሆንበታል።

ይህ የአእምሮ ቫይረስ ጭንቀት ነው። ጭንቀት አንድ እሳብ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ራሱን ያበዛና አእምሯችን በሙሉ ኃይሉ እንዳይሠራ፣ ነገሮችን በሥርዓት እንዳያለብና ሥራውን በፍጥነት እንዳያከናውን ይገታዋል። ጭንቀት ችግራችንን ያወሳስበውና ያከብደዋል እንጂ ፈጽሞ ወደ መፍትሄ አያደርሰንም። ይልቅ መውጫውን እንዳናይ ሁሉን ያጨልምብናል።

በዘመናችን ይህ ቫይረስ በከፍተኛ ፍጥነት በአለም አቀፍ ደረጃ እየተሰራጨ ነው። ወጣቱ ይጨነቃል፤ አዋቂው ይጨነቃል፤ ድሃው ይጨነቃል፣ ሃብታሙ ይጨነቃል፣ የተማረው ይጨነቃል፣ መሃይሙ ይጨነቃል፣ ገጠሬው ይጨነቃል፣ ከተሜው ይጨነቃል። ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? መፍትሄው እንደ ኮምፒውተሩ ፀረ-ጭንቀት ወይም ጭንቀት ማርከሻ መጫን ነው። "የእግዚአብሔር ሰላም" ፀረ-ጭንቀት ነው። ይህ ሰላም ዋጋው ውድ ቢሆንም ለሰው ሁሉ በነጻ ተሰጥቷል። ይህን ሰላም ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማድረግ ያለበት አንድ ነገር ብቻ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን። ያኔ ሰላም ከነነፍሱ በውስጡ ይገባል። ይህም ሰላም ችግር እንዳይገጥመው፣ ፈተና እንዳይደርስበት፣ እንዳች እንዳይጎልበትና ጠላት እንዳይነሳበት የሚያደርግ ሰላም አይደለም። ነገር ግን በእነዚህ ሁሉ ውስጥ እንኳ የውስጥ እረፍትና እስተማማኝ ጸጥታ እንዲኖረው የሚያደርግ ሰማያዊ ሰላም ነው። ታዲያ ምን እንጠብቃለን? የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እየጠራን ይህን የማይደፈርስ ሰላም በውስጣችን እናስገባ። ያኔ አዕምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንንና እሳባችንን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ማቴ. 6፥25፤ ምሳሌ 16፥3፤ መዝ. 55፥22**

### ጸሎት

*ጌታ ሆይ አንተ የሰላም አለቃ ነህ! ጭንቀት በሞላበት ዓለም ሰላምን ትሰጣለህ። አንተ የምትሰጠው ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም። ያንተ ሰላም በውጭ ሁኔታዬ ላይ ያልተመሠረተ፣ በልብ የሚፈልቅ፣ በኑሮዬ ሁሉ ውጤታማ የሚያደርገኝ ሰላም ነው። አባት ሆይ ተጨንቄ አንዳች እንደማላመጣ አውቃለሁ፤ ዛሬ ሰላምህን እሻለሁ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምህ በልቤ ይፍሰስ። አሜን።*



## 20
## አጃቢ ፖሊስ

*"አንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።" ማቴ. 5፡ 23-26*

አቶ አብርሃም ላለፉት ሦስት ዓመታት እስር ላይ እንዳሉ የማያውቅ ጎረቤት የለም። የተያዙበት ሁኔታና የፍርዱ ሂደት ለሠፈርተኛው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ዛሬ በባለቤታቸው ድንገተኛ ሞት የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ለመገኘት ከወህኒ ቤት ተፈቅዶላቸው በሕዝብ መሐል ተገኝተው ወዳጅ ዘመድ እያሰናበቱ ነው። የእሥር ጊዜያቸውን ጨርሰው የተፈቱ የመሰላቸው ሠፈርተኞች "እንኳን ለደጀ ሰላሙ አበቃዎ! እንኳን አስፈታዎ!" እያሉ ሲጠመጠሙባቸው በለሆሳስ "ተፈትቼ አይደለም፤ ለቀብር ተፈቅዶልኝ ወጥቼ ነው። ሥነ-ሥርዓቱ ሲያልቅ ተመልሼ እሄዳለሁ" በማለት ያስረዳሉ።

"እሥር ቤት" በሕዝብ ዘንድ የተለመደ መጠሪያ ይሁን እንጂ ትክክለኛና ሕጋዊ ስሙ "ማረሚያ ቤት" ነው። ዜጎች በሰላም ለመኖር ተስማምተው ያወጡትን ሕግ የሚተላለፉ ሰዎች በማረሚያ ቤት ገብተው፣ ከነጻነታቸው ተገድበው ይማራሉ። ይህ መብት የሚሰጣቸው ዜጎች ብቻ ናቸው። አንድ አገር ማረሚያ ቤት የሚያስቀምጠው ዜጋውን ነው። ዜጋው ያልሆነውን ሰው እየቀለበ የማስተማር ግዴታ ስለሌለበት በ24 ሰዓት ከአገር ያባርረዋል። ዜጋውን ግን ወዴትም ማባረር ስለማይችል ከሕዝብ በሚሰበሰብ ቀረጥ በሚተዳደር ማረሚያ ቤት ያስገባዋል። በአለም ላይ ማረሚያ ቤት የሌለበት አገር የለም። የሰለጠኑና ሰላም የሰፈነባቸው እገሮች እንኳ ማረሚያ ቤቶች አሏቸው። የመንግሥት መዋቅር፣ የጸጥታ ኃይሎችና የሕግ የበላይነት የሌለባቸው ከተሞች በአፍታ ወደ ጨረባ ተዝካርነት እንደሚለወጡ ለማረጋገጥ ጥልቅ ምርምር አይጠይቅም።

ይህን ያህል የማረሚያ ቤትን በጎ ገጽታ ያነሳሁት በእግዚአብሔር መንግሥት ማረሚያ ቤት መኖሩን ለመናገር ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ቦታ ሳይሆን በቦታ ላይ የሚገለጥ የእግዚአብሔር አስተዳደር ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ዳግም በመወለድ ሰማያዊ ዜጋ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የሚኖሩበት ሕይወት ነው። በዚህ ኑሮ ውስጥ የሚያጠፉና ሕግ የሚጥሱ ይኖራሉ። ስለዚህ እንዲህ አይነት ሰዎች የሚማሩበትና የሚታረሙበት ማረሚያ ቤት መኖሩ የግድ ነው። የመንግሥቱ ዜጎች ስለሆኑ ይታረማሉ እንጂ ወደ ውጭ አይጣሉም። ስለዚህ በእግዚአብሔር መንግሥት "እሥር ቤት" አለ ማለት ነው።

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖር ሰው ጥፋት ባጠፋ ቁጥር አይታሰርም። ጥፋቱ ምንም ይሁን ይቅርታ በመጠየቅ "ንስሐ በመግባት" ፈጣን መፍትሄ ያገኛል። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግሥት ይቅርታን የሚያስከለክልና የሚያሳስር አንድ ጥፋት አለ። ይህን ጥፋት ያጠፋ ሰው ጥፋቱን እስኪያስተካክል ድረስ በእስር ይቆያል እንጂ ፈጽሞ አይፈታም። ይህ የሚያሳስር ጥፋት ይቅርታ አለመጠየቅና ይቅርታ አለማድረግ ነው። ወደዚህ መንግሥት የገባነው፣ በመንግሥቱም ውስጥ የምንኖረው እግዚአብሔር ይቅር ስላለን ብቻ ነው። ስለዚህ ይቅርታ ሰማይና ምድርን ቀስቶ የያዘ የመንግሥቱ ምሰሶ ነው። ይህን ምሰሶ የሚያፈርስ ሰው ሁሉ ይናድበታል። ሌላው መተላለፍና በደል ሁሉ በንስሐ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ያገኛል፤ ይቅርታን አለመስጠትና አለመቀበል ግን ፈቅደን እስከንሰጥ ድረስ ወኅኒ እንጂ ምህረት የለውም። ምህረትን እየረገጡ ምህረት ማግኘት አይቻልማ! ይቅርታን እየነፈጉ ይቅርታን መሰመን አይሆንማ!

የበደሉንን ይቅር አላልንም ማለት፣ አሰርናቸው ማለት ነው። ሌላውን ስናስር እኛም እንታሰራለን። በውጭ ስንታይ በነጻነት የምንኖር ስለምንመስል መታሰራችንን ሌሎች ላያስተውሉ ይችሉ ይሆናል። በገሀዱ አለም ነጻ ብንመስልም በመንፈሳዊው ዓለም የታሰርን ነን። ከእግዚአብሔር ይቅርታን ከማጣት በላይ ምን እስር አለ? ሌሎች የፈሰገውን ያህል ቢበድሉን እኛ እግዚአብሔርን የበደልነውንና የምንበድለውን ያህል ሊበድሉን አይችሉም። እኛ ብንምር በሰው ምንዛሪ ስለሆነ ጥቂት ነው፤ እግዚአብሔር ሲምረን ግን በእግዚአብሔር ምንዛሪ



ስለሆነ ብዙ ነው። ከእግዚአብሔር ይቅርታን እንድናገኝ የግድ ይቅር ማለት አለብን። ይቅር ካላልን ይቅር አልተባልንም ማለት ነው። ይቅር ካልተባልን ደግሞ ዕዳ አለብን። ዕዳችንንም እስከንከፍል እስረኞች ነን።

ምናልባት አንድ ሰው "ከሌሎች ወገኖች ጋር የተጣሉ፣ ዕርቅ ያላደረጉ፣ ይቅርታ ያልጠየቁ የማውቃቸው ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን በነፃነት ይኖራሉ፤ ያመልካሉም፤ እንዲያውም እንዳንዶቹ በኃይል ያገለግላሉ። ስለዚህ እንዴት እስረኞች ናቸው ትላለህ?" ሊል ይችላል። መልሱ ቀላል ነው። እነዚህ ሰዎች እንደ አቶ አብርሃም ለተወሰነ ጉዳይ በእጃቢ ፖሊስ ለጊዜው በቤተክርስቲያን ተገኙ እንጂ ተፈተው አይደለም። በአካል ባይታሰሩም ሰላማቸውና በረከታቸው የታሰረ ነው። ለመፈታት መፍትሄው መፍታት ብቻ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ሉቃስ 12፥58፤ ምሳሌ 25፥8፤ ማር. 11፥25**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ቃልህ "የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ይማራሉና" ይላል፤ ያንተን ምህረት በብርቱ ያስፈልገኛል፤ ስለዚህ በመንገዴ ሁሉ የሚበድሉኝን ሰዎች ይቅር እንድልና ምህረት እንድሰጥ እርዳኝ። ይቅርታ ባለማድረግ ምክንያት ሰላሜ፣ ደስታዬ፣ በረከቴ፣ ጤናዬ፣ አገልግሎቴ እንዳይታሰር ጠብቀኝ። አሜን።*

# 21
# የተቀቀለ ቀንድ

*"የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፤ ጎብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጓልና፤ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደተናገረ፣ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቶልናል፤ ማዳኑም ከሚጠሉንና ከወደረኞቻችን እጅ ነው።" ሉቃስ 1፥68-71*

ይህን ወግ የሰማሁት በማላስታውሰው የጨቅላነት ዕድሜዬ ቢሆንም በትውስታዬ ይኖራል። በጥንት ዘመን የነበሩ ሰዎች አውሬ ሲያስቸግራቸውና ለመግደል መሣሪያ ሲያጡ የሚጠቀሙበት በቤት ውስጥ በቀላሉ የሚዘጋጅ መሣሪያ ነበራቸው። ቀንድ በውሃ ይቀቅሉና ሙክክ ብሎ እስኪበሰል ይጠብቃሉ። ቀንድ ጠጣርና ደረቅ ነገር ነው፤ ሆኖም ለረዥም ሰዐት ሲቀቀል ይላላና እንደ ሥጋ ይሆናል። ይህን የለሰለሰና የላላ ሥጋ መሰል ነገር ለአውሬው ይሰጡታል። አውሬው ሥጋ ያገኘ ስለሚመስለው አኘኮና አላምጦ ይውጠዋል። ሆኖም በሰላም ወደ ሆዱ የገባው የበሰለ ቀንድ ጥቂት ቆይቶ ችግር መፍጠር ይጀምራል። ምክንያቱም ሲቀቀል የለሰለሰውና ሥጋ የመሰለው ቀንድ ቆይቶ ሲቀዘቅዝ ይጠነክራል፣ ተመልሶ ቀንድ ይሆናል። ያኔ የበላውን አውሬ ሆድ ይወጋል፣ ያሰጨንቃል በመጨረሻም ሆዱን ይቀድና ይገድለዋል።

ቀንድ በጥንቷ እስራኤል በርካታ ነገሮችን ይወክላል። በድል ቀን፣ በበዓል ቀን የሚነፋ መለከት ነው፣ መጠጫ ነው፣ የዘይት መያዣ ነው፣ የውጊያ መሣሪያ ነው፤ ከሁሉ በላይ የጥንካሬ፣ የኃይል፣ የክብር፣ የንግሥና፣ የገዢነት፣ የጽንዓት ተምሳሌት ነው። የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት ትንቢት ሲናገር *"ከጥንት ዘመን ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደተናገረ፣ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቶልናል"* በማለት በወቅቱ ገና በድንግል ማርያም ማህፀን ውስጥ ያለውን ጌታ ኢየሱስን "እግዚአብሔር ያስነሳው የመዳን ቀንድ!" በማለት ይጠራዋል።

ዓለማት የተፈጠሩበት ኃያሉና ብርቱው ጌታ ሥጋ ለብሶ በመምጣት በድካምና በውሱንነት ተገለጠ። ከዚያም በዐመፀኞች እጅ ታልፎ ተሰጥቶ በመከራ እሳት ተቀቀለ፣ ዐቅም እንደሌለው ረዳት እንደሌለው ሰው በሚጠሉት እጅ ተሰቃየ፣ በመከራ ሰለለ፣ በድካም ተንገላታ፣ በቀራንዮ



መስቀል ላይ ሞተ። ሞቱን ሰምተው ሲዖልና ሞት በደስታ ፈነደቁ፤ በሞት ላይ ሥልጣን ያለው ዲያቢሎስም እልል አለ። ነገር ግን ሥጋ መሰሏት የዋጠችው ሲዖል፣ ሥጋ መስሎት ያላመጠው ሞት በሦስተኛው ቀን ተጨነቁ፣ ተረበሹ፣ ታወኩ፤ ኢየሱስ ከሙታን ሲነሣ የሞትና የሲዖል ሆድ ተቀደደ። በመዳን ቀንድ መነሳት ሞት ራሱ ሞተ፣ ሲዖልም ተራቆተ። ሥጋ ብቻ መስሎትና ተታልሎ ያን የተቀቀለ ቀንድ የዋጠ አውሬ ሆዱ ተቀዶ እንደሞተ ሲዖልና ሞት ተመሳሳይ ዕጣ ገጠማቸው። የቀረው ግብዓተ-መሬታቸው ብቻ ነው፤ ያም የመዳን ቀንድ ዳግም ሲመጣ ይከናወናል። እስከዚያው በሰሙ ያመኑ ከሞትና ከሲዖል አምልጠው ሌሎችንም እያስመለጡ በድል ይኖራሉ። እውነትም የመዳን ቀንድ!

**ተጨማሪ ንባባት፦ ሕዝ. 29፥21፤ መዝ. 132፥17፤ ሐዋ. 3፥21፤**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ! ምን እልሃለሁ? ብርቱ ሳለህ ደካማ መስለህ ነገር ግን በዋጠኝ ሞት በሚባል አውሬ አፍ ገብተህ፣ ወደ ሲዖል ሆድ ወርደህ፣ በኃይል በመነሳት እኔንም ስላወጣኸኝ ማዳንህን የምገልጽበት ቃላት የለኝም። የመዳን ቀንድ ሆነህ ከሚጠሉኝና ከወደረኞቼ እጅ ስላዳንከኝ ለዘለዓለም ስምህ ይባረክ። አሜን።*

# 22
# ብቻውን አትላከው

*"ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።" ማቴ. 6፥19-21*

ወዳጄ በሙያው ነጋዴ ነው፤ የተዋጣለት ነጋዴ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ ከተቀበለ አመታት ተቆጥረዋል። ወዳጄ ለጌታ ያለው ፍቅር ሁል ጊዜ ትኩስ ነው። የጸሎትና የጥሞና ጊዜውን በፍጹም አያስነካም። አንድ ቀን በጫወታችን መሐል እንዲህ ሲል ጠየቀኝ "ሁል ጊዜ ማለዳ ገና ዶሮ ሳይጮህ ከአንቅልፌ እነሳለሁ። ቤተሰቤን እንዳልረብሽ ወደ ሳሎን እሄድና ድምጼን ከፍ አድርጌ ወደ ጌታ እጮሃለሁ። 'ጌታ ሆይ የሕይወቴ ዋና ነገር ልቤ ነውና ልቤን እሰጥሃለሁ፤ ውሰደው፣ ግዛው፣ የአንተ አድርገው' እላለሁ። ነገር ግን ነግቶ ተጣጥቤና ቁርስ በልቼ ወደ ሥራ ስሄድ ልቤ ቀድሞ ገበያ ገብቶ ሲያተራምስ አገኘዋለሁ። ያ በማለዳ ወፍ ሳይንጫጫ ተነስቼ በጸሎት ወደ ሰማይ የላኩት ልቤ ከመቼው ወደ ምድር ተመልሶ እንደሚያተራምስ ሲገባኝ አልቻለም። ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?" በማለት አፋጠጠብኝ።

የወዳጄን ጥያቄ እየሰማሁ ሳለሁ ወደ ውስጤ የመጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጌታ ደቀመዛሙርቱን በተራራ ላይ ሲያስተምር ስለ ገንዘብና ስለ ልብ ተዛምዶ የተናገረው ቃል ነው። የክፍሉ ሀሳብ ገንዘብ ስለመሰብሰብ ሲሆን ጌታ ትኩረት የሰጠው በሚሰበሰብበት ቦታ ላይ ነው። በትምህርቱ ሁለት መሰብሰቢያ ቦታዎችን ጠቅሷል። አንደኛው በምድር ሌላኛው በሰማይ። በምድር አትሰብስቡ፣ በሰማይ ሰብስቡ ካለበት ምክንያቶች አንዱ ገንዘባችን የሚሰበሰብበት ቦታ የልባችንን አድራሻ ከመወሰን አንጻር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ ነው።

ልብ ባለቤቱ የፈለገበት ቦታ መሆን አይችልም። የሚሆንበት ቦታ አስቀድሞ ተወስኗል *"መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።"* ተብሎ እንደ ተጻፈ ልብህ የሚከተለው ገንዘብህን ነው። ገንዘብህ የተሰበሰበውና የተከማቸው እዚሁ ምድር ላይ ብቻ ከሆነ ልብህን ምንም



ያህል በጸሎት ትጋት ወደ ሰማይ ብትልከው ተመልሶ መምጣቱ አይቀሬ ነው። መዝገብህ ባለበት እንዲሆን ታዟላ! መዝገብህ ያለው በሰማይ ከሆን ደግሞ ልብህን ባትልከውም በሰማይ ይሆናል። ገንዘብህ ባለበት በዚያ እንዲሆን ታዟላ!

የዚህን ዓለም ገንዘብ ወደ ሰማይ የምልከው እንዴት ነው? ብለህ ከጠየቅህ መልሱ ቀላል ነው። አንተ ወደ ባንክ ሂሳብህ ገንዘብ ለማስገባት የግድ ሂሳብህ ወደሚገኝበት ቅርንጫፍ መሄድ እንደማትገደድ፤ ነገር ግን ባቅራቢያህ በሚገኝ ቅርንጫፍ በመሄድ ገንዘብህን ሂሳብህ ውስጥ ማስገባት እንደምትችል እንዲሁ ገንዘብህን በሰምህ ወደ ሰማይ ማስተላለፍ ከፈለግህ በአቅራቢያህ የሚገኝ የእግዚአብሔር መንግስት ቅርንጫፍ ፈልገህ ማስገባት ነው። ያኔ ገንዘብህ ምድርን አልፎ ወደ ሰማይ፣ ጊዜን አልፎ ወደ ዘላለም፣ ሰውን አልፎ ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል። መለኮታዊ የገንዘብ ዝውውር ይሏል ይህ ነው!

ምናልባት የእግዚአብሔር መንግሥት ቅርንጫፍ ባቅራቢያዬ የት አገኛለሁ ያልክ እንደሆን የትኛውም የወንጌል እውነት የሚሰበክበት፣ ሰዎች ንስሐ እየገቡ ዳግም የሚወለዱበት፣ አጋንንት የሚወጡበት፣ በሽተኞች የሚፈወሱበት፣ ችግረኞች የሚረዱበት፣ ደቀ-መዛሙርት የሚፈሩበት፣ የነገ መሪዎች የሚሠሩበት ቦታ ካገኘህ ያ የመንግሥተ ሰማያት ቅርንጫፍ ነው፤ ፍጹም ሳትጠራጠር ገንዘብህን አስቀምጥ፤ በሰምህ ወደ ሰማይ ይሄዳል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ሉቃስ 12፥33፣ 1ጢ.ሞ.6፥19፣ ዕብ. 13፥5**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ! ገንዘቤን በምድር ከምሬ፣ በጓዳዬ ቀብሬ፣ በየባንኩ አስሬ ልቤን እንካ ብልህ፣ ልቤ በምድር ታስሯልና ወደ አንተ ሊደርስ አይችልም። ይልቅ ለማያልፈውና ለዘለዓለም ጸንቶ ለሚኖረው ለሰማያዊው መንግሥት ሥራ በማዋል፣ የሚበሉትና የሚጠጡት ለሌላቸው በማካፈል፣ በጤናና በዕድሜ ምክንያት ወይም ደጋፊዎቻቸውን በማጣት ምክንያት ለሚቸገሩ በማካፈል ልቤን፣ ሃሳቤን፣ ስሜቴንና ፈቃዴን በሰማይ እንዳኖር እባክህ እርዳኝ። አሜን።*

# 23
# ምርጥ ድህነት

*"በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።"*
*ማቴ. 5፥3*

የከተማችን ባለ አምስት ኮከብ ቅንጡ ሆቴል ወትሮም በሰው የተጨናነቀ ቢሆንም የዛሬው ጥቂት ለየት ያለ ይመስላል። በዋናው አዳራሽ ውስጥ አንድ የእንግሊዝ ኩባንያ ጨረታ ያወዳድራል። የከተማው አንኳር ቱጃሮች በአዳራሹ ተሰብሰበው የተሰጣቸውን ቁጥር እያነሱ የገንዘብ መጠን ይጠራሉ። የሚጠሩት ቁጥር የዋዛ አይደለም። አንዱ ከአንድ ጥግ 'አሥር ሚሊዮን' ሲል ሌላው ከአንድ ወገን 'አሥራ ሦስት ሚሊዮን' ይላል። መጀመሪያ ላይ የቁጥሩ ንረት እስፈሪ ነበር፤ የኋላ ኋላ ግን የጠሪዎቹን ዐቅም እየፈተነና እያዘገመ መጣ። ጠሪዎቹ ተዳከመው ከሚሊዮን ወደ መቶ ሺዎች፣ ከመቶ ሺዎች ወደ አሥር ሺዎች ገቡ።

በአዳራሹ ውጥረት ነግሦ አየር እንኳ መንቀሳቀስ ያቆመ በሚመስልበት ሁኔታ፣ መሪው ጨረታውን ለመዝጋት "አንድ . . . ሁለት . . ." በማለት እየቆጠረ ሳለ ከበስተኋላ አንድ ድምጽ ጸጥታውን ሰበረው። የተጠራው የገንዘብ መጠን ከፍተኛና ማንም የማይደፍረው ስለነበር የሁሉን ቀልብ ገዛ። ተሳታፊው የተናጋሪውን ማንነት ለመለየት ድምጹ በመጣበት አቅጣጫ ይመለከት ጀመር። የሆቴሉ ባለቤት የታዋቂው ቱጃር ድምጽ ነበር። የጨረታው መሪ የጠሪውን ማንነት ለመለየት ፊቱ ላይ የሚበራበትን መብራት በእጁ ጋርዶ አሾለቀ። ቁጥሩን ሲመለከት እላመነታም 'አንድ . . . ሁለት . . . ሦስት' ብሎ ጨረታውን ዘጋው። ረዥሙ ጸጥታ በሹክሹከታና በጉምጉምታ ተተካ። የጉምጉምታው መንስኤ የአሁኑ ክስተት ብቻ እንዳልሆነ በቀደሙት ሁለት ተመሳሳይ ጨረታዎች የተሳተፉ የከተማው ባለሃብቶች ጠንቅቀው ያውቃሉ። እኚህ ቱጃር ተሳታፊዎቹ የአቅማቸውን ጠርተው እስኪጨርሱ ይጠብቁና አንድ የማይደፈር ትልቅ ቁጥር ጠርተው ይዘጉታል።

የጨረታው ኮሚቴ ሊቀመንበር ተሳታፊዎቹን ለማመስገን ሲነሱ ፊት ከተቀመጡት አገር በቀል ባለ ሀብቶች አንዱ እጃቸውን አነሱና "ጥያቄ አለኝ" በማለት ድምጻቸውን ከፍ አደረጉ። ግለሰቡ የተለያዩ ምርቶችን



ለገበያ በሚያቀርቡ ፋብሪካዎቻቸው ይታወቃሉ። የጉባኤው መሪ እንዲናገሩ በእጃቸው ሲያመለክቷቸው ከመቀመጫቸው ተነሱ። እግራቸው እንደ መንቀጥቀጥ እየዳዳው፣ ፊታቸው በላብ እየወዛ "እኔ የምለው ድሃ በዚህ አገር ላይ ሠርቶ መኖር አይችልም ማለት ነው?" በማለት ጠየቁ። አንዳንዶች ሳቃቸውን ማፈን አልቻሉም፤ አንዳንዶች ጥያቄው ስላልገባቸው የሚያስረዳቸው ፍለጋ ይዋትታሉ። ከንፈራቸውን በመምጠጥ ያገዟቸውም አልጠፉም። መቼም ሃብታቸውን የሚያውቅ በልቡ "ድንቄም ድሃ!" ሳይል የሚቀር አይመስለኝም። ምክንያቱም ሰውየው ከአብዝኛው የአገሩ ሰው አንጻር ሲታዩ የናጠጡ ሀብታም ናቸው። ነገር ግን ሀብታቸው ከእሳቸው ጋር በፍጹም ሊለካካ የማይችል መጠነ ሠፊ ሀብታም መጡና ድንገት የድህነት ስሜት ፈጠሩባቸው።

ለእድገትና ወደ ፊት ለመዘርጋት በር ይከፍታልና ይህ ስሜት ከፉ አይመስለኝም። ችግሩ ራሳችንን ከበታቾቻችን ጋር ብቻ አወዳድረን ከእኔ በላይ ማንም የለም ስንል ነው። ያኔ "ትልቅ እንቁራሪት ትንሽ ኩሬ ይወዳል" እንዲሉ እገር ይጠበናል። አንዳንዴ ትንሽ ቃሉ ስለ በራልን፣ ጥቂት ራዕይ ስለ ታየን፣ ሰዎች በእጃችን ስለ ተፈወሱ፣ የተናገርነው ትንቢት ስለ ተፈፀመ፣ አጋንንት ስለ ጮኸልን፣ ረዥም ሰዐት ስለ ጸለይን ወይም ሰብከታችን በሰዎች ስለ ተደነቀ መንፈሳዊ ባለጠጎች እንደ ሆንን ይሰማናል። ነገር ግን የልብ ዐይናችን ተከፍቶ የእግዚአብሔርን ባለጠግነት ስናይ፣ በክርስቶስ ውስጥ የተሰወረውን የጥበብና የዕውቀት መዝገብ ስንመለከት የድህነት ስሜት ይፈጠርብናል። ያኔ በመንፈስ ድሆች እንሆናለን። ያ ደግሞ እርሱን ወደ መምሠል እንድናድግ፣ ወደ ሙላቱ ልክ ለመድረስ እንድንተጋ ያግዘናል። ሆኖም እሱ የማይደረስበት ባለጠጋ ነውና መቼም ቢሆን የመንፈስ ድህነቱ አይለቀንም። ስለዚህ ዘወትር በመንፈስ ድህነት ውስጥ እንኖራለን። በዚህ የመንፈስ ድህነት ስሜት ተሞልተን ወደ ፊት ስንገሠግሥና ዕለት ተለት ከባለጠግነቱ ስንካፈል ጌታ በሚመጣበት ቀን "መንግስተ ሰማያት የእነርሱ ናት" የምንባል፣ ለዘለዓለም የማንሻር የመንግሥቱ ባለጠጎች እንሆናለን። ምርጥ ድህነት ይኋል ይህ ነው።

ተጨማሪ ንባባት፦ ሉቃስ 6፥20-21፤ ኢሳ. 66፥2፤ ያዕ. 2፥5

**ጸሎት**

*ጌታ ሆይ! ፍለጋ የሌለውን ባለጠግነትህን ግለጥልኝና ድህነቴን አስታውቀኝ። በጥቂት ሰኬት ከመመካትና ራሴን ከሌሎች ጋር እያወዳደርኩ በከንቱ ከመጽናናት አድነኝ። በመጣችው፣ ገናም በምትመጣው መንግሥትህ ውስጥ በጽድቅህ ባለጠጋ እንድሆን እርዳኝ። አሜን*



# 24
# ጸጸት

*«ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው» ነጢሞ. 5፥8*

በአሜሪካ ሚሺጋን ግዛት፣ ዴትሮይት ከተማ ውስጥ በምትገኝ የጎስቋሎች መንደር ያደግሁ ጥቁር አሜሪካዊ ነኝ። እናቴ ያሳደገችኝ ያለ አባት ነው፤ ሌሎች እኩዮቼ ከአባታቸው ጋር ሲጫወቱ፣ ሲገቡና ሲወጡ እኔ ያላባት ማደጌ ይሁን ወይም ሌላ ምክንያት አላውቅም ብቻ በውስጤ መራርነት ነበር። እናቴ አንድ ዓይናማ ነበረች፤ የማያየው አይኗ አብጥ ብሎ ያስፈራል። ስለዚህ እጠላት ነበር። ሥራዋ እኔ በምማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎችና ለመምህራን ምግብ ማብሰል ነው። ስለዚህ ሁል ጊዜ ላገኛት እገደድ ነበር። ዓይኗ ስለሚያስፈራ እፍርባት ነበር።

የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ አንድ ቀን ሊታየኝ ወደ ክፍላችን መጣች፤ እጅግ በጣም አፈርኩ፣ በተማሪው ሁሉ ፊት የተዋረድኩ መሰለኝ። «እንዴት እንዲህ ታደርገኛለች? በማለት ተቆጣሁ፤ ዘጋኋት፣ ፊት ነሳኋት፣ በጥላቻ አይን አይቻት ሮጬ ከከፍል ወጣሁ። በነጋታው አብሮኝ የሚማር የከፍሌ ልጅ «አንተ እናትህ እንዴት ያስፈራሉ አንድ ዓይን ብቻ ነው ያላቸው?» ሲል አላገጠብኝ። በዙሪያ የነበሩት ተማሪዎች ሁሉ ሳቁ፤ ተናደድኩ፤ የተናደድኩት ግን በልጁ ሳይሆን በእናቴ ነበር። በልቤ «መሳቂያ ልታደርገኝ ነው የመጣችው!» አልኩ። ይህ ደግሞ ጥላቻዬን አባባሰው። ምሬቴ፤ እኔ ብሞትና ብቀበር ወይም እሷ ብን ብላ ብትጠፋ አስመኘኝ። እናም ያን ቀን በተመረረ ስሜት «እኔን የጓደኞቼ መሳቂያና መሳለቂያ ከምታደርጊኝ ብትሞቺ ይሻለኝ ነበር» በማለት ፊት ለፊት ተናገርኋት። ያልኩትን ነገር ለአፍታ ደግሜ እንኳን አላሰብኩትም፤ ውስጤ በቁጣ ተሞልቶ ስለ ነበር ስሜቷ መጎዳቱ ደንታ አልሰጠኝም። እናቴ ግን አንዳች እልመለሰችልኝም።

ከዚያ ቤት ለመውጣትና እሷን ወደ ማላይበት ርቄ ለመኖር ያገኘሁት ብቸኛ ማምለጫ የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ስለነበር በአልህ ትምህርቴን በትጋት እከታተል ጀመር። እንደተመኘሁት አሥራ ሁለተኛ ከፍል ሳጠናቅቅ የትምህርት ዕድል እገኘሁና ርቄ ሄድሁ። በከፍተኛ ማዕረግ

ተመርቄ ዳጎስ ያለ ጥቅም የማገኝበት ሥራ ተቀጠርሁ። ቤት ገዛሁ፣ ብዙም ሳይቆይ ሚስት አገባሁና በተከታታይ ዓመታት ወንድና ሴት ልጆች ወለድሁ። በሥራዬ፣ በቤቴ፣ በሚስቴና በልጆቼ ደስተኛ ኑሮ ነበረኝ። በዚህ ሁሉ ግን ከእናቴ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ኖሮኝ አያውቅም። ለዓመታት አይታኝ አታውቅም፤ ሚስቴንና የልጅ ልጆቿንማ ፈጽሞ አታውቃቸውም።

አንድ ቀን እናቴ የምኖርበትን አፈላልጋ ልትጠይቀኝ መጣች። በሩን ስታንኳኳ የከፈተላት ወንዱ ልጄ ነበር፤ ተደስታ ልትስመው ስትጠጋ ስለማያውቃትና አንድ ዐይኗ ስለሚያስፈራ ልጄ እሪ ብሎ ጮኸ፤ እኔና ባለቤቴ ሮጠን ስንወጣ እናቴ በር ላይ ቆማለች። «ሳትጋበዢ ወይም ቀጠሮ ሳትይዢ ለምን መጣሽ?! ተናግረሽ ብትመጪ ኖሮ ልጄን እንዲህ ባላስደነገጥሽው ነበር» ብዬ ጮኹባት። በዚህ ሁሉ ግን በእናቴ ፊት ላይ ፈጽሞ ቁጣ አይነበብም፤ በለሰለሰ ድምጽ «እስቀድሜ ሳላሳውቅ በመምጣቴ እጥፍቻለሁ፤ ይቅርታ ይደረግልኝ» ብላ አያየናት ፊቷን እዙራ እብስ አለች።

ይህ ከሆነ ከወራት በኋላ ከልጅነት ትምህርት ቤቴ የቀድሞ ተማሪዎች ኅብረት የግብዣ ወረቀት ደረሰኝ። ይህ ጉዞ ወዳደኩበት ሥፍራ መልሶ ስለሚወስደኝ መጀመሪያ ላይ ላለመሄድ አመንትቼ ነበር በኋላ ግን የልጅነት ጓደኞቼን ሳስብ ለመሄድ ወሰንኩ ሆኖም እናቴ ወዳለችበት እንደምሄድ ለባለቤቴ ልነግራት እልፈለኩም። «ለሥራ ጉዳይ አንድ ቦታ ደርሼ እመጣለሁ» ብዬ ዋሸኋት።

ለረዥም እመታት ከተለየኋቸው እሁን በተለያየ ኃላፊነት ላይ ከሚገኙ የልጅነት ጓደኞቼና እስተማሪዎቼ ጋር መልካም ጊዜ እሳለፍኩ። እናቴ ከቀድሞ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች እንዷ ስለነበረች በበዓሉ ላይ አንደምትገኝ ገምቼ ነበር፤ ነገር ግን እልነበረችም። በዓሉ ሲጠናቀቅ ያደኩበትን ያን ደሳሳ ቤት ጉዱን ለማየት ወደ እናቴ ቤት አቅጣጫ እቀናሁ። ስደርስ የቤቱ በር ተገዘግቷል፤ እካባቢው ጭር ብሏል። ባንኳኳም የሚመልስ ድምጽ አልነበረም። ባትኖር ነው በሚል ተመልሼ ለመሄድ ሳመነታ ከጎረቤት አንዲት ሴት ወጥታ ሰላምታ ከሰጠችኝ በኋላ አናቴ ከቅርብ ጊዜ በፊት እንደሞተች አረዳችኝ። ስለ እናቴ ይሄ ነው የሚባል ጥሩ ትዝታ ስላልነበረኝ ከዓይኔ ዕንባ እልፈለቀም፣ ወዮ እናቴ



ብዬም እልጮኽኩም፤ ለጥቂት ደቂቃዎች በቆምኩበት ሳስብ ከቆየሁ በኋላ ለመሄድ ርምጃ ስጀምር የእናቴን መሞት የነገረችኝ ሴት ለእኔ ይደርሰኝ ዘንድ አናቴ ከመሞቷ በፊት የጻፈችውን ደብዳቤ እቀበለችኝ።

ደብዳቤው እንዲህ ይል ነበር፦

*«ውድ ልጄ፦ ስላንተ ሳላሰብ የዋልኩበት ቀን ትዝ አይለኝም፤ ሳላሳውቅህ ወደ ቤትህ መጥቼ ልጆችህን ስላስደነገጥኩ ይቅርታ አድርግልኝ። ወደ ቀድሞ ትምህርት ቤትህ በዓል እንደምትመጣ ሰምቼ ደስ ብሎኝ ነበር፤ ሆኖም ከህመሜ የተነሳ ከአልጋ ወርጄ መራመድ ስለማልችል በዓሉ ላይ ተገኝቼ የማይህ አይመስለኝም። ከልጅነትህ አንስቶ የዕፍረትህ ምክንያት እንደሆንሁ አውቃለሁ፤ በዚህም በጣም አዝናለሁ። ለእፍረትህ ዋና ምክንያት ስለሆነው አንድ ዓይኔ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ነግሬህ የማላውቀውን ታሪክ ላጫውትህ፤ ትንሽ ልጅ እያለህ አደጋ ደረሰብህና አንድ ዓይንህ ጠፋ፣ ዓይንህን ለማትረፍ የሌላ ሰው ብሌን ያስፈልግህ ነበር፤ ሆኖም በጊዜው ሊገኝ አልቻለም። ልጄ አንድ ዓይና ሆነህ ዘመንህን ሁሉ ስትቸገርና ስትሳቀቅ ማየት ስላልፈለግሁ የአንድ ዓይኔን ብሌን ልሰጥህ እንደምፈልግ ለሐኪሞቹ ነገርኩና ቀዶ ሕክምናው ተካሄደ። ዓይንህ ሙሉ ጤና መሆኑና ብርሃንህ መመለሱን ስሰማ እጅግ ተደሰትኩ፤ በእኔ ፈንታ ልጄ አዲስ ዓለም ስላየልኝ ትልቅ ኩራት ተሰማኝ። ዛሬ አለምን የምታይበት ዓይንህ ዓይኔ ነው። በዚህም እጅግ ደስ ይለኛል።*

*የዘወትር አፍቃሪ እናትህ*

ይህንን ታሪክ ያነበብን ሁሉ ስሜታችን መነካቱ፣ ዓይናችን እንባ ማቅረሩ የማይቀር ነው፤ ከዚያም እልፌን ልጁን ሳንፈርድበትና በልባችን ሳንረግመው የምንቀር እይመስለኝም። ሆኖም ትልቁ ቁም ነገር እኛስ ወላጆቻችንን እንዴት እያየናቸው ይሆን? የሚለው ነው። በልጅነታችን ያሳለፍናቸው መጥፎ ገጠመኞቻችን ዛሬ ላይ በውስጣችን ምን እየፈጠሩ ይሆን? እኛ አድገን ተምረንና ሥራ ይዘን ብዙ ሃብት እፍርተን ሊሆን ይችላል፤ በግልባጩ ትናንት ብርቱ ሠራተኞች የነበሩት ወላጆቻችን በዕድሜ ገፍተው፣ እርጅና ተጭኗቸው፣ ጤና እጥተው፣ አጃቸው እጥቶ

ነጥቶ ይሆን? ታዲያ በስሜትም፣ በቃልም፣ በገንዘብም ምን ያህል ፍቅራችንን እየገለጽንላቸው ይሆን? ምናልባት ነገ እስከ ወዲያኛው አናገኛቸው ይሆናል። ስለዚህ ፍቅርን ለመግለጽ ቀኑ ዛሬ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ምሳሌ 20፥20, ዘጸ. 20፥12, ማር. 7፥8-13**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ቃልህ አባትና እናታችንን እንድናከብር ያዘናል፤ ወላጅን ማክበር ልጆች ሳለን በመታዘዝ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፤ አድገን ራሳችንን ከቻልን በኋላም በመርዳትና በመንከባከብ የሚገለጥ ነው። በእነርሱ በኩል ወደዚህ ዓለም እንድመጣ ወላጆቼን የመረጥከልኝ አንተ ነህ። ምርጫህ ለኔ ቢመስለኝም ባይመስለኝም ትክክል ነው። በእርግጥ ወላጆቼ ፍጹም ስላይደሉ በአስተዳደጌ ላይ የተፈጠሩ፣ በልጅነት ልቦናዬ የተተከሉ ነገሮች ይኖራሉ፤ አባክህን አሁኑኑ ፈውሰኝ። የቱንም ያህል የተሳካልኝ ሰው ብሆን የወላጆቼን ነፍስ ሳላሳርፍ እውነተኛ ስኬት አይኖረኝምና ነገ ሳላጣቸው ዛሬ እነርሱን ደስ በማሰኘት አንተን እንዳከብር እርዳኝ። አሜን።*



# 25
# መገለጥ ወይስ መገልበጥ?

*"ከእርሱም ይልቅ አጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ፣ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፣ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ።" 2 ጴጥ. 1፥19*

ቤት ስገባ *"ሲመጣ በዚህ ቁጥር ይደውልልኝ!"* የሚል ጥብቅ መልዕክት ጠበቀኝ። የደዋይዋን ስም የማውቀው በሩቅ ነው፣ ብዙ ስለማንቀራረብ መደወሏ ጥያቄም መደነቅም በውስጤ ፈጥሯል። ደዋይዋ ትልቅ ድርጅት ውስጥ የምትሠራ፣ ደህና ኑሮ ያላት፣ ዕድሜዋ በሰላሳዎቹ መጨረሻ የሚገመት የአማኝ ቤተሰብ ልጅ ናት። በመደወያው ውስጥ ጣቶቼን እየሸነቆርኩ ቁጥሮቹን አዞርኩና በዚያ ወገን ምላሽ መጠባበቅ ጀመርኩ። ስልኩ ተነሳ፤ ማንነቴን ገለፅኩ። ወዲያው *"ስለ ደወልክ በጣም አመሰግናለሁ፤ የፈለግሁህ በሕይወቴ አንድ ወሳኝ ጉዳይ ላይ እርምጃ ልወስድ አስቤያለሁ ነገር ግን አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሳላማክር መወሰን አልፈለኩም፤ ሰው ሳስብ ደግሞ የመጣህልኝ አንተ ነህ፤ ስለዚህ ስልክህን አፈላልጌ ደወልኩ"* አለችና የእኔን ምላሽ በመጠባበቅ ጸጥ አለች። ጥቂት ካወጣሁና ካወረድሁ በኋላ ጥሪዋን ተቀብዬ በቀጠሯችን ሰዓት ወደ ቤቷ አቀናሁ።

ተገናኝተን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ብዙም ጊዜ ሳልወስድ *"እሺ እርምጃ ልትወስጂበት ያሰብሽው ጉዳይ ምንድነው?"* አልኩ። እርግጠኝነት በሚነበብበት ገጽታ *"አይ ጸልይና ጌታ ይንገርህ እንጂ እኔ አልነግርህም"* አለችኝ። *"እግዚአብሔር የሚናገረው የተሰወረን ምሥጢር ለመግለጥ ነው እንጂ ሰውን ለማስደነቅ አይደለም፤ ስለዚህ አንቺ ልትነግሪኝ የምትችይውን ከሰማይ መስማት አይኖርብኝምና አንቺው ብትነግሪኝ ይሻላል"* አልኳት። ጸልዬ *'የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይልሻል!'* ባለማለቴ አያዘነች *"ቢቃ ላገባ ነው"* አለችኝ። *"ታዲያ ምንድነው ችግሩ? ማግባት መልካም ነገር ነው"* አልኩ። ወዲያው በማከታተል *"ግን አማኝ አይደለም፣ ደግሞ ያጨሳል፣ ይጠጣል፣ ከሌላ ሴት ጋር ሰሰ ነበረ ቀማሽኝ ብላ መቆሚያ መቀመጫ አያሳጣችኝ ነው"* በማለት ያልጠበቅሁትን የመረጃ ዶፍ ታወርድብኝ ጀመር።

በማስከተል "ማዘጋጃ ቤት ለመፈራረም ለፈታችን ቅዳሜ ቀጠሮ ይዘናል" ብላኝ አረፈችው። የምትሄድበት መንገድ ትክክል አለመሆኑንና ወደ ፊት ትልቅ ችግር በሕይወቷ እንደሚያመጣ ገባኝ። ሆኖም ይህንን በቀጥታ ብነግራት እንደማትቀበለኝ አሰብኩ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍንትው ብሎ ከተገለጠበት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይልቅ ትንቢት ከፉኛ እንደምትወድ ስለ ተረዳሁ ነው። ስለዚህ ዐይን ዐይኗን እያየሁ "አንቺ ሴት የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይልሻል! የሚያምን ከማያምን ጋር ምንም ሕብረት የለውምና ይህን ሰው አታግቢው" አልኳት። "ግን እኮ ጥሩ ሰው ነው፤ እኔም ወድጄዋለሁ" አለችኝ ሃዘን በተቀላቀለበት ለሜት። ብታገባው ሊገጥሟት የሚችሉትን አደጋዎች ከእግዚአብሔር ቃል አንድ ባንድ እየዘረዘርኩ ካሳየኋት በኋላ ጸልዬላት ወጣሁ። እሷም የምትፈልገውን መገለጥ ስላላገኘች እያዘነች ተሰናበተችኝ።

ከአንድ ዓመት በኋላ ድንገት መንገድ ላይ ተገናኝተን ስለ ኑሮዋ ስጠይቃት "አገባሁት እኮ" አለችኝ። "እንዴት?" በማለት ጠየቅሁ። "አንተ ጸልየህ ጌታ የሚልህን ንገረኝ ብልህ እምቢ አልክ። ከአንተ በኋላ የጸለየችልኝ ሴት በትንቢት 'በአንቺ አማካይነት ወደ መንግሥቴ አመጣዋለሁ ይልሻል' አለችኝ፤ ተጋባን ይኸው ጥሩ ኑሮ እየኖርን ነው" አለችኝ ውስጧም ውጪዋም እየፈነደቀ። እኔም "አሁን አንዴ ተጋብታችኋልና ትልቁ ቁምነገር በፍቅርና በመከባበር መኖር ነው። እግዚአብሔር ትዳራችሁን ይባርክ" አልኩና ተለያየን።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ይህችው ሴት ፊቷ ጠቅሮ ሁለንተናዋ ውድቅ ብሎ ወደ ቢሮዬ ስትገባ በመስኮት ተመለከትሁና ፈጥና እንድታስገባት ለጸሐፊዬ የውስጥ ምልክት ሰጠሁ። ገብታ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ዕንባ በተቀላቀለበት ድምፅ "ዛሬ አንተ ጋ የመጣሁት እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ስለሆንክ ነው። ያኔ ያማከርኳቸው ሁሉ አይዞሽ ግቢበት ብለው ገፋፉኝ። አንተ ግን የሚደርሰብኝን ሁሉ አንደ ባንድ ነገርከኝ። በጊዜው አልሰማሁም፤ አሁን ግን የነገርከኝ ሁሉ ተራ በተራ ደረሰብኝ። አሁን ከአቅሜ በላይ ስለሆነ ልፈታው ወሰኛለሁ። የመጣሁትም እንድትጸልይልኝ ነው" በማለት መልሷን በጉጉት ትጠብቅ ጀመር።



ዛሬም እንደ እምናው ዐይን ዐይኗን እያየሁ "አንቺ ሴት የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መፋታትን እጠላለሁና ይህን ሰው አትፍቺው ይልሻል" አልኳት። የማውቀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በዚህ መንገድ የነገርኳት ቢቸግረኝ እንጂ ዘወትር የምናገርበት መንገድ ስለሆነ አይደለም። ነገር ግን በጥቁርና ነጭ ግልጥ ሆኖ ከተቀመጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይልቅ በሰዎች በኩል "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ተብሎ የሚነገረውን ቃል ከፉኛ እንደምትወድና እንደምታምን ስለተገነዘብኩ ምናልባት እውነቱን ተቀብላ ትተርፍ እንደው በሚል ነው። የሚያሳዝነው አሁንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንድ ሥፍራ አግኝቻት እንደ ፈታችው ነገረችኝ።

ትንቢትና የተለያዩ ጸጋ ሥጦታዎች ዛሬም በቤተክርቲያን አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ጌታም በዚህ መንገድ ሰዎችን ይናገራል፣ ይመክራል፣ ያንጻል፣ ያጽናናል። ሆኖም በየትኛውም ሥጦታ አማካይነት፣ በማንኛውም ሰው በኩል ቢነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ የተገለጠበትን የእግዚአብሔርን ቃል ሊተካከልም ሆነ ሊተካ አይችልም። ዛሬስ እኛ ምን ያህል በእግዚአብሔር ቃል ለተገለጠው እውነት የሚገባውን አክብሮት እንሰጣለን? የእግዚአብሔር ቃል የመለኮት ድምጽ፣ የመገለጦች ሁሉ መገለጥ፣ የሁሉ ዳኛ እና የመጨረሻ ባለ ሥልጣን መሆኑን ምን ያህል እናስተውላለን? ትንቢትን አለመናቃችን እንደ ተጠበቀ ሆኖ በሰዎች የሚመጡትን መልዕክቶችና የመልዕክተኞቹን ማንነት ምን ያህል በሰከነ ልብ በቃሉ እንመረምራለን? መገለጥ የሚያስፈልገው ለተሰወረ ነገር እንጂ ለተገለጠው አይደለም። ለተገለጠው የሚያስፈልገው መታዘዝ ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ለተገለጠ ነገር መገለጥ መፈለግ መገልበጥን ያስከትላልና እንጠንቀቅ!

**ተጨማሪ ንባባት፡- መዝ. 119፥105, መ. እያሱ 1፥8-9, መዝ. 1፥1-6**

## ጸሎት

ጌታ ሆይ፡- ትዕዛዝህ፣ ፍርድህ፣ ምሥክርህ፣ ሕግህ፣ ሥርዓትህ የሆነውን ቅዱስ ቃልህን ከየትኛውም መገለጥ በላይ እንዳከብር፣ በአግባቡ እንድንተረጉመውና በትጋት እንድፈጽመው ጸጋህን አብዛልኝ። ቃልህ ተቃልሎ የሰዎች ቃል በከበረበት፣ በእሳት የተፈተነው ቃል ተንቆ፣ ገና መመርመር ያለበት ትንቢትና መገለጥ በነገሠበት ዘመን መንፈስና ሕይወት ከሆነው ቃልህ ጋር እንድጣበቅ እርዳኝ። አሜን።

# 26
# ዝም አትበለኝ

*"የሥጋችን አባቶች... መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበርና፤ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል።" ዕብ. 12፥ 9-10*

*የአከላሆማ ከተማ የሆነችውን ብሮከንአሮ ን ለቅቄ የሳውዝ ዳኮታ ከተማ* ወደ ሆነችው ሱ ፎልስ ልበር ሻንጣዬን ሳሰናዳ፣ አንዱን ሳነሣ፣ እንዱን ስጥል እንቅልፍ በዐይኔ እልዞረም። በቺካጎ አቋርጬ ሱ ፎልስ ሂልተን ከገባሁ ጀምሮ የውስጥ ዕረፍት እልነበረኝም፤ ልቤ ዝም ብሎ ይረበሻል። "ስላልተኛሁ ይሆን?" እልኩና ያረፍኩበት ሆቴል ምቹ እልጋ ላይ ጋደም አልኩ።

ምንም እንኳ ትናንት ሌሊቱን ሙሉ ሳልተኛ ያደርኩ፣ ቀኑንም ሙሉ ስበር የዋልኩ ብሆንም ያ ወትሮ ጀርባዬ ከእልጋ ሲገናኝ የሚከደነው ዐይኔ ዕንቅልፍ ራቀው። በእልጋው ላይ እንዴ ወዲህ፣ አንዴ ወዲያ እንደ በር ማጠፊያ ብገላበጥም እንቅልፍ እምቢ እለኝ። ተነስቼ ላነብ ብሞክር፣ ልጸልይ ብታገል እንደ ወትሮው እልሆን እለኝ። መረበሼ ቀስ በቀስ ከፍተኛ ወደ ሆነ የነፍስ ሥቃይ እየተለወጠ መጣ። መቼም በጭንቅ ጊዜ የማይታሰብ የለምና "መንፈሳዊ ውጊያ ይሆን?" በማለት በጸሎት ለመቃወም ሞከርኩ፤ እሁንም ለውጥ የለም። ሌሊቱን ከተቆራረጡ ዕንቅልፎች በቀር ዕረፍት እልነበረኝም። እንዲሁ ወደ ጌታ ስጮህ እደርኩ። በውስጤ የሚንተገተገውን የጭንቅና ግራ የመጋባት ዝለት የማያውቁ የሱ ፎልስ ቅዱሳን የፕሮግራም ስዐት በደረሰ ቁጥር የቃሉን እንጀራ ይበላሉ። ምድር ውስጧ በእሳተ ገሞራ ቢታመስም ላይዋ እየታረሰ ለሰዎች እንጀራ እንደምታበላ ማለት ነው።

ረብሻውና ሥቃዬ እየጨመረ ሄደ እንጂ ሊወገድ ስላልቻለ ከዚህ ቀደም እንድ ቦታ ባስተማርኩት ትምህርት ጥያቄ ያነሱ ወገኖች ስለነበሩ በዚያ ጉዳይ ጌታ እዝኖ ይሆን?' ብዬ ራሴን ስጠይቅ ውስጤ ድምፅ በሌለው ድምፅ 'አይደለም!' ይለኛል። ያልሆነውን ማወቅ የሆነውን ለማወቅ አንዱ መንገድ ነውና ምክንያቱ ይሄ እለመሆኑን በማወቄ ጥቂት እፎይታ ተሰማኝ። ሆኖም የሥቃዬን ሰበብ መፈለግ እላቆምኩም።



የሱ ፎልስ እገልግሎቴን ጨርሼ ለሚቀጥለው ኮንፈረንስ ወደ ዴንቨር በረርሁ። በውስጤ 'መንፈሳዊ ውጊያ ከሆነ ከተማውን ስለቅ ይተወኛል' ብዬ እሰብኩ፤ ሆኖም እንዳሰብኩት እልሆነም፤ ይባስ እየጨመረ መጣ። በሕይወቴ አይቼው የማላውቅ ይህ መፈጠርን የሚያስጠላ፣ ሞት የሚያስመርጥ የነፍስ ሥቃይ ሲበረታብኝ ወዴትም መሄድ ስለማልችል በጌታ ፊት ተንበርክኬ የባጡን የቆጡን እያነሳሁ ንስሐ ብገባም ውስጤ ጭንቅላቱን ወደ ጎን እየነቀነቀ እንደሚመልስ ሰው 'እይደለም!' ይለኛል። ለ 20 ዓመታት በዓለም ታላላቅ ከተሞች እየተዘዋወርኩ ሳገለግል የበረታ ራስ ምታት እንኳ እሞኝ የማላውቀው ሰው እሁን ከገጠመኝ የልብ ሥቃይ ጽናት የተነሳ ሆስፒታል ለመሄድ ተገደድሁ። የማብድ፣ የምጠፋ፣ የምሞት መስሎ ተሰማኝ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕይወቴ ተስፋ ቆረጥሁ።

ከቆይታ በኋላ 'ይህ የሆነብህ በዚህ ነገር ስላሳዘንከኝ ነው!' የሚል ድምፅ በውስጤ እለፈ። ጌታ እንዳዘነበት የተናገረኝን ነገር ከባድ አድርጌ ስላልወሰድኩት በድምጹ ተገረምኩ። 'በውስጥህ ስለምኖር በድርጊትህ የተሰማኝ ስቃይ እንዲሰማህና ለወደፊቱ ለመገኘቴ ዋጋ እንድትሰጥ ስለምፈልግ ነው' እለኝ። በውስጤ 'ምነው ሌሎች ከዚህ የባሰ ስንት ነገር ያደርጉ የለ?' እልኩ። ወዲያው "እኔ ሰውን የምቀጣው ምን አደረግህ? ብዬ ሳይሆን ማነህ? ብዬ ነው" እለኝ። *"የጌታውንም ፈቃድ አውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል፤ ያላወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል። ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፥ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል።"* [ሉቃስ 12፡46-48] የሚለው ቃል ወደ ውስጤ መጣ። በእንባ፣ በብዙ ጩኸት ንስሐ ገባሁ። ቀስ በቀስ ሥቃዩ ከእኔ ሄደ፤ የተግሣጹ እሻራ ግን እስካሁን በውስጤ እለ።

ለረዥም ዓመታት ጌታ በእጄ ሲሠራ፣ በአፌ ሲናገር ካየሁት ያለፈ ሕልውናው እሁን ደምቆ ታየኝ። ቅድስናው በውስጤ ሲያብብ ተሰማኝ። እግዚእብሔርን መፍራት ማለት ምን እንደሆነ በጥቂቱ ገባኝ። ለካ አደጋው እግዚእብሔር ሲቀጣ ሳይሆን ዝም ሲል ነው። ለካ እግዚእብሔር የሚቀጣው ሊያድን፣ ዝም የሚለው ደግሞ ሊጥል ሲያስብ ነው። እግዚእብሔር የሚቀጣው የሚወደውን፣ በልጅነቱም የሚተማመንበትን ብቻ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ኤር. 31፥18, ዘዳ. 11፥2-9, 2ሳሙ. 7፥14**

### ጸሎት

*አቤቱ ለሞት እንዳልሠጥ ዝም አትበለኝ፤ መቀጣት ደስ የሚያሰኝ ባይሆንም ቅጣኝ፤ ይህን የምታደርገው ስለ ምትወደኝና ስለምትቀበለኝ ነውና ስትቀጣኝ እንዳልደከም፣ ቅጣትህንም እንዳላቃልል እርዳኝ። አሜን።*



# 27
# እውነት ውሸት እላችኋለሁ!

*"እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።" 2ጢሞ. 2፥15 (አ.መ.ት)*

በዓለም ላይ 196 አገሮች አሉ። ሁሉም የራሳቸው ሕጋዊ ገንዘብ ያላቸው ሲሆን የሁሉም ብርና ሳንቲም ባለ ሁለት ገጽ ነው። በተለምዶ አንበሳና ጎፈር እያልን የምንጠራውን የአገራችንን ሣንቲም ማሰብ እንችላለን። ገንዘብ ሁለቱም ገጽ ካልተሟላ በአንዱ ብቻ እውነተኛ ገንዘብ ሊሆን አይችልም። መታየት ያለበት ሁለት ገጽ መኖሩ ብቻ ሳይሆን ሁለቱም የተለያዩ መሆናቸው ጭምር ነው። የተለያዩ ሆነው አንድ ገንዘብ ይፈጥራሉ። የመጽሐፍ ቅዱስም እውነት እንዲሁ ነው። አንዱ እውነት ሁለት ገጾች አሉት። በየገጾቹ ያሉት እውነቶች የተለያዩ ሆነው አንድ እውነት ይፈጥራሉ።

'ነፈቀ'፣ 'መንፈቅ'፣ 'ንፍቀት'፣ 'ንፍቅ' ከሚሉት ቃላት የሚመነዘረው "ኑፋቄ" የሚለው ቃል በዚህ የእውነት ተፈጥሮ ላይ የሚፈጸምን ወንጀል የሚያሳይ ነው። ኑፋቄ ሁለት ገጽ ያለውን አንድ እውነት አንዱን ይዞና ሌላውን ጥሎ ወይም በሐሰት ቀይሮ ማስተማር ነው። አንድ እውነት አግባብ ያላቸው ሁለት ገጾቹ ካልተሟሉ በቀር የስህተት ትምህርት እንጂ ፈጽሞ የእውነት ቃል ሊሆን አይችልም። ይህ ባሕሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸውን መሠረታዊ እውነቶች ሁሉ የሚወክል ነው። ጥቂቶቹን ለአብነት እንመልከት። ለምሳሌ፦ "እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው!" ይህ እውነት ነው፤ ነገር ግን ብቻውን ሙሉ እውነት ሊሆን አይችልም። እንደ ገንዘቡ ኖት ሁሉ ጀርባውን ለማየት እንገደዳለ። ጀርባ መኖሩ ብቻ አያሳርፈንም። ጀርባው ትክክለኛና የራሱ መሆን ይኖርበታል። ስለዚህ "እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው" የሚለውን ነጠላ እውነት ሙሉ የሚያደርገውን ተጣማጅ እውነት መፈለግ ይኖርብናል። ለዚህ እውነት ተጣማጁ "እግዚአብሔር ሦስት የተለያዩ አካላት (persons) ነው" የሚለው ነው። እነዚህ ሁለቱ በአንድነት ሲመጡ ብቻ ስለ እግዚአብሔር አንድ ሙሉ እውነት አለን ማለት ነው።

ሌላ ምሳሌ እንመልከት፡- "ክርስቶስ ሰው ነው" የሚለው ዓረፍተ ነገር እውነትነት አለው፤ ነገር ግን ብቻውን ሙሉ እውነት ሊሆን አይችልም፤ ስለዚህ አጣማሪውን መፈለግ ይኖርብናል። አጣማሪው "ክርስቶስ አምላክ ነው!" የሚለው ነው። ሌላ ምሳሌ ለመጨመር ስለ ሰው ማንነት ማንሳት እንችላለን። "ሰው መንፈስ ነው" የሚሉ አሉ፤ በእርግጥ እውነትነት አለው። ነገር ግን በራሱ ብቻውን ሊቆም የሚችል ሙሉ እውነት አይደለም፤ ሰው ሥጋም ነውና። ስለ መዳናችን ስንመለከት "በክርስቶስ በማመን ድነናል" አዎን እውነት ነው፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ፊት እንደምንድንም ይነግረናል። "በክርስቶስ ተቀድሰናል" የሚለው ትክክል ነው፤ ነገር ግን "ቅዱሳን ልንሆን ተጠርተናል" የሚለው እውነት አብሮት ሊነሳ ይገባል። እንዲህ እያልን ብንቀጥል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ሁሉ ሁለት ገጽ እንዳላቸውና እውነቱ ሙሉ እንዲሆን ሁለቱም ገጾች በአንድ መጣመር እንዳለባቸው እንገነዘባለን። ይህን ካላስተዋልን ግን በቀላሉ እንስታለን።

የስህተት መናፍስትም ሆኑ የሚያደምጧቸው የስህተት አስተማሪዎች ተላሎችን በቀላሉ ለማሳት የሚሳካላቸው የሐሰታቸውን አንድ ገጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለሚወስዱ ነው። አንድ የስህተት ትምህርት ለመፍጠር አንድ ግንጥል እውነት ከመጽሐፍ ቅዱስ መውሰድ ግድ ይላል። የሌላው ገጽ ጉዳይ ግን ሰይጣንን አያሳስበውም፤ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና ከራሱ በተፈጠረ ሐሰት ይለብጠዋል። ሠራተኞቹ ለተከታዮቻቸው መጀመሪያ ላይ ደግመው፣ ደጋግመው የሚያሳዩት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደውን የእውነት ገጽ ብቻ ነው። በዚያ ከሰከሩ በኋላ ግን እውነት አልባ የሆነውን የፈጠራ ገጽ ቢያሳይዋቸውም እንደማይረዱትና እንደማይመለሱ ያውቃሉ። አንዱን ገጽ አሳምሮ ለሚያሳየው ሁሉ "አሰቲ ጀርባውን!" ብሎ የማይጠይቅ ተማሪ ለስህተት የተጋለጠ ይሆናል።

ሰይጣን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተናገራቸው ቃሎች ሁሉ በራሱ ሐሰት የተለበጡ ግንጥል እውነት ያነገቡ ስለመሆናቸው ብዙ ማስረጃዎች ቢኖሩም አንድ ሁለቱን ብቻ ለአብነት ላንሳ፡- *"ከእርሱዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ"* (ዘፍ. 3፥5) ሲል የተናገረው እውነት ነው። ይህንንም እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ በማለት በቃሉ አረጋግጦታል "እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ።" ነገር ግን ከጀርባው የለጠፈው በራሱ የተፈጠረ፣ ከእግዚአብሔር እውነት ጋር በቀጥታ የሚቃረን ሐሰት ነበር። *"እባብም ለሴቲቱ አላት፡- ሞትን አትሞቱም"* (ዘፍ. 3፥4)፤ የዚህ አባባል ሐሰትነት የሚረጋገጠው ቀደም ሲል እግዚአብሔር ራሱ ለአዳም በተናገረው ቃል ውስጥ ነው፡- *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።"* (ዘፍ. 2፥16-17)

ዲያቢሎስ ጌታን ወደ ቅድስት ከተማ ወስዶ፣ በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ ከመዝሙረ ዳዊት በመጥቀስ "መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል" (ማቴ. 4፥6) ሲለው ጥቅሱ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ አያጠያይቅም። ነገር ግን ከፍሉን ሙሉ እውነት የሚያደርገው የጀርባው ገጽ ዲያቢሎስ እንዳለው "የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር . . .።" (ማቴ. 4፥6) የሚለው ሳይሆን በዘዳግም 6፥16 እንደተጻፈው "ጌታን አምላክህን አትፈታተነው" የሚል ነበር።

የዛሬ 26 ዓመት አንድ ቀን የጌታን ቃል እያሰላሰልሁ ሳለሁ *"እውነት እውነት እላችኋለሁ . . . "* የሚለውን በወንጌላት ውስጥ በተደጋጋሚ የሰፈረውን የጌታን አባባል አገኘሁና እርሱ ራሱ በሥጋ የተገለጠ እውነት ሆኖ ሳለ አንድ እውነት ለመናገር ሲፈልግ "እውነት እውነት እላችኋለሁ" በማለት ቃሉን ሁለቴ የሚደግመው ለምንድነው? በማለት ጠየቅሁ። ለካ "እውነት እውነት እላችኋለሁ!" ይል የነበረው "እውነት ውሸት እላችኋለሁ" የሚል የሐሰት አባት ስላለ ነው አልሁ። ከ "እውነት ውሸት እላችኋለሁ" ለመዳንና በ "እውነት እውነት" ለመመሥረት እውነትን አገላብጠን እንይ። እውነት የተናገሩ ሁሉ እውነተኞች ናቸው ማለት አይደለምና እንጠንቀቅ። "የማይሠራና የቆመ ሰዓት እንኳ በቀን ሁለቴ እውነት ይናገራል" ይባል የለ!

ተጨማሪ ንባባት፦ 2ጢ.ሞ. 3፥13, 2ጴ.ጥ. 3፥16, 1ዮሐ. 2፥27

**ጸሎት**

*አባት ሆይ፦ አንተ የእውነት አምላክ ነህ! ልጅህ እየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ እውነት ነው! በውስጤ ያሳደርከው መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው! በእውነት በተለበጠ ውስጡ ግን ሐሰት በሞላበት ትምሕርትና ልምምድ እንዳልወሰድ የጠራውን እውነት እይዝ ዘንድ መመርመርን አስተምረኝ። አሜን።*



# 28
# ወርቁን ወይስ ባለ ወርቁን?

*"የወርቅ ቀለበት ያደረገና የጌጥ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባኤአችሁ ቢገባ፣ እድፍ ልብስም የለበሰ ድሃ ሰው ደግሞ ቢገባ፣ የጌጥ ልብስ የለበሰውን ተመልከታችሁ 'አንተስ በዚህ በመልካም ስፍራ ተቀመጥ' ብትሉት፣ ድሃውንም 'አንተስ ወደዚያ ቁም ወይም ከእግሬ መቀመጫ በታች ተቀመጥ ብትሉት ራሳችሁን መለየየታችሁ አይደለምን? ከፉ ሃሳብ ያላቸውም ዳኞች መሆናችሁ አይደለምን?" ያዕ. 2፥2-4*

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኝ 'በቅርብ ጊዜ ተከፈቱ' ከሚባሉ የወንጌላውያን አማኞች ቤተ ክርስቲያናት አንዱ ነው። ከተጀመረ ከአንድ ጊዜ በላይ መሄዴን አላስታውስም። አሁን ግን ጥያቄው ስለ በረታብኝ ከማገልገሌ በፊት ተካፋይ ሆኜ ልየው በሚል ጉባኤው ውስጥ ታድሜአለሁ። ዝማሬው ጦፏል፣ አዳራሹ ቢሞላም ሰው ለመግባት ይጣደፋል። አንድ ነገር ቀልቤን ሳበው፤ መደረኩ ፊትና ጎን ያሉ ያማሩ በርካታ ወንበሮች ሰው አልባ ናቸው። ሆኖም በር ላይ የቆሙት የዘነጡ አስተናጋጆች ወደ ውስጥ ለመግባት የሚከጅለውን ታዳሚ ወደ ጓሮ ይመራሉ። ዝማሬው እንደቀጠለ ነው፥ ነገር ግን እነዚያ ያማሩ የፊት ወንበሮች ግን አሁንም ባዶ ናቸው። የወንበሮቹን ባዶነት ከሩቅ ተመልከቶ ለመቀመጥ የሚጣደፍ ምዕመን በአስተናጋጆች ይመለስና ወደ ጓሮ ይመራል። እነዚህ በርካታ ያማሩ ወንበሮች ለማን ተጠብቀው ይሆን? የሚለው ሃሳብ ቀልቤን ገዛው። ዝማሬው እየተካሄደ እየተንጠባጠቡ የሚመጡ ጥሩ የለበሱና አንዳንዶቹን በዓይን የማውቃቸው ባለ ሀብቶች በአስተናጋጆቹ እየተመሩ ያማሩት ወንበሮች ላይ ተቀመጡ። ልቤ በሐዘን፣ አእምሮዬ በጥያቄ ተሞላ።

ያዕቆብ ይህንን ተግባር ፊት ለፊት 'ኃጢአት' ይለዋል። [ያዕ. 2፥9] ምንም እንኳ ኃጢአት ሲባል ቶሎ የሚመጣልን ማመንዘር፣ መግደል፣ መስረቅ . . . ብቻ ቢሆንም ሰውን በቆዳው ቀለም፣ በጾታው፣ በዘሩ፣ በኑሮ ደረጃው መዝኖ ከሌሎች መለየትና ማዋረድ ከእነዚህ የማይተናነስ መሆኑን ከዚህ ከፍል በላይ ማንም ሊነግረን አያስፈልግም [ያዕ. 2፥10, 11]። ለዚህ ነው ያዕቆብ ይህንን ድርጊት "አድሏዊነት፣ ራስን መከፋፈል፣ ከፉ ሃሳብ ያለበት ዳኝነት፣ ሕግ ተላላፊነት፣ በደለኝነት" በማለት የሚጠራው። የዚህን ኃጢአት ጥልቀት ለማሳየትና በተለይ በአማኞች ዘንድ ሊታሰብ

እንደማይገባው ለማስረዳት የተጠቀመባቸው የመከራከሪያ ሃሳቦች ከእምነታችን ጋር በጽኑ የተቆራኙ ናቸው።

አንደኛ፡- በሥጋ ድሃና የተናቀ ሆኖ የመጣውና ለሰላሳ ሶስት ዓመታት በምድር የኖረውን የናዝሬቱ ኢየሱስን "የክብር ጌታ ነው!" ብለን የምናምን ሁላችን ድሃን የመናቅና የማቃለል መብት የለንም። ከመሠረታዊ እምነታችን ጋር ይጻረራልላ። [ያዕ. 2፥1]።

ሁለተኛ፡- 'አንድ አካል እንሆን ዘንድ በአንድ አካል ተጠምቀናል፣ አንዱን መንፈስ ጠጥተናል' የምንል ከሆንን አማኞችን በኑሮ ደረጃ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በቆዳ ቀለም፣ በዘር፣ በቋንቋ ልንለይ መብት የለንም። ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው አንድ ያደረገውን አካል የማረድና የመበለት ወንጀል እየፈጸምን ነዋ። [ያዕ. 2፥4]!

ሦስተኛ፡- የስጠነው የዳኝነት ፍርድ ሲሆን ፍርዳችን በሰዎች ውስጣዊ ማንነት ላይ ሳይሆን በውጪያዊ ማንነታቸው ላይ የተመሠረተ ደካማ ፍርድ ስለሆነ ክፉ ሃሳብ ያላቸው ዳኞች ያደርገናል [ያዕ. 2፥4]።

አራተኛ፡- 'ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ' የሚለውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ንጉሣዊ ትዕዛዝ የሚጥል ነው። ምክንያቱም ሌሎች እኛን ውጫችንን አይተው ቢፈርዱብን የማንወድ ሲሆን እኛ ላይ ሊሆን የማንወደውን ሌላው ላይ መፈጸማችን 'ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው' የሚለውን የጌታን ትዕዛዝ መተላለፋችንን ያሳያል [ቁ. 8]።

አምስተኛ፡- ከጌታ ምህረት ለማግኘት ብቸኛው መፍትሄ ለሰዎች ምህረት ማድረግ ሆኖ ሳለ በሌሎች ላይ ያለ ምህረት መፍረዳችን በጌታ ፊት ምህረት የሚያሳጣን አደገኛ ጉዳይ መሆኑ ነው። [ያዕ. 2፥ 12, 13]።

ስድስተኛ፡- እግዚአብሔርን እንከተላለን እያልን ከእግዚአብሔር ጋር በምርጫ እንደ መስያየት የሚያስፈራ ነገር የለም። በእምነት ባለጠጎች እንዲሆኑ፣ ለሚወዱትም ሁሉ የሰጠውን ተስፋ እርሱም መንግስቱን እንዲወርሱ እግዚአብሔር ድሆችን ሲመርጥ እኛ ግን ድሆችን የምናዋርድ ከሆን ከእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ ጋር ተስያይተናል ማለት ነው። [ያዕ. 2፥5]



ሰባተኛና የመጨረሻው፡- እነዚህ በኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኞች የሆኑ አማኞች ከተፈተነው እምነታቸው የተነሳ ባለ ወርቅ ባይሆኑም በራሳቸው ወርቅ ናቸው። [1ጴጥ. 1፥6-7; ራዕይ 3፥17-18] ። ታዲያ ባለ ወርቁን የከበረ ቦታ አስቀምጦ ወርቁን ከትቢያ መጣል ምን የሚሉት ሥልጣኔ ነው?

**ተጨማሪ ንባባት፡- 2ቆሮ. 8፥8, ኢሳ. 53፥1-3, ዮሐ. 7፥24**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ አባክህ ሰዎችን በውጫዊ ሁኔታዎች ከመፍረድና ውሣኔ ከመስጠት ጠብቀኝ። የሰው ፊት አከባሪ፣ ለሀብት ሰጋጅና ተንበርካኪ ከመሆን አድነኝ። ይልቅ ሰውን በሥራው፣ በባሕሪው፣ በእምነቱና አንተን በመፍራቱ የማከብር እንድሆን እርዳኝ። አሜን።*

# 29
# ወፍጮ ቤት

*“ምስጉን ነው በከፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥* ***ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።*** *እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል፤ የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።” መዝ. 1፥1-3*

ከአሥራ ሦስት ዓመቴ ጀምሮ ያለውን የወጣትነት ዕድሜ ያሳለፍኩት ልደታ በመባል በሚታወቀው ሠፈር ነው። በልደታ ብዙ ትዝታዎች አሉኝ። ከማይረሱኝ አንዱ አህል ለማስፈጨት ስላክ ወፍጮ ቤት የማሳልፈው ጊዜ ነው። “ገረሡ ወፍጮ ቤት” በሠፈራችን ታዋቂውና ብቸኛው አህል ማስፈጫ ነበር። “ገረሡ” የባለቤቱ ሳይሆን የሥራ መሪው ስም ነው። ለያሜውን የሰጠው የአካባቢው ሕብረተሰብ ሳይሆን እንደማይቀር አገምታለሁ። ገረሡ ፈርጠም ያለ፣ ካኪ ቱታ ከገላው የማይለይ፣ ፀጉሩና ጢሙ ዱቄት እንደ ድር የሸፈነው፣ ፈቱም ድምጹም የሚያስፈራ ሰው ነበር። በገረሡ ወፍጮ ቤት ውስጥ ሦስት የወፍጮ ድንጋዮች ያሉ ሲሆን እያንዳንዳቸው ለተለያየ አላማ የሚያገለግሉ ናቸው። አንዱ ለበርበሬና ለምጥን ሽሮ፣ ሌላው ለጤፍ፣ ሌላው ለሽሮ አህል የተመደቡ ናቸው።

ታዲያ አንድ ሰው ተሳስቶ በጤፉ ወፍጮ በርበሬ ወይም የሽሮ አህል ቢጨምር የገረሡ ድምጽ በቁጣ ይባርቃል። ቢቆጣም እውነት አለው! እንደ ገና የመፍጨቱ ሂደት የሚቀጥለው ኤሌክትሪኩን አጥፍቶ፣ ወፍጮዎቹን ሁሉ አስቁሞ፣ የሚያሽከረክረውን ቹንጋ አውልቆ፣ ብረቶቹን ፈታቶ፣ ድንጋዮቹን አውጥቶና ጠራርጎ ለተመደበለት አገልግሎት ሲያዘጋጀው ብቻ ነው። ያኔ ችግሩ የገረሡ ብቻ ሳይሆን አህል ሊያስፈጭ የመጣው ሰፈርተኛ ሁሉ ሥራ በመፍታት የሚቋደሰው የጋራ ችግር ይሆናል። ለዚህ ነው ግራ የገባው አስፈጪ ይዞት የመጣውን አህል በማይሆን ወፍጮ ውስጥ እንዳይከት ገረሡ በተለመደ ተሰገምጋሚ ድምጹ የሚባርቀው።



አዕምሯችን ወፍጮ ቤት ነው። ያለማቋረጥ ሃሳብ ይፈጭበታል። የሚያርፍበት ጊዜ የለውም፤ ቀን ያስባል፣ ማታ ያልማል። ከረምት በጋ፣ ሠርክ እዘቦት ሃሳብ ከመፍጨት አይቦዝንም። አዕምሮ የሃሳብ መናኸሪያ ይሁን እንጂ ምንጮቹ ወይም አስፈጪዎቹ የተለያዩ ናቸው። ሃሳባት ከሰው ወይ ከእግዚአብሔር አልያም ከሰይጣን ሊመጡ ይችላሉ። መዳረሻቸው ግን የሰው አዕምሮ ነው። ብርሃን የተሞሉ ሃሳባት፣ ጨለማ ያነገቡ ሃሳባት በሰው አዕምሮ ውስጥ ይፋለማሉ። እግዚአብሔር ምን እንደሚያስብ ለማወቅ ፈጽሞ አስቸጋሪ አይደለም፤ ምክንያቱም ልቡን አሳትሞ ሰጥቶናል። የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ልብ ነው። የሰይጣንም ሃሳብ የእግዚአብሔርን ሃሳብ ከመጻረር አያልፍም። ታዲያ ከሁለቱ ሃሳባት አንዱ ገኖ የሚወጣውና በተግባር የሚገለጠው ሰው ሲቀበለውና በአዕምሮው ሥፍራ ሲሰጠው ነው። ሰው እንደሚያስብ እንዲሁ ነውና የአዕምሮውን ገዢ መሬት የተቆጣጠረ ኃይል ሁለንተናውን ይገዛል፣ በአካባቢውም ላይ ይሠለጥናል።

ታዲያ በእኛ አዕምሮ ሃሳብ የሚያስፈጨው ማን ይሆን? የወፍጮ ድንጋይ እንኳ ክብር ኖሮት በጤፉ በርበሬ፣ በስንዴው አተር የማይፈጭ ከሆነ የእኛም አዕምሮ ለቅዱስ ቃሉ የተለየ ሊሆን ይገባዋል። ነገር በቀረጢት ቋጥረው፣ ሐሜት በጆንያ ጠቅጥቀው፣ ጥላቻ፣ ፍርሃትና ጥርጥር አጋብሰው በአዕምሯችን ሊያስፈጩ የሚመጡትን መከልከል ይኖርብናል። እምቢ አሻፈረኝ ካላልን በስተቀር ነገራቸው በሥህተት ወደ ጆሯችን ከገባ ቀስ በቀስ ወደ ልባችን ይዘልቃል። ከዚያማ እንደ ገረሡ ፈታተን በቅዱስ ቃሉና በጸሎት ራሳችንን ካላነጻን እንደረከስን ውለን እናድራለን። መች የእኛ ብቻ የሚሰሙንን ሁሉ እናረክሳለን። ስለዚህ ለከፉ ሃሳብ አዕምሯችንን እንከልክል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ፊሊ. 4፥8, መዝ. 119፥15-16, ኢያሱ 1፥8**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ አዕምሮ የሰጠኸኝ አንተን እንዳውቅበት፣ ፈቃድህን ፈትኜ እንድለይበት፣ በፍጹም ሃሳቤ አንተን እንድወድበት ነው። ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ቃልህን በቀንም በሌሊትም ሳስብና ሳሰላስል ብቻ ነው። ስለዚህ አዕምሮዬን ከከፉዎች ምክር፣ ከኃጢአተኞች መንገድ፣ ከዋዘኞች ማህበር ጠብቄ ቃልህን ብቻ እንዳሰላስል እርዳኝ። አሜን!*

## 30
# ሕመም ማስታገሻ

*"የሰው ነፍስ ሕመሙን ይታገሣል፤ የተቀጠቀጠን መንፈስ ግን ማን ያጠንከረዋል?"*
*ምሳሌ 18፥14*

በማለዳ ከቤት ወጥቼ የመኪናዬን ሞተር እያሞቅሁ ሥር ላለመፍታት የሬዲዮኑን መክፈቻ ተጫንሁ። የነካሁት የዜና ጣቢያ ነበርና ዜናው በዝርዝር ቀጠለ። ጋዜጠኞቹ የአሜሪካንን የጤና ቢሮ በጭንቀት በስነገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ በስፋት ይወያያሉ። ወሬው የሥርጭቱ ሰፋትና የጉዳቱ ጥልቀት እረፍት ስለሚነሳው የአደንዛዥ ዕጽ ጥገኝነት ጉዳይ ነው። ይህ የብዙዎችን ሕይወት እየቀጠፈና የበርካቶችን ኑሮ እያመሳቀለ ያለው አደንዛዥ ዕጽ ከኮሎምቢያ ወይም ከሜክሲኮ በስውር የሚገባና በአሜሪካ ጎዳናዎች የሚቸበቸብ ሳይሆን በሕጋዊ መንገድ በየሆስፒታሉ በተመሠከረላቸው ሐኪሞች ለሕሙማን በመድኃኒት መልክ የሚታዘዝ ነው። ስሙ ኦፒዮይድ ይባላል። የሕመም ማስታገሻ ነው። በተከታታይ ከተወሰደ በማይበጠስ የሱስ ገመድ ይተብትባል፤ መጠኑ ከፍ ካለ ደግሞ ወሳጁ እስከ ወዲያኛው ያሸልባል። በ2015 ብቻ ይህንን እንክብል አብዝተው በመውሰድ 85,495 አሜሪካውያን ለሞት ተዳርገዋል። በቅርቡ "ሕመም ይሰማኛል" ብለው ሆስፒታል ለሄዱ 100 ሚሊዮን አሜሪካውያን ሐኪሞቹ 259 ሚሊዮን ኦፒዮኢድ እንዳዘዙና የመድኃኒት መደብሮች እንደቸበቸቧቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ የኪኒን ቁጥር 323,148,587 ለሆነው መላው የአሜሪካ ሕዝብ በነፍስ ወከፍ አንድ አንድ ጠርሙስ ይደርሳል። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ የሚወስደው ጉዳይ  የዕጽ ጥገኝነቱን በኦፒዮይድ የተለማመዱ ሰዎች መድኃኒቱ ስለሚወደድባቸው ሄሮይን የተባለ በዋጋ አራት እጥፍ የሚያንስ በአደንዛዥነቱ ግን በብዙ እጥፍ የሚብስ ሕገ-ወጥ አደንዛዥ ዕጽ ፍለጋ በየሥርቻው ለመንከራተት መዳረጋቸው ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ከተባለ መልሱ የአሜሪካ ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሕመምን የመታገስ አቅሙ እየመነመነ ስለመጣና ለትንሽ ለትልቁ ሕመም ማስታገሻ ስለሚፈልግ ነው።



የሕመም ስሜት ደረጃ አለው። አንዳንዱ ጥርስ ነክሶ ማለፍ ግድ ይላል። አሜሪካን የገነቧት አባቶች ይህ ሕመም ማስታገሻ አልነበራቸውም። ሕመምን የመታገስና የማሳለፍ አቅማቸው ግን ከፍተኛ ነበር። እስቲ ይህን እውነት ከክርስትና ሕይወታችን ጋር አዛምደን እንየው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ኑሮው የሕማም ሰው ነበር። ለተከታዮቹም መከራ እንደሚጠብቃቸው አስረግጦ ተናግሯል። ሐዋርያቱም ይህንኑ በኑሯቸው፣ በትምሕርታቸውና በብዕራቸው አጽንተውልናል። ጌታ ሲሰቀል በአንዳንድ በጎ አድራጊዎች ከእሞት፣ ከወይን ጠጅና ከከርቤ የተዘጋጀ ሕመም ማስታገሻ  ቀርቦለት ነበር፤ ነገር ግን ቀመሰው እንጂ ሊጠጣው ፈቃደኛ አልነበረም። ያንን ያደረገው ስለ ኃጢአታችን የሚቀበለውን መከራ እንደ ከብር ስለቆጠረው ሳይሰማው በማደንዘዣ ተሰውሮ እንዲያልፍ አልፈለገም ። ሰቃይ በሥጋ ሕመም ብቻ የሚገለጥ አይደለም፤ ዘርፈ ብዙ ነው። እንዲያውም የነፍስ ሥቃይ ከሥጋው በብዙ እጥፍ ይበረታል። ጌታ ኢየሱስም በመስቀል ላይ ያሳለፈው ሰቃይ የሥጋ ብቻ አልነበረም። በገዛ ወዳጆቹ የመሸጥና የመካድ ሰቃይ፣በቅርብ ተከታዮቹ የመተውና በጭንቅ ሰዓት ለብቻ የመቅረት ሕመም፣ የመናቅ፣ የመገፋት የመተፋት ዘግናኝ ስሜት በጸጋ አስተናግዷል። ነገር ግን አላማውን ስለሚያውቅ፣ ለማን እንደ ሆነ ስለሚረዳ፣ ለጥቂት ጊዜ መሆኑን ስለሚገነዘብና ከሰቃዩ ጀርባ ያለውን ደስታ ስለሚያይ ከሰቃዩ ለመዳን ጥረት አላደረገም።

በዘመናችን የከርስትና ሕይወት እውድማ ላይ እንደ ጥንቱ ስለ እውነት፣ ስለ ጽድቅ፣ ስለ ወንጌል፣ ስለ ፍቅር ዋጋ መክፈልና መከራን መቀበል እንደ ጦር እየተፈራ፣ እየተጠላና ኋላ ቀርነት ተደርጎ እየተቆጠረ መጥቷል። ከሰቃይና ከመከራ እንዲያድናቸው እንጂ ጌታ፣ ጌታ ስለሆነ የሚያመልኩት ቁጥር እየመነመነ ነው። እንዲህ አይነቶቹ መከራ የመጣባቸው ቀን ጀርባቸውን ሊሰጡ የተዘጋጁ የጉባኤ አድማቂዎች ናቸው። የደላን ቀን ጣፋጭ ምሥጋና እቅርበን የከፋን ቀን በምሬት እንጉርጉሮ ቅኝት የምንቀይር ቤቱ ይቁጠረን። ታዲያ ለምን ይሆን ስለ ሌላው ሕመምን መታገሥ የተሳነን? የመንፈሳችን መድከምና መላላት ነው። መንፈሳችን ሲጠነከር የሥጋችንን ሕመም መታገስ እንቾገርም። መንፈሳችን በኃጢአትና በዓለማዊ ምኞት ከተቀጠቀጠ ግን ማስታገሻ

ፍሰጋ በውጭ ሰመንከራተት እንገደዳሰን እንጂ ሰለ እውነት መገፋትን፣ መናቅን፣ መተውን፣ በሐሰት መወንጀልን፣ ሰብቻ መቅረትን መታገሰ እንችልም። ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? መንፈሳችን ጠንካራ እንዲሆን የእግዚአብሔርን ቃል ሳናሰልሰ መመገብ፣ የተመገብነው ከእኛ ጋር ተዋህዶ እንዲጠቅመን በቀንና በሌሊት ማሰላሰል፣ የተረዳነውን እውነት ሥራ ላይ ማዋል ነው። ሌላው መንፈስን የሚያጠነክረው ዘወትር ሳይታከቱ በጸሎት መጽናት ነው። ያኔ በጊዜውም አለ ጊዜውም ጸንተን እንቆማለን። ሕመምን እንታገሳለን።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ኢሳ. 53፥1-5፤ ማቴ. 27፥34፤1ጴጥ. 4፥19**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ፦ በጸጋህ ከኃጢአትና በኃጢአት ምክንያት ከሚያመጣው ዘላለማዊ ፍርድና ኩነኔ አድነኸኛል። ዘላለማዊ ክብርና ዕረፍት ከፊቴ እንደሚጠብቀኝ አውቃለሁ። ሆኖም በምድር ኑሮዬ ስለ ወንጌል፣ ስለ እውነትና ስለ ፍቅር በጽናት እንድቆም፣ መከራን እንድካፈል፣ ስቃይን እንድታገስ ትፈልጋለህ። እባክህ መንፈሴን በጸጋህ አጠንክረህ የውስጥንም ሆነ የውጭ ጊዜያዊ ሥቃይ መታገሥ አስተምረኝ።*



# 31
# የትውልድ ያለህ!

*"ትውልድ ሁሉ ደግሞ ወደ አባቶቻቸው ተከማቹ፤ ከእነዚያም በኋላ እግዚአብሔርን ለእስራኤልም ያደረገውን ሥራ ያላወቀ ሌላ ትውልድ ተነሣ። የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነ ነገር አደረጉ፥ በኣሊምንም አመለኩ። ከግብፅ ምድርም ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ተዉ፥ በዙሪያቸውም ካሉት ከአሕዛብ አማልክት ሌሎችን አማልክት ተከተሉ፥ ሰገዱላቸውም፤ እግዚአብሔርንም አስቈጡ።" መሳ. 2፥10-12*

ለወራት በትግራይ የገጠር ከተሞች ስዘዋወር ስለ ከረምኩ ከአገር ውስጥም ሆነ ከባሕር ማዶ ወሬዎች ጋር ፍቺ የፈጸምኩ ያህል ተሰምቶኛል። ወትሮ ሳልሰማው ውዬ የማላድረው የዓለም ዜና ለዓይኔና ለጆሮዬ ከራቀ ሰንብቷል። ከወራት በኋላ አገልግሎቴን ፈጽሜ ወደ መቀሌ ስመለስ ያረፍኩበት ቤት ያገኘሁት የውጭ ጋዜጣ "ሄራልድ ኦፍ ሂዝ ካሚንግ" (የምጽዓቱ ብሥራት) የሚልና በአሜሪካ የሚታተም መንፈሳዊ ጋዜጣ ነበር። አንደኛው ርዕስ ከሌሎቹ ይልቅ ቀልቤን ስለ ሳበው ትኩረቴን በጽሑፉ ላይ አድርጌ ማንበቤን ቀጠልኩ። ጥቂት እንዳነበብኩ ዓይኔን ማመን ተሳነኝ። "የፈሰገውን ያህል ከዜና ርቄ ብከርም እንዲህ የገዘፈ ለውጥና ክስተት ሊያመልጠኝ አይችልም" በማለት ከራሴ ጋር ተሟገትኩ። ጽሁፉ "አሜሪካ ባልታወቁ ኃይላት ተወረሰች" ይላል። አግራሞቴን ያባሰው የወራሪው ሠራዊት ቁጥር 3,999,386 (ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሦስት መቶ ሰማንያ ስድስት) መሆኑ ነው። ከመገረም ባሻገር ወደ ድንጋጤ የመራኝ ይህን ያህል ቁጥር ያሰው ኃያል ወደ ግዛቷ ዘልቆ የገባው አሜሪካ ስለ ጉዳዩ ምንም ምላሽ አለመስጠቷ ነው። ዋይት ሐውስ ያወጣው መግለጫ የለም፤ ሲ.አይ.ኤ እና ኤፍ.ቢ.አይ በቂ መረጃ የላቸውም፤ ፔንታገን ምንም መመሪያ አልደረሰውም። ጽሁፉ በመቀጠል እነዚህ በሰውር ወደ አሜሪካ ዘልቀው የገቡ ኃይላት በየቤቱ እንደተሰገሰጉና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዋይት ሃውስን፣ ፔንታጎን የተሰኘውን የመከላከያ መሥሪያ ቤት፣ ካፒቶል የተሰኘውን የመወሰኛ ምክር ቤት፣ ዎል ስትሪት የተሰኘውን የጅምላ ንግድ ማዕከል፣ ታላላቅ የዜና እውታሮችን እንዲሁም ወሳኝ የሆኑ ሥፍራዎችን በሙሉ እንደሚቆጣጠሩ ያትታል። መጨረሻውን ለማወቅ በመጓጓት ማንበቤን ቀጠልኩ። ለካ ጽሁፉ ማንነታቸው ያልታወቀ አሜሪካንን የወረሩ ኃይላት

የሚላቸው የራሺያን ጦር፣ የእስልምና አክራሪ ቡድኖች፣ የኢራን ወይም የሰሜን ኮሪያ ሰራዊት ሳይሆኑ እ.እ.አ በ1994 ዓ.ም አሜሪካ ውስጥ የተወሰዱ ሕጻናት ናቸው። ጽሁፉ በዚህ አላበቃም እነዚህ ድምጽ ሳያሰሙ፣ ድንበር ሳያቋርጡ በየቤታችን የገቡ ሕጻናት በወንጌል ካልተደረሱ፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር ካልተቀረጹ ነገ መሳ አገሪቱን እንደሚቆጣጠሩ ያስጠነቅቅና ይደመድማል። በረዥሙ ተነፈስኩ። የቀድሞ ስጋቴ የተወገደ ቢሆንም ጽሁፉ ያዘለው ቁም ነገር በውስጤ ተሰንቅሮ ቀረ።

እኛስ ዛሬ ስለ ትውልድ ምን እያሰብን ይሆን? በዕለት ተለት ጉዳይ ተወጥረን ደፋ ቀና ስንል ትውልድ እያመለጠን ይሆን? ትናንት በየሆስፒታሉና በየቤቱ የተወለዱ ጨቅላዎች ነገ አገራችንን እንደሚረከቡ፣ በወሳኝ ጉዳዮቻችን ላይ እንደሚበይኑ፣ እሴቶቻችንና ቅርሶቻችን ላይ እንደሚወስኑ ምን ያህል ተገንዝበናል? ዛሬ በየጓዳችን በእቅፋችን ያሉ እምቦቃቅላዎች ነገ እነማን እንደሚሆኑ የምናውቀው ነገር የለም። ያለን አማራጭ ሁሉንም በሚመጥናቸው መንገድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል መድረስና በእግዚአብሔር ቃል ንጽረተ ዓለም እእምሯቸውን ለመቅረጽ መረባረብ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጲያ ባሉ የአዳጊ ሕጻናት ቁጥር በሚበረከትባቸው አገራት ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና ወላጆች ለልጆች አገልግሎት ልዩ ትኩረት በመስጠት ከአመጽ መናጠቅ ይጠበቅባቸዋል። ለእፍታ ተዘናግተን ከእጃችን ካመለጡ ግን እስከ ወዲያኛው ላናገኛቸው እንችላለን። በምንኖርበት ሉላዊነትና ድህረ-ዘማናዊነት በነገሠበት፣ የኢንተርኔት ቴክኖሎጂ በረቀቀበት፣ እግዚአብሔርን መዳፈር፣ እውነትን ማቃለል፣ የተፈጥሮን ማዛባት፣ ለዘመናት የኖሩ እሴቶችን መናድ፣ ሥርዓትን መጻረር ጀብዱ ሆኖ በሚቆጠርበት ዘመን ወንጌል ቀድሞ ስፍራ ካልያዘ በልጆቻችን ልብ ዙፋናቸውን ሊዘረጉ ያሰፈሰፉ እኩይ ኃይላት ይቀድሙናል። ታዲያ ልጆችን በተመለከተ ምን እያደረግን ነው? ይህን ሰራዊት በመማረክ ከጥፋት ታድገን የጽድቅ ሰራዊት ለማድረግ እንሥራ።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ምሳሌ 22፥6, ዘዳ. 6፥5-9፤4፥9-10, ኤፌ. 6፥4**



## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ልጆች የአንተ ሥጦታዎች ናቸው። የሆድም ፍሬ የአንተ ዋጋ ነው። ሰው ለሚወደው ሰው ትልቅ ሥጦታ ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን ከአንተ በቀር ሕይወት ያለው፣ የሚያድግ፣ ለዘለዓለም የሚኖር ሥጦታ ሊሰጥ የሚችል ማንም የለም። ሥጦታን አክብሮ መያዝ የተቀባዩ ድርሻ ነው። ከእኔ የተወለዱት ብቻ ሳይሆኑ፣ በቤተክርስቲያኔ፣ በወዳጆቼ ቤት፣በጎረቤቶቼ ቤት ያሉ ሕጻናት ሁሉ የአንተ ሥጦታዎች እንደ ሆኑ ተገንዝቤ ለልጆች እንዳስብ፣ እንድጸልይ፣ መልካም ምሳሌ እንድሆን፣ በልጆች ላይ የሚሠሩ ድርጅቶችን በገንዘቤ እንድደግፍ፣ በልጆች አገልግሎት ውስጥ እንድሰማራ እርዳኝ። ለገዛ ልጆቼም በቂ ዳቦ ብቻ ሳይሆን በቂ ጊዜ እንድሰጥ፣ በቤቴ አብሬያቸው ቃልህን እንዳነብና እንድጸልይ፣ በጽድቅ እንዳሰለጥናቸውና በቀናው መንገድ እንድመራቸው ጸጋን አብዛልኝ።*

# 32
# ተረከዙ

*"ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል።" ምሳሌ 28፥13*

*አኪለስ* ከክርስቶስ ልደት በፊት በ8ኛው ዓመተ ዓለም የኖረ በጥንታዊ የግሪክ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው የትሮይ የጦር ጀግና የማይሚዶን ንጉሥ *የፌለስ* ልጅ ነበር። ይህን ሰው ለዓለም ያስተዋወቀው የጥንታዊያን የግሪክ ታሪኮችና እፈ ታሪኮች ጸሐፊው *ሆሜር* ነው። *ሆሜር* "ኢሊየድ" በተሰኘ ባለ ስድስት ቤት የግጥም መድበሉ የአኪለስን ጀግንነት እያወደሰ ይጽፋል። በትረካው ከሚያነሳቸውም ገድሎች እንዱ አኪለስ የትሮይ *መሥራች* የነበረውን የንጉስ *ፐሪያምን* የመጀመሪያ ልጅ ጦረኛውን ልዑል *ሄክቶርን* እንዴት እንደ ገደለና ግሪኮች ዘወትር የሚናፍቁትን ድል እንዳጎናጸፋቸው የሚያሳየው ክፍል ነው። ሆኖም በድል ታሪክ የሚጀምረው የሆሜር የግጥም መድብል የሚደመደመው የአኪለስን አሳዛኝ ሞት በመተረክ ነው። አኪለስ የሞተው በሌላ ጀግና እጅ አልነበረም፤ *ፓሪስ* የሚባል አንድ ተራ ሰው የወረወረው ቀስት ተረከዙ ላይ ወግቶ አቆሰለው። ቁስሉም ሊድን ስላልቻለ አመርቅዞ ገደለው።

*የሆሜር* የግጥም መድበል የአኪለስን በተረከዝ ቁስል መሞት ከግሪኮች እፈ ታሪክ ጋር ያቆራኘዋል። ታሪኩ እንዲህ ነው። "አኪለስ የተወለደው በትሮይ የይገባኛል ጥያቄ የዛኔው ዓለም በጦርነት ቢታመሰበት ወቅት ነበር። የንጉሥ የመጀመሪያ ልጅ ነውና ጦርነት ዕጣ ፈንታው እንደሚሆን የተረዳችው እናቱ *ቴቲስ* ልጇ ኢ-መዋቲ [የማይሞት] እንዲሆን መላ ስትፈላልግ ትቆያለች። በኋላም የግሪክ አማልክት ባለሚሎች ሞትን በሚገፍፈው *በስቴክስ* ወንዝ እንድትነከረው ይመክሯታል። እንደታዘዘችው ሕጻኑን በተባለው ወንዝ እርቃኑን ታጠምቀዋለች። ሆኖም ሁለንተናውን ስትነክር ሕፃኑን ያንጠለጠለችበት ተረከዙ ሳይነከር ይቀራል። የፈራችው አልቀረም በጎልማሳ ዕድሜው ተረከዙን ተመትቶ ሞተ። ከዚህ እፈ ታሪክ በመነሳት በአለማችን በብዙ ነገር ብርቱ የሆኑ የታላላቅ ሰዎች ስውር ድካም "አኪለስ ሂል" በመባል መጠራት ጀመረ።



ወደ እኛ ስንመጣ በሕይወታችን፣ በሥራችን፣ በአገልግሎታችን በብዙ መልኩ ተሳክቶልን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በውጭ ምንም ያህል ቢሳካልን በውስጥ እኛና ጌታ ብቻ የምናውቀውና የምንደከምበት "አኪለስ ሂል" ይኖረናል። ታዲያ ከዚህ ችግር በጊዜ እንዳንላቀቅ እንቅፋት ከሚሆኑብን ነገሮች እንደኛው ችግሩን ለይቶ አለማወቅ ሲሆን ሁለተኛው ብናውቀውም እንደ ችግር አለመቀበልና መድኃኒት ለመፈለግ ፈቃደኛ አለመሆን ነው። በሽታን ማወቅ፣ መቀበልና መድኃኒት መፈለግ በራሱ የፈውስ እጋማሽ ነውና በማንነታችን ጥግ በጨለማ የተቀመጡ ተገልጠው ለሰው የማይታዩ ነገር ግን በሥውር የሚታገሉንን እኩይ ባሕሪያት በእግዚአብሔር ፊት ገልጠናቸው መፍትሄ ልንሻ ይገባል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ለምናምናቸውና ብቃቱ ላላቸው የቅርብ ወገኖች ወይም ባለ ሙያዎች አማክረን መፍትሄ ልናገኝ ይገባል። አለዚያ ግን አንድ ቀን በገሃድ ጉድ እንደሚሰሩንና ካቀማችን በላይ ዋጋ እንደሚያስከፍሉን ሳይታለም የተፈታ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመረምር ግዙፍ ስፍራ የምንሰጣቸው ታላላቅ ነቢያት በእግዚአብሔር ጸጋና ረድኤት ካከናወኗቸው ግሩም ሥራዎች ባሻገር እንደ ሰው ድካሞች ነበሯቸው። ስለዚህ ደካማ ጎናችን ሲገለጥልን ተስፋ ልንቆርጥ አይገባም፤ ብቻችንን አይደለንማ። ኖሕ ከስካር፣ ያዕቆብ ከማታለል፣ ሙሴ ከቁጣ፣ ዳዊት ከዝሙትና ንጽሕን ሰው ከማስገደል ሴራ፣ ሰሎሞን ከጣዖት አምልኮ፣ ኤልያስ አስጊዜው ከሚመጣ የሞት አሳብ ጋር ውስጣዊ ትግል ነበረባቸው። እነዚህ ሁሉ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። ነገር ግን የራሳቸው *አኪለስ ሂል* ነበራቸው። ታዲያ ከመሸፋፈን ይልቅ አስቀድመው በእግባቡ ቢታገሉት ኖሮ ባልሰለጠነባቸውና ሩጫቸውን ባላቃጠለ ነበር። ዛሬስ የእኛ ትግል ከምን ጋር ይሆን? ስድካማችን መሸፈኛ ምክንያት መደርደራችንን አቁመን መድኃኒት መሻት ይኖርብናል። እኛ ብቻ የምናውቀውንና ለብቻችን የምናብሰለሰለውን የጨለማ ጥግ ለብርሃን ልንገልጠውና በጊዜ መፍትሄ ልንፈልግለት ይገባል። አለዚያ ግን አንድ ቀን የመውደቃችን ብሎም የመሞቻችን ምክንያት ይሆናል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ መዝ. 32፥5. 1ዮሐ. 1፥9. እዮብ 31፥33**

**ጸሎት**

*ልዑል ሆይ፦ አንተ ልብንና ኩላሊትን ትመረምራለህና ዛሬ የተሰወረ፣ ነገ ግን ተገልጦ ዋጋ የሚያስከፍለኝን ጠንቀኛ ባህሪ በቃልህ ብርሃን አሳየኝና ተግቼ እንድንሠራበት እርዳኝ። አሜን*



# 33
# የናት ልጅ

*"ምንጭህ ብሩክ ይሁን በልጅነት ሚስትህም ደስ ይበልህ። እርሷ እንደ ተወደደች ዋላ እንደ ተዋበች ሚዳቋ ናት . . . ።" ምሳሌ 5፥18-19 (አ.መ.ት)*

ሰብለን[2] በውጭ ብቀርባትም ወደ ቤቷ ሄጄ አላውቅም። ዛሬ ግን በረዥም አመት ትውውቃችን ለመጀመሪያ ጊዜ ቤቷ ምሳ ተጋብዣለሁ። ዕድሜዋ በሃምሳዎቹ መጨረሻ የሚገመት ቢሆንም ራሷን ስለምትጠብቅ ሁሌም ከወጣት የምትመደብ መልከ መልካም ሴት ናት። ጣት የሚያስቆረጥመውን ምሳ ለዛ ባለው ጫወታዋ እያወራረድኩ ሳላውቀው ሰዓቱ ነጎደ። በዛን ዕለት በርካታ ወጎች እንስተን የጣልን ቢሆንም ስለ ትዳር ያጫወተችኝ የልጅነት ወግ ግን መቼም ከውስጤ አይጠፋም።

ሰብለ በትዳር ሕይወቷ ስላገባቻቸው ሦስት ባሎች እያሰበች በትዝታ ሰጥማለች። *"ከመጀመሪያው ባሌ ጋር የተጋባነው ተዋደን ነው። አንድ ሴት ልጅ አፍርተናል። ታዲያ ምን ያደርጋል መናጢ ድሃ ነበር። ቤተሰቦቼ ደግሞ ያኔ ትልቅ ነን ብለው የሚያስቡ ስለ ነበሩ በትዳራችን ደስተኛ አልነበሩም። ሰበብ ፈልገው አፋቱኝ"* አለች ቁጭት በተሞላበት ስሜት፤ አሁንም ትዝታው በውስጧ ትኩስ መሆኑን ፊቷ እያሳበቀባት። *"ትንሽ ቆይተው ለአንድ በዕድሜ ብዙ ለሚበልጠኝ ሀብታም ሰው ዳሩኝ። ሆኖም ልንግባባና አብረን ልንሄድ አልቻልንም። ጥቂት አመታት አብረን ከኖርን በኋላ ተለያየን። ለተወሰኑ አመታት ብቻዬን ከኖርኩ በኋላ እኔንና የአሁኑን ባለቤቴን በቅርበት የሚያቁ የምናከብራቸው ሰዎች "ብዙ ነገራችሁ አብሮ ስለሚሄድ መጋባት አለባችሁ" ብለው ወተወቱኝ። የአሁኑ ባለቤቴ ሚስቱ ጥላው ሄዳ ስለነበር፣ እኔም ከባሌ ተለያይቼ ለአመታት ሌጣ ስለነበርኩ፣ እነዚህም ሰዎች የምናከብራቸውና የምናምናቸው ስለነበሩ ተስማማሁና ተጋባን። ይኸው ላለፉት አስራ ስድስት አመታት አብረን ኖረናል። ግን ኑሮ አይበለው። በምንም አብረን የማንሄድ እሳትና ውሃ ነን። ቢሆንም ምንም አማራጭ ስለሌለን፣ ይሉኝታም ስለሚያጠቃን በቤት ውስጥ ደባል፣ በውጪ ባልና ሚስት*

[2] ሰባለ ታሪኳ ክብር ሲባል ስም ተቀይሯል።

*ሆነን ይኸው እንኖራለን" አለችና በረኸሙ ተነፈሰች።* ሰብለ ከሦስቱም ባሎቿ ጋር የነበራትን የትዳር ሕይወት ትረካ የቋጨችልኝ በአንድ እለገራሚ የልጅነት ትዝታዋ ነበር። *"በሕጻንነቴ ቤታችን በሳምንት ሁለቴ እየመጡ እንጀራ የሚጋግሩ እሮጊት ሴት ነበሩ። በጣም እወዳቸው ነበር። ጋግረው እስኪጨርሱ ማዕድ ቤት ከስራቸው አልጠፋም። ከወላፈኑ ርቄ፣ ጥግ ላይ ቁጢጥ ብዬ አወራቸዋለሁ። ጫወታቸው ይጣፍጣል። ወላፈኑ እየፈጃቸው ሊጡን ቢጋለው ምጣድ ላይ እያሰፉ፣ ጥቂት ቆይተው እከንባሎውን ከፍተው እንፋሎቱ እየጠበሳቸው እንጀራውን በሰፌድ ሰቅሰቀው ሌማቱ ላይ እየቆለሉ "ልጄ የመጀመሪያ ባል የእናት ልጅ ነው፤ ሁለተኛ ባል ሰባራ ሰፌድ ነው፤ ሦስተኛ ባል ዘርዛራ ወንፊት ነው" ይሉኝ ነበር። ሦስቱንም በሕይወቴ እውን ሆነው እየሁ። አሁን ያ የመጀመሪያ ባሌና የልጄ አባት ብጠራውም አይሰማኝም። ሚሊየነር ሆኗል። በርግጥ ልጄን አሜሪካን አገር ጥሩ ቦታ እያስተማረ ነው። ግን ምን ያደርጋል?!"* እለችና ዳግም በትዝታ ለመጠች።

ዛሬ በትዳር ውስጥ የምንኖር ሁላችን ስለ ትዳራችንና ስለ ትዳር ጓደኛችን ያለን ምልከታ ምን ይሆን? ፈረንጆቹ "የዛኛው ቤት ሣር ሁልጊዜ ለምለም ነው" እንዲሉ የልጅነት ሚስታችንና የልጅነት ባላችንን እየነቀፍን በሩቅ የምናውቃቸውን ሌሎችን እያደነቅን ይሆን? በድምጽ ባናወጣውም በልባችን "ያቺን አግብቼ ቢሆን! ያንን አግብቼ ቢሆን!" እንል ይሆን? ሁለተኛ የማግባት ዕድል ቢሰጠን ከሱ ሌላ ወይም ከሷ ሌላ እንመርጥ ይሆን? የነ ሰብለ ቤት እንጀራ ጋጋሪ ምክር ለሁላችን የሚሠራ ይመስለኛል። *"ልጄ የመጀመሪያ ባል የ'ናት ልጅ ነው . . . "* ከከፋ ይጠብቀን!

**ተጨማሪ ንባባት፦ ዘፍ. 2፥18, 2ቆሮ. 6፥14-17, ኤፌ. 5፥25-33**

### ጸሎት

*ጌታ ሆይ፦ አንተ ድንቅ አጣማሪ ነህ። የትዳር ጓደኛዬን የመረጥኸልኝ አንተ ነህ። ለሷ እንደ እኔ፣ ለእኔም እንደ'ሷ ማንም የለም። የልጅነት ሚስቴን ከመበደል፣ የልጅነት ባሌን ከማቃለል ጠብቀኝ። በቅርብ የማላውቃቸው በሩቅ የማደንቃቸው ቢኖሩም ለእኔ ግን እንደ ትዳር ጓደኛዬ የሚሆን ማንም እንደሌለ እንዳስተውል እርዳኝ። ስለዚህ ቀሪ ዘመኔን በአንተ ረከቼ፣ ጥቃቅን ችግሮቼን ወደ ኋላ ትቼ በደስታና በርካታ እንድኖር እግዘኝ።*



# 34
# የጥበብ ያለህ!

*"ብረት ቢደነዝዝ ሰውም ባይስለው ኃይልን ሊያበዛ ይገባዋል፤ ጥበብ ግን ሥራውን ለማከናወን ትጠቅመዋለች።" መክብብ 10፥10*

ሁለት ሰዎች እንጨት ሊቆርጡ ወደ ጫካ ይሄዳሉ። እንደኛው ከማለዳ እንስቶ ያለ ዕረፍት ላቡን እያንጠፈጠፈ ሲቆርጥ ይውላል። ሌላኛው ግን ምንም እንኳ በትጋት ቢሠራ በየመሃሉ ያቆምና ለጥቂት ደቂቃዎች ያርፋል። ለራሱ ማረፉ ብቻ ሳይሆን ያለማቋረጥ የሚቆርጠውን ሰው "አባክህ እዚህ ጋ ና ና ትንሽ ዐረፍ በል፤ አንድ የሚጠቅምህ ነገር አሳይሃለሁ" ይለዋል። ያኛው ግን "ሌላ ጊዜ ታሳየኛለህ፤ አሁን ሥራ ላይ ነኝ፤ እንዲትም ደቂቃ ማባከን አልፈልግም።" በማለት ይመልሰለታል። በቀኑ መጨረሻ ሁለቱም የቆረጡትን እንጨት ሲሰበስቡ ከምራቸው ፈጽሞ የማይመጣጠን ሆነ። በየመሃሉ ቆረጣውን እያቆመ ያርፍ የነበረው ሰው ከዚያኛው ይልቅ እጅግ ብዙ እንጨት ሰብስቦ ነበር። ብዙ ሰዓት እንደሠራና በርካታ እንጨት እንደ ቆረጠ እርግጠኛ የነበረው ሰው በልዩነቱ ተደንቆ "ይሄ እንዴት ሊሆን ቻለ? ብዙ ሰዓት የሠራሁትና የበለጠ የደከምኩት እኔ ሆኜ ሳለ አንተ እንዴት ከእኔ የሚበዛ እንጨት ልትቆርጥ ቻልህ?" በማለት ጠየቀው። ሁለተኛውም ሰው በተረጋጋ ስሜት "እየህ እኔ በየመሐሉ ለማረፍ በተቀመጥሁ ቁጥር መጥረቢያዬን እስል ነበር" በማለት መለሰለት።

ከጓዳ ሙያ እንስቶ እስከ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች በርካታ ሥራዎች በብረት ይከወናሉ። ታዲያ ጊዜና ጉልበት ሳይባክን ሥራው በቅልጥፍና እንዲፈጸም ብረቱ ስል ሊሆን ይገባዋል። በደነዘ ቢላ ሥጋ መከተፍ ይቻላል፤ ሆኖም የሚከትፈው ሰው ኃይል እንዲጨምር ይገደዳል። ሰው መጥረቢያም ሆነ ቢላዋ ተጠቅሞ ሲሠራ ሥራው ብዙ ኃይል ከጠየቀው ብረቱ ደንዟል ማለት ነው። ይኼኔ መፍትሄው ሥራን ቆም አድርጎ ብረቱን መሳል እንጂ ኃይል እየጨመሩና፣ ጉልበት እያበዙ መሄድ አይደለም። ብረቱን ከሳለው ግን ብዙ ኃይል ሳይጠቀም ሥራውን ማከናወን ይችላል።

ታዲያ ይህ ያለ ብዙ ኃይል ሥራችንን የሚከውንልን ስለት ምንድነው? ጠቢቡ ሰሎሞን ስለቱ "ጥበብ" ነው ይለናል። የመምራት ጥበብ ሰዎችን በፈቃዳቸው በማስከተልና ለጋራ ጥቅም እንዲሰለፉ በማድረግ በፍጥነት ወደ ውጤት የምንደረስበት ስልት ነው። በየትኛውም ግንኙነት ውስጥ ኃይል መጠቀም ከተጀመረ ኃይል ተጠቃሚው አካል ግለቱ እንደ በረደና ስለቱ እንደ ዶለዶመ በግልጽ ያሳያል። ሰው ኃይል መጠቀም የሚገባው ከጠላቱ ጋር ሲፋለም ብቻ ነው። ነገር ግን የራሱ ከሆኑት ከወገኖቹ ጋር ባለው ግንኙነት ኃይል የሚጠቀም ከሆነ ግንኙነቱ ከወዳጅነት ወደ ጠላትነት ሄዷል ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ኪሣራው ብዙ ነው። ስለዚህ ባል ከሚስቱ፣ ወላጅ ከልጁ፣ አሠሪ ከሠራተኛው፣ እረኛ ከመንጋው፣ መንግሥት ከሕዝቡ ጋር ባለው ግንኙነት ኃይል መጠቀም አይኖርበትም። ሲጠቀም ከታየም ሊመከር እንጂ ዝም ሊባል አይገባም። እኛስ በግንኙነቶቻችን ውስጥ ኃይል ይሰተዋላል? ከሆነ ጊዜ ወስደን ልናስብ፣ ራሳችንን ልንመረምር፣ ላይኛይቱን ጥበብ ልንፈልግ ይገባናል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ 1ቆሮ. 14፥20, ኤፌ. 5፥15-17, ያዕ.1፥5**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ አንተ የጥበብ ራስ ነህ፣ የጥበብ ምንጭ ነህ። ከሰዎች ጋር ባሉኝ ግንኙነቶች በሙሉ ያንተ ጥበብ ያስፈልገኛል። ስለቴ ዶልዱም ኃይል አያበዛሁ ከዚህም፣ ከዚያም ጋር ከመጋጨት ጠብቀኝ። ጥበብ ሙላኝና ከራሴ ወጥቼ ስለ ሌሎች እንዳስብ፣ ልፍለፋዬን አቁሜ ሌሎችን እንዳደምጥ፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ ማለቴን ትቼ የሌሎችን ስሜት ለመረዳት እንድጥር እርዳኝ።*



# 35
# መውጫ አለው?

*"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና።" ዮሐ. 3፥16*

የአካባቢው ነዋሪዎች ከምሲን (በአረብኛ ሃምሳ) በማለት የሚጠሩትና ለሃምሳ ቀናት የሚቆይ እንደ እሳት የሚለበልብ የጅቡቲ አየር ከጠራው ሰማይ ሥር ይንቀለቀላል። በጅቡቲ ከተማ ውስጥ ባለ የፈረንሳይ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የእሁድ አገልግሎቴን እንደ ጨረስኩ ወንድም ጥሩዓለም እያጣደፈ ወደ ላንድ ከሩዘሩ ወሰደኝ። እሱ ቤት ምሳ ለመብላት ተቀጣጥረናል፤ ሆኖም ከምሳው ባሻገር ዋና ምክንያቱ በቅርቡ ከአዲስ አበባ ሥራ ፍለጋ ለመጣውና እሱ ጋ ላረፈው ዘመዱ ወንጌልን እንድመሰክርለት ፈልጎ ነበር።

ምሳ እንደ ቀረበ አንድ ፀጉሩ የተመሳቀለ፣ አለባበሱ እዚህ ግባ የማይባል የ23 ዓመት ወጣት ተቀላቀለን። አይዳኝ ይባላል፤ የጨርቆስ ልጅ ነው። ብዙም ትኩረት ሳልሰጠው በልተን ጨረስን። ጥሩዓለም በነፃነት እንድናወራ "መጣሁ ተጫወቱ!" ብሎን ወጣ። ለወጣቱ አይዳኝ አንዳንድ ጥያቄዎች ሰነዘርኩ። ቀስ በቀስ በመልሱ ያስደንቀኝ ጀመር። ውጪውን አይቼ ብዙም ስፍራ ያልሰጠሁት ይህ ወጣት ለካ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሲቪል ምህንድስና የተመረቀ እሳት የበላ ባለሙያ ነበር። መች ይሄ ብቻ በርካታ የውጪ ቋንቋዎችን የሚናገር፣በአንድ በሁለቱ የሚያስተምር ሲሆን በጥቂት ጭውውት ብዙ መጽሐፍት ያነበበ፣ ሰፊ ልምድ ያዳበረ፣ ብሩህ አዕምሮ ያለው ወጣት መሆኑን ተገነዘብኩ። በዚያው ልክ በወጣትነት ዕድሜ ሊሞከሩ የሚችሉ የዚህን ዓለም ልምዶችን ይህ ቀረህ እስከማይባል የሞከረ መሆኑን ከንግግሩ ተረዳሁ። ለማውራት የነበረኝ ፍላጎት ጨመረ፤ ጌታን ቢያገኝ ምን ሊሆን እንደሚችል አሰብኩ፤ እኔ ከአመታት በፊት በዚሁ በጅቡቲ ያገኘሁትን አዲስ ሕይወት እንዲያገኝ ተመኘሁ።

ይዤው ወጣሁና ባንድ ሥፍራ ሻይ እየጠጣን አንድ የምሥራች ልነግረው እንደምፈልግ ገለጽኩለት። "በደስታ" አለኝ። *"ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው፣*

*የኃጢአት ውጤት የዘለዓለም ሞት ነው፣ እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ሊያድነን አንድ ልጁን በሥጋ ወደ ምድር ላከ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ፤ አሁን በስሙ ብታምን የኃጢአትን ይቅርታ ታገኛለህ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ትታረቃለህ፣ ከሁሉ በላይ ወደ የዘላለም ሕይወት ትገባለህ።"* አልኩት። በተለይ *"ወደ ዘላለም ሕይወት ትገባለህ"* የሚለው ሃሳብ ቀልቡን እንደሳበው በሚገልጽ መልኩ እንድደግምለት ጠየቀኝ። ሁለንተናው ጆሮ የሆነ አስኪመስል ድረስ አየሰማኝ ስለ ነበር በመደሰት የዘላለም ሕይወትን በማውቀው ልማዳዊ መንገድ ለማብራራት ሞከርኩ። አሁንም አቋራጠኝና *"ጥያቄ መጠየቅ ይፈቀዳል?"* አለኝ። *"በሚገባ የፈለከውን ጠይቅ ትችላለህ"* አልኩት። *"ይሄ የዘላለም ሕይወት ያልከው ነገር ተመችቶኛል፣ ለመግባት ፈቃደኛ ነኝ ግን ምናልባት ከገባሁ በኋላ ቢደብረኝ መውጫ አለው?"* በማለት ጠየቀኝ። የመገረም ሣቅ እየሳቅሁ *"ምነው ገና ሳትገባ ስለመውጫው አሳሰበህ?"* አልኩት። *"አንዴ ምን ነካህ! አንኳን ዘላለምን የሚያህል ረዥምም ዘመን እስከ ዛሬ የኖርኩት 23 ዓመት አንኳ እንዴት ረዝሞብኛል መሰለህ፤ እኔ እኮ ለንት ጊዜ ሌሊት አልነጋ ብሎኝ ጣራ ስቆጥር አድሬያለሁ፣ ቀኑ አልመሽ ብሎኝ ሳውደለድል ውያለሁ፤ ዘላለም ውስጥ ገብቼ ቢደብረኝ ለዘላለም ሰደበር ልኖር ነው?"* አለኝና አረፈው።

ያኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ዘላለም ሕይወት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺ በጥልቀት ማሰብ ጀመርኩ። ለካ እግዚአብሔር በልጁ የሰጠን *"የዘላለም ሕይወት"* እንጂ *"የዘላለም መኖር"* አይደልም። በዘላለም ሕይወት ውስጥ ዘላለም መኖር ቢኖርም የዘላለም ሕይወት ግን ዘላለም ከመኖር የሚልቅ የከበረ የሕይወት ዓይነት እንደሆነ ተገነዝብኩ። ለካ ሕይወት ለመረረው ሰው ዘለዓለም ስለ መኖር እያወራሁ የመረረውን ኑሮ "በዘለዓለም ላባዛልህ" እያልኩ ሰው ሳደናብር እንደኖርኩ አስተዋልኩ። በጥልቀት ሳስበው የምሥራች የሰበክሁ መስሎኝ ምንም መስህብ የሌለው አሰፈሪ ነገር እያወራሁ እንዳለሁ ተከሰተልኝ። ለካ ሰው እግዚአብሔር ካልገለጠለት በቀር አሁን በሚኖርበት የሥጋ ሕይወት ውስጥ ቆሞ የዘላለም ሕይወትን ማሰብ እንደሚቸገር ገባኝ።



በዚህ ዓለም የዕፅዋት ሕይወት፣ የእንሰሳት ሕይወት፣ የሰው ሕይወት እንዳለ ሁሉ በመንፈሳዊው ዓለም የእግዚአብሔር ሕይወት አለ። ይህ ሕይወት የተለየ፣ የከበረ፣ ከፍ ያለ በክርስቶስ ኢየሱስ በምድር ላይ በሥጋ የተገለጠ የዘላለም ሕይወት ነው። ዕድሜ ለአይዳኝ ይኸው እስከ ዛሬ ድረስ የዘላለም ሕይወትን በተጻፈበት መንፈስና ብርሃን እንድረዳው ምክንያት ሆነኝ። አሁን አይዳኝ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ በዘለለም ሕይወት ይኖራል።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ነዮሐ. 2፥25, መዝ. 39፥1-7, ነዮሐ. 5፥13-14**

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ ስለማይነገር ሥጦታህ ስምህ ለዘለዓለም ይባረክ፣ ልጅህን ሰውተህ ለዚህ የከብር ሕይወት ብቁ ስላደረከኝና ልጅህ የመሆን ሥልጣን ስለ ለጠኸኝ ምሥጋናዬን የምገልጽበት ቃላት የለኝ። አሁንም በውስጤ ያደረውንና የተካፈልኩትን ይህን ሕይወት እንዳውቅና እንዳሳውቅ ፀጋህን አብዛልኝ። አሜን።*

# 36
# ዕረፍት

*"እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን" ዕብ. 12፥1*

ሀብታሙ በቅርቡ በሱሉልታ ከተማ የጀመረውን የከብት ማደለቢያ ጣቢያ ጎብኝቶ ወደ አዲስ አበባ እየተመለሰ ነው። የኅዳር የቀትር ፀሓይ ለጉድ ይንቀለቀላል፤ የሚነዳት ከኋላ ከፍት የዕቃ መጫኛ ያላት የሥራ መኪናው ጠመዝማዛውን የሱሉልታ ቁልቁለት በፍጥነት ትምዘገዘጋለች። ከአንዱ የቁልቁለት ጠርዝ ወደ ሌላው ሲታጠፍ ቀልቡን የሳበው ነገር አየ። አንዲት ሴት አንጨት አይሉት ቅርፊት፣ ቅጠል አይሉት ጭራሮ ተሸክመው ቁልቁለቱን ይወርዳሉ። ሃብታሙ ለጥቂት አልፏቸው ከሄደ በኋላ በድንገት ፍሬን ይዞ አቆመና ወደ ኋላ እየነዳ ተጠጋቸው። የዕድሜና የጉስቁልና ቅልቅል ፊታቸው ላይ ይነበባል። በጀርባቸው የተሸከሙት ጭነትና እሳቸው ፈጽሞ አይመጣጠኑም።

በሸክም የጎበጠውን ወገባቸውን እንደምንም ቀና አድርገው ተመለከቱት። "እማማ ወዴት ነው የሚሄዱት? ላድርሰዎት?" ብሎ ከፍ ባለ ድምፅ ወዳወረደው መስታወት አንገቱን አስግጎ ጠየቃቸው። ግራ መጋባትና ማመንታት በሚነበብበት የለሰለ ድምፅ "ግዴለም ልጄ እኔ እሄዳለሁ፤ ለምጄዋለሁ" አሉት። የሚሄዱት ወደ ከተማ መሆኑን ሲረዳና ርቀቱን ሲያስብ ግድ አላቸውና ተስማምተው ዕቃ መጫኛው ላይ እንዲወጡ ረዳቸው። ሆኖም ሴትየዋ መኪናው ላይ ተቀመጡ እንጂ ተሸክመውት የነበረው ያጎበጣቸው ሸክም አሁንም ከጀርባቸው ላይ አንዳልወረደ በኋላው መስታወት ተመለከተ። ሀብታሙ መኪናውን ጥግ ካለያዘ በኋላ በፍጥነት ወርዶ "እማማ! ሸክሙን ያውርዱት እንጂ!" አላቸው። ሴትዮዋም አርግጠኝነት በሚነበብበት ድምፅ "ልጄ እኔን መጫንህ አንሶ ሸክሜን ምን በወጣህ! እኔው አሸከመዋለሁ" አሉት። ሀብታሙም በመገረም ለማስረዳት እየተጣጣረ "እማማ እርሶም ሆኑ ሸክምዎ መኪናው ላይ ናችሁ፤ ተሸከሙትም፣ አወረዱትም ለመኪናው አንድ ነው፤ ስለ ተሸከሙት አይቀለውም፤ ስላወረዱት አይከብደውም" አለና እንዲያወርዱት ግድ አላቸው። ሴትየዋም ደረታቸው ላይ የተተበተበውን ቋጠሮ ፈትተው ሸክማቸውን ካወረዱ በኋላ ቀና ብለው ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ዛሬስ ስንቶቻችን ነን፣ ጌታ "እናንተ ደካሞች፣ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ" በማለት ከጠራን በኋላ አሁንም ከነ ሸክማችን በእርሱ ውስጥ ያለነው? እሱ ከነ ሸክማችን ተሸከሞናልና ስለ ተሸከምንለት አናቀልለትም። እሱ የዓለሙን ሁሉ ሸክም ተሸክሟልና የእኛ በተለየ ሁኔታ አይከብደውም። ይልቅ ሸክማችንን ሁሉ በእርሱ ላይ ጥለን በነጻነት እንድናመልከውና እንድናገለግለው ይፈልጋል።

በራሳችን ሕግን መፈጸም፣ በሥጋችን እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የማንችል ደካሞች ነን። 'ሕግን በሥጋ እተገብረዋለሁ!' ብለን ብንታገል አንኳ ጫንቃችንን የሚሰብር ጽኑ ሸክም ይሆናል እንጂ ፈጽሞ ወደ ጽድቅ አያደርሰንም። ለለዚህ መፍትሄው ሸክማችንን በጌታ ላይ ጥለን በእርሱ ማርፍ ነው። ያኔ እርሱ በእኛ አድሮ በተፈጥሯችን ልንሸከመው የማንችለውን የብዙዎችን ሸክም በእኛ ውስጥ ይሸከማል፤ እርፈን የምናሳርፍ ያደርገናል።

አንዳንዴ የማይገባ ሸክም የምንሸከመው በአገልግሎት ሰም ነው። ሆኖም አገልግሎት ጌታ በእኛ ውስጥ የሚያደርገው እንጂ  እኛ ለእሱ የምናደርግለት አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። አገልግሎት ሸክም ከሆነብን፣ ሸክሙም የሚያማርረን ከሆነ የተሸከምነው ብቻችንን ነው። ጌታ በእኛ ውስጥ ሲሸከመው ግን ከባድ የተባለው ሸክም ቀሊልና ልዝብ ይሆናል።

አንዳንዴ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች በክርስቶስ ያለውን እውነተኛ ዕረፍት ሳይለማመዱ ወደ አገልግሎት የመጡ ሰዎች ናቸው። አላፈፉምና ማሳረፍ አይሆንላቸውም። ክርስትና የሚጀምረው በሥራ ሳይሆን በዕረፍት ነው። ለዚህ ነው ቃሉ "በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን" (ኤፌ. 2፥7) የሚለው። ስለዚህ ሸክማችንን አውርደን እርሱ በሠራው ሥራ እንረፍ፣ እርሱ በእኛ ውስጥ አድሮ እንዲሠራ፣ ሌሎችንም እንዲያሳርፍ እንፍቀድለት። ያኔ እርፈን እናሳርፋለን።

ተጨማሪ ንባባት፦ ማቴ. 11፥28-30, ኤፌ. 4፥22, ኤር. 17፥21

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ፦ በሥጋ ጥረት አንተን ደስ ማሰኘት እንደማልችል አውቄ ሸክሜን በአንተ ላይ እንድጥል፤ በአንተ አርፌ ሌሎችን እንዳሳርፍ እርዳኝ። ሃሳቤ፣ ንግግሬ፣ አካሄዴና ተግባሬ የአንተን ማንነት የሚያንጸባርቅ ይሁንልኝ። አሜን*



# 37
# ከዚህም የሚበልጥ

*"አብ ወልድን ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። . . . በዚህ አታድንቁ።" ዮሐ. 5፥20፣ 29*

ኒክ ዋሌንዳ በገመድ ላይ በመራመድ የሰባት ትውልድ ታሪክ ካለው ቤተሰብ የተገኘ አለገራሚ ሰው ነው። በከፍታ ላይ በተወጠረ ገመድ በመራመድ ስሙ ዘጠኝ ጊዜ በዓለም የድንቃ ድንቆች መዝገብ ሰፍሯል። በጁን 15, 2012 ግን በአስገራሚነቱ ወደር የማይገኝለት ተግባር ሊፈጽም እንደሆነ ተገለጠ። አሜሪካንና ካናዳን የሚያዋስነውንና በትልቅነቱ በዓለም ቁጥር አንድ የሆነውን "ናያግራ ፎልስ" በመባል የሚጠራውን ፏፏቴ በገመድ ላይ እየተራመደ እንደሚያቋርጠው አስታወቀ።

ይህንን ልብ አንጠልጣይ ትዕይንት ለመታዘብ አዕላፋት ወደ ናያግራ ጎረፉ፤ የዓለማችን ታላላቅ የዜና አውታሮች የቀረጻ መሣሪያዎቻቸውን ደገኑ፤ ዘጋቢዎች በአንጻራቸው ተሰይመው በየቋንቋቸው ጉዳዩን ተነተኑ፤ አንድ ቢሊዮን የሚጠጋ የዓለም ሕዝብ ዓይኑን በቴሌቪዥን፣ ጆሮውን በሬዲዮ ላይ ተክሎ ተጠባበቀ። እርምጃው ተጀመረ። ኒክ ከሃያ ፎቅ ሕንጻ ጋር በሚስካካ ከፍታ ላይ በተወጠረ ገመድ ከሥሩ ሁለት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሰምንት ሊትር ውሃ እያጓራ ለሠላሳ ደቂቃዎች ያለ እንከን ተራመደ። ተመልካቹ ከአሁን አሁን ይወድቅ ይሆን በሚል ሰቀቀን ውስጡ እየነዘረው ሲጠባበቅ ኒክ ይባስ ብሎ የመጨረሻዎቹን ርቀቶች በሩጫ በመደምደም ተመልካቹን አስደነቀ።

ከኒያግራ ድል ማግሰት ኒክ ወደ መኖሪያ ከተማው ብራንደን ሲመለስ የአካባቢው ነዋሪዎች ደማቅ አቀባበል አደረጉለትና ወደ መድረክ ወጥቶ ጥቂት ነገር እንዲናገር ተጋበዘ። ንግግሩ በማንም ያልተጠበቀ ነበር "ገና ምን አያችሁ! ከዚህ የሚበልጥ ይሆናልና በዚህ አትደነቁ!" አለ። ኒክ ይህንን ሲል ወደ ፊት ሊያደርጋቸው በዕቅዱ የነበሩት የአትላንቲክ ሲቲና የግራንድ ካንየን ትዕይንቶች በውስጡ ነበሩ።

ሐዋርያው ዮሐንስ በወንጌሉ አምስተኛ ምዕራፍ ጌታ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው እያሌ በሽተኞች በሚተኙበት የቤተ-ሳይዳ መጠመቂያ በመሄድ ሰላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ የአልጋ ቁራኛ የነበረውን ሰው ከሽባነቱ ፈውሶ አልጋውን ተሸክሞ እንዲሄድ እንዳደረገው ያስነብበናል። ሠላሳ ስምንት ዓመት ሠፊ ታሪክ ሊኖረው የሚችል የአንድ ጎልማሳ ዕድሜ ነው። ጌታ ደግሞ እንዲነሣ ብቻ ሳይሆን ጉልበት የሚጠይቀውን አልጋ ተሸክሞ የመሄድ ሥራ እንዲሠራ ሲያዘው እናያስን።

ብዙን ጊዜ ይህን ታሪክ እንብበን የጌታ ኢየሱስን የመፈወስ ኃይል አድንቀን እናልፋለን። ጌታ ግን ይህን ተግባር የፈጸመው ከፈውስ ያለፈ ሌላ አስደናቂ ነገር ሊያሳየን ፈልጎ ነው። ይህንንም አይሁድ ላቀረቡበት ከስ ግብረ-መልስ ሲሰጥ በተናገረው ውስጥ እናገኘዋለን።

ጌታ ኢየሱስ በመልሱ "ከዚህ የሚበልጥ ሥራ አለና በዚህ አትደነቁ" አለ። ምን ማለቱ ነው? ይህን ምልከት ያደረገው የተመልካቾቹን ትኩረት ወደ እውነተኛ ማንነቱ ለመሳብና አውቀውት እንዲያምኑ፣ አምነውትም ሕይወት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። የጌታ ኢየሱስ እውነተኛ ማንነት በፈዋሽነት የሚወሰን አይደለም። አርሱ ትንሳዔና ሕይወት ነው። መንፈስንም ሆነ ሥጋን ከሞት የሚያስነሳ፣ ሕይወትን የሚሰጥና ለዘላለም የሚያኖር ጌታ ነው። ሆኖም ይህንን በቃል ብቻ ቢናገረው ሊረዱት ስለማይችሉ በተግባራዊ ምሳሌ ማሳየትን መረጠ። ስለዚህ ወደ ቤተ-ሳይዳ ሄዶ ይህን ከሞቱት የማይተናነስ ድኩም ሰው አስነሳ። ኃይል ሰጥቶ አልጋውን አሸከመው። ሰዎች ተደነቁ። ያኔ "በዚህ አትደነቁ፣ ከዚህ የሚበልጥ አለ!" በማለት ስለሚመጣው ትንሳዔ እንዲህ በማለት ተናገረ።

*"በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።" ዮሐ. 5፡21፣ 24-29*

በዘመናት ውስጥ በወንጌል አምነን የመንፈስ ትንሳዔ ሳገኘን፣ ወደ ፊትም በጌታ ዳግም ምጽዓት የሥጋን ትንሳዔ ለምንጠባበቅ ሁሉ የእምነታችን መሠረት የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት በኢየሩሳሌም የተፈጸመው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳዔ ነው። በጌታ ኢየሱስ ከሙታን መነሳት ወደ



ፊት የሚካሄደው የሙታን ትንሳኤ ተረጋግጧል። ስለዚህ በትንሳዔው ተስፋ ደስ ይበለን፣ በትንሳዔው ኃይል እንራመድ፣ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳዔ ለሌሎች እንመስክር።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ሮሜ 4፥16-17, ኢሳ. 25፥6-9. ዮሐ. 11፥23-26**

## ጸሎት

*እግዚአብሔር አባት ሆይ አንተ ለሙታን ሕይወትን የምትሰጥ፣ የሌለውንም እንዳለ አድርገህ የምትጠራ አምላክ ነህ። ይህንንም ኢየሱስ ክርስቶስን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከሙታን በማስነሳት አረጋግጠሃል። እኔንም አንድ ቀን በሥጋ ከሙታን እንደምታስነሳኝና እንደምታከብረኝ አምናለሁ። ጌታ ሆይ ይህ የትንሰኤ እውነት የማይናወጥ የእምነቴ መሠረት እንዲሆን እርዳኝ። ነገ የሚከብር ሥጋዬንም ዛሬ ከማንኛውም በዓለም ከሚገኝ እድፈት እንድጠብቅና በቅድስና እየኖርሁ ፈቃድህን እንድፈጽም እርዳኝ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።*

# 38
# ስረንጌቲ

*« እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ አይታከቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደከሙም።» ኢሳ. 40፥ 25-31*

«ስረንጌቲ» የሚለው መጠሪያ ለጆሮዎ እንግዳ፣ ለልሳንዎ ባዕድ ይሆን? በጥቂቱ ላስተዋውቅዎ።ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኝ በሰሜን ምዕራብ ታንዛኒያ እና በደቡባዊ ምዕራብ ኬኒያ የተንጣለለ በአለም ዝነኛ የሆነ ሰፊ የዱር አራዊትና የዱር እንስሳት መሠማሪያ ቦታ ነው።ስያሜው በማሳይ ቋንቋ «መጨረሻ የሌለው ሜዳ» ማለት ሲሆን ስፋቱ ሰላሳ ሺህ ስኩየር ኪሎ ሜትር ይጠጋል። ይህን አሃዝ በቀላሉ ለመረዳት ከስዊትዘርላንድ የቆዳ ሥፋት በጥቂት የሚያንስ፣ ከእስራኤል ምድር በመጠኑ የሚሰፋ መሬት ነው። በዚያ የሚኖሩት አራዊትና እንስሳት በዓይነት የተለያዩና በቁጥር የበዙ ሲሆን የሜዳ አህዮች ብቻ ወደ ሁለት ሚሊዮን እንደሚጠጉ ይገመታል።

ስረንጊቲ የብዙዎችን ቀልብ እንዲስብ ያደረገው ስፋቱና በውስጡ የያዛቸው የዱር እንስሳት ብዛት ሳይሆን በአመት ሁለቴ የሚካሄደው ፍልሰት ነው። ጎልቁ መሳፍርት የሌላቸው የዱር እንሰሳት ከጥር ወር ጀምሮ በለምለሙ የስረንጊቲ መስክ የበቀለውን እየበሉ እየወለዱና እየተዋለዱ ተረጋግተው ሲኖሩ ይከርሙና ወራቱ ወደ ግንቦት ሲቃረብ፣ የለረንጊቲ ልምላሜ እየከሰመ የሄደ ሲመስል በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሜዳ አህዮች፣ ሚዳቋዎች፣ ጎሾች፣ ድኩላዎች በጋራ ለምንት መቶ ኪሎ ሜትር አቋርጠው በተለመደው የፍልሰት ወግ ወደ ኬኒያዋ ማሳይ-ማራ ይተማሉ። ፈላሾቹ የዱር እንስሳት በማሳይ-ማራ ያገኙትን ልምላሜ እየተመገቡ በዚያም እየወለዱና እየተዋለዱ እስከ ወርሃ ጥቅምት ከሰነበቱ በኋላ በድጋሚ የማሣይ-ማራ ልምላሜ ድርቅ የመታው ሲመስልና ጥለውት የመጡት ለረንጊቲ እንደ ለመለመ ቀልባቸው ሲነግራቸው ማሳይ-ማራን ተሰናበተው ወደ መጡበት ስፍራ ዳግም ፍልሰት ይጀምራሉ። የዱር እንስሳቱን ፈለግ ተከትለው ይህን የፍልሰት አባዜ ለረዥም አመታት ያጠኑ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ልምላሜ ፍለጋ የሚደረገው የዚህ ፍልሰት ውጤት እጅግ አሳዛኝ ነው። በጥማት፣ በርሃብና በድካም በመንገድ ወድቀው በመቅረት እንዲሁም በናይል ወንዝ በሸመቁ አዞዎች በመበላትና በጎርፍ በመወለድ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ የሚጠጉ የዱር እንስሳት በየአመቱ ያልቃሉ።



በዘመናችን የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ሁኔታ ስንመለከት ከስረንጊቲ ታሪክ ጋር ይመሳሰላል። ድነን የገባንበት፣ የተጠመቅንበትና የቆረብንበት፣ ከወገኖች ጋር በክፉውም ሆነ በደጉም ፍቅርን የተካፈልንበት ሕብረት በእኛ ዕይታ ድርቅ የመታው ሲመስለን በሌላ ወገን በቅርቡ የተከፈተ ስምንተኛ ቤተክርስቲያን ሙዚቃው ሲነዝረን፣ ስብከቱ ሲጥመን እንደ ስረንጊቲዎቹ እንስሳት ፍልሰት እንጀምራለን። በፈለስንበት ጸንተን ብንኖር እሰየው ነበር። ነገር ግን ጥቂት ቆይቶ የሄድንበትም ቦታ በእኛ ዕይታ ድርቅ የጎበኘው ሲመስለን ሌላ የፍልሰት ምዕራፍ ይከፈታል። «ታዲያ ምንአለበት? ይህም የእግዚአብሔር ቤት ያም የእግዚአብሔር ቤት!» የሚል ይኖር ይሆናል። ችግሩ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት መሄዱ ሳይሆን እንደ ስረንጊቲዎቹ የዱር እንሰሳት በመንገድ ደክሞ የሚቀረው፣ የአውሬ ራት የሚሆነው ቁጥር መብዛቱ ነው። ታዲያ ከዚህ የፍልሰት አባዜ ለመዳን መፍትሄው ምን ይሆን? በማለት የሚጠይቅ አይጠፋም፣ መፍትሄው ሁለት ነው። አንድ አብረን የምናመልካቸው ወንድሞችና እህቶች በምርጫ ያገኘናቸው፣ በምርጫ የምንለያቸው ሳይሆኑ በዳግም ልደት ለዘለዓለም የተጣመርናቸው፣ ከአንድ አባት በመወለድ የተዛመድናቸው ቤተሰቦቻችን እንደ ሆኑ ማወቅ ሲሆን ሁለተኛው በመካከላችን ችግሮች ቢኖሩ እንኳ የማይደክመውን፣ የማይታክተውን፣ ማስተዋሉም የማይመረመረውን፣ ለደካማ ኃይል የሚሰጠውን፣ ጉልበት ለሌላው ብርታት የሚጨምረውን የልምላሜና የበረከት አምላክ በሥፍራችን ሆነን መጠበቅ ነው። ሁኔታዎች ሲለወጡ ይችላሉ እግዚአብሔር ግን አይለወጥምና በሥፍራችን ሆነን ብንጠብቀው እንለምልማለን እንጂ እንደርቅም፣ እንጠግባለን እንጂ በረሃብ እናልቅም።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ምሳሌ 27፥8, 1ጴጥ. 1፥22-25, ዕን. 3፥17-19**

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ፦ እንደ ስረንጌቲ የዱር እንስሳት ምግብ ፍለጋ ከሥፍራ ሥፍራ ከመንከራተት አድነኝ፣ አንተ የሕይወት ምንጭ ነህና በሥፍራዬ ሆኜ አንተን መጠበቅን አስተምረኝ። አንተን በመጠበቄ ለራሴ ብቻ ሳይሆን አብረውኝ ላሉት ሁሉ የበረከት ምክንያት እሆናለሁና ምንም እንኳ በለሰም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ በመጠባበቂያዬ ላይ እንድቆም አንተንም እንድጠብቅ ጸጋን አብዛልኝ።*

# 39
# ለቅሶ በለቅሶ

*«ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፣ ሳታቋርጡ ጸልዩ፣ በሁሉ አመስግኑ፣ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።» ነተሰሎ. 5፥16-18*

ቤተክርስቲያኒቱ ቅርብ ጊዜ የተጀመረችና ብዙ አባላት የሌሏት እንደ መሆኗ መጠን ገቢዋ ውሱን ነውና ለመጋቢያቸው የሚሰጡት የወር ቀለብ እዚህ ግባ አይባልም። መጋቢው ትዳር ከመሠረተ ጥቂት አመታት ቢሆነውም ባለቤቱ በየአመቱ ስለምትወልድ ትንሿ ቤቱ በልጆች ተጨናንቃለች። «የዛሬ ልጅ ወጪው የዋዛ አይደለም፣ በቀድሞ ዘመን እሥር ልጅ ለማሳደግ የማይወጣ ገንዘብ ዛሬ አንድ ልጅ ላይ ይውላል። ልጅ ሲታሰብ አብሮ የሚታሰበው መብል ብቻ መሆኑ ከቀረ ሰንበቷል፣ ሌላው ቀርቶ የዳይፐር (ዘመናዊ የሽንት ጨርቅ) ዋጋ ብቻውን ሥር የሚነቀንቅ ነው። ልጆቹ ከፍ እያሉ ሲመጡ ደግሞ ጥያቄውም አብሮ ከፍ እያለ ይሄዳል። 'አንዳቅሜ እኖራለሁ' አንዳይባል በሰፈር፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተክርስቲያን በልጆቹ መሃል የሚካሄደው የጫማ፣ የልብስና የመጫወቻ ውድድር አይጣል ነው። » እልጋ ላይ ሆኖ ይህን እና ሌሎች መሰል ነገሮች እያወጣና እያወረደ ሳለ በማለዳ እቅራቢያቸው የሚገኝ ክሊኒክ ደርሳ የምትመለስ ባለቤቱ ፈራ ተባ እያለች አራተኛ ልጅ ቅሪት መሆኗን መርዶ አይሉት ብሥራት ነገረችው።

መጋቢው ግራ ተጋብቶና በጥያቄ ተሞልቶ ወደ ቤተክርስቲያን አቀና። ቢሮው እንደገባ ማንንም ሳያናግር በሩን ቆልፎ ተንበረከከ፣ የተደገፈበት ወንበር በዕንባ እስኪርስ ድረስ ይንሰቀስቅ ጀመረ። «ጌታ ሆይ ምን አደረግሁህ? ሁኔታዬን እያወቅህ!» በማለት ጸሎት አይሉት እንጉርጉሮ፣ መዝሙር አይሉት ሙሾ መደርደሩን ቀጠለ። ድንገት ቢሮው ተንኳኳ፣ ዕንባውን ጠራርጎ ፊቱን አባብሶ በሩን ከፈተ። በሩቅ የሚያውቃት የቤተክርስቲያኑ አባል ናት። ፊቷ ላይ ጥልቅ ሃዘን ይነበባል፣ ብርቱካን የሚመስሉ ቀይ ጉንጮቿ የተጠበሰ ሥጋ መስለዋል። ያለ ቀጠሮ ስለመጣችና የግል ጊዜውን ስለ ወሰደች ይቅርታ ከጠየቀችው በኋላ «ፓስተር ልቤ በሃዘን ተሞቷልና እንድትጸልይልኝ እፈልጋለሁ» አለችው። የራሱን ሃዘን ዋጥ አድርጎ ወደ ቢሮው ገብታ እንድትቀመጥ ከጋበዛት በኋላ ረጋ ባለ ድምፅ «የሃዘንሽ ምክንያት ምንድነው? » በማለት ጠየቃት። «ፓስተር እንደምታውቀው እኔና ባለቤቴን እግዚአብሔር በብዙ ነገር ባርኮናል፣ የንግድ ድርጅታችን አድጎ ደንበኞቻችንን ማስተናገድ ስላልቻልን ሁለት ቅርንጫፎች ከፍተን እየሰራን ነው። ነገር ግን ከተጋባን አምስት አመት ቢሆነንም እስካሁን ልጅ አልወለድንም፣ ለመውለድ ያላደገግነው ጥረት የለም፣ ውጭ ድረስ ሄደን ተመርምረናል ግን ሊሆን አልቻለም» አለችና በድንገት ለቅለቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች። መጋቢው ግራ ተጋባ «እኔ ልጅ መጣ ብዬ እለቅሳለሁ፣ እሷ ልጅ ቀረ ብላ ታለቅሳለች፣ ይሄ ምን አይነት ለቅሶ ነው? » በማለት ራሱን ይጠይቅ ጀመር። ወዲያው ብድግ አለና የሣራ፣ የርብቃ፣ የራሄል . . . አምላክ ማህፀኗን እንዲከፍት፣ በልጆች እንዲባርካት አጥብቆ ከጸለየ በኋላ የራሱን ገጠመኝ በመመሥከር ልጅ ስለመጣም ሆነ ስለ ቀረ መፍትሄው ማልቀስ ሳይሆን እግዚአብሔርን በማመስገን ቸርነቱን መጠባበቅ እንደሆነ መከሯት ተለያዩ። እኛስ ዛሬ የምናዝንበትና የምናለቅስበት ነገር ምን ይሆን? ምን አልባት ሌሎች የእኛ ተቃራኒ በሆነ ጉዳይ እያለቀሱ ይሆን? ምን አልባት የምናለቅሰው ለጊዜው ችግር በሚመስለን ነገር ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር በጎነት ማየት ተስኖን ይሆን? የምናመልከው አምላክ ተግዳሮት የሆነብንን ነገር መለወጥ እንደሚችል ማመን አቅቶን ይሆን? ለሴቲቱ ልጅ፣ ለመጋቢውም ማሳደጊያ መስጠት የሚችል እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ አለ። የእኛንም ጥያቄ በጊዜውና በሰዐቱ በክብር ይመልሳል። ስለዚህ ቅዱስ ቃሉ እንደሚለን "ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበለን፣ ሳናቋርጥ እንጸልይ፣ በሁሉ እናመስግን፣ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እኛ ነውና።"

**ተጨማሪ ንባባት፡- ሮሜ 12፥12, ኤፌ. 5፥20, 2ቆሮ. 6፥10**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ በትልቁ በትንሹ እጨነቃለሁ፣ የማየው የራሴን ብቻ ነው፣ የዛሬውን ብቻ ነው፣ ስለዚህ በቀላሉ ተስፋ እቆርጣለሁ። እባክህ በጸሎትና በምልጃ ከምሥጋና ጋር ልመናዬን ላንተ እንዳስታውቅ እንጂ በእንዳች እንዳልጨነቅ እርዳኝ። አሜን።*

# 40
# ፈንጂ አምካኞች

*«እነርሱ በእምነት . . . የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ።» ዕብ. ፲፩፥33-34*

ሰናይት የአምነት ሴት ናት። በዘምድ አዝማድ መሃል፣ በጎረቤት፣ በዕድር፣ በመሥሪያ ቤት ጌታን በገሃድ እያመለኩ መኖር ዋዛ ባልነበረበት በዚያን ዘመን በእምነትዋ ጸንታ የቆመች አይበገሬ ሴት። ዛሬም ቢሆን መንገድዋ ውጣ ውረድ የሞላበት፣ ትግል ፈተና የበዛበት ነው። በተለይ በአንድ ወቅት ፋታ ሳይሰጥ ተደራርቦ የመጣባት የፈተና ናዳ በዙሪያዋ ያሉትን ወዳጆቿን ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎቿንም ግራ ያጋባ ነበር። ሆኖም ብዙም ሳይቆይ ትንሽ ትልቁ «የሰናይት አምላክ!» እንዲል ያደረገ ትዕይንት ነበር። ብዙዎችን ያሰደነቀው ከገባችባቸው ፈተናዎች በተዓምራት መውጣቷ ሳይሆን በመንገዷ እንደ ፈንጂ የተቀበሩት ፈተናዎች ፈንድተው እሷንም፣ ባቅራቢያዋ ያሉትንም ሳይጎዱ ያመከነችበት ጥበብ ነው።

ሰናይት ለረዥም አመታት በሠራችበት መሥሪያ ቤት ስለ ሥራ ትጋቷና ስለ ታማኝነቷ የማያውቅና የማያደንቃት የለም። የተቀመጠችበት ኃላፊነት ከገንዘብ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ቁልፍ ቦታ ስለሆነ በአፍቅሮተ ነዋይ የተነደፉ የሥራ ባልደረቦቿ አስቀድመው በሸረቡት የሙስና መረብ ሊያጠምዷት ያላደረጉት ጥረት አልነበረም። «አትበላ ወይ አታስበላ!» የሚለው ቅፅል ስሟ እስኪመስል ድረስ ስታልፍ ስታገድም የምትሰማው ቃል ነበር። ሆኖም ይህ ንጽሕናዋ ከሰው ፍርድ አላስመለጣትም። ጠላቶቿ ከቦታው እንድትነሳ በነበራቸው ጉጉት የውሸት ሰነድ አዘጋጅተው ከላይ እስከ ታች እንደ ሠንሰለት ተሳስረው ወነጀሏት። ነገሩ እስኪጣራ ለጥቂት ቀናት ፖሊስ ጣቢያ ሰነበተች፣ ከዚያም ከርቸሌ ወረደች። ንጽሕናዋን የሚያውቁ በሆነው ነገር በገኑ እሷ ግን ተረጋግታለች። ሊጎበኟት የሚመጡ ተጎብኝተው፣ ሊያጽናኗት የሚመጡት ተጽናንተው ይምለሳሉ።

በማረሚያ ቤት እያለች ሌላ የሚያሰደነግጥ ነገር ሆነ! በጣም የምትሳሳላት ሁለተኛ ሴት ልጇ ትምህርት ቤት ራሷን ስታ ትወድቅና ወደ ሃኪም ቤት ስትወሰድ የአንጎል ዕጢ እንዳለባትና በፍጥነት ወደ ውጭ ሄዳ ካልታከመች እንደማትተርፍ ይነገራታል። ቤተሰቦቿ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች



እንዳይነግሯት ቢያስቡም ያለርሷ ዕውቅና ምንም ማድረግ ስለማይችሉ ለመንገር ይገደዳሉ። ሰናይት አስደንጋጩን ዜና ስትሰማ ለጊዜው ብታዝንም ወዲያው በአምላኳ ልቧን አበርትታ «እርሱ ሳያውቀው፣ ሳይመዝነውና ሳይፈቅደው የሚሆን አንዳች ነገር የለም!» በማለት ተረጋጋች። ብቻ ማድረግ ያለባቸውን ነገሮች ተራ በተራ አስረድታ ወደ እሥር ክፍሏ አመራች። መች ይሄ ብቻ በማይጨበጥ ዐመሉ ዘወትር የሚያስቸግራት የማያምን ባለቤቷ ከጸሐፊው ጋር አጉል ግንኙነት እንደ ጀመረ የሰማችውም በዚያው እሥር ቤት ውስጥ ሆና ነበር። በቅርብ የሚያውቋት አንዳንዶች «አይ አሁንማ ይህን ሰምታ ሰው አትሆንም!» ብለው ሲሰጉ አንዳዶችም «ምን የተሰወረ በደል ቢኖርባት ነው?» ብለው በመላምት ሲፈርዱ እሷ ግን ወይ ፍንክች በዚያች ከብዙዎች ጋር በምትጋራት የተጨናነቀች የእሥር ቤት ክፍል ተንበርክካ በዕንባ ለጌታዋ ነግራ ሸክሟን ጥላ ትነሳለች። ችግሮች ዓይነት በዓይነት መጥተውባታል እሷ ግን እንደ ጠንቃቃ ፈንጂ አምካኝ ጉዳት ሳያደርሱ አምክናቸዋለች።

ሰናይት ከአመት በኋላ ፍርድ ቤት በነጻ ለቀቃት ለቤቷ በቃታለች፤ ልጇ ተፈውሳ ትምህርቷን ቀጥላለች፤ ባለቤቷም እግሯ ላይ ወድቆ ይቅርታ ጠይቋት፣ እሱም ጌታን ተቀብሎ በሰላም መኖር ቀጥለዋል። ትልቁ ጥያቄ እነዚህን ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰው ጋር የነበሯትን ግንኙነቶት ምስቅልቅሉን ሊያወጡ የሚችሉ በመንገዷ የተቀበሩ ፈንጂዎች እንዴት አመከነቻቸው?

የዕብራዊያን መልዕክት ጸሐፊ ገድላቸውን የሚዘክርልን እነዚያ የጥንቶቹ የእምነት ጀግኖች እንደ ሰናይት ፈንጂ አምካኞች ነበሩ። ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ በእምነት የአንበሶቹን አፍ ዘጋ እንጂ አንበሶቹን አልገደለም። አንበሳ ለመግደል የአዳኝነት ችሎታ እንጂ እምነት አይጠይቅም። አንበሶቹን ቢገድል ኖሮ የሚደነቀው እሱ እንጂ አምላኩ አይሆንም ነበር። ደግሞም አንበሶቹ ከጉድጓድ ከወጣ በኋላ ቀጣይ ሥራ ስላላቸው መሞት አልነበረባቸውም። ስለዚህ አንበሶቹ በሕይወት እያሉ የሚጎዳውን አፋቸውን በእምነት ዘግቶ በመካከላቸው አደረ። ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብድናጎም በእቶን እሳት ውስጥ በተጣሉ ጊዜ እምነታቸው እሳቱን አላጠፋውም፤ እሳቱን ቢያጠፉ ኖሮ ምን ይገርማል? የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞችም እሳት ያጠፉ የለ? እነሱ ግን እሳቱን ትተው የማቃጠል ኃይሉን ብቻ አጠፉ። ከዚያማ ገብተው ይመላለሱበት ጀመር። ከሰይፍ ስለት

አመለጡ የተባሉትም ከሰይፍ ቢያመልጡ ኖሮ ፈጽሞ አያስገርምም፤ ማንም ፈሪ ከሰይፍ ሸሽቶ ሊያመልጥ ይችላልና። እነዚህ የእምነት ጀግኖች ግን ሰይፉን ተጋፍጠው ከስለቱ አመለጡ። በሰው ላይ ጉዳት የሚያደርሱት የአንበሳም አፉ፤ የእሳትም የማቃጠል ኃይሉ፤ የሰይፍም ስለቱ መሆናቸው ግልጽ ነው። የእምነት ሰዎች ግን አንበሳውን ትተው አፉን ይዘጋሉ፤ እሳቱን ትተው ኃይሉን ያጠፋሉ፤ ሰይፉን ትተው ስለቱን ያመልጣሉ። ሁኔታውን ከውጭ የሚያዩ «ብቃ አስቀላቸው! » ቢሉም በኋላ በሚሆነው ነገር እግዚአብሔርን ማከበራቸው የማይቀር ነው። ፈንጂ አምካኝ ይሏል ይህ ነው።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ዕብ. 11፥11, 1ሳሙ. 17፥51, ዳን. 3፥23-25**

### ጸሎት

*ጌታ ሆይ፦ አባክህ ይህን እምነት አስታጥቀኝ! በችግሮቹ ገፅታና ግዝፈት ሳልታወክ ከችግሮቹ ሁሉ በላይ የሆንከውን አንተን እያየሁ የመጉዳት አቅማቸውን አምክኜ አንተ ለሰው የማይቻል በሚመስል ነገር ውስጥ እንዴት ማሳለፍ እንደምትችል ምስክር እንድሆን ጸንቼም ሰምህን እንዳስጠራ እርዳኝ። አሜን።*



# 41
# የቁም ቅዠት

*"እኛ ከጨለማ የተነሣ በሥርዓት መናገር አንችልምና የምንለውን አስታውቀን።" ኢዮብ 37፥19*

እድካሚውን የሲድኒ አገልግሎቴን እንደ ጨረስኩ የታየኝ ጥሩ ዕረፍት ነበር። ወንድሞች ከከተማ ይዘውኝ ሊወጡ ቃል ገብተውልኛል፤ ሆኖም ወዴት እንደሚወስዱኝ በግልጽ ስላልነገሩኝ ጉጉትም ጥያቄም በውስጤ ነበር። የቀጠሮው ሰዓት ደርሶ እንደተገናኘን የምንሄድበት ስፍራ ከሲድኒ በስተምዕራብ 175 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እንደሚገኝ ነገሩኝ። በጥር ወር የደቡብ ንፍቀ ከበብ ከሚገኙ ሀገራት በማራኪ አየሯና ነዋሪዎቿ "ከአባቶቻችን የወረስናት ብቻ ሳትሆን ከልጆቻችን የተዋስናት" በሚሏት ለምስሚቱ አውስትራሊያ ጉዟችንን ጀመርን።

ያቀናነው በጥንታዊነቱ ወደር አይገኝለትም ወደሚባለው፤ በየዓመቱ በርካታ ጎብኚዎች ወደ ሚያዘወትሩት ጀኖላን ዋሻ ነው። ይህ በኖራ ድንጋይ የተዋቀረ፤ ውስጥ ለውስጥ በኪሎሜትሮች የሚቆጠር ርቀት ለማስኬድ የሚያስችልና በጥልቀቱ እቻ የሌለው ዋሻ ከሥሩ ምንጭ ይንዶለዶላል፤ ወንዝ ድምፁን እጥፍቶ በለሆሳስ ይፈሳል።

ዋሻው ብዙ ዘመናት ያስቆጠረ ዕድሜ ጠገብ ቢሆንም አውስትራሊያኖች በዘመናዊ መልክ ደህና አድርገው ሠርተውታልና በሙብራትና በብልሃት በተበጀለት ደረጃ እየታገዝን በሚያስፈራው ዋሻ ውስጥ ርቀን ወደ ጥልቅ ወረድን። በየግድግዳውና በየጥጋጥጉ የተለያዩ የእንስሳትና የአራዊት ዐፅሞች፤ የተለያዩ ነገሮች ቅሪተ አካላትና የጥንታዊ የዋሻ ጽሁፎች ይታያሉ። በአውስትራሊያዊት አስጎብኚያችን እየታገዝን መኪናችንን ካቆምንበት ወለል ጠልቀን ወደ ዋሻው የመጨረሻ ወለል እንደደረስን አስጎቢኚያችን ሰው ሰራሹን መብራት ለአንድ ደቂቃ ያህል ልታጠፋው እንደ ሆነና ከስፍራችን እንዳንንቀሳቀስ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ሰጠችን። በማከልም በሕይወታችን አይተነው የማናውቀውን እውነተኛ ጨለማ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደምንለማመድ ነገረችን።

መጀመሪያ ላይ የምትለው ነገር መቀበል አዳግቶኝ ነበር «እንደ እኔ ያለ ከአፍሪካ ምድር የመጣ ሰው እንዴት ነው እውነተኛ ጨለማን

የማያውቀው?» በሚል፤ ነገር ግን ገለጻዋን በቀጠለች ቁጥር ለማለት የፈለገችውን መረዳት ቻልሁ። ለካ ሲመሽ የሚሰፍነውን ጨለማ ሙሉ ኃይሉን እንዳንገነዘብ የሚያግዱን አናሳ ብርሃናት አሉ! የጨረቃ ብርሃን፣ የከዋከብቱ ጭላንጭል፣ ከቅርብና ከሩቅ የሚመጣ የመብራት ወገግታ እውነተኛውን ጨለማ እንዳንለማመድ ያግዱናል። በዚህ ጥልቅ ዋሻ ውስጥ ግን ጨለማ ከነነፍሱ አለ። መብራቱ ሲጠፋ ምንም አይነት ተፈሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ብርሃን ጣልቃ ስለማይገባበት ጨለማ ጨለማ ሆኖ ይገለጣል። አስጎብኚያችን የዋሻውን ብርሃን ሙሉ በሙሉ አወደመችው። ጨለማ ነገሠ! ከአንድ ደቂቃ በላይ አጥፍታው ብትቆይ አንድ አስገራሚ ነገር እንደሚሆን እንዲህ ስትል አወጋችን «ይህ ድቅደቅ ጨለማ ለተጨማሪ ደቂቃዎች ቢቆይ ኖሮ ሁላችሁም ማየት ትጀምሩ ነበር። የምታዩት ግን ቅዠት እንጂ እውነተኛ ነገር አይደለም። አዕምሯችሁ እንዳች የብርሃን ፍንጭ ሲያጣ የራሱን ነገር መሳል ይጀምራል ያኔ «ሃሉሲኔት» ያደርጋል ማለትም መሠረት የሌላቸውን ነገሮች ማየት ይጀመራል። ከሥፍራችሁ እንዳትንቀሳቀሱ በማለት አስቀድሜ ጥብቅ ትዕዛዝ የሰጠሁት በዚህ ምክንያት ነው» ንግግሯን ስትጨርስ ምን አለ ጨለማውን ጥቂት አቆይታው ይህን የምትለውን ነገር ባየሁ! በማለት ተመኘሁ ነገር ግን ሌሎች ጎብኚዎች አብረውን ስለ ነበሩና ምንአልባትም የዋሻው ሕግ ይህን ስለማይፈቅድ ከመጠየቅ ታቅቤ ጉብኝቴን አጠናቅቄ ወጣሁ።

ሆኖም ግርምቱ ፈጽሞ አለቀቀኝም፤ ለካ አዕምሯችን ዙሪያችን ብርሃን አልባ መሆኑን ሲያረጋግጥ የራሱን ዓለም ይፈጥራል! የሌለ ነገር ይስላል! ለካ ብርሃን ሥፍራ ሲለቅ፣ ጨለማ ሲደላደል ጨለማ የራሱን የውሸት ብርሃን ይለኩሳል! አስፈሪ እውነት ነው። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ወደ አዕምሮዬ ይመጡ ጀመር። ሐዋርያው ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ማንነት ሲገልጽ «እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በርሱ ዘንድ ከቶ የለም!» ያለበት ምክንያት ገባኝ። ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ ሰይጣን ማንነት ሲጽፍ ለምን «የጨለማው ዓለም ገዥ፣ የጨለማው ሥልጣን » እንደሚለው ተረዳሁ። ለካ ጨለማ የራሱ የውሸት ዓለም፣ የመምሰል ከተማ አለው! ይህንን የሐሰት ከተማ እውነተኛ ብርሃን ካላፈራረሰው በቀር በሰው አዕምሮ ውስጥ ከትሞ ይኖራል። ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛ ብርሃን እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ሕይወት ሲበራ ግን



በጨለማ ጡብ የተገነቡ፣ በሐሰት ብርሃን ያሸበረቁ፣ በውሸት ዕውቀት የደመቁ የሃሳብ ከተሞች እንደ ጉም በነው ይጠፋሉ።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ኢሳ. 60፥2, ኤፌ. 4፥18, 2ቆሮ. 4፥4-6**

## ጸሎት

*«ጌታ ሆይ አንተ የሕይወት ብርሃን ነህ! ብርሃን ይታያል፣ ብርሃን ያሳያል፤ ብርሃኑን የሚቀበልና የሚያንፀባርቅ ሁሉ ብርሃን ይሆናል። ጌታ ሆይ ከብርሃንህ ፈቀቅ ከማለትና በጨለማ ከመዋጥ ጠብቀኝ። አንተ ተጓዥ ብርሃን ነህና ሁሉን ጥዬ እንድከተልህ እርዳኝ። አሜን።*

# 42
# የናይል ተፋሰሶች

*«አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባርያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።» 1 ቆሮ. 12፥13*

ከረዥም ጊዜ በፊት የተያዘ የለብለባ ቀጠሮዬን ለማክበር መንገዱ ሳይዘጋጋ በማለዳ ልወጣ በጥድፊያ ላይ ነኝ። በመስታወቱ ትይዩ ጸጉሬን እያበጠርኩ ሳለ ከሩቅ በሬዲዮ የሚሰማው የጠዋት ዜና ቀልቤን ወሰደው። አንባቢው በመረዋ ድምጽ ‹‹ከግብፅና ከሱዳን ውጪ ያሉት ዘጠኙ የአባይ ተፋሰስ አገሮች በውሃው ፍትሃዊ አጠቃቀም ላይ ውይይት ያደረጉ ሲሆን ከኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ በስተቀር ጉዳዩን በፓርላማዎቻቸው ለማጽደቅ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።» ሲል አንድ ያላዋቂ ጥያቄ በውስጤ አቃጨለ «ለመሆኑ እነዚህ አሥራ አንድ አገራት እነማን ናቸው? ደግሞስ በአባይ ውሃ ምን አገባቸው?» ይህንኑ እያሰላሰልኩና በቀጣይነት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ራሴን ማስተማር እንዳለብኝ እያሰብኩ መኪናዬን አስነስቼ ወደ ቀጠሮዬ መገሥገሴን ተያያዝኩ።

በርዝመቱ በአለም ወደር የማይገኝለት የናይል ወንዝ እንደ ስሙ ገዘፎ፣ በረሃ አቋርጦ ሱዳንንና ግብፅን እያለማ ወደ ሜዴትራሊያን ባህር የሚፈሰው ብዙ ትላልቅና ትናንሽ ገባር ወንዞችን አካትቶ ነው። ብሉ ናይል በመባል የሚጠራው ከኢትዮጵያ የሚነሳው ወንዝ ከአገር ውስጥ ተከዜን፣ ከኤርትራ መረብን፣ ከሱዳን አትባራን ቀላቅሎ ካርቱም ላይ ከዋይት ናይል ጋር ይዋሃዳል። ነጭ አባይ ከኪኪዚ ተራራ ሥር ከሚፈልቀው ከሩቶቩ ምንጭ ተነሥቶ የታንዛኒያውን ካጌራ ወንዝ ጨምሮ ወደ ቪክቶሪያ ሃይቅ ይፈሳል። የቡሩንዲው ሩቪሮዛና የሩዋንዳው ኒያባሮንጎ የታንዛኒያ ድንበር ላይ ይላተሙና ሩሰሞ የተሰኘውን ፏፏቴ ይፈጥራሉ። «ቪክትሮሪያ ናይል» ተብሎ የሚጠራው ከቪክቶሪያ ሃይቅ የሚነሳው ወንዝ በምዕራብ ዩጋንዳ ያቋርጥና የኪዮጋን ሃይቅ መግቦ የካሩማንና የሙርቺሶን ፏፏቴዎች ፈጥሮ ከኮንጎ ስማያዊ ተራሮች ከሚነሳው አልበርት ሃይቅ ጋር ይቀላቀላቀልና ወደ ደቡብ ሱዳን በማቅናት የተራራው ናይል ወይም 'ባሕር አል-ጀበል' የተሰኘውን ስያሜ



ይይዛል። ወዲያው የዲንካ ሰዎች ከሚኖሩበት 'ኖ' ሃይቅ ጋር ተቀላቀሎ ዋይት ናይል የሚለውን ስያሜ ያገኝና ከኢትዮጵያ ከሚመጣው ብሉ ናይል ጋር ካርቱም ላይ ተዋህዶ ወደ ግብፅ ረዥሙን የበረሃ ጉዞ ይጀምራል።

አስገራሚውን የናይልን አፈጣጠር ካጠናሁ በኃላ ወንዙን የተንተራለ ተምሳሌታዊና ትምህርታዊ ሃሳብ በልቤ ተጫረ። «ለመሆኑ የኮንጎው አልበርት፣ የዩጋንዳው ኪዮጋ፣ የታንዛኒያው ካጌራ፣ የቡሩንዲው ሩቪሮዛ፣ የሩዋንዳው ኒያባሮንጎ፣ የዩጋንዳው ኪዮጋን፣ የደቡብ ሱዳኑ ኖ ሲገናኙና አንድ ወንዝ ሆነው ወደ ካርቱም ሲፈሱ እኔ ኮንጓዊ ነኝ ከዩጋንዳው ውሃ ጋር ጎን ለጎን አልሄድም፣ እኔ ታንዛኒያዊ ውሃ ነኝ ከቡሪንዲ ውሃ ጋር አልቀላቀልም ይሉ ይሆን? የኤርትራው መረብ ከኢትዮጵያው አባይ ጋር ሲገናኝ ካንተ አጠገብ አልፈስም ብሎ ጥግ ጥጉን ይሄድ ይሆን? ነጩና ጥቁሩ አባይ ካርቱም ላይ ሲገናኙ የቀለም አብዮት ፈጥረው እርስ በርስ ይናናቁ ይሆን? በቋንቋ ይጋጩ ይሆን?» ስል ራሴን ጠየቅሁ። ውኆቹ ምንም እንኳ ባገራቸው የተከበሩ፣ ስም የወጣላቸው፣ ቅኔ የተዘረፈላቸውና የተቀነቀነላቸው ቢሆኑም የፈለቁበት ምድር ባሕል ሳይበግራቸው፣ ቋንቋና ቀለም ሳይለያቸው፣ የፖለቲካ አመለካከት ላያጣላቸው፣ ታሪክ ሳያጨቃጭቃቸው ተዋደውና ተዋህደው በአንድ ስም እየተጠሩ ይፈሳሉ።

እኛም በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን በአንዱ መንፈስ ስንጠመቅ አንድ የዘላለም ሕይወት ወንዝ ውስጥ ገብተናል። በራሳችን የፈለገውን ያህል ዝና፣ ክብር፣ ታሪክ፣ ስም፣ ሃብት የነበረን ብንሆን በዚህ የሕይወት ወንዝ ውስጥ ስንገባ የቀድሞው ማንነታችን በክርስቶስ ማንነት ተውጦ ጠፍቷል። አሁን ታሪካችንም መጠሪያችንም እርሱ ነው። ብዙዎች በገቡበት መጠን እያደገና እየሰፋ የሚሄደው ይህ ክርስቶስ የሚባል ወንዝ ሁሉን እያሸነፈ፣ እየገዛና እየጠቀለለ ይተማል። በዚህ የሕይወት ወንዝ ውስጥ የገቡ ሁሉ ማንነታቸውን እየጣሉ የእርሱን ማንነት ለብሰው ወደ ዘላለም ይገሰጋሳሉ። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ «በዚያም የግሪክ ሰው፣ አይሁዳዊም፣ የተገረዘም፣ ያልተገረዘም፣ አረማዊም፣ እስኩቴስም፣ ባሪያም፣ ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው።» (ቆላ. 3፥11) ያለው።

ተጨማሪ ንባባት፦ ዮሐ. 7፥39, ገላ. 3፥28,

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ ከአንተና ከበጉ ዙፋን ከሚፈልቀው የሕይወት ወንዝ ገባር ስላደረከኝ አመሰግንሃለሁ። በዚህ የሕይወት ወንዝ ውስጥ ከሌሎች ገባሮች ጋር ሰፈስ አሮጌ የሥጋ ታሪክ አየደረደርኩ የራሴን ኩሬ እንዳልሰራ እባክህ ከራሴ አድነኝ! እኔነቴን ጥዬ ባንተ ተጠቅልዬ እንድኖር ዕርዳኝ! ከወገኖቼ ጋር በውጭ ያለኝን ልዩነት ሳይሆን በውስጥ በአንተ ያለንን የሕይወት አንድነት እያየሁ በቅዱስ ሕብረት አብሬያቸው እንድፈስ ዕርዳኝ። አሜን።*



# 43
# የተቀደዱ ጉድጓዶች

*"ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና፤ እኔን የሕያውን ውሃ ምንጭ ትተውኛል፤ የተቀደዱትንም ጉድጓዶች ውሃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች ለራሳቸው ቆፍረዋል።" ኤር. 2፥13*

በጥንት ዘመን ድርቀት በሚያጠቃው በከነዓንና በፍልስጤም ምድር በአስተማማኝ ሁኔታ ውሃ ለማግኘት የማይደረግ ጥረት አልነበረም። ጥንታዊያኑ ውሃን በተመለከተ አስተማማኝ አቅርቦት ሲፈልጉ ጉድጓድ ይቆፍራሉ፤ የጉድጓድ ውሃ ከተገኘ ታላቅ ደስታ ይሆናል። ለጉድጓዱም ስም ያወጡለታል፤ አካባቢውም በዚያው ስያሜ ይጠራል። በቅርብና በሩቅ ያሉም እየመጡ በዋጋ ይቀዳሉና የተገኘው ጉድጓድ ለባለቤቶቹ አስተማማኝ የብልጥግና ምንጭ ይሆናል።

በነቢዩ በኤርሚያስ ዘመን ግን አንድ አዲስ "ቴክኖሎጂ" የመጣ ይመስላል። የኖራ ድንጋይ ይሠረሥሩና በሰፋት ያጎደጉዱታል። ይህን የሚያደርጉት ውሃ እንዲያመንጭ ሳይሆን በዝናብ ወራት የሚወርደውን ውሃ አቁሮ እንዲያቆይላቸውና በሌላ ጊዜ መጠቀም እንዲያስችላቸው ነው። ሆኖም ይህ አዲስ ግኝት የራሱ ችግር ነበረው፤ አንዳንዴ የኖራው ድንጋዩ ይሰነጠቅና የተከማቸው ውሃ ውስጥ ውስጡን ፈሶ መና ይቀራሉ።

እግዚአብሔር እሱን በመተውና እንግዶች አማልክትን በማምለክ የፈጸሙትን የሕዝቡን እኩይ ተግባር ፍንትው አድርጎ ለማሳየት የውሃ ምንጭ ጉድጓድንና የኖራ ድንጋይ ውሃ ማቆሪያን ያነጻጽራል። እሱ ለሕዝቡ በራሱ ውሃ እንደሚያፈልቀው፣ ከዓመት ዓመት እንደማይነጥፈው የውሃ ጉድጓድ ሆኖ ሳለ፣ እነርሱ ግን እርሱን ትተው በራሳቸው ውሃ እንደሌላቸው፣ ተሰንጥቀው እንደሚያፈሱ የኖራ ጉድጉዶች የሆኑትን አማልክት ለማምለክ እየደከሙ እንዳሉ ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር ይህንን ተግባር *"ሕዝቤ ያደረጉት ሁለቱ ክፉ ነገሮች"* ብሎ ጠርቶታል። አንደኛው የሕይወት ውሃ ምንጭ የሆነውን እርሱን መተዋቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ውሃ ይይዙ ዘንድ

የማይችሉትን፣ የተቀደዱ ጉድጓዶች የሚመስሉትን እንግዶች አማልክትን ለማምለክ መማለናቸው ነው።

በምንኖርበት በዚህ በሠለጠነ ዓለም እግዚአብሔርን ትቶ ከወርቅ ከብር፣ ከናስ ወይም ከእንጨት የተሠሩ ጣዖታትን ለማምለክ የሚፈተን ክርስቲያን አይኖር ይሆናል። ነገር ግን ዕለት ተዕለት ልባችንን የሚያርዱ ጣዖታት በዙሪያችን ሞልተዋል። 'ያሳርፉናል፣ ደስታን ይሰጡናል፣ በክፉ ቀን ይደርሱልናል' ብለን በልባችን የምንታመንባቸው ጣዖታት አሉ። እነዚህን ጣዖታት ለመከተል እግዚአብሔርን መተው ግድ ይላል፤ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው የለምና። ይህ ደግሞ ከፋቱን እጥፍ ያደርገዋል። አንደኛው፥ እግዚአብሔርን መተው ሲሆን ሁለተኛው፥ የአምላከነት ባሕሪ የሌላቸውን ሌሎችን መከተል ነው። ለመሆኑ እነዚህ ጣዖታት እነማን ናቸው? አፍቅሮተ ነዋይ ወይም ለገንዘብ መንምዝት ወይም መስገብገብ አንዱ ጣዖት ነው። ሆዳምነት ወይም ስለ መብል መገዛት ሌላው ነው። ምቾትንና ድሎትን መመኘት፣ ክብርን፣ ኃይልንና ዝናን መውደድ ሌሎቹ ጣዖታት ናቸው። ከላይ የተዘረዘሩትን "ጣዖታት" ያልናቸው በዘፈቀደ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሳያቅማማ በዚህ ሥም ይጠራቸዋል። ጌታ ኢየሱስ በተራራው ትምሕርት ገንዘብን ከእግዚአብሔር በማነጻጸር ጣዖትነቱን ያረጋግጣል (ማቴ. 6፥24) ። ሐዋርያው ጳውሎስ "ሆድ" ለአንዳንዶች እምላክ መሆኑን (ፊሊ. 3፥19)፤ ገንዘብን መመኘት ጣዖትን እንደ ማምለክ መሆኑን (ኤፌ. 5፥5፡ ቆላ. 3፥ 5) በግልጽ ይጽፋል። እነዚህን ሁሉ ለማግኘት መድከም በተሰነጠቀ ጉድጓድ ውስጥ ውሃ ለማስቀመጥ እንደ መሞከር ነው።

ታዲያ ዛሬ ለእግዚአብሔር እየተገዛን ነው? ወይስ ለእነዚህ ጣዖታት እየተንበረከክን? እነዚህን ሕይወት የማያፈልቁ፣ ያለንንም የሚነጥቁ ዘመነኛ ይምሰሉ እንጂ ጥንትም የነበሩትን ጣዖታት እናስወግድና የዘላለም ሕይወት ምንጭ የሆነውን ጌታ በንጹሕ ልብ እናምልክ።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ኤር. 17፥13፤ የሐ. 4፥10፤ መዝ. 36፥9**

**ጸሎት**



*የሕይወት ራስ ሆይ! አንተ ዛሬም ለዘለዓለምም ጽኑ መታመኛ ነህ። ለገንዘብ መንምዝትንና ስግብግብነትን፣ ሆድ አምላክነትን፣ ለምቾት መገዛትንና ለከንቱ ውዳሴ ማጎብደድን አስወግጄ በአንድ ሓሳብና በንጹሕ ልብ አንተን ብቻ እንዳመልክ ጸጋህ ይብዛልኝ። አሜን።*

# 44
# የክብር መንገድ

*"ጌታም የጭንቀትን እንጀራና የመከራን ውሃ ቢሰጥህም አስተማሪህ እንግዲህ ከአንተ አይሰወርም፤ ዐይኖችህ ግን አስተማሪህን ያያሉ፣ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ ብትል ጆሮችህ በኋላህ፦ መንገዱ ይህች ናት በእርሷም ሂድ የሚለውን ቃል ይሰማሉ" ኢሳ. 30፡ 20-21*

ሰሞኑን ጥሩ ስሜት አልነበረኝም፣ ልቤ በሃዘን ተሞልቷል፣ ደስታ ከእኔ ከራቀ ሰንብቷል፣ ተስፋ መቁረጥ በዙሪያዬ ያንዣብባል። ከስደት ከተመለስኩ ብዙ ወራት ባስቆጥርም ስመጣ የነበረኝ ቁርጠኝነትና እርግጠኝነት ተሸርሽሮ ትክክለኛ ውሳኔ ስለ መወሰኔ ጥርጥር ገብቶኛል። የኔ ምኞትና የማልፍበት መንገድ ለየ ቅል ሆነው በቁሜ እየፈረስኩ፣ ወደ ሞት አሸዋ እየወረድኩ እንዳለሁ ይሰማኛል። እሱን ብዬ፣ ሁሉን ጥዬ የተከተልኩት ጌታ ትቶኝ ፈቀቅ ያለ በሚመስል ስሜት ተወጥሬያለሁ።

የልደታ መካነ የሱስን የዓርብ ምሽት አምልኮ ለመካፈል እግሮቼ በደመ-ነፍስ በአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ በሚያቋርጠው መንገድ አዘገሙ። ስደርስ አዳራሿ ጢም ብላ ሞልታ ጠጠር መጣያ ቦታ የለም። የቤተክርስቲያኒቱ የመዘምራን ቡድን ጣዕመ ዜማ ያፈሳሉ። አማራጭ ስላልነበረኝ መድረኩ ጥግ ከኔ ብጤዎች ጋር ቁጢጥ አልኩና ዐይኔን ጨፍኜ ዝማሬውን ማድመጥ ቀጠልሁ። ዘማሪያኑ በምናልፍበት መንገድ ጌታን ስለመታመን ያቀነቅናሉ። ሳላውቀው ተመስጦ ውስጥ ገባሁ። በራዕይ አንዲት እናት ልጇን ለማስዋብና ደስ ለማሰኘት አስባ የጆሮ ወርቅ ገዝታ ስትመጣ አያለሁ፤ ሆኖም ልጅቷ ጆሮዋ ስላልተበሳ የገዛችላትን ወርቅ ልታደርግላት ትቸገራለች፤ ስለዚህ ክስል አቀጣጥላ፣ ወስፌ አግላ፣ ልጅቱን በጭኖቿ ሥር አስገብታ በእግሮቿ ቆልፋ ይዛ ጆሮዋን ስትበሳት አያለሁ። ልጅቷ ህመሙ ጸንቶባት እሪ ትላለች፤ በልቧም በእናቷ ጭካኔ ትመረራለች። ድንገት ባንኜ ነቃሁ። አሁንም ልደታ መካነ የሱስ መድረክ ጫፍ ላይ ቁጢጥ ብያለሁ። ዘማሪያኑም ጣዕመ ዜማ ያፈሳሉ። ያየሁት ራዕይ ትርጉም ሲገባኝ የመንፈስ ደስታ በልቤ ፈሰሰ። የውስጥ ሕመም የተሰማኝ ጌታ ስለተወኝ ሳይሆን በጸጋው ሊያስውበኝ ባሕሪዬን እየሠራ እንደሆነ ስለገባኝ ሥራውን እስኪጨርስ መታገስ እንዳለብኝ ተገነዘብኩ። ለሥጋዬ ሕመም፣ ለመንፈሴ ግን ሕይወት የሆነው ይህ መንገድ በፍጻሜው ለስሙ



ክብር፣ ለብዙዎች ጥቅም፣ ለእኔም ዘላቂ ደስታ እንደሚያጎናጽፈኝ ገባኝና ተስማማሁ።

እግዚአብሔር ለክብር እንጂ ለመከራ አልጠራንም። ነገር ግን ወደ ክብር የሚወስደው መንገድ መከራ አለበት። ክብር የዘላለም መኖሪያችን ነው። መከራ ግን ጊዜያዊ መንገዳችን ነው። ጌታ ሥጋዊውን፣ አዳማዊውን፣ አሮጌውንና የኃጢአት ዝንባሌ ያለውን ተፈጥሯችንን አስወግዶ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ሊያጎናጽፈን ሲል የሚወስደን መንገድ ለሥጋችን ቢያምም ለመንፈሳችን ግን ሕይወት ነው። ከላይ በነቢዩ በኢሳያስ ትንቢት እንዳነበብነው እግዚአብሔር እልከኛዋንና አመጸኛዋን እስራኤልን የጭንቀትን እንጀራ አብልቶ፣ የመከራ ውሃ አጠጥቶ ወደ ራሱ ከመለሰ በኋላ የዐይኗን ሞራ ገፎ አስተማሪዋን የምታይ፣ የደፈናትን ኩክ አውጥቶ ድምፁን የምትሰማ እንዳደረጋት እናያለን። ለእኛም እንዲሁ ይሁንልን!

**ተጨማሪ ንባባት፦ ኢሳ. 35፥8፤ መዝ. 80፥5፤ መዝ. 27፥8-9**

## ጸሎት

*ቅዱስ ጌታ ሆይ! እባክህ ለእልከኝነቴና ለልቤ ፈቃድ አሳልፈህ አትስጠኝ። በከንቱ የሚጨነቀውን፣ ሥጋዊ መፍትሄ የሚሻውን፣ በአንተ መታመን የማይቀናውን ሥጋዊ ማንነቴን አስወግደህ፣ ክብርህን የሚያይ፣ ድምፅህን የሚሠማ፣ በመንገድህም የሚሄድ ማንነት በውስጤ ፍጠር። አሜን።*

## 45
# “ይቅርታ! አንተ ኢየሱስ ነህ?”

*«እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።» (1 ቆሮ. 11፥1)*

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ ከተማ የሚኖሩና በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ አራት ጓደኛሞች ራቅ ያለ ከተማ በተዘጋጀ የንግድ ስብሰባ ላይ ለመካፈል ወደ አይሮፕላን ማረፊያ ያቀናሉ። የተጓዙት ሰኞ ሲሆን ቅዳሜ ምሽት በመኖሪያ ከተማቸው በተዘጋጀው የራት ግብዣ ላይ ለመታደም ቀደም ብለው እንደሚመለሱ ለሚስቶቻቸው ቃል ገብተዋል። ስብሰባቸውን ዓርብ ማታ ጨርሰው ስላደሩ ቅዳሜ በማለዳ ወደ ከተማቸው የሚመለሱበትን አይሮፕላን ለመያዝ ከሆቴላቸው ተነሱ። የመኪናው ጭንቅንቅ መንገድ ላይ አዘግይቷቸው ስለነበር አይሮፕላን እንዳያመልጣቸው በመስጋት የመሳፈሪያ ትኬት ወደ ሚያገኙበት ባንኮኒ ተጣደፉ። አስተናጋጇ ለጥቂት ከመቅረት እንደ ተረፉ ነግራ አሁንም መግቢያው ሳይዘጋ ወደ በሩ እንዲፈጥኑ አስጠንቅቃ ትኬቶቻቸውን ሰጠቻቸው። አራቱም ለሚስቶቻቸው የገቡትን ቃል እንዳያፈርሱ በመስጋት የእጅ ሻንጣዎቻቸውን እየጎተቱ በረዥሙ የአየር ማረፊያው ኮሪደር ሩጫቸውን ተያያዙት። በጥድፊያው መሃል ከመካከላቸው አንዱ ሳያውቀው በእጅ ሻንጣው በኮሪደሩ ጠርዝ ላይ የቆመ የጠረጴዛ እግር መታ። በጠረጴዛው ላይ ተደርድረው የነበሩት ፍራፍሬዎች በወለሉ ላይ ወዲህና ወዲያ ተበተኑ። ሁሉም ጠረቤዛው እንደ ተመታና ፍሬዎቹ እንደ ተበተኑ ቢያውቁም ወደ ኋላ ለማየት ፋታ አልነበራቸውምና ወደ አይሮፕላኑ መግቢያ በር ሩጫቸውን ቀጠሉ። በሩ ሲዘጋ ጥቂት ሲቀረው ደረሱና ትኬታቸውን እያሳዩ መግባት ጀመሩ።

ነገር ግን ከመካከላቸው አንዱ ቆም ብሎ ለአፍታ አሰበ! በረዥሙ ተነፈሰና ወደ ኋላ ዞር ብሎ ተመለከተ። ፍራፍሬውን ደርድራ ስትሸጥ ሳለ ጠረጴዛው የተመታባትና የተበተነባት ልጃገረድ ግራ በመጋባት ቆማ አያት። የሆነ ነገር አንጀቱን አናወጠው፣ የርህራሄ ስሜት አሸነፈው፤ወደ ኋላው ዞር ብሎ በመሳፈር ላይ ለነበሩት ጓደኞቹ በስንብት አጁን እያወዛወዘ ጉዟቸውን እንዲቀጥሉ ካመለከተ በኋላ ስባለቤቱ በዚህ በረራ መድረስ እንዳልቻለ ነገር ግን በሚቀጥለው እንደሚመጣ እንዲነግሩለት



ተማጽኖና በኮሪደሩ ጥግ ተሰፋ በመቁረጥ ወደ ቆመችው ልጃገረድና በወለሉ ላይ ወደ ተበታተኑት ፍሬዎች አመራ።

ይህን ውሳኔ በመወሰኑ እጅግ የተደሰተው አንድ ነገር ሲያውቅ ነበር። ስካ ጓደኛው ጠረቤዛውን በመግጨቱ ደርድራ ትሸጥ የነበረውን ፍራፍሬው የበተነባት የ16 ዓመት ወጣት ልጃገረድ ዓይነ ሥውር ነበረች። ትኩር ብሎ ሲመለከታት ግራ በመጋባትና ተሰፋ በመቁረጥ ቆማ ድምጽዋን ሳታሰማ ታነባለች። የዕምባ ዘላዎች በጉንጮቿ ላይ እየተንከባለሉ ቀሚሷን ያርሳሉ። ስለ ተበታተኑት ፍሬዎቿ ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ገብቷት በርክክ ብላ በዳበሳ ትፈልጋለች። ምንም እንኳ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው መንገደኞች በአጠገቧ እንደ ጎርፍ ቢፈሱም ሊረዳት የቆመ አንድም ሰው አልነበረም።

ይህ ስለ እርሷ ከመንገዱ የተስተጓጎለ ሰው ግን ከእርሷ ጋር በርክክ ብሎ ፍራፍሬውን ከተበታተነበት እየለቀመ በጠረጴዛው ላይ እስተካክሎ ይደረድር ጀመር። አንዳንዶቹ ፍራፍሬዎች በመውደቃቸው ምክንያት ስለ ተቀጠቀጡና ስለበለዙ ለብቻ በቅርጫት ውስጥ አኖራቸው። በምትኩ ከኪሱ ሃያ ዶላር አውጥቶ በእጇ ላይ ካኖረ በኋላ «ይሄ ስተበላሹት መተኪያ ይሁንሽ» አላት። ወዲያው ፊቷን ትኩር ብሎ እያየ «ደህና ነሽ አይደል?» በማለት ጠየቃት። ዕንባዋ ዱብ ዱብ እያለ ራሷን በመነቅነቅ በአዎንታ መለሰችለት። በመቀጠልም «መቼም ፈጽመን ቀንሽን እንዳላበላሸነው ተስፋ አደርጋለሁ» አላትና ለመሄድ ፊቱን አዞረ። ብዙም ሳይራመድ በድርጊቱ የተመሰጠችው ዓይነ ሥውር ወጣት «ይቅርታ ጌታዬ» ብላ መናገር ስትጀምር ዘወር ብሎ እነዚያን የማያዩ ነገር ግን የሚያነቡ ዓይኖች ተመለከተ። ልጅቷም ቀጠል አድርጋ «ይቅርታ አንተ ጌታ ኢየሱስ ነህ? » ስትል ጠየቀችው።

ለጥያቄዋ መልስ አልሰጠም፤ ነገር ግን በመደነቅ ተሞላ፤ ጥያቄውን እያብሰለሰለ የሚቀጥለውን አይሮፕላን ለመያዝ ወደ መሳፈሪያው አዘገመ።የተሳፈረበት አይሮፕላን ምድርን ለቆ ከደመናት በላይ መንሳፈፉን ቀጥሏል፤ በእሱ ውስጥ ግን ከዓይነ ሥውሯ አንደበት የወጣው ጥያቄ እንደሚንቀለቀል እሣት ይነዳል፤ በልቡ ያስተጋባል፤ ከሃሳቡ ጋር እየተላተመ ከወዲህ ወዲያ ይመላለሳል። «አንተ ኢየሱስ ነህ?» ጥያቄዋ ገረመው።

ለመሆኑ ሰዎች መልካም ሥራችንን አይተው ኢየሱስ መስለናቸው ከሱ ጋር ያማቱን ይሆን? በዚህ ቢሳሳቱብን እንዴት ያለ ትልቅ መታደል ነበር። ለነገሩ የተጠራንለትና የተመረጥንለት የመኖር ግባችን ይኸው አይደል? ጌታ በምድር ሳለ እብን በሥራው እንዳሳየ፣ በተግባሩ እንደ ተረከ እኛም በተግባራችን እሱን እንድንገልጥ ተመርጠናል። ለፍቅሩ፣ ለምህረቱና ለጸጋው እውር በሆነው ዓለም ውስጥ ስንመላለስ ሰዎች ልዩነታችን ጠፍቶባቸው እስኪምታቱ ድረስ እሱን ልንመስል ተጠርተናል። እናውቀዋለን ካልን እሱ እንደኖረ ልንኖር፣ እሱ እንደተመላለሰ ልንመላለስ ይጠበቅብናል። እርሱን ማወቅ ቤተከርስቲያን ከመሄድ፣ ከመዘመርና ጥቅስ ከመጥቀስ ያልፋል። ትምህርቱን በመከተል በኑሮ እርሱን መምሰልን ይጠይቃል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ሮሜ 8፥28, ዮሐ. 14፥8-11, 1ቆሮ. 4፥16**

### ጸሎት

*አ ጌታ ሆይ አባክህ እንድመስልህ እርዳኝ! ኑሮና ተግባሬ ለሌሎች አንተን ያሳይ። አሜን።*



# 46
# የነፍስ ጥም

*"ኢየሱስም መልሶ፦ ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።"*
*ዮሐ. 4፥13-14*

ጊዜው 1978 ዓ.ም ነሐሴ አጋማሽ ላይ ነው፤ ከምሽቱ ሦስት ሰዐት ገደማ ከአዲስ አበቤዎቹ ከመስፍንና ከጥበቡ እንዲሁም ከሐረሬዋ ከድጃ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ከተገናኘንበት ቤት ወጥተን ወደ መልካጀብዱ የሚወስደውን መንገድ እንዳጋመስን የሚመራን ኩቱቢሌ (እስኮብላያችን) ሚኒ ባሱ እንዲቆም አዘዘና ወረድን። በዚህ ሁኔታ በድቅድቅ ሌሊት በጥሻ ውስጥ የተጀመረ የእግር ጉዞ ለቀናት አልተጠናቀቀም።

መንገድ ላይ የውሃ ጥማቱ አይጣል ነበር። አንድ ቀን በውሃ ጥም ተቃጥዬ ከሚመሩን ኩቱቢሌዎች አንዱን በአስተርጓሚያችን በከዲጃ በኩል "ውሃ ጋ የምንደርሰው መቼ ነው?" ብዬ ጠየኩት፤ ከጥቂት እርምጃ በኋላ የምንደርስበት ይመስል "እዚያ ጋ ነው" ብሎ እጁን ወደ ፊት ቀሰረ። ለሱ ሁሉ ነገር "እዚያ ጋ" ነው። በውሃ ጥም ምክንያት መራመድ ስላልቻለ ጥበቡን መንገድ ጥለን መጥተናል፤ እኔም እግሮቼ በደመ-ነፍስ ይራመዱ እንጂ ውስጤ በጥም ተቃጥሎ አሯል። ከጥቂት ሰዐታት ጉዞ በኋላ ግን የደፈረሰ የውሃ ጉድጓድ ጋ ደረስን። ስለ ንጽህናውና ውስጡ ስላለው ነገር ለመጠየቅ ጊዜ አልነበረኝም በደረቴ ተደፍቼ አፌን ጉድጓዱ ውስጥ ደቀንሁ፣ ጠጣሁ፣ ረካሁ።

እኔን እንዲህ ያደረገኝ የሥጋ ጥም ነው። የነፍስ ጥም እንዴት ይብስ ያቃጥል? ምክንያቱም የነፍስ ጥም በተፈጥሮ ውሃ አይረካም። ሊያረካው የሚችል የሕይወት ውሃ ብቻ ነው። ይህ የሕይወት ውሃ በገንዘብ፣ በሥልጣን፣ በዝና፣ በክብር፣ በዘር በኃይማኖት አይገኝም። በሕይወት በረሃ በጥም ስሚቅበዘበዙ ሁሉ ይህን ውሃ ሊሰጥ የሚችል የሕይወት ውሃ ባለቤት አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም መድኃኒትና ጌታ የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው። እሱ የሚሠጠው ይሄ ውሃ እንደ ሌሎች ውሃዎች

እየተደጋገመ መጠጣት አያስፈልገውም፤ አንዴ ከተጠጣ በሆድ ውስጥ የሕይወት ምንጭ ሆኖ ይፈልቃል። ከዚያማ መጠጣት ብቻ ሣይሆን ማጠጣት ነው። "እናንተ የተጠማችሁ! ኑ ወደዚህ የሕይወት ውሃ ምንጭ ቅረቡና ጠጡ፣ ጠጡና እርኩ፣ እርኩና ዕረፉ፣ ዕረፉና እናንተም ሌሎችን ተጣሩ!" ብሎ መጮህ ነው።

እኔም ያንን ድፍርስ ውሃ በምድረበዳ ጠጥቼ ብቻ አልቀረሁም። ከ 6ወራት በኋላ በጅቡቲ ከተማ የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ተመስክሮልኝ ይህንን የሕይወት ውሃ ጠጣሁ፣ ረካሁ፣ ዐረፍኩ፣ እነሆ ላለፉት 30 ዓመታት ለተጠሙ ሁሉ "ኑና ከዚህ የዘላለም ሕይወት ውሃ ጠጡ! እያልኩ እጮኃለሁ። ቅዱስ ቃሉ "መንፈሱና ሙሽራይቱም ና ይላሉ፤ የሚሰማም ና ይበል፤ የተጠማም ይምጣ፣ የወደደም የሕይወትን ውኋ እንዲያው ይውሰድ።" [ዮ. ራዕይ 22፥17] እንዲል።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ኢሳ. 49፥10፤ ራዕይ 7፥16፤ ዮሐ. 7፥38**

**ጸሎት**

*ጌታ ሆይ፦ ለዘለዓለም የሚያረካ የሕይወት ውሃ ስለሰጠኸኝ አመሠግንሃለን፤ ክብር ሁሉ ለስምህ ይሁን። አሁንም እረከቼ እንዳልቀመጥ ነገር ግን ለተጠሙ ሁሉ የዘለለም ሕይወት ምንጭ መሆንህን የምሥራች እንድናገር ፀጋን አብዛልን። አሜን።*



# 47
# የድሆች እናት

*«እጅዋን ወደ ድሀ ትዘረጋለች፥ ወደ ችግረኛም እጅዋን ትሰድዳለች።» ምሳ. 31፥20*

ወደ ሜክሲኮ ዋና ከተማ የሚበረው አይሮፕላን ለበረራ የሚያስፈልገውን መሰናዶ ፈጽሞ ለማኮብኮብ በዝግጅት ላይ ነው። መንገደኞች ቦታ ቦታቸውን ይዘውና የመቀመጫ ቀበቷቸውን አስረው የበረራ አስተናጋጇ የምትሰጠውን መመሪያ በጥሞና ይከታተላሉ። አብራሪዎቹ ከበረራ መቆጣጠሪያ ማማው ይሁንታ ባገኙ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አይሮፕላኗ መሬትን ተሰናብታ አየር ውስጥ ተወለደች። ጉዞ ወደ ሜክሲኮ ሲቲ።

አሥር ሺህ የሚጠጉ አይሮፕላኖችና አምስት መቶ ሺህ የሚሆኑ ተሳፋሪዎቻቸው በየትኛውም ቅፅበት በአየር ላይ እንደሚበሩ በሚነገርበት ዘመን ይህንን በረራ ልዩ የሚያደርገው አንዳች ነገር አልነበረም። ሆኖም በውስጡ የጫናቸው አንዲት ሴትና የፈጸሙት ተግባር በረራውን አይረሴ አድርጎታል። ለመሆኑ እኚህ ሴት ማናቸው? ምንስ አደረጉ?

እኚህ ሴት በቀድሞው ዩጎዝላቪያ አሁን የመቄዶኒያ ሪፓብሊክ ዋና ከተማ በሆነችው ስኮፒያ ውስጥ ነሐሴ 26፣ 1910 ዓ.ም ከአንድ ተራ ቤተሰብ ተወለዱ። በተደወለዱ ጥቂት ቀናት ውስጥ ሲጠመቁ አግነስ ጎንግዚቦ ጃግሲሁ የሚል ስም ተሰጣቸው። በ 12 ዓመታቸው በሚማሩበት የክርስቲያን ትምህርት ቤት በተዘጋጀ ጉዞ ላይ ሕይወታቸውን ለጌታ ሰጡ። ዕድሜያቸው 18 ሲሞላ በሚከተሉት የካቶሊክ እምነት ለመመንኮስ ወሰኑና ይህንንም ለማከናወን ወደ አየር ላንድ ዋና ከተማ ደብሊን አቅንተው ሥርዓቱን ፈጸሙ።

እኚህ ሴት የጆግራፊና የታሪክ መምህርት ሆነው ወደ ሕንድ በማቅናት በርካታ ድሆች በሚኖሩበት የካልካታ መንደር ውስጥ በልጃገረዶች ትምህርት ቤት ውስጥ ማስተማር ጀመሩ። ትምህርት ቤቱ የሚገኘው ያጡ፣ የነጡ ድሆችና «አይነኬ» የሚባሉት የቤንጋሊ ቤተሰቦች የሚኖሩበት አካባቢ ስለነበር ውሎ አዳራቸው ከድኾች ጋር ሆነ።

የልጃገረዶቹ ሕይወት በትምህርት ተለውጦ ለማየት ከነበራቸው ጥልቅ ፍላጎት የተነሳ በአጭር ጊዜ የቤንጋሊና የሂንዱ ቋንቋ አቀላጥፈው መናገር ቻሉ።

ከዓመታት የማስተማርና የርዕሰ መምህርነት ሥራ በኋላ እሳቸው ከምንኩስናቸው ቀጥሎ «ሁለተኛው ጥሪ» የሚሉት ድሆችን የመሰብሰብ፣ የተጣሉትን የማንሳትና በደዌ የሚማቅቁትን የማስታመም ጥሪ ከጌታ ተቀብለው የዕርዳታ ሥራቸውን ተያያዙ። ይህ ጥረታቸው ፍሬ አፍርቶ በአለም ከ100 በሚበልጡ አገሮች 4000 የበጎ አድራጎት ማዕከል ለመክፈት በቁ። በተግባራቸው የዓለም ሕዝቦችን፣ የኃይማኖት መሪዎችን፣ ርዕሳነ ብሔራትን አስደመሙ፤ ፍቅር በሰጣቸው ሥልጣን በነገሥታት ፊት ተከበሩ፣ የኖቤልን የሰላም ሽልማት ተቀበሉ ሆኖም በፈቃዳቸው ከምድር ድሆች እንደ አንዱ ሆነው ኖሩ። እኚህ ሴት ማዘር ቴሬዛ ናቸው።

ይህንንም በረራ ልዩ ያደረገው የሳቸው በአይሮፕላኑ ውስጥ መሳፈር ነው። አይሮፕላኑ የአየር ልኩን ይዞ አስተናጋጆች ለተሳፋሪው ምግብ ማቅረብ ሲጀምሩ፣ አስተናጋጇን ጠርተው «ይህ ምግብ ስንት ያወጣል?» በማለት ያልተለመደ ጥያቄ አቀረቡላት። የበረራ አስተናጋጇም አብረዋት ካሉ ሠራተኞች ጋር ከመከረች በኋላ «ሐሥር የአሜሪካን ዶላር» በማለት መለሰችላቸው። «እንግዲያስ ገንዘቡ ይሰጠኝና ድሆችን አመግብበታለሁ» አሏት። ወዲያው አጠገባቸው ተቀምጦ የነበረ ሰው «እኔም እሳቸውን መከተል እፈልጋለሁ ስለዚህ ምግቤ በገንዘብ ተለውጦ በእሳቸው በኩል ለድሆች ይሰጥልኝ» አለ። ወሬው በአይሮፕላኑ በሙሉ ተሰማና ተሳፈረው ሁሉ ምግቡን እየመለሰ ገንዘቡ ለእሳቸው እንዲሰጥ ወሰነ።

አይሮፕላኑ ሜክሲኮ ሲቲ ደርሶ ገንዘቡን ከተቀበሉ በኋላ ሊወርዱ ሲሉ በድጋሚ ወደ መሪ አስተናጋጇ ጆሮ ጠጋ ብለው «ለመሆኑ ይህንን ከተሳፋሪው ሁሉ የተመለሰ ምግብ ምን ታደርጉታላችሁ? » ብለው ጠየቋት፤ አስተናጋጇም በቁርጠኝነት «የአይሮፕላኑ ሕግ ስለሚያስገድደን እንደፋዋለን! » በማለት መለሰችላቸው። ማዘር ቴሬዛም ቆፍጠን ብለው «ለድሆች እመግበዋለሁና ይሰጠኝ! » ብለው ጠየቁ፤ እንዳሉትም



ተደረገላቸው። ሜክሲኮ ሲቲ ለሚያገኟቸው ድሆች ገንዘብና ትኩስ ምግብ ስለ ሰነቁ እየተደሰቱ መንገዳቸውን ሄዱ።

የእኚህን እናት ተግባር ስናነብ እኛ ዛሬ በዙሪያችን ያሉ ድሆችን እንዴት እንደምናይ ከሚሞግተን እውነት ጋር ፊት ለፊት መፋጠጣችን የማይቀር ነው። እግዚአብሔር በሰጠን ጤና፣ ዕውቀት፣ ኃይልና ብርታት ያካበትነውን ሃብት ማብቂያ ለሌለው የሥጋችን ምኞትና የቅንጦት ሱስ እናውለዋለን ወይስ በዙሪያችን ያሉትን ድሆች እናስባለን። የድሆች ነገር ዛሬ የእምነታችንን እውነተኝነት የሚፈትን፣ ነገ በሚመጣው ዓለም ዘላለማችንን የሚወስን ጉዳይ መሆኑን እንድናስተውል እግዚአብሔር ይርዳን።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ምሳሌ 31፥9, ሮሜ 12፥13, ዘዳ. 15፥11**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ቃልህ ስለ ድሆች ለሚናገረው ተገቢ ትኩረት አልሰጠሁም፤ ይልቅ የራሴን በረከት ሳሳድድ ኖሬያለሁ። ሳይኖረኝ በመጎምጀት፣ ሲኖረኝ በመሰሰት እንተን በድያለሁ፤ አሁን ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ። ከዛሬ ጀምሮ ድሆችን እንድወድ፣ ከሰጠኸኝ እንዳካፍል፤ ሌሎች እየተራቡና እየታረዙ እኔ በቅንጦት ከመኖር እንድቆጠብ እርዳኝ።*

# 48
# አዙሪት

*"ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ፤ በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፥ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።" መዝ. 46፥10*

ያ ዘመን በአገር ውስጥ ለመኖር ፈፅሞ አይመችም ነበር። በተለይ ለወጣቱ የምድር ሲዖል ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን በአሜሪካና በአውሮፓ ይማሩ የነበሩ በቁጥር ጥቂት የሚባሉ ኢትዮጵያውያን የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ከሁለት ወር ዕረፍት በኋላ ትመረቃላችሁ ሲባሉ «ዲግሪውን በፖስታ ላኩልን» ብለው ወደ አገራቸው ይመለሱ ነበር ይባላል። እኔ ባደኩበት ዘመን ግን ይህንን ማሰብም ሆነ ማመን አይቻልም። ማንኛውም ሰው በሆነ ምክንያት የኢትዮጵያን ድንበር ካቋረጠ ተመልሶ የአገሩን አፈር የሚረግጥበት አጋጣሚ ውሱን ነበር። ሰው በድኑ አገር ውስጥ ይሁን እንጂ ነፍሱ እንደ ወፍ ወደ ውጭ በራለች። ውጭ መውጣት ዳግም መወለድ፣ እንደ ገና መፈጠር ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ ነበር።

እኔም የ 18 ዓመት የልደት ሻማዬን ባጠፋሁ ጥቂት ወራት ውስጥ በድሬዳዋ በኩል ወደ ጅቡቲ ተጓዝኩ። ተጓዝኩ ስል በጣም ቀላል ይመስላል። መልካቸውን፣ ቋንቋቸውንና ባሕላቸውን ፈጽሞ ከማላውቀው አስኮብላዮች ጋር፣ በማላውቀው አቅጣጫ፣ ወደ ማላውቀው መዳረሻ፣ ለዘጠኝ ቀናት በእግር ተጓዝኩ። በረሃብ፣ በጥም፣ በሞት ፍርሃት፣ በወንበዴ ፍርሃት፣ በአውሬ ፍርሃት፣ በሚመሩኝ አስኮብላዮች ፍርሃት በሞትና በሕይወት መካከል ተጓዝኩ። ምንም እንኳ በትክክለኛው መንገድ እግዚአብሔርን ባላውቅም፣ ሰው ሁሉ ሲጨንቀው እንደሚያደርገው ወደ እግዚአብሔር ጮኽኩ። ቃል ኪዳን ያዘለ የጭንቅ ልመና «እግዚአብሔር ሆይ በሰላም ወደ ጅቡቲ ብታደርሰኝ በቀሪው ዘመኔ ሁሉ እመልክሃለሁ» የሚል።

እንደማይደረስ የለምና ዘጠኝ ዓመታት ከሚመስሉ ዘጠኝ ቀናት በኋላ ዲክል በምትባል ስደተኞች የሚጠለሉባት የጅቡቲ ከተማ ደረስኩ። በዚሁ መንገድ ከእኔ ቀደም ከአገር የወጡ የተለያየ የቆይታ ዘመን ያላቸው በርካታ ስደተኞች በድንኳን ይኖራሉ። ድንገት የምድረበዳ ቃል ኪዳኔ



ትዝ አለኝ «እንደ ለመንኩት እግዚአብሔር ጅቡቲ አድርሶኛል፤ ታዲያ የትና መቼ? ከማንስ ጋር ነው የማመልከው?" የሚለውን ለማወቅ አንድ የምቀርበውን ሰው አነጋገርሁ። ያናገርኩት ሰው አሁን እግዚአብሔርን ለማምለክ ዝግጁ እንዳልሆነ ነገር ግን እግዚአብሔር ከዚህ እሳት አውጥቶ ጣሊያን ቢያገባው በቀሪው ዘመኑ ሁሉ ሊያመልከው እንደ ተሳለ ገለጸልኝ። በእርግጥም ከጅቡቲ የሄዱ በርካታ ስደተኞች ሮም ጣሊያን ውስጥ እንደሚገኙ ሰምቻለሁ። «በዚያ እግዚአብሔርን እያመለኩ ይሆን? » የሚል ጥያቄ አደረብኝ። በቅርቡ ከጅቡቲ የሄደ ጓደኛው ከጣሊያን ደብዳቤ የጻፈለትን የድንኳን ጎረቤቴ ሲያነብልኝ፣ አብዛኞቹ ስደተኞች ሮም ገብተው፣ ቫቲካን የሚገኘው የቅዱስ ጴጥሮስ ካቴድራል በረንዳ ላይ ተኮልኩለው፡- «እግዚአብሔር ሆይ አሜሪካ ብታገባን በቀረው ዘመናችን እናመልክሃለን» እንደሚሉ ተረዳሁ። ከዚያ በኋላማ በአሜሪካ ያሉት ምን ይሉ ይሆን? የሚለውን ለማወቅ የነበረኝ ጉጉት ጨመረ። በርግጥ አሜሪካ ነዋሪዎቿ ራሳቸው «የነጻዎች ምድር፣ የጎበዞች አገር፣ የእድል መገኛ፣ የደስታ» በማለት የሚወድሷት አገር ናትና ሰው ገነትን ካልሆነ በቀር ከአሜሪካ በኋላ ምን ሊመኝ ይችላል? የሚል ጥያቄ አደረብኝ። ሆኖም ምንም ብጓጓ በጊዜው አሜሪካ የሚኖር የማውቀው ሰው ስላልነበረኝ ከኢትዮጵያ ወጥተው በተለያየ አቅጣጫ አሜሪካ የገቡ የአገር ልጆች ተሳክቶላቸው እግዚአብሔርን እያመለኩ ይሆን? የሚለውን ለማወቅ ተሳነኝ። ሆኖም ከጥቂት ቀናት በኋላ እስቴር አወቀ የምትባል ዘፋኝ የለቀቀችው አዲስ ዘፈን በየሃበሻው ቤት ያስተጋባ ጀመር።

«እኔም አገር፣ አገር፣ አገር አለኝ፣ አገር፣ አገሬ ብርቁ፣ እኔም አገር አገር አገር አለኝ፣ አገሬ የሚታይ በሩቁ »

ጥቂት ካደመጥኩ በኋላ «ለካ ነገሩ አዙሪት ነው» አልኩ። ከኢትዮጵያ አውጥቶ፣ በጅቡቲ አዙሮ፣ በጣሊያን አሽከርክሮ፣ በአሜሪካ አሳብሮ፣ መልሶ ኢትዮጵያ የሚከት እዙሪት። ለካ እግዚአብሔር ያደለው ሰው የትም ይሁን የት እሱ ባስቀመጠው ሥፍራ ተደስቶና ተደላድሎ፣ አምላኩን እያመሰገነ፣ ባለው እየረካ የሚኖር ሰው ነው! ወደሚለው ድምዳሜ ደረስኩ።

አንተስ ፣ አንቺስ፣ እርስዎስ ሁላችን እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ የእርሱን አምላክነት አውቀን፣ በኃይል በችሎቱ አርፈን እየኖርን ነው?

ወይስ እየተቅበዘበዝን? አሁን ባለንበት ያላመለክነውን እግዚአብሔር ነገ የተሻለ ያልነው ቦታ ስንደርስ ማምለካችን እጠያያቂ ነው። ጎበዝ! ነገርየው እዙሪት ነውና ቀጠሮውን ትተን አሁን በቆምንበት ለእርሱ ልባችንን እንክፈት፣ እጃችን እናንሳ።

**ተጨማሪ ንባባት፦ ዘፍ. 26፥1-2, 12፤ ዘፍ. 46፥1-30, 1ቆሮ. 7፥20**

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ፣ ዓለሙ ሁሉ ያንተ ነው። ባንተ ዘንድ ውጭ አገርና ውስጥ አገር የለም። ለሰው የማይመች ሥፍራ ከአንተ ውጭ መሆን ብቻ ነው። በአንተ ውስጥ እንደ መሆን በሰማይም ሆነ በምድር የሚያረካ አንዳች ነገር የለም። ውስጡ ባንተ ያላረፈ ሰው የትም ቢሄድ አያርፍም። እባክህ ነፍሴን አሳርፍልኝ፤ ባስቀመጥኸኝ ሥፍራ ጸንቼ እንድቆይ፣ በቆየሁበት ብዙ ፍሬ እንዳፈራ እርዳኝ። አሜን።*



# 49
# ሠሪው ጋ ይላኩት

*"ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ኤርምያስ የመጣ ቃል፥ እንዲህም አለው፦ ተነሥተህ ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ውረድ፥ በዚያም ቃሌን አሰማሃለሁ። ወደ ሸክላ ሠሪው ቤትም ወረድሁ፥ እነሆም፥ ሥራውን በመንኰራኵር ላይ ይሠራ ነበር። ከጭቃም ይሠራው የነበረ ዕቃ በሸክላ ሠሪው እጅ ተበላሸ፥ ሸክላ ሠሪውም እንደ ወደደ መልሶ ሌላ ዕቃ አድርጎ ሠራው።" ኤር. 18፥1-4*

የወንጌልን እውነት ለትልቅ ለትንሹ፣ ለተማረው ላልተማረው፣ ለከተሜው ለገጠሬው በማያሻማና ግልጽ በሆነ መንገድ በመስበክ የሚታወቁት የ20ኛው ክፍለ ዘመን የወንጌል አርበኛ ቢሊ ግርሃም በአንድ ወቅት እንዲህ ዓይነት ነገር ገጥሟቸው ነበር። የመጀመሪያ ልጃቸው ጂጂ ግርሃም እጮኛ ትይዛለች። እጮኛዋ ዶ/ር ስቴፋን የሚባል የስዊትዘርላንድ ነዋሪ ነው። ስቲፋን አሜሪካ ለሚኖሩት የእጮኛው አባት ሥጦታ ይልክላቸዋል። መቼም ከስዊዝ ምን ዓይነት ሥጦታ ሊልክላቸው እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። ስዊዝ ከምታመርታቸው ውድ ነገሮች መሃል እንዱና ዋነኛው ሰዓት ነው። እሱም የላከላቸው ሥጦታ የስዊዝ ሥሪት የሆነ ሰዓት ነበር። ይህ ሰዓት ለረዥም እመታት ከቢሊ ግርሃም እጅ ሳይለይ ኖረ። ሆኖም እንድ ቀን ተበላሸና መሥራት እቆመ። ከዚህ በፊት እንደሚያደርጉት አንድ ሰዓት ሠሪ ቤት ወሰዱት። ሰዓት አዳሹ እንደ ሌሎች የሚያውቃቸው ሰዓቶች ሊከፍተው ቢታገል በቀላሉ እልሆን ይለዋል። ከሁለት ቀን በኋላ እንዲመለሱ ቀጠሮ ይሰጣቸውና ሠርቶ እንደሚጠብቃቸው ቃል ይገባላቸዋል። ቢሊ ግርሃም በቀጥሮአቸው ሊሄዱ ሰውየው ይዞ የጠበቃቸው መልዕክት እንዲህ የሚል ነበር "ሰዓቱን በሚገባ ተመልክቼዋለሁ በከፍተኛ ጥንቃቄ በእጅ የተሠራ፣ በቁጥር የተመረተ፣ ረቂቅና ውድ ሰዓት ነው። እንደ እኔ፣ እንደ እኔ የምመክሮት በማያውቅ ሰው እንዳያስጎረጉሩት ነው። ይልቅ የሠሪዎቹ አድራሻ ካሎት ቢልኩላቸው እድሰው የሚመልሱሎት ይመስለኛል" አላቸው። ሥጦታው ከተሰጣቸው ረዥም እመት ቢሆነውም ማህደሩ ውስጥ የሠሪዎቹ አድራሻ ነበርና ወደ ስዊትዘርላንድ በፖስታ ላኩት። ከጥቂት ሣምንታት በኋላ ካምፓኒው ሰዓቱን እድሶ መልሶ ላከላቸው።

እንደ ሰው በሕይወት ጉዟችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ይገጥሙናል። ታዲያ ለችግሮቻችን መፍትሄ ፍለጋ ፈጥነን የምንሄደው ወደ ማን ይሆን? ቀላልና አቋራጭ መፍትሄ የሚሰጡ በርካታ አዳሾች ባቅራቢያችን ሊኖሩ ይችላሉ። ችግሩ ሊያድሱ የሚሞክሩት ከመሠረቱ ያልሠሩትን ነውና ከሚጠግኑት ይልቅ የሚሰብሩት ስለሚበዛ ችግራችንን ከፊት ይልቅ ያባብሱታል። ምንም እንኳ በዕውቀትና በልምድ የዳበሩ የምክር ባለሙያዎች ቢኖሩም የሠራንን የማያውቁ ብቻ ሳይሆኑ የሥራውን ሥርዓት የሚቃወሙና የሚንቁ ሆኖም ሰውን በተጣመመና በተዛባ መንገድ ሊያድሱ የሚሞክሩ ጥቂት አይደሉም። እነዚህ ጎርጓሪዎች የሰውን ጊዜያዊ ሕይወት እናድስ ብለው ዘላለማዊ ማንነቱን ያንኮታኩታሉ። በመንፈሳዊ ሕይወት ሆነ በሥነ-ልቦና፣ በሥነ-ጾታ ሆነ በሥነ-አዕምሮ፣ በሥነ-ስብዕ ሆነ በሥነ-ባሕሪ፣ በሥነ-ፍጥረት ሆነ በትዳር፣ በልጆች አስተዳደግ ሆነ በማሕበራዊ ኑሮ ዘይቤ ሊያማክሩንና ብልሽታችንን ሊጠግኑ የሚሞክሩት ከተሠራንበት ዓላማ ውጪ ማለትም ማንዋላችን ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በሚጻረር ወይም ከዚያ ባነሰ መልኩ ከሆነ ከመጎርጎርና ከማበላሸት ያለፈ የሚፈይዱት አንዳች ነገር አይኖርም። ሰው የሰው ምክር አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የባለሙያ እገዛ እንደሚያስፈልገው የታወቀ ነው። ሆኖም አደሳው በተሠራበት ዓላማ ውስጥ ሊሆን ግድ ይላል።

"ይህን ውድ ሰዓት ሰፈር ውስጥ ከማስጎርጎር ይልቅ ወደ መጀመሪያ ሠሪዎቹ ቢልኩት ይሻላል" በማለት ለወንጌላዊው ምክር እንደ ሰጠው እንደዚያ ሰዓት ሠሪ፣ ሰውን ከዘላለም አቅዶ ወደ ፈጠረው፣ በገዛ እጆቹ ወደ ሠራውና ጠንቅቆ ወደሚያውቀው ወደ እግዚአብሔር የሚመሩ ባለ ሙያ አዳሾች ቢበዙ ምንኛ መልካም ነበር? ሆኖም የዘመናችን ሰው ጠጋኝ ነን ባዮች ሰውን የሚያህል ክቡር ፍጡር ያለ ባለቤቱ ማንዋል ለመጠገን እየሞከሩ መጋዘናቸውን በሰው ስብርባሪ ሞልተዋል።

እግዚአብሔር ፈጣሪ ብቻ አይደለም። አዳሽም ነው። በእጁ የሠራው ሰው እንከን ሲገጥመው ፈታቶ፣ እከሞ መጠገን ያውቅበታል። ስለዚህ ክቡር ማንነታችንን ሰፈር ከምናስጎረጉር ወደ ሠሪው እንመልሰው፣ በአድራሻው እንላከለት፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንቅረበው፣ እንደ ንሥር ያድሰናል፣ አዲስ አድርጎ ይመልሰናል።



**ተጨማሪ ንባባት፦ ዘፍ. 2፥7, መዝ. 95፥6-7, ዮሐ. 1፥9**

## ጸሎት

*እግዚአብሔር ሆይ ግሩምና ድንቅ አድርገኸ ስለፈጠርከኝ አመሰግንሃለሁ። ሆኖም በኃጢአት ከተበከለው የዓለም ሥርዓት፣ በዙሪያዬ ካሉ ከፉ ሰዎች፣ ከእኔም ከራሴ የተዛባ ማንነት የተነሳ ብዙ ነገሬ ተበላሽቷል። መፍትሄ ብዬ የምከርኳቸው አማካሪዎችና የመሩኝ የፍልስፍና መንገድ ችግሬን አባባሰው እንጂ አልጠቀመኝም። ዛሬ ግን ጌታና ክርስቶስ በሆነው በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም የተበላሸ ማንነቴን ወደ አንተ አመጣለሁ እንደ ወደድህ ሥራና አድሰኝ።*

# 50
# ጉድፍና ምሰሶ

*«እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም? (ማቴ. 7፡1-5)*

ምንተስኖት ጅቡቲ በምትገኝ የኢትዮጵያውያን ስደተኞች ቤተክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ ነው። የጅቡቲ አየር ንብረት ባመዛኙ ሙቀት የሚያይልበት ስለ ሆነ ቲ ሸርት መልበስ የተለመደ ነው። ምንተስኖት ስደተኛ እንደ መሆኑ መጠን የገንዘብ አቅም ስለሚፈታተነው የሚፈልገውን አማርጦ መግዛትና መልበስ አይችልም። ስለዚህ እንደ አብዛኞቹ ስደተኞች ለማስታወቂያነት በነጻ ከሚታደሉ ካኒቴራዎች አንዱን ለብሶ ከቤት ወጣ። ዕቃ ለመግዛት ወደ አንድ ሱፐር ማርኬት ጎራ ሲል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በርቀት የሚያውቃት እህት ጋር ይገናኙና ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

ጥቂት ከተጫወቱ በኋላ ያች እህት ስለ አንድ ጉዳይ ልታነጋግረው እንደምትፈልግ ትገልጽለታለች። ምን ልታነላልኝ ይሆን በማለት ጥቂት ካወጣና ካወረደ በኋላ ከፈለገች አሁንም ልታነጋግረው እንደምትችል ይገልጽላታል። እሷም ቆፍጠን ብላ «አንተ አገልጋይ ነህ፤ ለብዙዎች ምሳሌ መሆን ይጠበቅብሃል። ይህ ደረትህ ላይ ለጥፈህ የምትሄደው የቱበርግ ቢራ ምስል ምንድን ነው? ለሚያዩህስ ሰዎች ምን መልዕት የሚያስተላልፍ ይመስልሃል?» በማለት ስለ ለበሰው የቢራ ማስታወቂያ ቲ ሸርት በሰላ አንደበት ገሠፀችው። ምንተስኖት አማራጭ አጥቶና ተቸግሮ እንጂ ትክክል እንዳልሆነ ስለሚያውቅ መከራከሪያ መልስ አላቀረበም። ነገር ግን አንገቱን አቀርቅሮ ሂሱን መዋጥ ቀጠለ። ሆኖም ባቀረቀረበት በትኩረት ሲመለከት የምትወቅሰው እህት እቃዋን የያዘችበት ፌስታል የዊኒስተን ሲጋራ ማስታወቂያ ነበር።

ዓይናችን ከራሳችን ይልቅ ሌሎችን መመልከት ይቀናዋል። በሌሎች ጉዳይ መግባትና እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር፣ እርምጃቸውን መዳኘት እንወዳለን። ስማችን በከፉ ሲነሳ ያንገበግበናል፤ የሌሎችን ስም ማንሳትና



ማብጠልጠል ግን ውሃ እንደ መጠጣት ይቀለናል። በሰዎች ላይ ስንፈርድ ያሉበትን ሁኔታና ችግራቸውን ለማየት ፈጽሞ ፋታ አንሰጥም። የምንፈርደው ድርጊታቸውን ሳይሆን ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊያየውና ሊፈርደው የማይችለውን የልብ ሃሳባቸውን ነው። የሰዎች መውደቅ እኛን የሚያቆመን፣ የሰዎች ድካም እኛን የሚያበረታን ይመስል የሰማነውን ለማሰማት እንጣደፋለን፣ የቆሙትን ለመጣል፣ የወደቁትን ለመቅበር እንጣደፋለን። በፍጻሜ ቀን የሚሆነውን የመጨረሻውን ፍርድ በተመለከተ እግዚአብሔር በእኛው እጅ የተወው ይመስላል። በሌሎች ጉዳይ የምንፈርደውን ያይና ያንኑ በእኛ ላይ ያጸናዋል። በምሕረት ከፈረድን በምሕረት ይተውልናል። ያለ ምሕረት ከፈረድን ያለ ምሕረት ይፈረድብናል። ያዕቆብ በመልዕክቱ *«በነጻነት ሕግ ፍርድን ይቀበሉ ዘንድ እንዳላቸው ሰዎች እንዲህ ተናገሩ፥ እንዲህም አድርጉ። ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል።»* (ያዕ. 2፡12-13) በማለት እንደጻፈው ነው።

ከሰው ጋር የምንኖር፣ ስለ ሰው ከፉ ደግ ሳንሰማ የማናመሽ፣ የሰውን ብርታትና ድካም ሳናይ ውለን የማናድር እንደ መሆናችን መጠን በሰው ላይ ሳንፈርድ መኖር ፈጽሞ አዳጋች ነው። ሆኖም የማረም እርምጃችን የሳተውን የሚመልስና የሚያድስ እንጂ መልሶ የሚያደፈርስ እንዳይሆን የሌላውን ጉድፍ ለማውጣት ከመገበዛችን በፊት የራሳችንን ምሰሶ እንድናወጣ የጌታ ቃል ይመክረናል። ስለዚህ ሌሎችን ከመንቀፋችን በፊት «እኔስ በዚህ አቅጣጫ እንዴት ነኝ? በማለት ራሳችንን እንመርምር። ጉድፍ ለማንሳት ከመሄዳችን በፊት የራሳችንን ምሰሶ ለማጥራት ቅድሚያ እንስጥ። ያኔ ምክራችን እንደጠሊቅ ውሃ ጥብብን ያመነጫል።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ያዕ. 4፥11-12, ሉቃስ 6፥37, ሮሜ 2፥1,3**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ! ነቢዩ ናታን ለንጉሥ ዳዊት ኃጢአቱን በሌላ ሰው ታሪክ አስመስሎ በነገረው ጊዜ «ይሄ ሰው ሞት የሚገባው ነው! » በማለት ሳያውቀው በራሱ ላይ እንደ ፈረደ፣ እኔም በሌላው የፈረድኩ እየመሰለኝ በራሴ ስፈርድ እንዳልገኝ ጠብቀኝ። ቃልህ «የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፤ ይማራሉና» እንደሚል፣ ምሕረት ለማይገባቸው ከአንተ በነጻ የተቀበልኩትን ምሕረት በመስጠት በብጽዕናን እንድኖር እርዳኝ።*

# 51
# ወርቃማ ቃል!

*"ዳዊትም ሰይፉን በልብሱ ላይ ታጠቀ፥ ገናም አልፈተነውምና መሄድ ሞከረ። ዳዊትም ሳኦልን፦ አልፈተንሁትምና እንዲህ ብዬ መሄድ አልችልም አለው። ዳዊትም አወለቀ" (1ሳሙ. 17፡39)*

በ1960ዎቹ አጋማሽ ማሳቹሰትስ በምትገኘው ካምብሪጅ ከተማ የሚኖር ኬን ጋልብራይዝ የሚባል ታዋቂ ኢኮኖሚስት ነበር። አንድ ቀን ኬን ከሥራ ገብቶ ራት ከበላ በኋላ ማንም እንዳይቀሰቅሰው ለሠራተኛው ተናግሮ ጋደም ይላል። ጥቂት ቆይቶ የቤቱ ስልክ አቃጨለ። የኬን ሠራተኛ እጀታውን አንስታ በለሆሳስ «ሄሎ» አለች። ከዚያ ወገን «ጋልብራይዝን አቅርቢልኝ! » የሚል ቆፍጣና ድምጽ መጣ። ሠራተኛይቱ «ጌታዬ፣ እቶ ጋልብራይዝ ተኝተዋል፤ ስለዚህ ላቀርብሎት አልችልም» አለች። ለካ ደዋዩ የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሊንዶን ጆንሰን ኖረዋል። «እኔ ፕሬዚደንት ጆንሰን ነኝ፤ ቶሎ ቀስቅሺና አቅርቢልኝ» አሉ። ሠራተኛይቱም «ክቡር ፕሬዘዳንት፣ ሚስተር ጋልብራይት የተኙት ማንም እንዳይቀሰቅሰኝ በማለት ትዕዛዝ ሰጥተው ነው፤ ስለዚህ ከትልቅ አክብሮት ጋር ልቀሰቅሳቸው አልችልም። ደግሞም እኔ የምሠራው ለእሳቸው እንጂ ለእርሶ አይደለም» በማለት እንደ መለሰችላቸው በታሪክ ማህደር ሠፍሯል።

«እምቢ ሁልጊዜ ከፉና አሉታዊ ቃል ነው!» ያለው ማን ነው? ትክክል ላልሆነ ነገር ‹እምቢ› ሰንል፣ ትክክል ለሆነው ነገር ‹እሺ› እያልን እንደሆነ ምን ያህል አስተውለናል? አውጥቶና አውርዶ ሌሎችን ‹እምቢ› የሚል ሰው፣ አስቀድሞ ለራሱ ‹እሺ› ያለ ብቻ ነው። ምንም እንኳ ‹እምቢ› የሚለውን ቃል እንደ መልስ የማይቀበሉና እንደ ዐመጽ የሚቆጥሩ ሰዎች በዙሪያችን ቢኖሩም ጨክነን ልንለምደውና ልናስለምደው የሚገባን ቃል ነው። ባስፈላጊው ቦታ ከአክብሮት ጋር ‹እምቢ› ማለት ለባዩ ጤና የሚሰጥ፣ እረፍት የሚያጎናጽፍ፣ ከጸጸት የሚታደግ፣ ቀጣይ ግንኙነትን



የሚያለምር ፍቱን መድኃኒት ነው። ማንንም ላለማሳዘን ለሁሉ 'እሺ' የሚል ሰው በቀኑ መጨረሻ ሁሉንም ማሳዘኑ አይቀርምና።

ከባህላችንና ካስተዳደጋችን የተነሳ "እምቢ" ወይም "ይቅርታ አልችልም" የሚሉት ቃላት ለብዙዎቻችን ፈጥነው የማይመጡልንና ለአፋችን እንደ ጥንብ የሚከብዱን አዳጋች ቃላት ናቸው። ሆኖም በቁርጠኝነት ራሳችንን ማስልጠን ይኖርብናል። አለበለዚያ ለአፍታ ላለማሳዘን በሚል የማንችለውን እሺ እያልን በብዙ ወዳጆቻችንን ዘንድ ለዘለቄታው ተዓማኒነትን በማጣት በፍጻሜው ሰው አልባ ሆነን እንቀራለን። ሲጠየቁ እምቢ ወይም አልችልም ማለት ተስኗቸው ዕድሜ ልካቸውን ሲያፍሩ፣ ሲሸማቀቁ፣ ሲላቀቁና ሲጸጸቱ የሚኖሩ ሰዎች ቤቱ ይቆጠራቸው። "እምቢ! አልችልም!" ማለት እያለብን አለማለታችን የሚያስከትልብን ችግር ቃላችንን አለማክበራችንን ተከትሎ የሚመጣው ዕፍረት ብቻ ሳይሆን ከአቅማችን በላይ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለመፈጸም በምናደርገው ትግል ለከፍተኛ ውጥረትና ለጤና መዛባት መዳረጋችን ነው።

በእርግጥ እምቢታ በሚገባ ታስቦበት፣ በቂ ምክንያት ቀርቦበት፣ ከአክብሮት ጋር ሲነገር የሚባው ቃል እንጂ እንዲሁ በግብታዊነት የትም የሚዘራ ቃል መሆን የለበትም። ያ ስንፍና፣ ዳተኝነትና እልከኝነት ይሆናል። ታስቦበት ሲባል ግን እምቢ ወርቃማ ቃል ነው። ማህተመ ጋንዲ እንዳለው "ካልታሰበበት የአንገት በላይ "እሺታ" የታሰበበት የአንጀት "እምቢታ" ይበልጣል።" ስለዚህ እምቢ ማለትን፣ ሌሎች እምቢ ሲሉን አክብሮ መቀበልን ባህላችን ለማድረግ እንጀምር። እንደ ወላጅ ለልጆቻችን፣ እንደ እሠሪ ለበታቾቻችን፣ እንደ በታች ሠራተኛ ለአለቆቻችን፣ እንደ ባል ለሚስታችን፣ እንደ ሚስት ለባላችን፣ እንደ አገልጋይ ለምዕመናን፣ እንደ ምዕመን ለመሪዎቻችን፣ እንደ መንግሥት ለሕዝባችን፣ እንደ ሕዝብ ለመንግሥታችን ማለት በሚገባን ጊዜ ሁሉ "እምቢ" ወይም "ይቅርታ አልችልም" እንበል። "እምቢ" በቦታውና በጊዜው የተባረከ ቃል መሆኑን እንርሳ።

የሰው ግርማ ሳያስፈራን፣ ማዕረግ ሳያስደነግጠን፣ ጥቅም ሳያጓጓን፣ ተንኮል ሳይበግረን እምቢ ማለት ባለብን ቦታ ሁሉ « እምቢ! » ማለት እንዴት ያለ ብጽዕና ነው። ትንሹ የበጎች እረኛ ዳዊት ንጉሡን ሳዖልን በበቂ ምክንያትና በአክብሮት "እምቢ" ማለት ከቻለ እኛም በዙሪያችን

ላሉ እምቢ ማለት ሊሳነን አይገባም። ታዲያ እምቢ የሚለውን ቃል ሥራ ላይ ማዋል ያለብን ለሌሎች ብቻ አይደለም። በግል ሕይወታችን ከራሳችን ጋር ባለን ግንኙነት በአስፈላጊው ሰዓት ለነፍሳችን ደኅግመን የምንነግራት ቃል መሆን ይኖርበታል። በምድር ስንኖር ሥጋዊ ተፈጥሯችን የሚንስፈስፍላቸውና "ካላገኘሁ ሞቼ እገኛለሁ" የሚላቸው መጠይቆች ሥፍር ቁጥር የላቸውም። ሁሉን በእሺታ ከታዘዝነው መጨረሻችን ሞት እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። ስለዚህ ጥርሳችንን ነክሰን ለምኞት፣ ለእጉል ልማድ፣ ለቅንጦት፣ ለጊዜያዊ ደስታ፣ ለከንቱ ውዳሴ፣ ለሚያልፍ ክብር የሚቀርቡልንን ጥያቄዎች ሳናመነታ እምቢ እንበል። እምቢ በቦታው የጀግና እንጂ የፈሪ ቃል አይደለምና እምቢ ለማለት ራሳችንን እናስለምድ።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ቲቶ 2፥11-14, ዕብ. 11፥24, ዘፍ. 39፥7,8**

## ጸሎት

*አባት ሆይ አሺ ማለት ባለብኝ ጊዜ አሺ እያልኩ ፣ እምቢ ማለት ባለብኝ ጊዜ እምቢ እያልኩ እንድኖር ጸጋህን አብዛልኝ።*



# 52
# ማቃለልና መድከም

*«እንደ ልጆችም ከእናንተ ጋር፦ ልጄ ሆይ፥ የጌታን ቅጣት አታቅልል፥ በሚገሥጽህም ጊዜ አትድከም፤ ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል ብሎ የሚነጋገረውን ምክር ረስታችኋል» ዕብ. 12፡5-6*

እዜብ ታላቅ እህቴ ናት። ተከታታይና በዕድሜ ተቀራራቢ ስለሆንን በልጅነታችን ፍቅራችንም ሆነ ጠባችን፣ ልማታችንም ሆነ ጥፋታችን አንድ ላይ ነበር። እናታችን ከሥራ ስትመለስ የጥፋታችን ወሬ ከደረሳት ያለ ምንም የማጣራት እርምጃ ሁለታችንንም እስገብታ ትገርፈናለች። አባታችን በቅርብ ስላልነበር እናታችን ተወልዳ ባደገችበትና በተከበረችበት ሰፈር ልጆቿ «የሴት ልጅ» እንዳንባልባት ቅጣቷ የመረረና የከረረ ነበር። ምንም እንኳ እሷ የምትቀጣን ወደ ፊት ሰው እንድንሆላት አስባ ቢሆንም ጩቅላ አእምሯችን ያን ለመገንዘብ የሚበቃ አቅም አልነበረውም።

ታዲያ የምንቀጣው ቅጣት አንድ አይነት ቢሆንም የእኔና የእህቴ ምላሽ ግን ፈጽሞ የተለያየ ነበር። እዜብ እናታችን የምትገርፈን ስለማትወደን እንደሆነ ስለምታስብ ይመስለኛል በማልቀስ ልታስደስታት ወይም በልመና ልትሸነፍላት አትፈልግም። ይልቅ ጥርሷን ነክሳ እጇን እያፈራረቀች በመስጠት ግርፋቷን እንደ ውሃ ትጠጣዋለች። ሕመሙ ቢጠዘጥዛትም ትውጠዋለች እንጂ አታለቅስም። እናቴ እጇ ዝሎ ስትተዋት «ምንም አልሆንኩም!» በሚል እልህ ትወጣና እያየቻት መጫወት ትጀምራለች። ባጭር ቃል ቅጣቱን ታቃልለዋለች። በተቃራኒው የእኔ ተራ ሲደርስ እናቴን መማፀን እጀምራለሁ፤ ለማስረዳት እጥራለሁ፤ ቀድሜ እነፈርቃለሁ። በለቅሶና በመንፈራገጥ ግርፋቴን እጠጣና ደክሟት ስትተወኝ በረንዳ ላይ እወጣና አለቅሳለሁ። እንደ እዜብ "እላመመኝማ!" ብዬ ወደ ጫወታ መመለስ ፈጽሞ አይሆንልኝም። እተክዛለሁ፣ እቆዝማለሁ፣ ሁሉ ያስጠላኛል። በተግባር ባላደርገውም በሃሳብ «እዚህ ቤት መኖር አልፈልግም፣ ጠፍቼ ገዳም እገባለሁ!» በማለት እጉረመርማለሁ። ባጭር ቃል ከቅጣቱ የተነሳ ፈጥኜ ተስፋ እቆርጣለሁ። እዜብ ስለምታቃልለው፣ እኔ ደግሞ ፈጥኜ ስለምደክም ሁለታችንም በልጅነታችን ከእናታችን ቅጣት ልናገኝ የሚገባንን ተግሣጽና ምክር

ያገኘን አይመስለኝም። የዕብራዊያን መልዕክት ጸሐፊ ከምሳሌ መጽሐፍ በመጥቀስ የእግዚአብሔርን ቅጣት አቃልለው ወይም በተቃራኒው በተግሣጹ ደክመው ከቅጣቱ ፍሬ ነገር እንዳይጎድሉ የቀደሙትን አማኞች በአፅንኦት ይመክራል። ካላስተዋልን በቀር በቅጣት ወቅት ከሁለት በአንዱ ጽንፍ ልንወድቅ እንችላለን። ቅጣት ማቃለል ወይም በቅጣት መድከም። ጌታ የሚቀጣን ስላጠፋን ብቻ ሳይሆን በውስጣችን ያለውን አደገኛ የሆነ የማጥፋት ዝንባሌ ከወዲሁ ለማረቅና መልክ ለማስያዝ ነው። ከአባታችን ከአዳም የወረስነው የአመፅና የኃጢአተኝነት ባሕሪ ዛሬ በቅጣት ካልተቀረፈ ነገ አድጎ ለጠላታችን መጠቀሚያ፣ ለአምላካችን መስደቢያ፣ ለእኛም መጥፊያ እንደሚሆን ጌታ ስለሚያውቅ እጁን ልኮ ሥጋዊነትን ከላያችን ይገፋል። በምትኩ የልጁን ባሕሪ በውስጣችን በማሥረጽ የቅድስናው ተካፋዮች እንድንሆን ያደርገናል።

ጉዳዩ የመቅረጽና የመሥራት ከሆነ ለምን «ቅጣት» ተባለ? ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል። በእርግጥ እኛ ቅጣትን የምናውቀው ከጥፋት ጋር በተያያዘ ብቻ ነው። እውነቱ ግን ከዚህ ይለያል። ወላጆቻችን የሚቀጡን ስላጠፋን ብቻ አልነበረም፤ ያ ቢሆንማ ኖሮ ፍርድ እንጂ ቅጣት ተብሎ አይጠራም ነበር። ነገር ግን የልጅነት የጥፋት ዝንባሌያችን ወደ ፊት አድጎ ወንጀል እንዳይሆንብንና እንዳያስፈርድብን በልጅነታችን ለማቅናት ይቀጡን ነበር። እግዚአብሔርም የሚገሥጸን ባሕሪያችን በጊዜ ሳይገራ ቀርቶ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጠዋቱ ሊያቀናን ነው። መቼም ቅጣት በጊዜው ደስ እንዲያሰኘንና ሃሌሉያ እንድንል አይጠበቅብንም። እውነቱ ይህ ነው ቅጣት ሁሉ ለጊዜው ያማል፣ ስለዚህም ያሳዝናል። ነገር ግን ስሜቱ ላይ ማተኮራችንን ትተን ዓላማው ላይ ብናነጣጥር የመታገሥ ዕድል እናገኛለን። ስንለምደው ፍሬውን ስለምናጣጥም የበለጠ እንታገሣለን። ቀስ በቀስ ቅጣት የልጅነት ዕዳ ሳይሆን የልጅነት መብት እንደ ሆነ ይገባናል። ዲቃላ አይቀጣምና። መቀጣታችን የልጅነታችን ማህተም እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህ ማቃለሉንም ሆነ መድከሙን ትተን ዘላለማዊ ትሩፋቱን እያየን ለመንፈላችን አባት እየተገዛን በሕይወት እንኖራለን።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ምሳሌ 3፥11, 12፤ አዮብ 5፥17፤ መዝ. 94፥12**

**ጸሎት**



*ጻድቅ አባት እግዚአብሔር ለፍጥረትህ የበኩራት አይነት እንድሆን አስበህ በእውነት ቃል ስለ ወለድኸኝ ዘወትር አመሰግንሃለሁ። ምንም እንኳን ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ አንተ ምሳሌ አዲስ ሆኜ ብፈጠርም በሥጋዬ አሁንም የኃጢአት ዝንባሌ ያለው አሮጌ ተፈጥሮ አለ። ከዚህ ለሞት የሚጣደፍ ማንነት የሚያድነኝ ዕለት ተለት የሚመራኝ እጅህ ነው። ይህ ሂደት ልጅነት ወራት የወላጅ ቅጣት ተመስሏል። እናም ለራሴ ጥቅም ስትቀጣኝ ቅጣትንህ እንዳላቃልል በሌላ በኩል ተስፋ በመቁረጥ እንዳልደክም እርዳኝ። ይልቅ የምትወደውንና የምትጠላውን፣ ደስ ያሚያሰኝህንና የሚያስዝንህን ለይቼ የማውቅበት፣ ከከፉ የምርቅበት መልካሙን የምይዝበት አድርግልኝ።*

# 53
# "ሳልሠራህ አልሠራብህም!"

*"የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ይህ ሸክላ ሠሪ እንደሚሠራ በውኑ እኔ በእናንተ ዘንድ መሥራት አይቻለኝምን? እነሆ፥ ጭቃው በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ፥ እንዲሁ እናንተ በእኔ እጅ አላችሁ።" ኤር. 18፥ 5-6*

ጊዜው ፀሐይ አደራዋን ለጨረቃ ልታስረክብ የተዘጋጀችበት አመሻሽ ላይ ነው። አንደ ልማዴ ቀን ሳነብ የዋልኩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለማሰላሰል ከምኖርበት ከልደታ ተነስቼ ፖስታ ቤት ደርሼ ለመመለስ በዝግታ እርምጃ የቢሪሞን ዳገት ማዝገም ጀምሬአለሁ። ወቅቱ የደርግ የመጨረሻ አመታት አካባቢ ሲሆን እኔም በስደት ከቆየሁበት ከጅቡቲ ከተመለስኩ በርካታ ወራት ተቆጥረዋል።

በረዥም ጊዜ ዝግጅት፣ በሦስት ወራት የድሬደዋ ቆይታ፣ በዘጠኝ ቀን አስልቺ የእግር ጉዞ በሕይወትና በሞት መሃል ተጉዤ ጥዬ የወጣሁትን አገሬን ዳግም ከተቀላቀልሁ አንድ ዓመት ሊሆነኝ የቀሩት ጥቂት ቀናት ናቸው። የተመለስሁት ከውጭ እንደሚመጡ እንደ ሌሎች ዲግሪ ጭኜ፣ ዶላር ቋጥሬ፣ ንብረት ከምሬ ባይሆንም እንኳ ባዶ አይደለሁም። የተመለስሁት ጌታን አግኝቼ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ፣ የሕይወትና የአገልግሎት ዓላማ ሰንቄ ነው።

በዚያን ዘመን በለስ ቀንቶት ከአገር የወጣ ሰው ተመልሶ ይመጣል ብሎ ማሰብ ዘበት ነበር። የጓደኛዬ እባት መጀመሪያ ያገኙኝ ዕለት በቁጭትና በመገረም እየተመለከቱኝ "ልጄ . . . እናት ልጇን የምትደብቅበት አጥታ እንደ ገና ሆዷ ውስጥ በገቡ ብላ በምትመኝበት ዘመን ደህና ከወጣህበት አገር ለምን ተመለስህ?" በማለት በጥያቄ ያፋጠጡኝን አልረሳውም። "የሄድከበት አገር እንዴት ነበር?" ሳይሉኝ በቀጥታ ወደ ቁጣ መዝለቃቸው አስገርሞኛል። እውነት ግን እኔ ለምን መጣሁ? ጓደኞቼ ወደ አሜሪካ፣ ካናዳና አውስትራሊያ ሲያቀኑ እኔ ለምን ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ? መልሱ "ድምጽ ሰምቼ" የሚል ነው። "የምን ድምጽ?" ትሉኝ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ድምጽ ነዋ! ብቻ እንዴት ሰማኸው? አትበሉኝ እንጂ ለመስማቴ ምንም ጥርጥር አልነበረኝም። "ወደ አባቶችህ አገር



ተመለስ፣ እኔም ቸርነትን አደርግልሃለሁ" የሚል ድምጽ በውስጤ ሰማሁ። ምንም እንኳ መጀመሪያው ላይ ነካ ያረገኝ የመሰላቸው ወገኖች ቢኖሩም በስተኋላ ግን "እግዚአብሔር የወደደው ይሁን!" በማለት በክብር ሸኝተውኝ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስሁ።

አሁን ዳግም የአዲስ አበባ ነዋሪ ሆኛለሁ። ከስደት ከተመለስሁ ጀምሮ ዋና ሥራዬ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ያነበብሁትን ማሰላሰል ነው። ዛሬም ልማዴን ለማድረስ ሰዐይን ያዝ ሲያደርግ ቀን ያነበብኩትን ቃል እያሰላሰልሁ ከልደታ ተነስቼ ፖስታ ቤት ከሚገኘው ካፌ ቡና በወተቴን አጣጥሜ ጨለማው ከመበርታቱ በፊት በእግር ጉዞ ወደ ቤት ማዝገሜን ቀጠልሁ። ስሞኑን በማነበው የባሕር ማዶ መጽሐፍ ያየኋቸው እግዚአብሔር በአስገራሚ መንገድ የተጠቀመባቸው ሰዎች ታሪክ ውስጤን በቅንዓትና በናፍቆት እንድዶታል። ድንገት "ጌታ ሆይ የምትጠቀምብኝ መቼ ነው? በኔ የምትሰራው መቼ ነው?" የሚል የማያባራ ጩኸት ከውስጤ ይፈልቅ ጀመር።

የሚከሲኮን አደባባይ እያቋረጥኩ ሳለ በቁስል ላይ እንደሚፈስ ዘይት ልብን የሚያረሰርስ ድምጽ በውስጤ ሲፈስ ተሰማኝ። "ልጄ ሆይ! ሳልሠራህ አልሠራብህም!" የሚል። ለካ ሰው በኃጢአት በመውደቁ ችግር የገጠመው መንፈሱ ብቻ አይደለም! ሃሳቡ፣ ስሜቱና ፈቃዱም የውድቀት ሰለባ ሆነዋል። በዚህ ምክንያት ሰው በክርስቶስ ትንሳኤ በማመን መንፈሱ ዳግም ቢወለድም አዕምሮው ካልታደሰ፣ ስሜቱ ካልተገራና ፈቃዱ ካልተቃኘ በእግዚአብሔር እጅ የሚጠቅም መሣሪያ መሆን አይችልም። ለጊዜው ቢጠቀምበትም እንኳ ዘላቂነቱ አጠያያቂ ይሆናል። የመጀመሪያውን ሰው ከምድር አፈር በእጁ እንዳበጀው ሁሉ አሁንም በክርስቶስ ያዳነውን ሰው ዳግም በእጁ ሊሠራው ይፈልጋል። እግዚአብሔር በእጁ በሠራው መሥራት ይወዳልና። የእግዚአብሔር እጅ የሠራው ሰው "ለክብር የሚሆን፣ የተቀደሰ፣ ለአምላኩ የሚጠቅም፣ ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ" መሆኑ አያጠያይቅም።

በትንሿ አዕምሮዬ ይህ ትልቅ እውነት ሲገባኝ "አቤቱ ትሠራኝ ዘንድ እነሆኝ!" አልሁ። ለካ ሳላውቀው ብዙ ተራምጄ ኖሮ ራሴን ቤታችን በራፍ ላይ አገኘሁት።

ተጨማሪ ንባባት፡- ኤፌ. 2፥10፤ ቆላ. 1፥21-22, 28፤

**ጸሎት**

*ጌታ ሆይ አንተ ድንቅ ሠራተኛ ነህ፣ እጅህ ሰማይና ምድርን በውስጣቸውም ያሉትን ሁሉ ሠርታለች፣ አንተ ስትሠራ ሕይወትንና ውበትን ታጎናጽፋለህ። አባክህ ትሠራብኝ ዘንድ በቃልህና በመንፈስህ አስቀድመህ ሥራኝ። አሜን።*



# 54
# ቀኝ ኋላ ዙር!

*«ከፍ ከፍ ስትል ስንፍናን ያደረግህ እንደሆን፥ ክፉም ያሰብህ እንደ ሆነ፥ እጅህን በአፍህ ላይ ጫን» ምሳ. 30፡32*

ጊዜው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሚያዝያ 1982 ዓ.ም ነው። በደቡብ አትላንቲክ ጦርነት ነግሷል። በፎክላንድ ደሴቶች የይገባኛል ጥያቄ በተቀሰቀሰው ግጭት የአርጀንቲናና የእንግሊዝ ሠራዊት በአየር፣ በየብስና በባሕር ለ 10 ሳምንታት ሲዋጉ ከርመው ጦርነቱ በእንግሊዝ አሸናፊነት ተጠናቋል። ከአሥር ሳምንታት በፊት ደሴቶቹን የወረሩት በወታደራዊው መንግሥት የሚመሩት የአርጀንቲና የመከላከያ ሠራዊት አይቀሰሱ ቆስለውና አፈግፍገው ከባሕር ማዶ ድንበራቸው ላይ ለፍረዋል።

ጦርነቱ ከመጀመሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ እስቸኳይ የዕርዳታ እህል፣ መድኃኒቶችና የተለያዩ ቁሳቁሶች ጭኖ ወደ አገሩ ወደብ የሚያመራ የኡራጓይ መርከብ በአርጀንቲናና በፎክላንድ መሃል ስንጥቆ በሚያልፈው የባሕር መስመር ለመጓዝ መንገድ ጀምሯል። ሆኖም በጦርነቱ መጀመር ሳቢያ ላለፉት አሥር ሳምንታት በውሃ ላይ መከረም ግድ ይሆንበታል። ጦርነቱ ቢጠናቀቅም አንዳቸው ሌላቸው ላይ መሣሪያቸውን ደቅነው በተጠንቀቅ በሚጠባበቁት ጠበኞች መሃል ለማለፍ መሞከር ራስን የማጥፋት ውሳኔ መሆኑን የተረዱት የመርከቡ ሠራተኞች ምን እንደሚያደርጉ ጠፍቷቸው በጭንቀት ተውጠዋል። ሌላ ተጨማሪ ጊዜያት ውሃ ላይ ለማሳለፍ ቢያስቡ በነዳጅና በሥንቅ እጥረት የባሰ አደጋ ላይ እንደሚወድቁ ስለሚያውቁ ምን እንደሚወስኑ ግራ ገብቷቸው ያምጣሉ።

ድንገት የመርከቡ መሪ አንድ አብደት የሚመስል አስገራሚ ሃሳብ መጣለትና በደስታ ፈነደቀ። ወዲያው ሠራተኞቹን ሁሉ ሰብስቦ ሃሳቡን አካፈላቸው፤ መስማማታቸውን በሆታ ገለጹለት። ወዲያው ሃሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀመሩ። ሃሳቡ እንዲህ ነበር፤ መርከባቸው የጦርነት ቀጠናውን የሚያልፈው አርጀንቲናን በግራ፣ ፎክላንድ ደሴትን በቀኝ አድርጎ ነው። ስለዚህ የመርከቢቱን ግራ ጎን

ከዳር እስከ ዳር በአርጀንቲና ባንዲራ፣ ቀኝ ጎኗን ደግሞ በእንግሊዝ ባንዲራ በመቀባት ያለምንም ችግር ወደ ኡራጓይ ማቅናት ።

የመርከቡ ሠራተኞች በሙሉ ለሁለት ቀናት ቀለም በመቀባት ሥራ ተጠምደው ከዋሉ በኋላ መሪው ሁለቱም ጎን በሚገባ መቀባቱን አረጋግጦ ወደ ጦር ቀጠናው መንዝ ጀመሩ። መሪው የወሰደው እርምጃ በመርከቡ ላይ ያሉትን ሰዎችና ንብረት አደጋ ላይ የሚጥል አሰጊ ውሳኔ ቢሆንም የሁለቱን አገሮች የጦር ኃይላት ባቋረጠበት ጊዜ የሆነው ነገር ፈጽሞ የማይታሰብ ነበር። የአርጀንቲና ሠራዊት የአገራቸውን ባንዲራ በመርከቡ ላይ ሲያዩ መሣሪያዎቻቸውን አስቀምጠው በአክብሮት ሰላምታ ሰጡ። የእንግሊዞቹም በመደናገጥ ለባንዲራቸው ሰላምታ ሰጡ። መርከቡዋ ያለ አንዳች ችግር በታላቅ ክብር የጦር ቀጠናውን አቋረጠች።

የመርከቡ ካፒቴን ጮቤ ረገጠ፤ ሠራተኞቹ ፈነጠዙ፤ መሪያቸውን ተሸከመው ጨፈሩ፤ መጠጥ ዐይነት በዐይነት ተከፈተ፤ ትልቅ ፌሽታ ሆነ። ተበላ፤ ተጠጣ ተሰከረ። ሰካር ያናወዛቸው ሠራተኞች ሳይታወቃቸው መሪውን ሲሸመልሉ መርከቧ አቅጣጫ ቀይራ በመጣችበት መንገድ መመለስ ጀመረች። ከሞቅታውና ከሆታው የተነሣ የሚሆነውን የሚያስተውል አንድ ሰው በመርከቧ ላይ አልነበረም። ሁሉም የነቁት ወደ ጦር ቀጠናው ገብተው የተኩስ ዕሩምታ ከግራ ከቀኝ ሲዘንብባቸው ነው። አሁን በአርጀንቲናም ሆነ በእንግሊዝ ጦር ወገን እንደ ቅድሙ የሚያዩት የአገራቸውን ባንዲራ ሳይሆን የጠላት ባንዲራ ስለነበር ከመተኮስ ሊታቀቡ አልቻሉም። ዘግይተው ከሰካር የነቁት መሪውና ሠራተኞቹ ነጭ ጨርቅ እያውለበለቡ ቢማጸኑም በጥይት ከመደብደብ አልተረፉም።

እግዚአብሔር ድል ሲሰጠን፣ ከፍ ከፍ ሲያደርገን፣ ትልማችን ግብ ሲመታ፣ ሃሳባችን ሲሰምር ምላሻችን ምን ይሆን? በችሎታችን ተመከተን፣ በአድናቂዎቻችን ሆታ ተውጠን እንፈነጥዛለን ወይስ ስኬት ለሰጠን ለእግዚአብሔር በአክብሮትና በፍርሃት እንሰግዳለን? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው ለትምህርታችን የተጻፈልን አያሌ ነገሥታት እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ባስገዛላቸው፣ ጎረቤቶቻቸውን ባስገበረላቸው ጊዜ በራሳቸው ኃይልና ብርታት ያመጡት እየመሰላቸው በከፍታቸው ታብየው ቁልቁል የወረዱ፣ ለአሕዛብ መተረቻና መዘበቻ



የሆኑ ጥቂት አይደሉም። እኛም ዛሬ በስኬት ሳንደለል፣ በከንቱ ውዳሴ ሳንፈታ በተከናወነልን ቁጥር እግዚአብሔርን ለማከበር እንትጋ።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ሚኪ. 7፥16፣ 2ዜና 26፥1-23፣ መዝ. 10፥4**

## ጸሎት

*ጌታ ሆይ ጥጋብን፣ ከፍታን፣ ድልን፣ ስኬትን ያለ አንተ መሸከም አይቻልም። በእነዚህ ውስጥ ከየት እንደተነሣን፣ ትናንት ማን እንደነበርን፣ አንተ ምን እንዳደረክልን ለመርሳት እንጋለጣለን። በቀላሉ እንሰታለን። አቤቱ! እባክህ ከመታበይ ጠብቀኝ፣ ከስንፍና ሃሳብ አድነኝ። ድል ስትሰጠኝ የድሉ ባለቤት አንተ መሆንህን አስተውዬ የሚገባህን ክብር እንድሰጥህ እርዳን።*

# 55
# የተሰወረው ሲገለጥ

*“ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን . . . የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸከመን እንዞራለን” 2ቆሮ. 4፡ 7. 10-12*

በታይላንዷ ዋና ከተማ ባንኮክ ቻይናውያን በብዛት በሚኖሩበት ዋት ቾታናራም ተብሎ በሚጠራ ሠፈር የሚገኝ ከሸክላ የተሠራ የቡድሃ ኃውልት ነበር። ኃውልቱ የሱኮ-ታይ ሥርወ መንግሥት ታይላንድን በሚገዛበት በ 13ኛውና በ14ኛው ክፍለ ዘመን በህንድ የሥነ ቅርጽ ጠበብቶች እንደተሠራ ይነገርለታል።

ከብዙ ዘመናት በኋላ የቻይናዎቹ ሠፈር እየተዳከመና እየወደቀ መሄዱን የተመለከቱት ባንኮካዊያን እየደመቀ በመጣውና ዋት ትሬሚት ተብሎ በሚጠራው አዲስ የከተማዋ ማዕከል ያማረ መቅደስ ሊገነቡለት ይነሳሉ። ምንም እንኳ ግንባታው በ 1954 ቢጠናቀቅም በሁለቱ ሠፈርተኞች መሃል “ይሄዳል፣ አይሄድም” በሚል የተነሳው እስጥ አገባ ለአንድ ዓመት ጉዞውን ያዘገየዋል። ከብዙ ውዝግብ በኋላ “ይሂድ” በሚለው ሃሳብ ስምምነት ላይ ይደረስና ግንቦት 25፣ 1955 ዓ.ም ግዙፉን ሃውልት የማንቀሳቀስ ሥራ ይጀመራል።

ከስድስት መቶ ዓመታት በላይ የኖረ ታሪክ እንዳለው የሚነገርለትን የሸክላ ሃውልት ያለ እንዳች እንከን አዲሱ ህንፃ ለማድረስ ከታይላንድ ቤተ-መንግስትም ሆነ ከቡድሃ ቤተ-መቅደስ ጽኑ አደራ የተቀበሉት የሥራው መሪዎች የከባድ ዕቃ ማንሻ መሣሪያዎቻቸውን ደቅነው፣ ጠንካራ ገመዶቻቸውን ወጥረው ለዘመናት ከተቀመጠበት ዓምድ ላይ ለማንሳት ወዲና ወዲያ ይራወጣሉ። ዕቃ ማንሻ መሣሪያው ሐውልቱን የተወሰነ ከፍታ አንስቶ በተዘጋጀለት የጭነት መኪና ላይ ለማስቀመጥ ሲታገል ድንገት ገመዱ ይበጠስና ሃውልቱ መሬት ላይ ይከሰከሳል። ባዩት ሁሉ ውስጥ ድንጋጤ ነገሠ።

ሆኖም በዙሪያ ያሉት ሁሉ እንደጠበቁት ኃውልቱ ዶግ አመድ አልሆነም። የሥራ ኃላፊዎቹ የጉዳቱን መጠን ለመመልከት ሲጠጉ ያዩትን ማመን አልቻሉም። በአንድ ወገን ሸክላው ፈርሷል ነገር ግን ሸክላው በፈረሰበት



በኩል የሚያበራና የሚያንጸባርቅ ነገር ይታያል። ኃላፊዎቹ በፍጥነት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ባለ ሥልጣናት የሆነውን ይገልጹና የማጓጓዙ ሥራ ቆሞ በሃውልቱ ላይ ጥናትና ምርምር ይጀመራል። ለካስ ከራስ እስከ እግሩ 3.91 ሜትር የሚረዝመው፣ 5,500 ኪሎ ግራም የሚመዝነው ሃውልት የተሠራው ከሸክላ ሳይሆን ከወርቅ ኖሯል! ጥናቱ እንዳረጋገጠው ጸጉሩ ብቻ የተሠራበት ወርቅ 45ኪሎ ግራም የሚመዝን 99% ንጹህ የሆነ 18ካራት ወርቅ ነው።

የወርቁ ሐውልት ከፍጥረቱ በሸክላ የተሸፈነ አልነበረም። የጥንቶቹ የታይላንድ ሰዎች በ1767 ዓ.ም ከዘመቱባቸው የበርማ ወራሪዎች ለማዳን ሲሉ ሸክላ በሚመስል ስቱኮ ለበጡት። ከእነርሱ በኋላ የተተኩትም ነገሥታት የጠላትን ትኩረት እንዲስብ ስላልፈለጉ በዚያው ሁኔታ ትተውት አለፉ። ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ምሥጢሩ ሳይተላለፍ ቀርቶ እንደ ሸክላ እየተቆጠረ ኖረ። ነገር ግን ዘመን መጥቶ ከስፍራው በመንቀሳቀሱና ለጊዜው ሁሉን ያስደነገጠ አደጋ በመፈጠሩ የሃውልቱ እውነተኛ ማንነት ሊገለጥ በቃ። እነሆ ዛሬ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ጎብኚዎች ይህን የወርቅ ሃውልት ለማየት ከዓለም ዙሪያ ይጎርፋሉ።

ዳግም የተወለደ አማኝ ሁሉ እንደዚህ ሃውልት በሸክላ የተለበጠ ወርቅ ነው። ከውጭ የሚታየው የተዋረደው የሥጋ ሕይወት ቢሆንም ውስጡ ከወርቅ የሚከብረው የክርስቶስ ሕይወት አለ። የእግዚአብሔር ናፍቆት ይህ የውስጡን ሕይወት የሸፈነ የሥጋ ሕይወት ተወግዶ የልጁ ሕይወት እንዲገለጥ ነው። ሆኖም የአማኝ ውስጣዊና እውነተኛ ማንነቱ እንዲገለጥ የውጪው ሊፈርስ ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር ይህን ለማድረግ ከሚጠቀምባቸው ነገሮች አንዱ የምንኖርበትን ኑሮ ነው። አንዳንዴ ለኛ አደጋ የሚመስለን፣ የሚገድለንና የሚያጠፋን የሚመስለን ሁኔታ በውስጣችን ያለውን የልጁን ክቡር ሕይወት የሚገልጥበት መንገድ ሊሆን ይችላል።

የተጠራነው የክርስቶስ ሕይወት እንዲገለጥልን ብቻ ሣይሆን እንዲገለጥብን ጭምር ነውና እግዚአብሔር ከሥፍራችን ሲያንቀሳቅሰን፣ ከምቾቶቻችን ሲያወጣን፣ በቃ አለቀልኝ በምንልበት መንገድ ሲያሳልፈን አንታከት። ይልቅ ከሐዋርያው ጋር እንዲህ እንበል፦ “ስለዚህም አንታከትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ

ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው" 2ቆሮ. 4:16-18

**ተጨማሪ ንባባት፦ 2ቆሮ. 13፥5፣ ሮሜ 8፥10፣ ገላ. 1፥15-16**

**ጸሎት**

*ክቡር ጌታ ሆይ፦ አንተ ስትመጣና መንግሥትህን ስትመሠርት የአሁኑ ዓለም ሥርዓት እንደሚቀየር፣ እንባዎች ሁሉ ከዓይኖች እንደሚታበሱ፥ ሞትም እንደሚሻር፥ ኀዘንም ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ እንደማይሆን አምናለሁ። ዛሬ ግን እኔን ለዘለዓለሙ መንግሥት ለማዘጋጀት የምትሠራበት ጊዜ እንጂ የእረፍትና የምቾት ዘመን እንዳይደለ ተረድቻለሁ። ስለዚህ በውስጤ ያለው የልጅህ ሕይወት እንዲገለጥ፣ የሸፈነው የሥጋ ሕይወት እንዲወገድ የምትሠራውን ሥራ ሁሉ ያለ ማጉረምረም እንድሰማማ፣ ያለማመንታት እንድቀበል፣ ያለ መታከት እንድሄድበት ጸጋን አብዛልኝ።*



# 56
# ድምጽን በድምጽ መፈተሽ

*"ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን . . . ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት" ዕብ. 1፥1-2፣ 2፥3*

በአንድ ወዳጃችን ቤት ሳሎን ውስጥ ተሰብስበን እንጫወታለን። ምስል ከሳቹ መስኮት (ቴሌቪዥን) ቢከፈትም ቀልቡን የሰጠው አልነበረም። ታዋቂው የኬብል ኒውስ ኔት ወርክ (ሲ ኤን ኤን) ጋዜጠኛ ታነበንባለች። ድንገት አናቱ ላይ ነጭ ጨርቅ የጠመጠመ፣ ከውስጥ በለበሰው ባሕላዊ ልብስ ላይ ዥንጉረጉር የወታደር ጃኬት የደረበ፣ ቀይ መልከ መልካምና ገራም ፊት ያለው ሰው እመልካች ጣቱን ቀስሮ በአረብኛ ቋንቋ ንግግር ያደርጋል። እለምን በፍርሃት ከሰነገው የቅርብ ጊዜው ድርጊት የተነሳ የሁላችንም ትኩረት ወደ ምስል ከሳቹ ተሳበ፣ ድምጹ ተጨመረ፣ ዜናውን ሁላችንም በጥሞና መከታተል ጀመርን። የሚታየው ምስልና የሚያጅቡት ተንቀሳቃሾች ምንጫቸው ያልታወቀ፣ በባለ ሙያ ያልተቀረጹ ከአፍጋኒስታንና ከፓኪስታን ተራሮች የመጡ መሆናቸውን ለማወቅ ጥልቅ ምርምር የሚጠይቅ አልነበረም። ርዕሰ ዜናው የወቅቱ የአለም ቁጥር አንድ አሸባሪ በቅርቡ በአውሮፓና በአሜሪካ ላይ የሽብር ጥቃት እንደሚያደርስ የሚያስጠነቅቅ መልዕክት በድምጽ ተቀንብብሮ በድረ-ገጽ መለቀቁ ነበር። ያን ሰሞን ደጋግመን ከመስማታችን የተነሳ የሰውየውን ድምጽ ስላጠናነው እሱ መሆኑን ለመደምደም ጊዜ አልወሰደብንም ነበር። ሆኖም ጋዜጠኛዋ ባለሙያዎች አቅርባ ካነጋገረች በኋላ ድምጹ የሱ ይሁን፣ አይሁን አልተረጋገጠም ተባለ።

ይህ አባባሏ በመካከላችን ያልታሰበ ውይይት ጫረ። ድምጹ የሱ ለመሆኑ እኛ እንኳ እርግጠኞች ሆነን ሳለ እንዴት ነው እነርሱ "አልተረጋገጠም" የሚሉት? መቀበል ስላልፈለጉ ነው? ወይስ ሌላ ምሥጢር አለው? ጠየቅሁ። ከመካከላችን አንዱ ሳይበር ሴኩሪቲ (የመቀመሪያ መረጃ ደህንነት) ያጠና ነበርና ስለ ድምጽ የማናውቀውን አንድ ምሥጢር አጫወተን። "አንድ ስሕዝብ ደህንነት ስጋት የሆነ ሰው ሲሰወርና በድምፅ የተቀረጸ መልዕክት ሲያስተላልፍ የደህንነት ባለሙያዎች ከመሰውሩ

በፊት በገሃድ ሲናገር የተቀረጸውን ድምጽ ፍለጋ ይጀምራሉ። መቼም በዚህ በሠለጠነ የመረጃ ዘመን የሰውን ድምፅ ቅጂ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደማይሆን እሙን ነው። የሰውየው እንደሆነ መቶ በመቶ የታመነበትን ቅጂ ካገኙ በኋላ የርሱ መሆኑ የታመነበትን የቀደመ ድምጽና አሁን ተለቀቀ የተባለውን ድምጽ በረቀቀ መሣሪያ ውስጥ ያስገቡና ያስተያያሉ መሣሪያው የድምጽ ርግብግቢቱን፣ ቃናውንና አሻራውን ያስተያይና "ነው!" ወይም "አይደለም!" ይላል።" በማለት አጫወተን።

ይህ ዘመን አመጣሽ የሥልጣኔ ውጤት አንድ ዘላለማዊና ዘመን የማይሽረው እውነታ እንዳስብ አደረገኝ። ከዚያም ይህ የማይታይ ተናጋሪን የድምጽ መልዕክት እውነተኝነት ለመለየት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልንጠቀምበት የሚገባ አይነተኛ መንገድ መሆኑን ተገነዘብኩ። ጥንት ለአምነት አባቶቻችን በብዙ ዓይነት መንገድና ጎዳና የተናገረው እግዚአብሔር ዛሬም ይናገራል። ሆኖም ዛሬ በየጓዳውና በየአደባባዩ እግዚአብሔር ተናገረ የሚባሉትን ድምጾች በእርግጥ እግዚአብሔር ተናግሯቸው እንደ ሆነና እንዳልሆነ ለመለየት የምንቸገርባቸው ጊዜያት ቀላል አይደሉም። አንዳንዴ ባይጥመንም በእግዚአብሔር ስም ስለተነገሩና ባንቀበላቸው መንፈስ ቅዱስን እንዳልተቀበልን ተቆጥሮ ስለሚያስወግዘን ዝምታን እንመርጣለን። አሁን ግን ከላይ ያነበብነው ሥልጣኔ የወለደው መፍትሄ በመንፈስ ቅዱስ አማኞችም ዘንድ ሥራ ላይ መዋል ያለበት ይመስላል። ብዙዎች ከተገለጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይልቅ "ጌታ እንዲህ አለ" "እንዲህ ይልሃል" "እንዲህ ይልሻል" የሚለውን ድምጽ በፍቅር ስለሚወዱ ነው።

ስለዚህ እኛም እንደ ደህንነት ባለሙያዎቹ የእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን ያልተጣራውን የዛሬውን ድምጽ ምንነት ለመለየት የእግዚአብሔር ድምጽ መሆኑ መቶ በመቶ የተረጋገጠለትን ድምጹን መፈለግ፣ ቃናውንና አሻራውን መለየት ይኖርብናል። የእግዚአብሔር መሆኑ የተረጋገጠው ድምጽ ቅዱስ ቃሉ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በአንጾኪያ ምኩራብ ለተሰበሰቡት አይሁድ "በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችና አለቆቻቸው እርሱንና በየሰንበቱ የሚነበቡትን የነቢያትን ድምጾች ስላላወቁ በፍርዳቸው ፈጽመዋልና" (ሐዋ. 13፥27) እንዳለ የተጻፈውና በእጃችን ያለው የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ድምጽ ነው።



መመርመሪያው መሣሪያ ደግሞ በውስጣችን ያሳደረው ሕያው መንፈስ ነው። ስለዚህ ዛሬ ተናገረ የተባለውን ድምጽና ቀድሞ የተናገረውን የቃሉን ድምጽ ፊት ለፊት አምጥተን በመንፈስ በመመርመር እርግጠኛውን ልናውቅ ከስህተትም ልንጠበቅ እንችላለን።

**ተጨማሪ ንባብት፡- 2ጴጥ. 1፥19-21, ዕብ. 4፥12, መዝ. 119**

## ጸሎት

*ቅዱስ እግዚአብሔር አንተ የምትናገር አምላክ ነህ። ጥንት ተናግርሃል፣ ዛሬም ትናገራለህ። በአንዳችን ለሌላችን ትናገራለህ። ነገር ግን አንተ የተናገርከውን ካልተናገርከው ለመለየት የምቸገርባቸው ጊዜያት ጥቂት አይደሉም። የትኛውንም በስምህ የሚነገር ድምጽ ለመለየት ስለ ሰጠኸኝ የቃልህ ድምጽ አመሰግንሃለው። አሁንም የዛሬውን ድምጽ በጥንቱ የቃልህ ድምጽ እንድመረምር አሠልጥነኝ። ራሴንም የሚሰሙኝንም ከሥህተት እንድታደግ እርዳኝ።*

# 57
# እንደ ፀሐይቱ

*"የቃልህ ፍቺ ያበራል፥ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።" መዝሙረ ዳዊት 119፡ 130*

ጊዜው የሰሜን ንፍቀ ክበብ አገራት ከረዥም ወራት ቅዝቃዜና ጨለማ ወጥተው የበጋውን ፀሐይ የሚያጣጥሙበት የበጋ መዳረሻ ነው። ከጀርመን ከተሞች አንዷ የሆነችው ዱዝልዶርፍ ገና በጠዋቱ ደማምቃለች። በከተማዋ የወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ ለመሰበክ የተጋበዘው ወንጌላዊ ሬኄናርድ ቦንኬ ትናንት ምሽት ከሎንዶን ገብቶ አድሯል። ቦንኬ ከጥሩ ዕረፍት በኋላ ከእንቅልፉ የቀሰቀሰው የከፍሉን መስታወት ዘልቆ የገባው የፀሐይ ጨረር ነው። ካደረበት የሆቴል ከፍል ወርዶ ቁርሱን ካደረሰ በኋላ የማለዳዋን ፀሐይ ከዱዝልዶርፍ ነዋሪዎች ጋር ለመሻማት እዝጋሚ የእግር ጉዞ ጀመረ።

የሚሰብከውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እያሰላሰለ ሲራመድ ከቆየ በኋላ ከተማው መሃል ወዳለ መናፈሻ ደርሶ ወንበር ላይ አረፍ አለ። ባጠገቡ ዕድሜው በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገመት ጀርመናዊ ወጣት ተቀምጦ ፀሐይ ይሞቃል። ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥታ ከነገሠ በኋላ ቦንኬ ዘወትር እንደሚያደርገው ይህንን አጋጣሚ ለወጣቱ የወንጌልን የምሥራች ለመንገር ሊጠቀምበት ፈልጎ "የማለዳው ፀሐይ እንዴት ነው?" በማለት ዝምታውን ሰበረው። ወጣቱም "በጣም ቆንጆ ነው፣ ደስ ይላል" በማለት ምላሽ ሰጥ። ቦንኬ በመቀጠል "ይህን ውብ ፀሐይ በነፃ የሰጠን ማን እንደሆነ ታውቃለህ?" አለው። ልጁም ግራ በመጋባት "አላውቅም!" በማለት መለሰለት። ቦንኬም ቀጠል አድርጎ "መጽሐፍ ቅዱስ ታነባለህ?" አለው። ልጁም ፊቱን ጭፍግግ አድርጎ "አላነብም! ለምንድነው የማነበው? መጽሐፍ ቅዱስ ያረጀ መጽሐፍ ነው። እንደምታየኝ እኔ ወጣት ነኝ፤ የሃያ አንደኛ ከፍለ ዘመን ሰው ነኝ፤ ለዘመኔ የሚመጥኑ አዳዲስ ፍልስፍናዎችን የያዙ መጻሕፍት እንጂ ያረጀና ዘመን ያለፈበት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ሊያደርግልኝ እነባለሁ?" አለው።

ቦንኬ ለጥቂት ቅፅበት ዝም ካለ በኋላ ድንገት የውይይቱን ርዕስ የቀየረ በሚምስል መንገድ "አሁን እዚህ ምን ትሠራለህ?" ሲል ጠየቀው።



ወጣቱም ዘና ብሎ "እንደምታየው ፀሐይ እየሞቅሁ ነው" አለው። ቦንኬም ቆፍጠን ባለ ድምጽ "ፀሐይ ለምን ትሞቃለህ? እንዳንተ ዓይነት የሃያ አንደኛ ከፍለ ዘመን ወጣት ይህችን አሮጌ ፀሐይ መሞቅ አይኖርበትም፤ የፀሐይ ዕድሜ በብዙ ሚሊዮን ዓመት እንደሚቆጠር ከሳይንስ እንደ ተማርህ እርግጠኛ ነኝ። ስለዚህ እንዳንተ ያለ ወጣት የሚመጥነው አዲስ ነገር መፈለግ ይኖርበታል እንጂ አሮጌ ፀሐይ መሞቅ አይኖርበትም" አለው ምፀት በሞላበት ንግግር። ወጣቱ ግራ በመጋባት የቦንኬን ንግግር በጥሞና ማዳመጥ ጀመረ። ቦንኬም በመቀጠል "እየህ፣ ፀሐይ ዕድሜዋ ረዥም ቢሆንም ዛሬም ብርሃን ትሰጣለች፤ ሙቀቷ አልደከመም፤ ድምቀቷ አልቀነሰም። ዘር፣ ቀለም፣ ኃይማኖት ሳትለይ ለሁሉ ታበራለች፤ መጽሐፍ ቅዱስም እንደዚሁ ነው፤ የተጻፈበት ዘመን ረዥም ቢሆንም ዛሬም ለሰው ዘር ሁሉ ያበራል፤ ነጻ ያወጣል፣ ይለውጣል። የፀሐይ ብርሃን ወደ እንተ የመጣው ከዘጠና ሦስት ሚሊዮን ማይልስ ርቀት ነው። አንተ ግን ወደ ፀሐይ ለመድረስ ብዙ አልተጓዝከም። ሲነጋ ለፀሐይ በርህን ከፈትህ፣ አሁን ደግሞ ወጥተህ በፀሐይ ፊት ተቀምጠህ ሁለንተናህን ለብርሃኗና ለሙቀቷ ሰጠህ። የእግዚአብሔርንም ቃል በተመለከተ ከአንተ የሚጠበቀው ይኸው ነው። ልብህን ለቃሉ ኃይልና ብርሃን ከፈት፣ በውስጡ ላለው እውነት ራስህን ስጥ" ወጣቱ ሳይታወቀው ፊቱም ልቡም በራ፣ በጉጉት ማድመጡን ቀጠለ።

የእግዚአብሔር ቃል እያረጅም፤ ኃይሉ አይደከምም፤ ብርሃኑ አይደበዝዝም፤ ሙቀቱ አይቀዘቅዝም። ሰው በኃጢአት የታወረው የልብ ዐይኑ ሲበራ፣ ሰይጣን ከዘጋበት የጨለማ ጉድጓድ ሲወጣ፣ የሸፈነው መጋረጃ ሲቀደድ፤ የዐይኑ ቅርፊት ሲወገድ፤ የክብርን ጌታ በውበቱ ያየዋል። የምህረትና የርህራሄ ነፀብራቅ፤ የፍቅርና የቸርነት ፀዳል፤ የሕይወትና የልምላሜ ወጋገን ያርፍበታል። ከቃሉ የሚመነጨው የሕይወት ብርሃን በውስጡ የተዳፈነውን እምነትና ተሰፋ ቀስቅሶ ወደ ዘላለም ሕይወት አድማስ ይመራዋል።

ይህን የተረዳ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ከልቡ ሲወድ፣ ሳያስተጓጉል ሊያነብ፣ ሳያሰልስ ሊያሰላስል፣ ሳያመነታ ሊታዘዝና በትጋት ለሌሎች ሊያካፍል ይገባዋል።

ተጨማሪ ንባባት፡- መዝ. 102፥27-28, ኢሳ. 40፥8, ዕብ. 1፥11

**ጸሎት**

*አቤቱ በቃልህ የፈጠርካት ፀሐይ አንኳ ሳትደክም እስከ ዛሬ ታበራለች፤ ቃልህማ ምንኛ! ስለ ቃልህ ምን ብዬ አንደ ማመሰግንህ አላውቅም፤ ቃላት ያጥረኛል፤ ቋንቋ ይገድበኛል። በዘመኔ ሁሉ ቃልህን ግለጥልኝ፤ በሥርዓት አንድተረጉመው፣ በጽናት አንድታመነው፣ በትጋት አንድታዘዘውና በኃይል አንዳውጀው እርዳኝ። አሜን።*



# 58
# ያን ሰው አገኘሁት!

*"ነገር ግን መጽሐፍ፡ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤" (ያዕ. 2፡8)*

ከ 1898 እስከ 1963 ዓ.ም የኖረው ብሪታኒያዊው ምሁርና ደራሲ ሲ. ኤስ. ሉዊስ ለበደሉን ሰዎች ይቅርታ ማድረግን አስመልክቶ ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር፡- "ልጅ ሳለሁ ዘወትር እሁድ ከወላጆቼ ጋር ቤተ ክርስቲያን እሄድ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ስለ ይቅርታ አብዝተው ይሰብኩ ነበር። አንድ እሁድ ለበደሉን ሰዎች ይቅርታ ስለ ማድረግ ሲናገሩ እንዲህ አሉ፡- 'ሰዎችን ይቅር ለማለት አስቀድመን እነርሱንና ሥህተታቸውን መለየት መቻል አለብን። ያኔ እነርሱን መውደድ፣ ሥህተታቸውን መጥላት እንችላለን። ይህ ደግሞ ይቅር እንድንላቸው አቅም ይሰጠናል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል፤ ሰውን ግን ይወዳል፤ ስለዚህ የሰውን ኃጢአት በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ኮንኖ ሰውን መማር ቻለ። እኛም ሰዎችን ከሥህተታቸው ለይተን እንይ፤ ሥህተታቸውን እንጥላ፣ ሰዎቹን ግን እንውደድ ያኔ ያለ ምንም ችግር በደላቸውን ይቅር ማለት እንችላለን የልጅነት አዕምሮዬ ይህን ከትቦ ይዟል።

የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ጨርሼ ወደ ዩኒቨርስቲ ስገባ 'እግዚአብሔር የለም' በሚል የክህደት ፍልስፍና ተጠመድሁና ሠላሳ ሁለት ዓመት እስኪሞላኝ ድረስ የወጣልኝ ከሃዲ ሆንኩ። ታዲያ አልፎ አልፎ የልጅነት የቤተ ክርስቲያን ትዝታዬን ሳስላስል ደጋግሞ ወደ አዕምሮዬ የሚመጣው "ሥህተቱን ጥላው፣ ሰውየውን ግን ውደድው" የሚለው የመጋቢው አባባል ነበር። ትዝ ባለኝ ቁጥር "እነዚህ ሰባኪዎች እንዴት ያሉ ግብዞች ናቸው? ሥህተቱን የሠራው ሰውዬው ራሱ ነው፤ እንዴት አድርጌ ነው ሰውየውን ከሥህተቱ የምለየው? እንዴት ነው ሥህተቱን ጠልቼ ሰውየውን የምወደው? ይሄ እጉል ጸጉር ሰንጠቃ ነው!" እል ነበር።

አንድ ቀን ግን የተለየ ነገር ሆነ፤ ወደ ጌታ ከተመለስኩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ ሥፍራ ስጥሞና ተቀምጬ ሳለሁ ያን ሰውዬ አገኘሁት፤ ያኔ ልጅ ሆኜ መጋቢያችን ስህተቱን ጥላው፤ እሱን ግን ውደደው የሚሉትን ሰው

እገኘሁት። ለካ ያ ሰው እኔ ራሴ ነበርኩ! "ስውየውንና ስህተቱን መለየት እንዴት ይቻላል፤ ሥህተቱን ጠልቼ ሰውየውን የምወደው እንዴት ነው?' እያልኩ የምጠይቀው ጥያቄ ሁሉ በቅፅበት መልስ አገኘ። ለሠላሳ ሁለት ዓመታት ከራሴ ጋር ስኖር ለቁጥር የሚያዳግቱ ሥህተቶች ሠርቻለሁ፤ ነገር ግን ምንም ያህል በሥህተቴ ባዝንና ብበሳጭ፣ በራሴ ላይ ብቆጣና ባጉረመርምም እንዴት ሥህተቴን አስተካከዬ፣ የተሻለ ሰው ሆኜ እንደምቀጥል እሰባለሁ እንጂ አንድም ቀን ራሴን ይቅር ማለት ተስኖኝ አያውቅም። በፍጹም! ለምን? ራሴንና ሥህተቴን ለይቼ ስለማይ ነዋ! ሥህተቴን ብጠላውም ራሴን ስለምወድ ነዋ!"

ይህ የሲ. ኤስ. ልዊስ መረዳት ለሁላችን የሚሠራ፣ የማይሻርና ጸንቶ የሚኖር መርህ ያስገነዝበናል። ዛሬ እኛ በደል የፈጸሙብንን ሰዎች ይቅር ማለት ቸግሮን ይሆን? ከቸገረን እነርሱንና ሥህተታቸውን ለይተን ማየት አለመቻላችንን ያሳያል። እነርሱንና ሥህተታቸውን ለይተን ማየት ለምን እቃተን? ስለማንወዳቸው ነዋ! አዎን! እንደራሳችን አድርገን ስለማንወዳቸው ነው። እንደ ራሳችን ብንወዳቸውማ ራሳችንን በየቀኑ ይቅር እንደምንል ይቅር እንላቸው ነበር። ሰው ራሱን ይቅር ካላለ በሕይወት መኖር አይችልም። ሌሎችን ሰዎች ይቅር ማለት ቢያቅተው በተለያየ መንገድ ሊሸሻቸው ይችላል፤ ሰው ግን ከራሱ ወዴት ሊሸሽ ይችላል? የክርስቶስ ደም በልባችን የተረጨው እኮ እግዚአብሔር እኛን ይቅር እንዲለን ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ይቅር በተባልንበት ይቅርታ ራሳችንንም ይቅር ማለት እንድንችል የእግዚአብሔርን የይቅርታ ድምፅ በሕሊናችን እንዲያስተጋባ ነው።

ራሳችንን እንደምንወድ ባልንጀራችንን (ሌላውን ሰው) ብንወድ ራሳችንን ይቅር እንደምንል የበደሉንን ይቅር ማለት እንችላለን። ይቅር ካላልናቸው ግን እንደ ራሳችን አልወደድናቸውም ማለት ነው። እንደ ራሳችን ካልወድደናቸው ደግሞ *"ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ"* የሚለውን የንጉሣችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አንድና ብቸኛ ትዕዛዝ አልፈጸምንም ማለት ነው። ይህንን እውነት መረዳትና መለማመድ እንችል ዘንድ እኛም እንደ ሲ. ኤስ. ልዊስ *"ያን ሰው"* እንድናገኘው እግዚአብሔር ይርዳን።

**ተጨማሪ ንባባት፡- ማቴ. 22፥36-40, ዮሐ. 13፥34-35, ሮሜ 12፥10**



## ጸሎት

*ጻድቅ አባት ሆይ! በእርግጠኝነት የማውቃቸውን፣ ፈፅሞ ይቅርታ የማይገባቸውን በደሎቼን ብዙ ጊዜ ይቅር ብለኸኛል። እኔ ግን ሌሎችን ይቅር ማለት ዘወትር ይቸግረኛል። አሁን ግን ምክንያቱን አግኝቼዋለሁ። ራሴን እንደምወድ ሌሎችን ብወድ ኖሮ ሥህተታቸውን ይቅር ማለት አይከብደኝም ነበር። አሁንም ሌሎችን እንደራሴ በመውደድ በእውነተኛ ይቅርታና ከዚያም በሚመነጭ ፍቅር እንድኖር እርዳኝ።*

# 59
# ራስህ ዞር በል!

*"ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው" (መዝሙረ ዳዊት 119፡105)*

ጨለማ የነገሠበትና ማዕበል የበዛበት ሌሊት ነበር። የባሕር ኃይል ማዘዣ የሆነውና ከባድ የጦር መሣሪያዎች የጫነው ግዙፉ የጦር መርከብ ጉሙን እየሰነጠቀ ይገሠግሳል። ድንገት ከመርከቡ ሠራተኞች አንዱ ሲበር መጥቶ የካፒቴኑን መኝታ ክፍል እያንኳኳ "ካፒቴን፣ ካፒቴን እባክዎ ይነሱ!" በማለት ተጣራ። ካፒቴኑ ከእንቅልፍ ነቅተው "ምንድነው? ችግር አለ እንዴ?" በማለት ጠየቁ። "ጌታዬ፣ ከእንቅልፍ ስለ ቀሰቀስኩዎት በጣም ይቅርታ። አንድ ከባድ ችግር ገጥሞን የእርሶ እገዛ የግድ ስላስፈለገን ነው" አለ። ካፒቴኑ ቀልጠፍ ብለው ልብሳቸውን ከለበሱ በኋላ የመኝታ ክፍላቸውን በር እየከፈቱ "ችግሩ ምንድነው?" አሉት። የመርከቡ ሠራተኛም "በሃያ ማይልስ ርቀት ላይ የእኛን የባሕር መሥመር ይዞ የሚመጣ መርከብ አለ፣ በሬዲዮ አግኝተነው ዞር እንዲል ብንነግረው እሻፈረኝ አለ።" ካፒቴኑ ግራ መጋባትና ቁጭጣናነት በተቀላቀለበት ስሜት "እምቢ አሉ ማለት ምንድን ነው? ዞር እንዲሉ ንገራቸዋ!" አሉት። የመርከብ ሠራተኛው በደከመ ድምፅ "ጌታዬ ደጋግመን ነግረናቸዋል፤ ነገር ግን ዞር ለማለት ፈቃደኞች አይደሉም።" አለ። ካፒቴኑ ቀበል አድርገው "እንግዲያስ እኔ እነግራቸዋለሁ" አሉና የሬዲዮኑን እጀታ ከሠራተኛው ተቀብለው መነካካት ጀመሩ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ የሬዲዮው መሥመር ሲገባላቸው "ትሰማኛለህ? በፍጥነት 20 ዲግሪ ወደ ቀኝ ታጠፍ!" አሉ ጠንከር ባለ ድምፅ። ከወዲያ ወገን "ራስህ 20 ዲግሪ ወደ ቀኝ ታጠፍ!" የሚል ምላሽ መጣ። ካፒቴኑ መደነቅና ግራ መጋባት በተቀላቀለበት ስሜት "ይሄ የማይታመን ነገር ነው። እ . . . እኔ የመርከቡ ካፒቴን ነኝ። ሌሎች ኃላፊዎች አብረውህ ካሉ እኔ ማን መሆኔን አስረዳቸው። 20 ዲግሪ ወደ ቀኝ እንድትታጠፍ የማዝህ ካፒቴን ሆራቲዮ ሆርንብሎወር 26ኛ ነኝ" አሉት። ካፒቴኑ ተናግረው እንደ ጨረሱ ከዚያ ወገን "እኔ ሲ ማን (ጀማሪ የባሕር ኃይል ወታደር) ካርል ጆንስ 2ኛ ነኝ፤ በፍጥነት 20 ዲግሪ ወደ ቀኝ እንድትታጠፍ አዝሃለሁ።" አለ። ካፒቴኑ በንዴትና በድንጋጤ ተውጠው ዙሪያቸው



ለተሰበሰቡት መኮንኖች "ምን አይነት ዕብሪት ነው? ማለቴ ምን አይነት ለአደጋ የሚያጋልጥ አጉል ግትርነት ነው? ለማችሁ አንድ ተራ ሲ ማን እኮ ነው እኔን የጦር መርከብ ካፒቴኑን ሲያዘኝ የሚፈልገው። በአንድ የመድፍ ጥይት አጋይቼ ከውሃ ላወጣው እንደምችል የተገነዘበ አልመሰለኝም። ከማን ጋር እየቀለደ እንዳለና ይሄ ቀልድ ምን እንደሚያስከትልበት ቢያውቅ ኖሮ ፈጽሞ አያደርገውም ነበር።" ካሉ በኋላ የሬዲዮኑን እጀታ ዳግም አንስተው "ለማህ! ይህ የአሜሪካንን ባንዲራ የሚያውለበልብ ታላቁ የሚዙሪ 7ኛ የባሕር ኃይል የጦር መርከብ ነው።" ሲሉ ከዚያ ወገን "ይህ ደግሞ ለመርከቦች ምልክት የሚሠጥ ላይት ሃውስ (የወደብ ፋና) ነው።" በማለት መለሰ።

ከጨለማውና ከጉሙ የተነሳ የጦር መርከቡ አዛዥና ሠራተኞች ከፊት ለፊታቸው እየመጣ ያለ መርከብ የመሰላቸው ነገር ለካ ላይት ሃውስ (የባሕር ማማ) ኖሯል። ላይት ሃውስ በባህር ዳርቻ ባሉ ትላልቅ ቋጥኞች ላይ የሚሠራ መርከቦች ወደ የብስ መድረሳቸውን እንዲያውቁና ከቋጥኙ ጋር እንዳይጋጩ የሚያስጠነቅቅ የመብራት ማማ ነው። ላይት ሃውስ ወደ ግራና ወደ ቀኝ እንዲዞሩ መርከቦችን ያዛል እንጂ ራሱ ወዴትም ዞር ሲል አይችልም። ይህም ታሪክ በአሜሪካ የባህር ኃይል ቃለ ጉባዔ መዝገብ ውስጥ "ላይት ሃውስን እንደ መርከብ በመቁጠር የተፈጠረ ችግር" በሚል ሰፍሮ የሚገኝ እውነተኛ ታሪክ ነው።

በሕይወት ጉዟችን ምንም ያህል ታላቅ ብንሆን ልንታዘዛቸው እንጂ ልናዛቸው የማንችል እንደ ላይት ሃውስ የማይነቃነቁ የሕይወት መርሆዎች አሉ። የእግዚአብሔር ቃል በመርሆች የተሞላ ነው። የት እንዳለንና በምን ሁኔታ ውስጥ እንደምንገኝ ያሳየናል፤ ወዴት አቅጣጫ መሄድ እንዳለብን ያመለክተናል፤ በሕይወት ማዕበል ውስጥ ስንሆንና ግራ ሲገባን ወደ ዕረፍት ይመራናል። ችግሩ የቃሉን መርህ መታዘዝ ትተን እኛ ወደ ምንፈልገው አቅጣጫ ልንጠመዝዘው ስንሞክር ነው። ከዚህ ሥህተት ፈጥነን ካልተመለስን በእኛ ይብስብናል፤ የምንላተመው ከጽኑ ዓለት ጋር ስለሚሆን እኛ ፈራርሰን እንወድቃለን እንጂ ዓለቱ ጸንቶ ይኖራል። ስለዚህ በጊዜውም አለ ጊዜውም ለእግዚአብሔር ቃል መርህ እንገዛ።

ተጨማሪ ንባባት፡- መዝ. 119፥105, ኢሳ. 41፥1-29, ዮሐ.8፥12

**ጸሎት**

*ጌታ ሆይ ቃልህ ሕያው ነው። ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃልህ ግን አያልፍም። ለቃልህ መርህ ብገዛ በዋነኝነት የምጠቀመው እኔ ነኝ፤ ባልገዛ በመጀመሪያ ደረጃ የምጎዳው እኔ ነኝ። አባክህ በራሴ ማስተዋል ከመደገፍ ጠብቀኝ። በመንገዴ ሁሉ አንተን እንዳውቅ እርዳኝ። ባልገባኝ ጊዜ እንኳ እንደ ሞኝ እንድታዘዝህ፣ እንደ እውር እንድከተልህ እርዳኝ።*



# 60
# የልጁ ታሪክ

*"ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።"*
*1ዮሐ. 5፡12*

እጅግ ባለጠጋ የሆነ ሰውና ብቸኛ ወንድ ልጁ በአንድ ከተማ ውስጥ ይኖሩ ነበር። አባትና ልጅ በዓለም ላይ ውድ የሆኑና ታዋቂ ሥዕሎችን የመሰብሰብ ልማድ ነበራቸው። በስዕል ስብስባቸው ውስጥ ከፒካሶ እስከ ራፋኤል ባሉ ታዋቂ ሰዓሊዎች የተሠሩ ውድ ስዕሎች ነበሩ። አባትና ልጅ የዕረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ታላላቅ የስዕል ሥራዎችን በመግዛትና በማድነቅ ነበር።

በቬይትናምና በአሜሪካ መካከል ጦርነት በተጀመረ ጊዜ ልጁ በብሔራዊ ውትድርና ወደ ቬይትናም ዘመተ። በውጊያ ላይ ጀብዱ የሚሠራ፣ ጠላትን ለመጋፈጥ ወደ ኋላ የማይል ጀግና ነበረ። አንድ ቀን አጠገቡ ቆስሎ የወደቀ ወታደር ለማዳን በወሰደው እርምጃ በጠላት ጥይት ተመትቶ ተሰዋ። የልጁን ወሬ በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው አባት የአንድ ልጁን ሞት ሲረዳ ከፉኛ በሃዘን ተመታ።

ይህ በሆነ ስድስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በልደት በዓል ዋዜማ፣ አባትየው ብቻውን በቤት ተቀምጦ ሳለ የውጭው በር ተንኳኳ፤ በሩን ሲከፍት አንድ ወጣት ትልቅ የታሸገ ነገር ይዞ ቆሟል። እንግዳው ወጣት ሰላምታ ከሰጠው በኋላ "ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ፣ እኔን በአካል አያውቁኝም፤ እኔ ልጅዎ ሕይወቱን ስጥቶ ያዳነኝ ወታደር ነኝ። በዛን ቀን ልጅዎ የታደገው የእኔን ብቻ ሳይሆን የብዙዎችን ሕይወት ነው። በጥይት ተመትቼ ወድቄ ሳለሁ ተሸክሞኝ ወደ መጠለያ ሥፍራ ሲሄድ ደረቱ ላይ በጥይት ተመቶ ወዲያው ሞተ። ጦር ሜዳ እያለን ዘወትር ስለ እርሶ ያወራልን ነበር፤ በተለይ ለስዕል ያሎትን ፍቅርና አድናቆት ያጫውተን ነበር።

እንግዳው ወጣት ይህንን ብሎ በእጁ የያዘውን ዕቃ ለአባትየው እያቀበለ "ትልቅ ነገር አይደለም፤ እኔ ያን ያህል ጎበዝ ሰዓሊ አይደለሁም፤ ግን ይህን ቢያዩ ልጅዎ የሚደሰት ስለመሰለኝ ነው።" አለ። አባትየው ተቀብሎ

አሽጉን ፈታ፤ በወጣቱ ወታደር እጅ የተሳለ የገዛ ልጁ ምስል ነበር። አባትየው በአክብሮትና በመሳሳት ዓይኖቹን በስዕሉ ላይ ተክሎ ለጥቂት ደቂቃዎች ሲመለከተው ቆየ። ወታደሩ የልጁን በጎነት በቀለምና በብሩሽ እንዴት ሊገልጸው እንደሞከረ ዕምባ ባዘሉ ዓይኖቹ በአድናቆት አየ። ለወጣቱ ምስጋናውን ካቀረበ በኋላ ለድካሙ የሚገባውን ገንዘብ ሊከፍለው እንደሚፈልግ ገለጸለት። ወጣቱ ግን ፈጠን ብሎ "በፍጹም ጌታዬ! ልጅዎ የዋለልኝን ውለታ በምንም ነገር ልመልሰው አልችልም፤ ይሄ ስጦታ ነው" ብሎ ወደ መጣበት ተመለሰ። አባትየው ስዕሉን በቤቱ መግቢያ ኮሪደር ላይ ሰቀለው። ዘወትር ጎብኚዎች የስዕል ስብስቦቹን ሊያዩ ሲመጡ ሌሎቹን ታላላቅ ሥራዎች ከማሳየቱ በፊት የልጁን ምስል የያዘውን ስዕል ያሳያቸው ነበር።

ከጥቂት ወራት በኋላ አባትየው ሞተና ለረዥም ዘመናት የሰበሰባቸውና ከፍተኛ ገንዘብ የሚያወጡ ስዕሎቹ ሐራጅ ወጡ። የሰውየውን ማንነትና የሰበሰባቸውን ውድ ውድ ስዕሎች የሚያውቁ ታላላቅ ሰዎች ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው በዓለም ላይ በጥቂት ሰዎች እጅ የሚገኙትን ውድ ስዕሎች እጃቸው ለማስገባት ጓግተው ከየስፍራው ተሰበሰቡ።

አዳራሹ በሰዎች ተጨናንቋል፤ መድረኩ ላይ የሰውየው ልጅ ምስል ተሰይሟል። የጨረታው መሪ የእንጨት መዶሻውን ከምስባኩ ጋር አጋጨና "ጨረታውን የምንጀምረው በዚህ ልጅ ምስል ነው። ማነው ለዚህ ስዕል የሚጫረት?" በማለት ተጣራ። አዳራሹ በጸጥታ ተሞላ። ወዲያው ከአዳራሹ በስተኋላ የመጣ ድምጽ ዝምታውን ሰበረው። ተናጋሪው ጮክ ብሎ "አባክህ ይህንን እለፈው! እኛ ታዋቂዎቹን ስዕሎች ቶሎ ማየት እንፈልጋለን" አለ። መሪው ግን ቆፍጠን ብሎ "አይ! እንዲህ አይሆንም፤ የምንጀምረው ከዚህ ነው!" አለና "ይህን ስዕል ከ 200 ዶላር በመነሳት ለመውሰድ የሚጀምር?" ብሎ ተጣራ። ጥቂት ቆየና "እሺ በ 100 ዶላር የሚጀምር?" በማለት ጠየቀ። መልስ አልነበረም። በመጨረሻም "እሺ እናንተ በፈለጋችሁት ቁጥር ጀምሩ" አለ። ሌላ ቁጣ የተቀላቀለበት ድምፅ ከጉባኤው መጣ "እኛ ይህን ስዕል ለማየት አልመጣንም፤ የመጣነው የቫን ጎህን፣ የሬምብራንድን ሥራዎች ለማየት ነው። አባክህ ቀልዱን ተውና ወደ እውነተኛው ጨረታ ፈጥነህ ግባ" አለው። ሆኖም አጫራቹ ቀጠለ "የልጁ ምስል! የልጁ ምስል! ማነው የልጁን ምስል



የሚወስድ?" ብሎ ጮኸ። ጥቂት ቆይቶ አንድ ደካማ ድምፅ ከአዳራሹ መውጫ በር አጠገብ መጣ። ተናጋሪው ለረዥም ዘመን ለአባትና ልጅ አትክልተኛ ሆኖ ያገለገለ ድሃ ሰው ነበር። "ለልጁ ምስል 10 ዶላር እሰጣለሁ" አለ። ሰውየው ድሃ እንደመሆኑ መጠን በኪሱ የነበረችው 10$ ብቻ ነበረች። አጫራቹ ቀበል አድርጎ "እሺ 10 ዶላር አግኝተናል፤ ማነው 20 ዶላር የሚሰጥ?" በማለት ጠየቀ። ታዳሚዎቹ "በ 10 ዶላር ለሰውየው ሰጠውና ዋናዎቹን ስዕሎች ለእኛ አውጣልን" በማለት ተንጫጩ። መሪው "እሺ የ10 ዶላር ዋጋ ተሰጥቷል፤ ማነው ከፍ አድርጎ የሚወስደው?" ሲል በድጋሚ ጠየቀ። የጉባኤው ቁጣ እየናረ መጣ። የልጁን ስዕል ማየት ፈጽሞ አልፈለጉም። ሁሉም ውድ የሆኑትን፣ ታላላቅ ዋጋ ያላቸውን ሥራዎች ተጫርተው ለመግዛት ተጣድፈዋል። የጨረታው መሪ ፊት ለፊቱ ያለውን ጠረቤዛ በእጁ በያዘው የእንጨት መዶሻ ሦስት ጊዜ እየመታ "ሊሄድ ነው . . . አንድ! ሊሄድ ነው . . . ሁለት! ሊሄድ ነው . . . ሦስት! ለ 10 ዶላር ተሸጧል!" አለ። በሁለተኛው ረድፍ ተቀምጦ የነበረ ሰው ጮኽ ብሎ "አሁን ወደ እውነተኞቹ የስዕል ስብስቦች እንሂድ" አለው። አጫራቹ ግን መዶሻውን አስቀመጠና "በጣም አዝናለሁ ጨረታው እዚህ ላይ ተጠናቋል" በማለት ተናገረ። አዳራሹ በጉምጉምታ ድምጽ ተሞላ። ሁሉም "እንዴ! ሌሎቹስ ስዕሎች?" በማለት ተንጫጩ። የጨረታው መሪ "አዝናለሁ፤ ይህንን ሐራጅ ለማካሄድ ስጋበዝ በኑዛዜው ላይ የተቀመጠ ሁኔታ መኖሩ በምሥጢር ተነግሮኝ ነበር። ይህን ሁኔታ እስከዚህች ደቂቃ ድረስ የመግለጥ ሥልጣን አልነበረኝም። አሁን ግን ስለተጠናቀቀ እነግራችኋለሁ። በዚህ ወቅት ለጨረታ የቀረበው ስዕል የልጁ ምስል ብቻ ነው። የልጁን ምስል የሚወስድ ሰው ንብረቱን በሙሉ እንዲወርስ ባለቤቱ ተናዟል። ንብረቱን በሙሉ ሲባል የስዕል ስብስቦቹንም ይጨምራል። ስለዚህ ልጁን ያገኘው ሰው ሁሉን ወስዶታል" በማለት ስብሰባውን ዘጋ።

እግዚአብሔር የዛሬ 2000 ዓመት ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ እንዲሞት ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ልኮታል። እርሱም ሞትን አሸንፎ ተነስቶ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀምጧል። ዛሬ የእግዚአብሔር መንፈስ ልክ እንደ ጨረታው መሪ በሥፍራ ሁሉ "ልጁን . . . ልጁን . . . ልጁን የሚወስድ!" በማለት ይጮኻል። አባት ልጁን የሁሉ

ወራሽ አድርጎታል። በልጁ የሚያምን ከልጁ ጋር ሁሉን ለዘላለም እንደሚወርስ ቅዱሉ ቃሉ ይመሰክራል። ወንድሜ ልጁ አለህ? እህቴ ልጁ አለሽ? አባቴ፣ እናቴ ልጁ አለዎት? ሐዋርያው ዮሐንስ እንደጻፈው "ልጁ ያለው (የዘላለም) ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው (የዘላለም) ሕይወት የለውም" ።

**ተጨማሪ ንባብ፡- ዮሐ. 3፥16, 20፥30-31, ራዕይ 20፥15**

## ጸሎት

*እግዚአብሔር አባት ሆይ፡- አንተ ጻድቅ ነህ! እኔ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ! የኃጢአት ውጤት የዘላለም ሞት እንደሆነ አውቃለሁ። ነገር ግን እኔን ከኃጢአትና ከዘላለም ሞት ለማዳን ቅዱስ ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ ወደ ምድር ልከሃል። ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ዕዳዬን፣ ፍርዴንና ዕርግማኔን ተሸክሞ በቀራንዮ መስቀል ላይ ስለ እኔ ሞቷል፣ ተቀብሯል። ነገር ግን ሞቶ አልቀረም በሦስተኛው ቀን ሞትን አሸንፎ በአካል ተነስቷል፣ ወደ ሰማያትም ሄዶ በቀኝህ ከብሯል። ይህ ኢየሱስ የነፍሴ መድኃኒት፣ የሕይወቴ ጌታ ነው። ዛሬ ልቤን ከፍቼ ወደ ሕይወቴ አስገባዋለሁ። ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ና ወደ ልቤ ግባ፣ ከኃጢአቴ በደምህ አንጻኝ፣ አዲስ ሰው፣ አዲስ ፍጥረት አድርገኝ። ከዛሬ ጀምሬ ለዘለዓለም አመልከሃለሁ፣ አከተልሃለሁ። አሜን።*

“እፎይ-ታ” በዚህ ሩጫ በበዛበት ዓለም ውስጥ የተመጋቢውን ጊዜ ሳትሻማ የነፍስን ረሃብ የምታስታግስ ጣፋጭ ሕብስት ናት። አንባቢ ለጥናት ሰፊ ጊዜ መመደብ ሳያስፈልገው በ 5 ደቂቃ ውስጥ ሊያጣጥማትና ተግባሩን እየከወነ በማሰላሰል ሊያመነዥጋት የሚችል ምጥን ጉርሻ ናት። በየዕለቱ የምትነበብ እንደመሆኗ መጠን ሳያሰልሱ የእግዚአብሔርን ቃል የማንበብና የማሰላሰል ብሎም የመተግበር ልማድ በአንባቢዎቿ ውስጥ ታዳብራለች። በውስጧ 60 የተለያዩ ተረኮችን ያዘለች እንደ መሆኗ ሳይታወቅ እየጣፈጠ እንደሚወርድ ምግብ ወደ ውስጥ ገብታ መድኃኒት የምትሆን በልክ የተሰነገች የጥሞና መድብል ናት።

ከመጽሐፉ መግቢያ የተወሰደ



ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁን ላለፉት 27 ዓመታት በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ በመዘዋወር ወንጌልን አገልግሏል። ያሬድ የጎልደን ኦይል አገልግሎት መሥራች ሲሆን በሥልጠና፣ በሥነ-ጽሁፍ እና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የክርስቶስን ሕይወት በማካፈል ይታወቃል።

GOLDEN Oil Ministries
Sharing the Life of Christ

$14.99
ISBN 978-0-9987038-0-0
51499>
9 780998 703800